# መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በተለይም፤ በወጣቶችና ሴቶች ላይ እያሳደሩት ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ

በ

1. ኃይሉ ዲንቃ
2. ተዋበች ተድላ

ህዳር 2004

## ምስጋና

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወቅታዊና ጊዜው የሚዋጀውን አንገብጋቢ ጉዳይ በማንሳት መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል ሳይንሳዊ ጥናት እንዲጠና በማድረጉ ላቅ ያለ ምስጋና ይገባዋል፡፡

በመቀጠልም ውድ ጊዜያቸውን በመስጠት የጽሑፍ መጠይቁን በመሙላት፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይትና በቃለ መጠይቅ በመሳተፍ መረጃ ለሰጡን የከተማዋ ነዋሪዎች፣ የተለያዩ የመንግስት ድርጅቶችና የእምነት ተቋማት ተወካዮች ትልቅ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

በተጨማሪም የጽሑፍ መጠይቁን በየቤቱ በመሄድ ላስሞሉ ወጣቶችና የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ቃለ መጠይቅና ተሳትፎአዊ ምልከታው በተገቢውና በተሳካ ሁኔታ ለተገበሩ ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች ለተውጣጡ ባለሙያዎች የከበረ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

**1. መግቢያ**

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር ነባራዊ ሁኔታ ..... 3

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች ..... 5

1.3.1. ዋና ዓላማ ..... 5

1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች ..... 5

1.4. የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ..... 5

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 6

1.6. የጥናቱ ወሰን ..... 7

1.7. በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ቃላት ያላቸው ትርጉም ..... 8

**2. ሀሳባዊ ትስስርና የተዛማጅ ጽሑፎች ክለሳ**

2.1. ሀሳባዊ ትስስር ..... 9

2.2. የተዛማጅ ጽሑፎች ክለሳ ..... 11
2.2.1. የባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች ምንነት ..... 11
2.2.2. ባህልና ልምድ ከኢትዮጵያ አንጻር ..... 12
2.3. ወጣቶችና ሴቶች ከልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ያላቸው ትስስር አጠቃላይ ሁኔታ..... 15
2.4. አደንዛዥ ዕጾችን የሚጠቀሙ ወጣቶችና ሴቶች ልዩ ባሕሪያት ..... 16
2.5. ወጣቶችና ሴቶችን ወደ መጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚገፋፉ ምክንያቶች ..... 17
2.5.1. ዓለምአቀፋዊነት ..... 17
2.5.2. መገናኛ ብዙሃን ..... 18
2.5.3. የታዋቂ ሰዎች/ዝነኞች ተፅዕኖ ..... 20
2.5.4. የዕፅና የአልኮል ነፃ ዝውውር ..... 20
2.5.5. ማህበራዊ ሁኔታዎች ..... 21
2.5.6. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ..... 24
2.6. መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና በሴቶች ላይ የሚያስከትሏቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎች ..... 25
2.6.1. ማህበራዊ ተፅዕኖዎች ..... 25
2.6.2. ስነልቡናዊ ተፅዕኖዎች ..... 28
2.6.3. ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ..... 29

3. የጥናቱ ዘዴ
3.1. የመጠናዊ መረጃ ናሙና ምጣኔ ..... 31
3.1.1. የናሙና ምጠና ስሌት ..... 31
3.2. የመጠናዊ መረጃ ናሙና አመራረጥ ስልት ..... 32
3.3. የዓይነታዊ መረጃ አሰባሰብ ስልት ..... 34
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ..... 34
3.5. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ..... 35
3.6. የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ..... 35
3.7. የጥናቱ ህጋዊነት ..... 36

## 4. የጥናቱ መረጃ ግኝት

4.1. የመጠናዊ መረጃ ግኝት ..... 37

4.1.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ ..... 37

4.2. ተዛምዶአዊ ትንተና ..... 58

4.2.1. የተሳታፊዎች ግላዊ ሁኔታ(ያታ፣እድሜና የትምህርት ደረጃ)
ከመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ያላቸው ተዛምዶ ..... 58

4.2.2. መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች አነዱ ከሌላኛው
ጋር ያላቸው ተዛምዶ ..... 62

4.3. የዓይነታዊ መረጃ ግኝት ..... 64

4.3.1. በሴቶችና ወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ
መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ..... 64

4.3.2. ወጣቶችና ሴቶችን ለመጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች
የሚያጋልጧቸው ምክንያቶች ..... 74

4.3.3. መጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ
የሚያደርሱትን ተፅዕኖና ችግር ..... 90

4.3.4. ችግሩን ለማስወገድ ከተሳታፊዎች የቀረቡ የመፍትሔ
ሀሳቦች ..... 95

## 5. የጥናት ግኝት ትንተና

5.1. በሴቶችና ወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉት መጤ
ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ..... 99

5.2. ሴቶችና ወጣቶችን ለመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች
የሚያጋልጧቸው ምክንያቶች ..... 104

5.3. መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ወጣቶች
ላይ እያከተሉት ያለው ተፅዕኖ ..... 113

## 6. ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ

6.1. ማጠቃለያ ..... 119
6.2. የመፍትሔ ሀሳብ ..... 121
አባሪዎች .....

## የሰንጠረዥና ግራፍ ዝርዝር

### የሰንጠረዥ ዝርዝር

ሠንጠረዥ 1፡ የወረዳዎች ብዛትና ስብጥራዊ ናሙና አወሳሰድ

ሠንጠረዥ 2፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ

ሠንጠረዥ 3፡ የመዝናኛ፣ የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 4፡ የወሲብ ፊልም የተመለከቱ ተሳታፊዎች ፊልሙን ያገኙበት መንገድ

ሠንጠረዥ 5፡ የተለያዩ አልኮል መጠጦች አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 6፡ የተለያዩ አነቃቂ እጾች አጠቃቀም በመቶኛ

ሠንጠረዥ 7፡ የዕፅና የመጠጥ ተጠቃሚዎች የሚደርስባቸው የስነ-ልቦናዊ እና ማህበራዊ ችግሮች

ሠንጠረዥ 8፡ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች አነዱ ከሌላኛው ጋር ያላቸው ተዛምዶ/Correlation

### የግራፍ ዝርዝር

ግራፍ 1፡ የወሲብ ፊልም የተመለከቱ ተሳታፊዎች በመቶኛ

ግራፍ 2፡ ሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቅመው የሚያውቁ ተሳታፊዎች በመቶኛ

ግራፍ 3፡ ተሳታፊዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ የፈጸሙበት የዕድሜ ክልል በመቶኛ

ግራፍ 4፡ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የወሲብ ግንኙነት አድርገው የሚያውቁ ተሳታፊዎች በቁጥር

**ግራፍ 5፡ በወጣቶች እና በሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የመዝናኛ ቦታዎች**

**ግራፍ 6፡ ለአላስፈላጊ መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ተጋላጭ የሆኑ የህብተረተሰብ ክፍሎች**

**ግራፍ 7፡ ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና አላስፈላጊ ባህሪያት የሚያጋልጡ ማህበራዊ ምክንያቶች**

**ግራፍ 8፡ ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና አላስፈላጊ ባህሪያት የሚያጋልጡ አካባቢያዊ፣ የሚዲያና የአቻ ጓደኛ ተፅዕኖዎች በመቶኛ**

**ግራፍ 9. ሴቶችን ለመጠ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡ ሁኔታዎች**

**ግራፍ 10. ወጣቶችን ለመጠ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡ ሁኔታዎች**

## <u>ምህፃረ ቃል</u>

➢

**ዋና ዓላማ፡-** የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በህብረተሰቡ በተለይም፤ በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተሉት ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቡናዊ ተፅዕኖዎችና ቀውሶች በማጥናት የችግሮቹን ምንጭ ለይቶ በማወቅ፤ የመፍትሄ ሀሳብ ማመንጨት ነው፡፡

**ዝርዝር ዓላማ፡-** መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተሉ ያሉትን ማህበራዊ፣ ስነልቡናዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች መዳሰስ፤ የችግሮቹን መሠረታዊ መንስኤዎች እና የሚያስከትሉትን ተፅዕኖዎች መለየት፤ የመጤ ባህሎችንና ልማዳዊ ድርጊቶችን አወንታዊና አሉታዊ ጎን በመለየት አሉታዊ ተፅዕኖአቸው የሚቀንስበትን ሁኔታ መለየት፤ እንዲሁም ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን አንጥሮ ማውጣት እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቀጣይ ለሚወስዳቸው የማስተካከያ እርምጃዎች እና በዚህ ዙሪያ ለሚያጠኑ ባለሙያዎች የመረጃ ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል አስተዋፅኦ ለማበርከት ነው፡፡

**የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች፡-**

- በሴቶችና ወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያስከተሉ ያሉ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?
- መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተሉ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ምንድን ናቸው?
- ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ስነልቡናዊ ችግሮች ካልተገቡ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ያላቸው ትስስር ምን ይመስላል?
- ለሱሰኝነት ኢጋላጭ የሆኑ ቦታዎች መበራከት ላልተገቡ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች መስፋፋት ያላቸው አስተዋፅኦ ምን ይመስላል?
- የዓለምአቀፋዊነት፣ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ መረቦች መስፋፋት በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ምንድን ነው?
- የህብረተሰብ፣የቤተሰብ፣ የትምህርት ቤቶችና የመኖሪያ አካባቢዎች ነባራዊ ሁኔታ፤ በሴቶችና ወጣቶች ባህሪ ላይ እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ምንድን ነው?

# 1. መግቢያ

## 1.8. የጥናቱ ዳራ

የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለሥልጣን በ1999 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ ባካሄደው የህዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 73,918,505 እንደሚሆን የተገመተ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ አብዛኛውን ክፍል (95 በመቶ) የያዙት ዕድሜያቸው ከ50 ዓመት በታች ያሉ ወጣቶችና ሴቶች መሆናቸው ተገልጿል።

በተመሳሳይ አጠቃላይ የአዲስ አበባ ነዋሪ 2,739,551 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,434,164 የሚሆኑት ሴቶች፤ የተቀሩት 1,305,387 ደግሞ ወንዶች ናቸው፡ከአጠቃላዩ የአዲስ አበባ ነዋሪ ውስጥም የወጣቱ ቁጥር 1,161,988 ነው። ከዚህ ውስጥ የሴት ወጣቶች ቁጥር 644,704፤ የወንዶች ቁጥር ደግሞ 517,284 መሆኑን መረጃው ያሳያል። በአጠቃላይ እነዚህ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶችና ሴቶች በልማት፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ላይ ያላቸው ተሳትፎና አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

ይሁን እንጂ በህብረተሰቡ ውስጥ ባለው የግንዛቤ እጥረት ለሴቶችና ወጣቶች የሚሰጣቸው ግምት ማነስና፤ የሚገባውን ያህል ያለመሆን፤ በዕድገትና ልማት ላይ ሊያበረክቱት የሚገባቸውን ከፍተኛ ድርሻ እንዳያበረክቱ አስተዋጽዖ እያደረገ ይገኛል።

ለወጣቶች የተመቻቹ የስራና የትምህርት ዕድሎች ቢኖሩም፤ ከችግሩ ስፋትና ከወጣቶቹ ቁጥር መብዛት አንጻር ለሁሉም ተደራሽ ባለመሆኑ ችግሮች ይስተዋላሉ። በዚህም የተነሳ ከሥራ ዕድል ውስንነት ፤ከትምህርትና ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ተያያዥ በሆኑ ችግሮች ፣በመንግስት ጤና ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች፤ በመዝናኛና የንባብ ቦታዎች እጥረትና በስፖርት ተቋማት ውስንነት ምክንያት ለተለያዩ ሱሶችና ለሥነ-ተዋልዶ ጤና ችግሮች ሲጋለጡ ቆይተዋል። በተጨማሪም ያላቸውን ዝንባሌ፣ ተሰጥኦና የሕይወት ክህሎት ለይተው በማወቅ የሚያዳብሩበት  ዕድላቸው ጠባብ የነበረ ሲሆን በፖለቲካው ዘርፍም ይህ ነው የሚባል ተሳትፎና አስተዋፅየ ሳይኖራቸው ቆይቷል።

በተመሳሳይ መልኩ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚንጸባረቁ የተዛቡና ኢ-ፍትሀዊ የያታ አመለካከቶች የተነሳ ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የነላ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዳይኖራቸው አድርጓል። በተጨማሪም ያላቸውን ዝቅተኛ

ተሳትፎ ለማጎልበት የተወሰዱ በጎ እርምጃዎችም በአፈፃፀም ላይ ባሉ ክፍተቶችና የቁርጠኝነት ማነስ የተነሳ የሚጠበቀውን ያህል ውጤት አላስገኙም፡፡ በመሆኑም የልማት ባለቤት የሆኑ ሴቶችና ሀገር ተረካቢ ወጣቶች በአላስፈላጊ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በመጠመድ ለሀገርና ለወገን ሊያበረክቱ የሚገባቸውን አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዳያበረክቱ እያገዳቸው ይገኛል፡፡

በሴቶችና ወጣቶች ላይ የሚስተዋሉትን ውስብስብ ችግሮች ከመቅረፍ አኳያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፡፡ ከነዚህም መካከል ሴቶችና ወጣቶችን በግልም ሆነ በማህበር በማደራጀት፤ የሙያ ሥልጠና ፣ የማምረቻ ቦታ፤ የምክርና የብድር አገልግሎት እንዲያገኙና በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተሠማርተው ራሳቸውን እንዲችሉ እያደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም የአቅም ክፍተቶችን ለመሙላት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችና የቁሳቁስ ድጋፎች እያደረገላቸው ይገኛል፡፡

በተጨማሪም የከተማዋ ወጣቶች በሥነ ምግባራቸው የተሻሉ ዜጎች ሆነው እንዲወጡ ለማድረግ የሥነ-ምግባርና ሥነ-ዜጋ ትምህርት በየትምህርት ቤቶች በተጠናከረ መልኩ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በላይ የፈረቃ ትምህርትን በማስቀረት ተማሪዎች ሙሉ ቀን በመማር የተሻለ ጥራትና ጥልቀት ያለው ትምህርት እንዲያገኙና ከአልባሌ ቦታዎችም እንዲርቁ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በላይ  በርካታ የወጣት ማዕከላትና የተወሰኑ ቤተ-መፃህፍት ተገንብተው ለወጣቱ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት አበረታች ተግባራት እየተከናወኑ ቢሆንም ሴቶችና ወጣቶች በሀገራችን ተቀባይነት ካለው ባህሪ በማፈንገጥ ላልተፈለጉና ጠቀሜታ ለሌላቸው መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች እየተጋለጡ ያሉበት ሁኔታ እየተስተዋለ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ  ወጣቶች ከትምህርት ገበታቸው በመቅረት፣ ከቤተሰብ ያኮረፉ ወጣቶችና ሴቶች ወደ ጎዳና በመውጣት ለወጣት ጥፋተኝነት፣ ለወንጀል፣ ለጎዳና ተዳዳሪነት፣ ለወሲብ ንግድና ስደት እየተጋለጡ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ለመጠጥ፣ለጫት፣ ለሀሺሽ፣ ለወሲብና የመሳሰሉት ድርጊቶች ተጋላጭ በመሆን የደባል ሱሶች ተጠቂ ከመሆናቸውም ባሻገር ጥንቃቄ በጎደለው የግብረስጋ ግንኙነት የተነሳ ላልተፈለገ እርግዝና፣ ለኤች አይ ቪ/ኤድስና ለሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ሰለባ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም በሴቶችና ወጣቶች ዙሪያ የሚታየውን፤ በመጤ ባህሎችና አላስፈላጊ ድርጊቶች የመጠመድ ችግሮችን በመለየት፤ አስፈላጊውን የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ ይቻል ዘንድ ጥልቀት ያለው ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ሴቶችን የሚማርኩ አላስፈላጊ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ወደነዚህ የሚገፏፏቸውን ምክንያቶችና በነዚህ ምክንያት የሚደርሱትን ተፅዕኖዎች በመለየት የመፍትሔ ሐሳብ ማቅረብ ነው፡፡

## 1.9. የጥናቱ መነሻ ችግር ነባራዊ ሁኔታ

ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ዓለማቀፋዊና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሴቶችና ወጣቶች ለተለያዩ ችግሮች እየተጋለጡ ይገኛሉ፡፡ በተለይ ወጣትነት በርካታ አካላዊ፣ስሜታዊና ሥነ-ልቦናዊ ለውጦች የሚስተዋሉበት፤ ለቀጣይ ህይወትና ማንነት መሠረት የሚጣልበት፤ ባህላዊ እሴቶችንና ልምድ የሚቀሰምበት፤ ዝንባሌና ተሰጥዖን ለመለየት ጥረት የሚደረግበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አካላዊና ሥነልቦናዊ ለውጦችን ተከትለው የሚመጡ አለመረጋጋቶች የሚስተዋሉበት፤ የወሲብ ፍላጎትና ማንነትን የመፈለግ ጥያቄዎች የሚከሰቱበት የእድሜ ክልል መሆኑን የስነ-ልቦና ባለሙያዎች ያስረዳሉ (Bandura,2001)፡፡ ከዚህም ባሻገር በማህበራዊ፣ሥነልቦናዊ፣ሞራላዊና አካላዊ አቋም ረገድ ራስን ማዕከልና የበላይ አድርጎ የማሳየት፤ በማኝኛውም የግንኙነት ዘርፎች በሙሉ ነፃነት የመንቀሳቀስ፣ በአጠቃላይ ራስን በራስ ለማስተዳደርና ለመምራት ጽኑ ፍላጎት መያዝና ማንኛውንም አዲስና አደገኛ ነገሮችን የመሞከር ከፍተኛ ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ወቅት ነው፡፡

በሌላ በኩል ሴቶች ለዘመናት ሰፍኖ በቆየው የተዛባ የፆታ አመለካከት የተነሳ ይህ ነው የማይባል ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ደረጃ ይዘው እንዲኖሩ ተገደዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ የተሰጣቸው ዝቅተኛ ቦታ ሊያበረክቱት የሚገባቸውን ያህል ፋይዳ ያለው አስተዋጽዖ እንዳያበረክቱ ያገዳቸው ሲሆን፤ ትምህርትና የተሻለ ገቢ የማግኘት ዕድላቸውም ዝቅ ያለ በመሆኑ ለፆታዊ ጥቃት፣ ስራ አጥነት፣ ለወሲብ ንግድና ስደት ሲዳረጉ ይስተዋላል፡፡

ከአዲስ አበባ አጠቃላይ ነዋሪ ውስጥ 52.4% የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ ከአጠቃላይ የህዝቡ ቁጥር ከ15-29 ዓመት ያሉት ወጣቶች 42.42% ናቸው፡፡ በጥቅሉ ከ72% በላይ የሆኑት የከተማው ነዋሪዎች ሴቶችና ወጣቶች ቢሆኑም ከቁጥራቸው አንፃር ለሀገር ዕድገት እያበረከቱት ያለው አስተዋፅየ የሚጠበቀውን ያህል አይደለም፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ዓለምአቀፋዊነት፣ አካባቢያዊና ሌሎች ተዛማጅ ምክንያቶች ሴቶችና ወጣቶችን ለሱስ አስያዥ ዕፆችና የአልኮል መጠጦች ተጠቃሚነትና ለመጤ የባህል ወረርሽኞች እንዲጋለጡ አድርገዋቸዋል፡፡በተለይ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ወጣቶች የአፍላነት ዕድሜ በሚያስከትላቸው፤ ነባራዊ ሁኔታን ያላገናዘበ እና መሰረታዊ ያልሆነ ፍላጎት አለመሟላት ምክንያት አፈንጋጭ በመሆን፤ ከባህላችን ጋር ለማይሄዱ ያልተገቡ ተግባራት ተጋላጭ ሆነዋል፡፡

በአዲስ አበባ ደረጃ ሴቶችና ወጣቶችን ከላይ ለተዘረዘሩት መሰረታዊ ችግሮች ተጋላጭ እንዲሆኑ ከሚያደርጓቸው አካባቢያዊ ምክንያቶች መካከል፤ የሺሻ ማጨሻ፣ የጫት መቃሚያ፣የቁማር፣ የህገወጥ ቪዲዮ ማሳያ፣ የቀንና የሌሊት ጭፈራ፣ የራቁት ዳንስ፣ የግብረ ሰዶም(ተመሳሳይ ፆታ ወሲብ) መፈጸሚያና ጥንቃቄ የጎደለው ገላጣ ወሲብ መፈጸሚያ ቤቶች መስፋፋት ትልቁን ድርሻ የያዘ ሲሆን፤ ከአስሩም ክፍለ ከተሞች የፖሊስ መምሪያዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ወደ 3,691 የሚደርሱ ቤቶች ለዚህ ጉዳይ ማስፈጸሚያነት ይውላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ወጣቶችንና ሴቶችን ወደ ወንጀል፣ ፣ የአልኮልና የአደንዛዥ ንጥረ ነገሮች ሱሰኝነት፣ ላልተፈለገ እርግዝናና ወሊድ፤ ለአባለዘር በሽታዎች/ኤች.አይ.ቪ ኤድስ፤ለትምህርት ማቋረጥ፣ ለጎዳና ተዳደሪነት፣ ለኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ወይም ስራ ፈትነትና ስራ መጥላት፣ ለልመና፣ ለዝርፊያ፣ለስደትና ለመሳሰሉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች እያጋለጣቸው ይገኛል፡፡

## 1.10. የጥናቱ ዓላማዎች

### 1.10.1. ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በአዲስ አበባ ነዋሪዎች በተለይም በወጣቶችና ሴቶች ላይ እያስከተሉት ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቡናዊ ተፅዕኖዎችን በማጥናትና የችግሮቹን ምንጭ ለይቶ በማወቅ፣ የመፍትሄ ሀሳብ ማመንጨት ነው።

### 1.10.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተሉ ያሉትን ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች መዳሰስ፣
- መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተሉ ያሉትን ማህበራዊ ተፅዕኖዎች መዳሰስ፣
- የችግሮቹን መሠረታዊ መንስኤዎች እና የሚያስከትሉትን ተፅዕኖዎች መለየት፣
- የመጤ ባህሎችንና ልማዳዊ ድርጊቶችን አወንታዊና አሉታዊ ጎን መለየት፣
- የመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች አሉታዊ ተፅዕኖ የሚቀንስበትን ሁኔታ መለየት፣
- ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን አንጥሮ ማውጣት እና
- የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በቀጣይ ለሚወስዳቸው የማስተካከያ እርምጃዎች እና በዚህ ዙሪያ ለሚያጠኑ ባለሙያዎች የመረጃ ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል አስተዋፅኦ ለማበርከት ነው።

## 1.11. የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች

- በሴቶችና ወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያስከተሉ ያሉ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?
- መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተሉ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ምንድን ናቸው?
- ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ስነልቡናዊ ችግሮች ካልተገቡ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ያላቸው ትስስር ምን ይመስላል?
- ለሱሰኝነት አጋላጭ የሆኑ ቦታዎች መበራከት ላልተገቡ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች መስፋፋት ያላቸው አስተዋፅኦ ምን ይመስላል?

- የዓለምአቀፋዊነት፣ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ መረቦች መስፋፋት በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ምንድን ነው?
- የህብረተሰብ፣የቤተሰብ፣ የትምህርት ቤቶችና የመኖሪያ አካባቢዎች ነባራዊ ሁኔታ፤ በሴቶችና ወጣቶች ባህሪ ላይ እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ምንድን ነው?
- በመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች አሉታዊ ተፅዕኖ ምክንያት ላልተገቡ ባህሪያት እየተጋለጠ ያለውን ትውልድ ለመታደግ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

## 1.12. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህን ጥናት ማካሄድ ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት፡-

1. ቁጥራቸዉ ጥቂት የማይባል የከተማችን ሴቶችና ወጣቶች አላስፈላጊ በሆኑ የባህር ማዶ ድርጊቶች በመሳብ የስብዕናና የባህል ተጽዕኖ ችግር ውስጥ በመግባት ለባህር ማዶ የአኗኗር ዘይቤና እሴቶች፤ትውፊቶች (አለባበስ፣የፊልምና የዘፈን ምርጫዎች) እና አላስፈላጊ ቁሳዊ አስተሳሰብን ማዳበር፤ የሌሎችን የማድነቅ፤ በተለይ በምዕራቡ አንጉል ባህሎች የመማረክ አደጋ ውስጥ እየገቡ ይገኛሉ፡፡ ይህ የስብዕናና የባህል አሉታዊ ተጽዕኖ ከመደበኛ ክስተትነት እያለፈ ወደ ችግርነት በመለወጥ ላይ ይገኛል፡፡ ይህን ዓይነቱ አፍራሽ አዝማሚያ በጥናት በተደገፈ መረጃ መፍትሄ ካልተቀመጠለት፤ እንደ ካንሰር ጊዜዉን ጠብቆ ትውልድን በሙሉ በመበከልና በማጥፋት ከተማችንን ብሎም አገራችንን ለከፋ አደጋ የሚዳርግ ይሆናል፡፡በመሆኑም ሴቶችና ወጣቶች ጠቃሚ፤ ነባራዊና ባህላዊ ትውፊቶችንና ማህበራዊ እሴቶችን ተገንዝበውና አውቀው፤ በባለቤትነት የሚንከባከቡበትን የመፍትሔ አቅጣጫ ለማመላከት በማስፈለጉ፤

2. በሴቶችና ወጣቶች ላይ ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ከሚያሳድሩ ተግባራት አንዱና ዋነኛው የሥራ ክቡርነትን ካለመረዳት ጋር የተያያዘ ችግር ነዉ፡፡ በመሆኑም በከተማችን ያሉ ጥቂት የማይባሉ ሴቶችና ወጣቶች ራስን አሳንሶ መመልከት፤ ሥራን መናቅ፤ በጥረት ለማደግ/ለመለወጥ አለመፈለግ፣ የቢሮ ሥራ ብቻ መፈለግ፤ ከከተማ ወጥቶ መሥራት አለመሻት፤ ወዘተ..... ጋር የተያየዙ ችግሮችን በጥናት ፈትሾ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤

3. ከእድሜ ደረጃቸው ጋር ተያይዘዉ በሚመጡ አካላዊና ስሜታዊ ለውጦች የተነሳ ወጣቶች የተለያዩ አዳዲስ ነገሮችን በድፍረትና በጀብደኝነት ያለምንም ፍርሀት ይፈፅማለ፡፡ለምሳሌ፡-ሱስ አስያዥ ዕፆችንና አልኮል መጠጦችን የመጠቀም ሁኔታዎችን በድፍረት በመሞከር ጀምረው ወደ ሱሰኝት ደረጃ ሲደርሱ የገንዘብ ወጪያቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡በተጨማሪም ትምህርት አቀባበላቸውና ፍላጎታቸው፣ ለሥራ ተነሳሽነታቸውን እንዲሁም ከቤተሰብ ፣ ከማህብረሰቡና ከመንግስት አካላት ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት እንዲሻክር ያደርጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ገንዘብ ለማግኘት ከቤተሰባቸው ጀምሮ በተለያዩ ወንጀሎች ውስጥ እንዲሳተፉ ተፅእኖ ያሳድርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከዚህ የዕድሜ ክልል ውጪ ያሉ አንዳንድ ሴቶችም፤ በቤተሰብ መፍረስ፤ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ፤ሥርዓት በጎደለው ተዝናንኦት፤ተስፋ በመቁረጥ እና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት ወደነዚህ ያልተገቡ ድርጊቶች ውስጥ ይገባሉ፡፡ ስለሆነም እነዚህን ችግሮች በደንብ አጥንቶ ወንጀል ነክ ጉዳዮችን ከምንጫቸው ለማድረቅ የሚያስችሉ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ በማስፈለጉ እና፤

4. የሴቶችና ወጣቶችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ሥነ-ልቡናዊ እና ከፀጥታ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመለየት፤ በጥና ላ የተመሠረተ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥና እነዚህም የሚተገበሩበት ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት የሚነደፍበትን መንገድ በመረጃ ማስደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ ጥናቱ እንዲከናወን ተፈልጓል፡፡

## 1.13. የጥናቱ ወሰን

ይህን ጥናት የተሟላ ለማድረግና የታለመውን ግብ ለማሳካት በከተማዋ የሚገኙትን አስሩም ክፍለ ከተሞች እንዲሸፍን ተደርጓል፡፡

## 1.14. በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱ ቃላት ያላቸው ትርጉም

- ሴት - ዕድሜያቸው ከ15-29 እና ከዛ በላይ ያሉ ሴትችን የጠቃልላል
- ወጣት - ዕድሜያቸው ከ15 — 29 ያሉ ወንድና ሴቶችን ያጠቃልላል
- ልማድ - በተደጋጋሚ የሚከወን ድርጊት

- ባህል - የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ፣ወግ ልምድ ወዘተ ያጠቃልላል
- መጤ - ሀገር በቀል ያልሆነና ከሌላ የተወሰደ
- ግብረ-ሰዶማዊነት - ከተመሳሳይ ፆታ ማለትም ወንድ ከወንድ ወይም ሴት ከሴት ጋር የሚፈጸም የወሲብ ግንኙነት
- ሱስ አስያዥ ዕፆች - ጫት፣ ሺሻ፣ ሲጋራ፣ ሀሺሽ፣ ሄሮይን ወዘተ
- የተተኳሪ ቡድን ውይይት- ለጥናቱ ተገቢነት ካላቸው ግለሰቦች ጋር የተደረገ ውይይት
- ተሳትፎአዊ ምልከታ-አጥኚው በድርጊት የተሳተፈበት ጥናታዊ እይታ

# 2. ሀሳባዊ ትስስርና የተዛማጅ ጽሑፎች ክለሳ

## 2.1. ሀሳባዊ ትስስር

በዚህ ጥናት የተነሱ ሀሳቦችን ትስስር ለማሳየት ከጥናቱ የተገኙ ግኝቶችንና ተዛማጅ ጽሑፎችን መሰረት በማድረግ በጥናት ቡድኑ የተዋቀረ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተለው የሀሳቦች ትስስር ማሳያ ተዘጋጅቷል፡፡

ከታች የተቀመጠው ሀሳባዊ ትስስር የሚያሳየው፤ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶችና መነሻ ምክንያቶች ከሚያደርሱት ተፅዕኖ ጋር ያላቸውን ተዛምዶና አመክንዮ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚባሉት ሱስ አስያዥ ዕፆችንና አልኮል መጠጦችን መጠቀም፣ የቀን፣የምሽትና የራቁት ሞዴፈራ ቤቶችን መጠቀም፣ ግብረሰዶማዊነት፣ የግለኝነት አስተሳሰብና ያልተገባ የአለባበስ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ በትስስሩ መሰረት እነዚህ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲከሰቱና እንዲደራጁ የሚያደርጉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ማህበራዊ፣ ስነልቡናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ዓለምአቀፋዊነት፣የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ መረቦች፣ የአላስፈላጊ ድርጊቶች መፈጸሚያ ቦታዎች መስፋፋትና የፖሊሲና የህግ ክፍተት መኖርና የተፈጻሚነት መላላት የሚሉት በምክንያትነት የተነሱ ሲሆን ምክንያቶቹ በራሳቸው አንዱ ከሌላው ጋር ተያያዥነት ያላቸውና የአንዱ መከሰት ለሌላው ምክንያት የሚሆኑ ናቸው፡፡

በመቀጠል ከላይ በተዘረዘሩት ነገሮች ምክንያትነት የተከሰቱት መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በማህበረሰቡ በተለይም፤ በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያስከትሏቸው የተለያዩ ተፅዕኖዎች አለ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱት ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቡናዊ እና የፀጥታ ተፅዕኖዎች ሲሆኑ፤ እነዚህም አንዱ ለሌላው ምክንያት የሚሆኑና የተሳሰሩ ናቸው፡፡

## *የሀሳቦች ትስስር ማሳያ*



## 2.2. የተዛማጅ ጹሑፎች ክለሳ

### 2.2.1. የባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች ምንነት

#### ሀ. የባህል ምንነት

ባህል የሚለዉ ጽንሰ ሀሳብ አጅግ ሠፊና በርካታ ጉዳዮችን አካቶ የያዘ ሲሆን፤ እንደየሙያ ዘርፉም የተለያየ ግንዛቤ ሲኖረውና ትርጉም ሲሰጠው ቆይቷል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ ሣይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በሜክሲኮ በ1982 ባካሄደው ዓለም አቀፍ የባህል ፖሊሲ ጉባኤ ስምምነት ላይ በደረሰው መሰረት፤ የኢፌዴሪ የባህል ፖሊሲ ባህልን፤

> *...የሰዉ ልጅ ሰብአዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንዲሆን ያስቻሉት ወይም ከሌሎች ፍጡራን ለመለየት ያበቁት ማንኛዎቹም ሥነ-ምግባራዊ፣አካላዊ፣ፖለቲካዊና ሌሎቹም ሥራዎች ሁሉ እንዲሁም የሰዉ ልጅን የመማር በሞራል፣በቴክኒክና በአእምሮ እውቀት ራሱን የማሰልጠን ሁኔታዎችን የሚያጠቃልል ነዉ፡፡ እንዲሁም አንዱ ህዝብ ከሌለዉ ተለይቶ የሚታወቅባቸዉን የአኗኗር ዘይቤዎችን፣ እምነቶችን፣ ትውፊቶችን፣ በአጠቃላይም ቁሳዊና ህሊናዊ ሀብቶችን የሚያካትት ሠፊ ፅንሰ ሀሳብ ነዉ...* (1995 ዓ.ም.፡ ገጽ 5) ይላል፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላትም፤ ባህልን፤ የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ፣ ወግ፣ ልምድ፣ እምነትና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ሲል (1993 ዓ.ም) ይፈታዋል ፡፡ በዚህ መሰረት ባህል፤ የአንድ ሀገር ህዝብ፣ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደየሚኖሩበት አካባቢ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የመግባቢያ ቋንቋዎቻቸው፣ አመጋገብና አለባበስ ሥርዓታቸው፣ የሥራና ልምድና የአኗኗር ፍልስፍና ዘይቤዎቻቸው መስመራዊነታቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ የሚደረግበት የጋራ መግባባት መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ሀብታሙ በጽሑፋቸው፤ ባህል ተለጣጣቂና ተከታታይነት ያለው ጉዳይ መሆኑን ሲያጠናክሩ፤ ባህል ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ የሚተላለፍ፤ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ተቀባይነት ያለው፤ የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘዴ፤ (ታሪክ፤ ቋንቋ፤ ሥነምግባር፤ማህበራዊ ግንኙነቶች፤የማምረቻና የመጠቀሚያ መሳሪያዎች፤ የምግብ፤ የመጠጥና የአልባሳት አሠራርና አጠቃቀም፤ወዘተ...)፤ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ቁሳዊ ሁኔታዎቹን፤ አመለካከቶቹንና ልማዳዊ ድርጊቶቹን ሁሉ ያጠቃልላል ሲሉ(1996 ዓ.ም) ይገልጻሉ፡፡በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት የንድፈ ሀሳብ ብያኔዎች የምንረዳው፤ባህል ህዝቦች በማህበራዊ ኑሯቸው ውስጥ እርስ በእርስቸው በሚያደርጉት ግንኙነቶች የሚማሩት የሚለዋወጡትና የሚያዳብሩት መሆኑን ነው፡፡

### ለ. የልማድ ምንነት

ልማድ ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ሁነት ሆን ተብሎም ይሁን በአጋጣሚ በተደጋገሚ በአንድ ግለሰብ ወይም በማህበረሰብ ሲከወን፤ ሲሠራ፤ ወይም ሲነገር ለዚያ ሁኔታ ወይም ሁነት የሚሰጥ ስያሜ ነው በማለት በ(Dorson,1972) መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ልማድ በመደረግ፤ በመገለጽ፤ በመከወን እና በመነገር የሚተላለፍ በዘር ፤በቀዬ ፤በክልል ፤በሥራ ፤በሃይማኖት፤ በያታ ወይም በዕድሜ ተለይተው ሊቆሙ ለሚችሉ ቡድኖች መታወቂያ እንደሆነ (አዳነች አበራ፡ 2001 ዓ.ም) በጥናታቸው ጠቅሰዋል፡፡

የልማዳዊ ድርጊቶች መከወኛ ቡድኖች ከተሰበሰቡበት ዓላማና ከሚፈጽሟቸው ክዋኔዎች ይዘት በመነጨ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ሀገረሰባዊ/ባህላዊ ቡድን ሲሆን፤ የራሱ የሆነ ያልተፃፈ ህግና መመሪያ ኖሮት፤ “ተው”ብሎ የሚከለክልበት፤ “ሽጋ” ብሎ የሚያበረታታበት፤ “እደግ” ብሎ የሚመረቅበት፤እሴት/አግባብ አለው፡፡ሁለተኛው ደግሞ በሥራ ወይም አንዳች ተግባር ለመፈጸም የሚግባቡበት የጋራ የሆነ ጉዳይ ያላቸው ቡድኖች ወይም የማህበረሰብ ክፍሎች ስብስብ ሲሆን፤ “ነውር” የሚባለውን በአንድ “ጥሩ” የሚባለውን በሌላ ወገን ለመመደብ የሚያስችል ልማዳዊ መመሪያ የላቸውም በማለት (አዳነች ካሣ፡2002 ዓ.ም) በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡

### 2.2.2. ባህልና ልማድ ከኢትዮጵያ አንፃር

ባህልና ልማድን፤ የበርካታ ብሔር፤ብሔሰቦችና ሕዝቦች መገኛ ከሆነችው ኢትዮጵያ አንፃር ስንመለከተው፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች አንዳቸው ከአንዳቸው የሚለዩበትን፤ ማህበራዊና ሥነልቦናዊ ሁኔታዎቻቸውን፤ ታሪክና ቋንቋቸውን፤ልብስና የአለባበስ ሥርዓታቸውን፤ ምግብና የአመጋገብ፤ እንዲሁም የአጠጣጥ ሥርዓታቸውን፤ የአለባበስ፣ አጊያጌጥና የሥነውበት ግንዛቤያቸውን፤ ሃይማኖታዊና የእምነት ቱውፊቶቻቸውን፤ ከወሊድ ከሠርግና ከሞት ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎቻቸውን፤ በዝምድና፤ በጉርብትናና በሌሎችም ግንኙነቶች ላይ የተመሠረተ መተጋገዝና መተሳሰባቸውን፤ መጥፎውን ከደግ የሚለዩበት፤ የሚያስተምሩና የሚገስጹበት ባህላዊ የአስተዳደር/የዳኝነት ሕግና ሥርዓቶቻቸውን፤ እንዲሁም ሀገረሰብአዊ የጤና አጠባበቅ ዘዴዎቻቸውን ሁሉ ማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የልጆች አስተዳደግ የቤተሰብም ሆነ የህብረተሰብ አመራር ሥርዓታቸውን

በአጠቃላይ እየኖሩባቸው ያሉ በራስ ማንነት ላይ የተመሠረቱ የአኗኗር ዘይቤና ልማዶቻቸውን ሁሉ ያጠቃልላል በማለት (እንደቀደመው) አመልክተዋል፡፡

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ጉዳይ ከላይ የተጠቀሱት የየማህበረሰቡ እሴት የሆኑ ባህላዊ ክዋኔዎች ከማንነት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ የአንድ ህዝብ/ብሔርና ብሔረሰብ መለያ ምልክቶች ናቸው፡፡ ይህን አስመልክቶ Mathisen,Fekade የማስተማሪያ ጥራዝ ውስጥ ሲገልጽ ማንነት በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው የማንነት ጽንሰሀሳብ የነገሮች በተመሳሳይ መልኩ መቀጠል ወይም የቀጣይነት ስሜት ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ከሌሎች ተለይቶ መታየት ነው (2003) ይላል፡፡

ሌላው የ"ፎክሎር"/ባህል ጥናት ምሁር Johonsonንም ማንነትን አስመልክቶ በDundes ጥናት ውስጥ ሲያብራራ፤ ማንነት በግለሰብ አልያም በህብረተሰብ ደረጃ ሊገለፅ ይችላል፡፡ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች በሚጋሯቸው የጋራ ጉዳዮች መኖር ምክንያት ሀገራዊ ማንነት ይፈጠራል፡፡ ይኸውም ከሌላው አካል እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋቸዋል(1965)፡፡ የየማህበረሰቡን ማንነትም አጉልተው ሊያሳዩ የሚችሉ በርካታ የባህል መገለጫዎች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ አለባበስ ሲሆን እንደማሳያነትም ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

የአንድ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ልብስ ነው፡፡ ልብሶችም የአንድን ሰው ሴትም ሆነ ወንድ/ወጣት ሀገራዊ፣ ጎሳዊና ክልላዊ አልያም ክልላዊነትን ሊነግሩን ይችላሉ ስትል የኔዓለም(2000 ዓ.ም) በጥናቷ ገልጻለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Lurie (1981) ልብስን የምንለብሰው የሥራም ሆነ የኑሮ ሁኔታችንን ጤናማ ለማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ማንነታችንን ለማሳየትና ሌሎችን ለመሳብ ሲባል ነው በማለት አስቀምጦታል፡፡ ልብስ የሚለበስበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ከማንነት ጋር በእጅጉ የተያያዘ መሆኑን Lurie, ሲገልጽ፤ አልባሳት ያግባባሉ፤ ቁሳዊ ተግባቦት ከቃላዊ የበለጠ የማግባባት አቅም አለው፡፡ በመሆኑም የአለባበስ ሁኔታን በማየት የግለሰብ ብሎም የማህበረሰብ ማንነትን መገመት እና  መናገር ይቻላል፡፡ ሌላው ልብስን የመልበሻ ምክንያት ተብሎ በሦስተኛነት የተገለጸው የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ነው የሚል ሲሆን በአራተኛነት የተነሳው ደግሞ ከሰዎች ኑሮ ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው አልባሳት የማግባባት አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የአንድን ሰው የኑሮ ደረጃና ማህበራዊ ሥፍራ በአልባሳት አማካኝነት መረዳት ይቻላል ሲል ያብራራል፡፡

ከላይ ለመመልከት እንደተቻለው የአንድ ህዝብ ማንነት በመጠቀሚያ ቁሶቹ እንደሚለይ ነው፡፡ የበርካታ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያ/ኢትዮጵያውያንም መለያ የሆኑ ዓይነታቸው የበዛ አልባሳት፣ምግብና የአመጋገብ ስርዓት በአጠቃላይ ቁሳዊ፣ መንፈሳዊና ቃላዊ ሀብቶች አሉ፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ጠንካራ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቦናዊ ፋይዳ ያላቸው የባህል እሴቶች አሁንም የነበረ ባህላዊ መሠረታቸውን እንደያዙ በሀገራችን አሉ ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ በተጨባጩ ሀገራዊና ዓለምአቀፋዊ ያኗኗር ዘይቤ ለውጥ አስገዳጅነት ምክንያት ያስተናገዷቸው ለውጦች አሉ፤ ለምን “ባህል ትኑ ትክል አይደለም”፤በጊዜና ሁኔታዎች አስገዳጅነት ለውጥን ያስተናግዳል፡፡ በለውጡም ወይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ሊገኝ ይችላል ሲለ (ፈቃደ በአዳነች ውስጥ፣ 2002 ዓ.ም)ያስገነዝባሉ፡፡

ሌላው ምሁር Chalfart (1988) ደግሞ ይህንን ሀሳብ በጥናቱ ሲያጠናክር ከጊዜ ጋር የለውጦች መታየት የባህል ቋሚ ባህሪና እውነታ ነው ይልና የዚህን ምክንያት ሲገልጽ “ለውጥ የተፈጥሮ ሕግ ነውና”፤ በማለት ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም የRosenberg(1987) ጥናት ሲያብራራ የባህል ለውጥን ከሚያፋጥኑ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ቴክኖሎጂ መሆኑን ጠቅሶ፤ ቴክኖሎጂ መረጃን ለማሰራጨትና ግንኙነትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡ በአንጻሩ ግን መገናኛ ብዙሃንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የማህበረሰብን ግንኙነትና የዕለት ከዕለት ህይወትን ለውጥ የሚያፋጥኑ እንደሆኑ ሰዎች ሊያውቁ ይገባል በማለት ይጠቁማል፡፡ አክሎም፤ አጠቃቀማቸው ግን ጤናማና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ፤ ዕድገትና ብልጽግናን በሚያፋጥን መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡”በተለይም የሰው ሀብት ብልጽግናን”፤ካልሆነ ጥፋቱ ወይም ውድቀቱ ያመዝናልና ጥንቃቄና ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል ሲል ያሳስባል፡፡

ከላይ በተነሱት ንድፈ ሀሳቦች ውስጥ ቴክኖሎጂን አስመልክቶ ሁለት ነጥቦች ተነስተዋል፡፡ የመጀመሪያው ቴክኖሎጂ ለማህበራዊ ግንኙነትም ሆነ፤ ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የሚገልጽ ነው፡፡ ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ፤ እነዚህ ለማህበረሰብ ግንኙነት፣ ለሰው ልጅ ህይወት መለወጥና ማደግ ጠቀሜታቸው የጎላ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አጠቃቀም

ላይ ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ነው። ቴክኖሎጂ የሰው ልጅ አኗኗርን ቀላል ለማድረግና ወደ ስልጣኔ ለማምራት የግድ አስፈላጊና የማለፊያ መስመሩም ነው። በመሆኑም በውስጡ ማለፍ የግድ ይሆናል። ኢትዮጵያ/አዲስ አበባ /ም የራሷን ታሪክ፣ ባህልና እምነት ጠብቃ የኖረች ቢሆንም፤ ከተጨባጩ ዓለምአቀፋዊ ሁኔታ ማምለጥ ስለማይቻል ለነዚህ የሳይንስ ውጤቶች መግባት በሯን ዝግ አታደርግም።

ስለዚህ የተፈጥሮ ህግ የሆነውን ለውጥ፤ ትውልድን ሊታደግ በሚችል አግባብ ተቀብሎ ማስተናገድ ይቻል ዘንድ፤ ቀዳሚው ተግባር የማህበረሰቡ አስተሳሰብ/አመለካከት ላይ መስራት ይሆናል። ነባርና ጠቃሚ የማህበረሰቡን ባህላዊ/ማንነት/ እሴቶች በመጠበቅ ከመጪውም ጠቃሚ ጠቃሚውን መርጦ በነባሩ ላይ በመጨመር መጠቀም ተገቢ ይሆናል።

## 2.3. ወጣቶችና ሴቶች ከልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ያላቸው ትስስር አጠቃላይ ሁኔታ

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ወጣቶች ሁሉን ነገር ለማወቅ ካላቸው ጉጉት የተነሳ ሀገር በቀል ለሆኑም ሆነ ከሀገር ውጪ ለሚመጡ ልማዳዊ ድርጊቶች (ለአደንዛዥ እጾች፣ለትንባሆ፣ ለአልኮል መጠጥና ለልዩ ልዩ ሱሶች) የሚጋለጡበት ሁኔታ ይበዛል። ለምሳሌ፡- አጥኚዎች እንደገለጹት በአሜሪካን ሀገር ከጠቅላላው ወጣቶች ቁጥር ግማሽ ያህሉ የመጠጥ እና የተለያዩ አደንዛዥ እፆች ተጠቃሚ ሲሆኑ ወጣቶቹ ወደነዚህ ጎጂ ድርጊቶች ውስጥ የሚገቡበትን ምክንያት አንድም ለመነቃቃት በሌላ በኩልም ጭንቀትን ለማስወገድ ሲሆን ወደነዚህ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚገቡት በአብዛኛው እድሜያቸው ከ12 እስከ 17 የሆኑት ታዳጊዎች መሆናቸውን (Jan, Nssi እና RN.BS, 2008) ገልጸዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ Lopezና Costa የታዳጊ ወጣትነት እድሜ ለሕይወት አደገኛ የሆኑ ባህሪያትን ለምሳሌ እንደ አደንዛዥ እጽ ያሉትን ነገሮች ለመጀመር ምቹ እና ተጋላጭ የሆነ የእድሜ ክልል ነው በማለት (2008) ያስቀምጡታል።

በአሜሪካ እና በካናዳ በዓመት በጠቅላላው በመጠጥ ምክንያት ከ100,000 በላይ ወጣቶችና ሴቶች እንደሚሞቱ (Professional Guide to Starting a Day Care) በተባለ መመሪያ ተጠቁሟል።

ጫት ካታ ኢዱሊስ ፎርስክ (Catha edulis forsk) የተባለ ትኩስ ቅጠሎችን እና ግንዶችን በያዘበት ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውል የአትክልት አይነት ሲሆን በኢትዮጵያ፣ በኬንያና በሶማሊያ አገር በቀል ተክል ሆኖ በሰፊው የሚዘወተር የዕፅ ዓይነት እንደሆነ (እያሱ,2005)

በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡ ጸሐፊው አክለውም ከ10 ዓመት ገደማ በፊት በተወሰደ መረጃ 50% በሚሆነው የኢትዮጵያ ክፍል በተለይም በከተሞች አካባቢ የሚዘወተር ሲሆን፣ ወጣቶችና ሴቶች ችግሩ በስፋት የሚስተዋልባቸው የህብረተሰብ ክፍል መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል ሱስ አስያዥ ዕፆችንና አልኮልን የመጠቀም ሁኔታ እያደገ ከመሄዱ ጎን ለጎን አየተስፋፋ የሄደው ችግር ከዕፆች የሚገኘውን የጊዜያዊ ደስታ ስሜት ለማሳደግ እየተባለ ዕፆቹን አየቀላቀለ የመጠቀም ሁኔታ ነው፡፡ ከነዚህም ልምዶች ውስጥ አዲስ አበባን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወነ ጥናት እንደሚያሳየው ቶባኮን ከካናቢስ፣ ጫትን ከቶባኮና አልኮል ጋር፣ ጫትን ከቶባኮና ጠላ ወይም ጠጅ ጋር፣ ጫትን ከቡና ወይም ሻይ ጋር፣ ቶባኮን ከአልኮልና ቤኒዚን ጋር፣ ጫትን ከካናቢስና አልኮል ጋር እና ጫትን ከቶባኮ ጋር ቀላቅሎ የመጠቀም ሁኔታዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጫት፣ ቶባኮ፣ ካናቢስና ኮኪይን ወይም ሄሮይንን ቀላቅሎ የመጠቀም ሁኔታም በተወሰነ ደረጃ እንዳለ ተገልጿል፡፡ በየጊዜው ከሚያዙ አንፊታማይን(Amphetamine)፣ ባርቢቹሬተስ(Barbiturates)፣ ካናቢስ፣ ኮኬይን፣ ሞርፊን/morphine/ እና ሊሰርጂክ-አሲድ/Lysergic acid/ ከሚባሉ ዕፆች ውስጥ ካናቢስ/አፀፋሪስ/ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ የነዚህ አደገኛ ዕፆች አጠቃቀም ቀለል ያሉ እንደ ጫት ያሉ ዕፆች መጠቀሚያ ቦታዎችን እንደሸፋን በማድረግ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ የህግ ቁጥጥር የመኖርና ያለመኖር ሁኔታም በዕፆቹ ዝውውርና መጠቀም ስፋት ላይ ተፅእኖ ማሳደሩ በ (ሥዩም,1996) ተገልጿል ፡፡

## 2.4. ሱስ አስያዥ ዕፆችን የሚጠቀሙ ወጣቶችና ሴቶች ልዩ ባሕሪያት

ሱስ አስያዥ ዕፅ የሚጠቀሙ ሰዎች ከዚያ በፊት በተፈጥሮ እና በሂደት ካዳበሩት አንፃራዊ የሆነ ጤነኛ ባሕሪ ለየት ባለ ሁኔታ እነርሱነታቸውን በመቀየር ዕፁ በሚያሳድርባቸው ተፅዕኖ ምክንያት በሕብረተሰቡ የማይፈለጉ ወይም ነውር የሆኑ ባሕሪያትን እንዲፈጽሙ እና የወሰዱት ባእድ ነገር በመራቸው ሁኔታ እና ቦታ ላይ ሊያውላቸው ይችላል፡፡ በተለይ መጠጥ የሚጠቀሙ ወጣቶች የሚታይባቸውን ባህሪን በተመለከተ፤ The Higher Education Center for Alcohol and other Drug Abuse and Violence Prevention የተሰኘ ህትመት፤ ዱለኞች፤ተደባዳቢዎች፣ አጉራ ዘላሎች፣አስገድዶ ደፋሪዎች፣ሕገወጥ ወሲብ ፈፃሚዎች፣ እና አዋኪዎች ናቸው (2010) በማለት ያብራራዋል፡፡

## 2.5. ወጣቶችና ሴቶችን ወደ መጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚገፋፉ ምክንያቶች

### 2.5.1. ዓለምአቀፋዊነት

ዓለምአቀፋዊነት በተለያዩ የአለም ክፍል የሚኖሩ ህዝቦች የየራሳቸው ባህል፣ ቋንቋና የአኗኗር ዘይቤ ቢኖራቸውም በፍጥነት እየተስፋፋ ባለው የመገናኛና የትራንስፖርት እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት የመተሳሰርና የመወራረስ ሁኔታን የሚወክል ነው፡፡ በማለት(Zuckerman, D. and Dubowitz, N. (2005) ይገልፃል፡፡

ዓለምአቀፋዊነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የጋራ ማህበረሰባዊ ዕሴቶችን ለመፍጠር የሚያስችል ሂደት ነው (UN,1999)፡፡ ነገርግን ዓለማቀፋዊነት ያለው አወንታዊ ተፅዕኖ የጎላ ቢሆንም በአንጻሩ ደግሞ አሉታዊ ጎንም አለው፡፡ ከዚህ አኳያ UNESCO በ2004 ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ዓለምአቀፋዊነት በታዳጊ ሀገሮች እያስከተለ ያለው ተጽዕኖ በዝርዝር ተነስቷል፡፡ ለምሳሌ፡- የአልጀሪያ፣ የሊቢያና የፊንላንድ ተወካዮች ዓለምአቀፋዊነት የታዳጊ ሀገሮችን የአኗኗር ዘይቤ እየጎዳ መሆኑን አትተው ይህንንም ለመቋቋም እ.ኤ.አ. በ1995 በኮፐንሃገን የጸደቀው የማህበራዊ ልማት ፕሮግራም በበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ስራ ላይ መዋል እንደሚገባው አንስተዋል( 59th General Assembly 3rd Committee Report, 2004)፡፡

በአጠቃላይ በጉባኤው ሴቶችና ወጣቶች የራሳቸው ባልሆነ ልማድ እየተጠመዱና የሃገራቸውን ባህል የሚጣረስና ንቃተ ህሊናቸውን ባልመጠነ መልኩ እየተገበሩ ያሉት ድርጊት ባሳደረባቸው ተጽዕኖ ራሳቸውንም ብሎም ህብረተሰቡን እየጎዳ እንደሆነ አስረድተዋል (እንደቀደመው)፡፡

Douglas የተባለ ተመራማሪ እንዳስቀመጠው ዓለምአቀፋዊነት በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መስተጋብር ወይም ህይወት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ እንደተመራማሪው አባባል ዓለምአቀፋዊነት የማህበራዊ መስተጋብርንና እሴትን ለውጥ የሚያፋጥን ክስተት ሲሆን፤ ይህ የማህበራዊ መስተጋብር ለውጥ በዓለምአቀፍ ደረጃ ግለሰባዊና ሀገራዊ ማንነትን ቦታ የሚያሳጣ ነው (2008) ፡፡

ለዓለምአቀፋዊነት አሉታዊ ተፅዕኖ ቀጥተኛና ዋና ሰለባ የሆነው ወጣቱ ክፍል ሲሆን በዚህ ተፅዕኖ ስር እንዲገባ የሚያደርጉት የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎቹ እንደሆኑ ጥናቶች

ያሳያለ፡፡ እነዚህ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎች የሚባሉት፤ የወጣቶቹ የሥራ ቦታና ሁኔታ፣ የጓደኞቻቸው ብዛትና ባህርይ፣ ለኢንተርኔት ያላቸው ቅርበት፣ ያላቸው ማህበራዊ መስተጋብር፣ ለተለያዩ ብዙና ሰፊ የባህል ተፅዕኖዎች ያላቸው ተጋላጭነትና የአኗኗር ዘይቤያቸው ለሌሎችም የዓለምአቀፋዊነት ተፅዕኖ ያላቸውን ተጋላጭነትን የሚያጠናክሩ ክስተቶች ናቸው (Kenway & Bullen, 2008) ፡፡

ዓለምአቀፋዊነት ወጣቶችን በተለያየ መልኩ በተፅዕኖው ስር የሚያስገባቸው ሲሆን ብዙ ጊዜ ስለማንነታቸውና በማህበረሰቡ ውስጥ ስላላቸው ሚና ቦታ እንዲያስቡና እንዲያሰላስሉ የሚያስገድድ ኃይል አለው፡፡ Jeffrey የተባለች የጥናት ባለሙያ እንዳስቀመጠችው ዓለምአቀፋዊነት በወጣቶች ላይ የስነ-ልቡናዊ፣ ማህበራዊና የባህል ተፅዕኖዎች ያሳድራል(2002)፡፡ በተጨማሪም ዓለምአቀፋዊነት የሀገሮችን ድንበር ክፍት እንዲሆን ባደረገው አስተዋፅዖና ሴቶች ባላቸው ዝቅተኛ የትምህርትና የኢኮኖሚ አቅም የተነሳ ለስደትና ለሴተኛ አዳሪነት እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል Ilanna(2008)፡፡

### 2.5.2. መገናኛ ብዙሃን

የመገናኛ ብዙሃንን መቆጣጠር ማለት መልካም ገጽታን ግንባታና ባህልን መጠበቅ ማለት ነው ሲሉ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡ በተለይ የመገናኛ ብዙሃን በሴቶችና ወጣቶች ላይ የሚያስከትሉት ተጽእኖ ዘርፈ ብዙ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ የሙዚቃ ፊልሞች፣ የታዋቂ ሰዎች ስብእና፣ አለባበስ፣ ባህሪ፣ የአኗኗር ዘይቤ የመሳሰሉት ሴቶችንና በተለይ ወጣቶችን በእጅጉ ሲጎዱ ይስተዋላል፡፡ (Underwood, 2000፤ Glen, 2003):: የተፅዕኖ መጠናቸው እንደየመገናኛ ብዙሃኑ ባህሪ የሚለያይ ቢሆንም ሁሉም ባህልንና መልካም ገጽታን የመገንባት ወይም የማበላሸት ሚናቸው የላቀ ነው፡፡

#### ሀ. የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ

በመገናኛ ብዙሃን በተለይም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ተጽእኖ የተነሳ ወጣቶችና ሴቶች ለተለያዩ የባህሪና የወንጀል ድርጊቶች እየተጋለጡ ይገኛሉ፡፡በተለይም በአሜሪካን ሀገር ከ1994 ጀምሮ በወጣቶች የተፈጸሙ የግድያ፣ድብደባና፣አስገድዶ መድፈር ወንጀሎች ቁጥር እየጨመሩ ሲሆን ለነዚህ ወንጀሎች እንደ ምክንያት የተነሳው የመገናኛ ብዙሃን ተጽእኖ መሆኑ ተነስቷል፡፡ ለምሳሌ አንድ ፖሊስ ገድሎ የተያዘ ወጣት ለምን ወንጀሉን

እንደፊጸመ ለፍርድ ቤት ሲገልፅ የቱፓክ ሻኩር ዘፈን የሆነው “2 pacalypse” የተሰኘውና ፖሊስ ስለመግደል ጀብደኝነት የሚያወሳ ዘፈን ተገፋፍቶ እንደሆነ ጥናቶች ገልጸዋል (Glen, 2003)። ጥናቶች የአሜሪካ ብሄራዊ የመገናኛ ብዙሃንና የቤተሰብ ተቋምን (National Media and Family Institute) ጠቅሰው ሲተነትኑ የአሜሪካ ወጣቶች በሳምንት 22 ሰዓት ቲቪ በማየት እንዲሁም ሌላ 22 ሰዓት ደግሞ ሙዚቃ በማድመጥ ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ይህም ሁኔታ በአስተሳሰብና አኗኗራቸው ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሯል (Cashmore, 2006)።

በተጨማሪም በአብዛኛው በቴሌቪዥን በሚተላለፉ የአመፅና የብጥብጥ ፕሮግራሞች በወጣቶችና ሴቶች ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ የንዴት ባህሪ የመጨመር አጋጣሚው የሰፋ እንደሆነና በረዥም ጊዜም ለማይታወቅ አደገኛ ለሆነ የነውጥ ባህሪ እንዲኖራቸው የራሱ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድራል (እንደቀደመው) ።

### ለ. የመረጃና የመገናኛ ዘዴዎች

የመገናኛ ዘዴዎች እንደ ኢንተርኔት፣ስልክ፣የቪድዮ ጫወታዎችና የመሳሰሉትን ያካትታል። ከአንድ የማህበረሰብ ድረ- ገጽ የተገኘ ጥናት፤ የነዚህን ዘዴዎች ተጽዕኖ ሲያብራራ፤ በ1946 የመጀመሪያው ዲጂታል ኮምፒውተር ሥራ ላይ ከዋለበት ግዜ ጀምሮ ተጽዕኖውም ከሰው ልጅ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ፤ በመኖሪያ ቤት፣ በትምህርት ቤት፣ በቢሮዎችና በመዝናኛ ስፍራዎች ጭምር በእጅጉ አይሎ መስተዋሉን (Dawursk, 2003)ያሳያል። እነዚህ የመረጃና መገናኛ ዘዴዎች የሰው ልጆች ከተለያየ ስፍራ በቀላሉ እንዲገናኙ እያገዘ ይገኛል። ይሁን እንጂ በነዚህ ዘዴዎች የሚተላለፉ መልዕክቶች አላስፈላጊና የህብረተሰባችንን ባህል ያልጠበቁ ናቸው።

### ሐ. የህትመት ውጤቶች

የህትመት መገናኛ ውጤት የሆኑት እንደ መጽሄቶችና ጋዜጦች በተለይም ትኩረታቸው በፋሽን፣ውበትና የተቃራኒ ጾታ ፍቅር ላይ የሆኑ፤ በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ እጅግ የጎላ ነው። ለምሳሌ- የታዋቂ ሰዎች አለባበስ፤ ጸጉር አስራር፣ የመዝናኛ ማዘውተሪያ እና ግለ ታሪክ በነዚህ የህትመት ውጤቶች ላይ በስፋት ይወጣል። ይህም ወጣቶችና ሴቶች ላይ ከፍተኛ ጉጉትን ስለሚያሳድር ሲተገብሩት በአስተሳሰባቸዉ፣በአለባበሳቸው፣በትምህርታቸው፣ በጤናቸው እና ባጠቃላይ በማህበራዊ ህይወታቸው ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥርባቸዋል (Thomsen, Welber እና Brown 2002)።

### 2.5.3. የታዋቂ ሰዎች/ዝነኞች ተፅዕኖ

ብዙ ሴቶችና ወጣቶች በተለያየ የመገናኛና የህትመት ውጤቶች በሚያዩአቸውና በሚያነቧቸው የታዋቂ ሰዎች አኗኗርና ድርጊት ይመሠጣለ፡፡ይህም ከተጨባጩ ዓለምና የእነርሱ አኗኗር ሁኔታ ጋር ባይጣጣምም ይተገብሩታል፡፡በዚህም በእጅጉ ለተዛባ የአኗኗር ሁኔታ ሲጋለጡ ይታያሉ (Cashmore, 2006.):: ከዚህም በተጨማሪ Thomsen እና Brown የነዚህ ታዋቂ ሰዎች ተፅዕኖ ለአንዳንድ ወጣቶችና ሴቶች እንደ ሀይማኖት አስከ መከተል ሲያደርሳቸው ተስተውሏል፡፡ ለዚህም ከተሰጠዉ የተጋነነ ትኩረት የተነሳ ተዛማጅ ለሆኑ ጎጂ ድርጊቶች ማለትም፡-ለዕፅ ተጠቃሚነት መጋለጥ፤በመጠጥ ሱስ መውደቅ፤ብዙ የወሲብ ጓደኞችን መያዝና ጥንቃቄ ለጎደለው ወሲብ መጋለጥ ወዘተ... እንደዳረጋቸው ተገልጿል(2002)፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ጎጂ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ የባህሪ መበላሸት፤ የህብረተሰቡን ልማድ መጣስ፤ ነውጠኝነት፤ እራስን ማጥፋት፤ ሱሰኝነት፤ ሥራ መጥላት፤ አደገኛ የወሲብ ባህሪና የመሳሰሉት አለታዊ ተፅዕኖዎች መድረሳቸዉ ተጠቅሷል (Jennifer, 2005; Strasburg & Wilson 2002)፡፡

### 2.5.4. የዕፅና የአልኮል ነፃ ዝውውር

የተባበሩት መንግስታት የአደገኛ ዕፅ ቁጥጥር ክፍል ያቀረበው ጥናት እንደሚያሳየው አነቃቂ ዕፆችን(psychotropic substances) እንደ ጫት፣ ካናቢስ (ዕፀፋሪስ) እና የሌሎች ተዛማጅ ዕፆችን ስርጭት በተመለከተ እድሜቸው ከ15 እሰከ 29 ዓመት ያሉ ወጣቶች ዕፁን በማሰራጨትና በመጠቀም በዋነኝነት ተዋናይ መሆናቸዉ ተገልጿል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እነዚህን ዕፆች ከማዘዋወር፤ ከመጠቀምና ከማምረት ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ የጨመሩበት ሁኔታ እንዳለ ፤(ሥዩም,1996) ተጠቁሟል፡፡

በሀገራችን በሱስ አስያዥ ዕፅ ዙሪያ በስፋት የተጠኑ ጥናቶች ባይኖሩም በ1995 እ.ኤ.አ በተመረጡ 25 በሚሆኑ የኢትዮጵያ ከተሞች እስከ 3200 ተሳታፊዎችን ያካተተ ጥናት እንዳሳየው ሃሺሽ፣ ጫት፣ አልኮል፣ ትምባሆ እና በትንፋሽ የሚወሰዱ ዕፆች በሁሉም ማህበረሰብ እንደሚጠቀሙ በጥናቱ ታይቷል፡፡ ጫት መጠቀም ለረዥም ጊዜ ከባህልና ልምድ ጋር በተያያዘ በጥቂት ቦታዎች የቆዬ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን በሚያስገርም ፍጥነት በወጣቱ ዘንድ፤ ሃይማኖትና ባህል ሳይገድበው በመስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ ጫት

በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች እየተስፋፋ ያለ ተክል ሲሆን ከኢትዮጵያ ወደ ውጪ ከሚላኩት የተክል አይነቶች ከቡና ቀጥሎ ሁለተኛውን ደረጃ ይይዛል(ኃይሉ, 2002 ዓ.ም)።

በአዲስ አበባ ተጨባጭ ሁኔታም ወጣቶችና ሴቶች በብዙዎች ዘንድ ከተለመዱት ጫት እና መጠጥ ጀምሮ አደገኛ የአደንዛዥ እፆችን እስከ መጠቀም እና በትምህርት ተቋማት ሳይቀር እስከማዘዋወር የተደረሰበት ሁኔታ እንዳለ በአዲስ አበባ ትምህት ቢሮ በ2002 እና በ2003 ዓ.ም የተጠኑ ጥናቶች ያመላክታሉ።

### 2.5.5. ማህበራዊ ምክንያቶች

#### ሀ. የቤተሰብ ሁኔታ

ወጣቶችንና ሴቶችን ለመጤ ደባል ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ከሚገፋፏቸዉ ምክንያቶች አንዱ ልጆችና ቤተሰብ ያላቸዉን መብትና ግዴታ ጠንቅቀዉ ካለመገንዘብ የመነጨ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ (Balderu, 2002)። እንደ ጥናቱ አባባል ወጣቶችና ቤተሰብ ተመሳሳይ መብትና ግዴታዎች ሲኖራቸው ወጣቶችና ሴቶች ሀሳባቸውን የመግለጽ፤ የመደመጥና የማዳመጥ፤ የሌሎችን ሃሳብ የማክበር፤ ከወላጆቻቸዉ ምክር የማግኘት መብት አላቸው።በተመሳሳይ መልኩ ወላጆች ልጆቻቸውን የመምከር፤ጥሩውን ከመጥፎ ለይቶ የማስተማር፤የልጆችን ክብርና ሥነ-ልቦና በማይነካ መልኩ፤ ሥነ-ምግባር የተላበሱና የመጭዉን ትዉልድ የሚረከቡ ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት አለባቸዉ። ይህ ከሆነ ወጣቶችና ሴቶች ፍቅር የሚያድርባቸው፤የሌሎችን ሃሳብ የሚያከብሩ፤ በራሳቸው የሚተማመኑና ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር የሚችሉ ይሆናሉ። በዚህ ውስጥ የሚያልፉ ወጣቶችና ሴቶች ፈታኝ ከሆኑ የወጣትነት መሰናክሎች አምልጠው ከወጡ ኃላፊነትን የሚሸከሙ ሀገር ተረካቢዎች መሆን እንደሚችሉ አስምሮበታል። ሆኖም ግን ሁለቱም ወገኖች መብትና ግዴታቸዉን አዉቀዉ የማይተገብሩ ከሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነቱ የላላና የደፈረሰ ከመሆኑም ባሻገር ወጣቶችም ሆኑ ሴቶች ከቤተሰብ አፈንግጠዉ እንደሚወጡና ለደባል ባህሪያት ተገዥ እንደሚሆኑ ይጠቁማል (Balderu, 2002)።

#### ለ. አካባቢያዊ ሁኔታዎች

Clacherty(2003) እንደጻፈዉ በወጣትነት የዕድሜ ክልል በአብዛኛዉ ወጣቶች እራስን ሆኖ ለመገኘት ሳይሆን ሌሎችን መስሎ ለመታየት የሚፈልጉበት ወቅት በመሆኑ ማድረግ

የሚፈልጉትን ከማድረግ አይቆጠቡም፡፡በመሆኑም ወጣቶች ዕያችንና ልማዳዊ ድርጊቶችን መጠቀም የዘመናዊነት ምልክት አድርገዉ ስለሚቆጥሩ በደረሱበት ዕድሜ መፈጸም ያለባቸዉ ተግባር አድርገው በመውሰድና በአካባቢያቸዉ ካሉ ሌሎች የተግባሩ ተዋንያኖች በመኮረጅ የራሳቸዉ ያልሆነዉን የራሳቸዉ አድርገዉ ሲጠቀሙ ይታያሉ ሲል ያስገነዝባል፡፡

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ የወጣቶችንና የሴቶችን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ የሚያደናቅፉና  ዉሷቸዉን ባልባሌ ቦታ እንዲያሳልፉ የሚገፋፉ አዋኪ ሁኔታዎች እንዳሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ (የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ,2002 እና 2003 ዓ.ም)፡፡ እንደ ጥናቶቹ አባባል በት/ቤቶች አካባቢ ያሉት አዋኪ ሁኔታዎች ወጣት ተማሪዎችን ለአልባሌ ተግባራት የሚገፋፉ መሆናቸው ተገልጿል፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በገበያ አካባቢ በመሆናቸው በተለይ ሴቶች ሲወጡና ሲገቡ ከገበያተኞቹ ጉንተላና የዓታ ግንኙነት ጥያቄ የሚቀርብላቸው መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም በየት/ቤቶቹ አካባቢ ቡና ቤቶች ፣ የሲኒማ፤ የቪዲዮ፤የጫትና የሺሻ መጠቀሚያ ቤቶች እንዳሉም አመላክቷል፡፡ የአንዳንድ ሲኒማ ቤቶች የመግቢያ ዋጋ በሥራ ሰዓት ስለሚቀንስ ብዙ ወጣቶች በትምህርት ሰዓት ከትምህርት ቤት በመቅረት ወደዚህ እንደሚመጡ ጠቅሶ፤ ሲኒማ ቤቶች የወጣቶቹ ዋና መገናኛ ቦታ መሆናቸውንና ከዚያ በኋላም ወደ ዴይ ሆም ፓርቲዎች ወይም ወደፈለጉበት ቦታ በመሄድ አላስፈላጊ ነገሮችን ሲያደርጉ እንደሚውሉ ጥናቱ ያብራራል(እንደቀደመው)፡፡

### ሐ. ሥርዓተ ትምህርት

የተባበሩት መንግሥታት ሪፖርት(2002) እንደሚያሳየው በተለያዩ ሀገራት በትምህርት ቤት የሚገኙ ወጣቶች ለአላስፈላጊ ሱሶች ተጋላጭ መሆናቸው ተገልጿል፡፡ በዚሁ ሪፖርት ላይ ተማሪዎች ከአላስፈላጊ አደገኛ እያችና ሱሶች የጸዱ ሆነዉ እንዲያድጉ የትምህርት ሥርዓቱ (ሥርዓተ ትምህርት) ሲዘጋጅ በወጣቱ ላይ የባህሪ ለዉጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ መሆን እንዳለበትም አመልክቷል ፡፡

በሌላ በኩል በሼና የዕጽ መከላከያ ቢሮ በ(2002) በተደረገ ስብሰባ የአደገኛ ዕጽ ተጠቃሚነትን ለማጥበብ የሚደረገው ትኩረት አናሳ መሆኑ ተገልጿል። በመሆኑም ትምህርት ቤት ተኮር የሆነ የዕጽ ጥቃት መከላከያ ትምህርት ሊኖር እንደሚገባና

የትምህርቱ አቀራረቡም የአደገኛ ሱሶችን የመከላከል ዓላማ ያለው እና በመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ተካቶ መሰጠት እንዳለበት አስገንዝቧል(እንደቀደመው)።

መ. የአቻ ጓደኛ ግፊት

ወጣቶችና ሴቶች ብዙውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከአቻ ጓደኞቻቸው ጋር በመሆኑ የአቻ ጓደኞች ግፊት በባህሪያቸውና አመለካከታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ጥናቶች ሲያሳዩ በተለይም ዕፅ ተጠቃሚነት በሚሠሩት የስራ ዉጤት ላይ ሁሉ ጫና ይፈጥራል (Hops et al., 1999; Dishion et al., 1995; Evan et al., 1992; Galambos et al.,1992; Bankston,1997)ይላሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በጓደኛ ጫና ምክንያት ለመጠ ባህሎችና አልባሌ ልማዳዊ ድርጊቶች (ለሲጋራ፣ ለጫት፣ ለመጠጥ፣ ለሀሺሽና ላልተፈለገ የግብረ ሥጋ ግንኙነት) የተጋለጡ ወጣቶችና ሴቶች መኖራቸውን ጥናቶች ያሳያሉ(የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ,2003 ዓ.ም)። በዚሁ ጥናት ዉስጥ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የሁለቱም ፆታ ወጣት ተማሪዎች በትምህርት ሰዓት ከትምህርት ቤት በመውጣት ተያይዘው የሚሄዱ መሆኑንና በሲኒማ ቤቶች ወይም በኤግዚቪሽንና ሌሎች የዝግጅት ቦታዎች በመቀጣጠር የሚጠጡና ወሲብ የሚፈጽሙ ተማሪዎች መኖራቸው ተጠቅሷል(እንደቀደመው)።

### 2.5.6. ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች

ወጣቶችና ሴቶች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ መጠ ያልተገቡ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚገፋፉ ሲሆን አንዱና ዋነኛዉ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ሁኔታ መሆኑን ጥናቶች ጠቁመዋል። እንደ (Clacherty, 2003) ጥናት በኢኮኖሚ በጣም ከበለጸጉ ወይም ካደጉ ቤተሰቦች የተገኙ ወጣቶች በአብዛኛው አዝናኝ በሚሏቸው እጾችና ደባል ልማዳዊ ድርጊቶች ተጠቂ እንደሆኑ ይገልጻል(እንደቀደመው)።

በተቃራኒዉ በኢኮኖሚ አቅሙ ዝቅተኛ ከሆነ ቤተሰብ የሚገኙ ወጣቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸዉ አድርገዉ ስለሚገምቱና በተለይ በጣም ታዋቂ ከሆኑ አንድአንድ የህብረተሰቡ ክፍሎች ጋር በአለባበስም ሆነ በወጪ ደረጃ ሲነጻጸሩ የአቻነት ስሜት ስለማይሰማቸዉ ራሳቸዉን ከማህበረሰቡ ለማግለል ወደ አላስፈላጊ እጾችና ደባል ልማዳዊ

ድርጊቶች ይገፋፋሉ (Kettakamp ,1954)። በተጨማሪም በከፍተኛና ዝቅተኛ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኑሮ ዉስጥ ባሉ ቤተሰቦች መካከል የሚፈጠረዉ የኑሮ ልዩነት ወጣት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት መቅረትና ማቋረጥ ምክንያት ሊሆን ሲችል ይህ ሁኔታ በሂደት በወጣቶች ሥነልቡና ላይ የሚፈጥረው ጫና ወደ መጠ ደባል ባህሎችና ድርጊቶች ለመገፋፋት አስተዋጽዖ ያደርጋል (Kimmel, 1985)።

ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ጥናቶች እንደአመላከቱት ከቤተሰብ የኢኮኖሚ ሁኔታ በተጨማሪ ስራ አጥነትና ቤት አልባ መሆን ሴቶችንና ወጣቶችን ወደ ደባል ሱሶችና አላስፈላጊ መጠ ባህሎች እንደሚገፋፉ ሲሆን፤ ሴቶችና ወጣቶች በድህነትና ሥራ ማጣት ምክንያት ተስፋ በመቁረጥ ወደ ጎዳና ለመውጣት ስለሚገደዱና በጎዳና ህይወት ዉስጥም ከሚያጋጥሟቸዉ አስከፊ መሰናክሎች ለማምለጥ ሲሉ ለአላስፈላጊ ሱሶችና ደባል ባህሪያት ተጋላጭ ይሆናሉ (Clacherty,2003)።

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በአብዛኛዉ የባሕሪይ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የኋላ ታሪክ ሲታይ ሁለት መልክ አለው። በአንድ በኩል ከድሃ ቤተሰብ የመጡ፣ ወላጆቻቸው በጫት፣ በሲጋራና በሌሎች ተመሣሣይ ሱስ በሚያስይዙ ነገሮች (ጠላ፣ አረቂና ሌሎች መጠጦች) ንግድ ላይ የሚሣተፉና ወላጆች ራሳቸው በነዚህ ሱሶች የሚታወቁ መሆናቸው ነዉ። በሌላ በኩል ኑሮ ከቀናቸዉ ሃብታም ቤተሰቦች የሚመጡ ወጣቶች ከቤተሰቦቻቸው በሚዘገንላቸው ከፍተኛ ገንዘብ እራሳቸውን ለማዝናናት በሚል እንደቀልድ በሚጀምሩት ድርጊት እየተላመዱ የሚመጡ ናቸው።

## 2.6. መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና በሴቶች ላይ የሚያስከትሏቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎች

### 2.6.1. ማህበራዊ ተፅዕኖዎች

#### ሀ. ስደት

ወጣቶችና ሴቶችን ወደ መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ከሚገፋፉ ማህበራዊ ተፅዕኖዎች መካከል ስደት አንዱ ሲሆን ዜጎች በተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች መነሻነት በአገራቸው ውስጥ ለመኖር የማያስችል ሁኔታ ሲገጥማቸው ሀገራቸውን ጥለው ወደ ሌላ ባዕድ ሀገር ይሰደዳሉ (ስንቅነሽ,1997 ዓ.ም)። እንደ አጥኚዋ የምርምር ውጤት ዜጎች በሀገራቸው በቂ የሥራ ዕድል ካላገኙ፤ ወይም ባላቸው ዕዉቀት ከሀገራቸው ውጭ ቢሠሩ

የተሸለ ኑሮ ሊኖሩ እንደሚችሉ ሲገምቱ፤ከሀገራቸው ወጥተው ሠርተውና ተምረው ለመሻሻል ወገንንም ለመርዳት ሲያስቡ፤ በህጋዊ አለያም በህገወጥ መንገድ ይሰደዳሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ እነዚህ ዜጎች በባዕድ ሀገር የሚገጥማቸው ችግር ከፍተኛ ነው፡፡ከዚህም የተነሳ እንዳሰቡት ሳይሆን ይቀርና ብዙዎች ሥነምግባር በጎደላቸውና ስብዕናን በሚያጎድፉ ተግባራት ላይ ይሠማራሉ፡፡ ኢ-ሰብአዊ የሆኑ ድርጊቶችን እና ወንጀሎችን ይፈጽማሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡ ወደ ሀገራቸው ሲመለሱም የወረሱትን እኩይ ባህሪና ልምድ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ በማምጣት ያስፋፉታል፡፡ ስለሆነም ስደት ለመጤ ባህሎችና ልምዶች ወደ ሀገራችን መምጣት፤መስፋፋትና አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረስ ምክንያት በመሆኑ በዚህ ዘመን የህዝቦችንና የመንግሥትን ትኩረት የሳበ ጉዳይ ሆኗል (እንደቀደመው)፡፡

## ለ. ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ መስተጋብር መላላት

የመጀመሪያው በማህበራዊ ህይወት ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ የጥንታዊ ቤተሰባዊ መስተጋብር መላላት የሚባለው ነው፡፡ የዚህ ተፅዕኖ ሰለባዎች የሚሆኑት ራሳቸውን ለመርዳት አቅም የሌላቸው አረጋውያን፣ ህፃናትና አካል ጉዳተኞች ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት ማግኘት የሚገባቸውን የቤተሰብ ድጋፍ እንዳያገኙ የሚያደርግ ፤በቤተሰብ መካከል ያለውን የመቀራረብና የመረዳዳት ባህል የሚያስቀር ሂደት ነው Jeffrey (2002) ገልፃለች ፡፡

ሌላው በማህበራበራዊ ተፅዕኖ ሥር የሚነሳው እና በወጣቱ ዘንድ እንደ ችግር የሚታየው ጉዳይ ቁሳዊ አስተሳሰብን ማዳበር ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ወጣቱ የራሱ የሆነውን ባህልና ወግ እንዲሁም አለባበስና አስተሳስብ በመተው ከቴሌቪዥን፣ ከማስታወቂያና ከፊልም ፕሮግራሞች ከምዕራባውያኑ የወሰደውን ወደ ራሱ በማምጣት አመለካከቱን፣ ባህሪውንና አለባበሱን እየቃኘ ይገኛል (Jeffrey,2002)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ወጣቱ ለለውጥ ራሱን ያጋለጠ በመሆኑ በምዕራቡ ዓለም እየተንሰራፉ ያሉትንና በነፃነት የሚንቀሳቀሱትን የግብረሰዶማውያንን ህብረት በመከተል የራሱን የማህበራዊ ህይወት መስተጋብር እያበላሸ እንደሚገኝ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ(እደቀደመው)፡፡

በኢትዮጵያ በተለይም እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ግብረሰዶማዊነት (የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነት) እየተስፋፋ መሆኑን በአዲስ አበባ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ (ሞገስ, 2008) ፡፡ እንደ ጥናቶቹ ዘገባ በተለያዩ ዕፆችና መጠጦች አነሳሽነት ወጣቶች ከተመሳሳይ ፆታዎች ጋር የወሲብ ተግባር

እንደሚፈጽሙ ገልፆ ድርጊቱን የሚያከናውኑት ከተለመደው ወጣ ባለ መልኩ በአፋቸው(Oral Sex) እና በዓይነ ምድር መውጫ(Anal Sex) እንደሆነ ተብራርቷል። በተለይም ቆንጆና በትምህታቸው ጎበዝ ሴት ተማሪዎች በሌሎች ተማሪዎች በመመልመል ለችግሩ ሰለባ እንዲሆኑ መደረጋቸውን በተለያዩ ምሳሌዎች አስረድቷል(እንደቀደመው)።

## ሐ. በጤና ዘርፍ የሚታዩ አሉታዊ ተፅዕኖዎች

የጤና ችግር አንዱና ዋነኛ የማህበረሰብ ችግር ሲሆን ፣ይህንን ችግር ከሚያስከተሉ ምክንያቶች መካከልም መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶቸች ተጠቃሽ ናቸው።

ከነዚህ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ተያይዘው የሚመጡ ባህሪያት ድንገተኛ ወሲብ የመፈፀም ድርጊትን በማስፋፋት ለተላላፊ የአባላዘር በሽታዎች በተለይም ለኤች.አይ.ቪ ኤድስ የመጋለጥና በሽታውንም የማስፋፋት ችግሮችን እንደሚያመጣ እ.ኤ.አ በ2005 በአፍሪካ የኤድስ ምርምር መጽሔት ላይ ተገልጿል። በተጨማሪም ጫት መቃም፣ ለአልኮል ሱሰኝነት መጋለጥና በአጋላጭ ወሲባዊ ባህሪ የመጠመድ ሁኔታዎች ጠንካራ ቁርኝት እንዳላቸዉ ተጠቅሷል።

በሌላ በኩል የጨጓራ ህመም፣ የሆድ ድርቀት፣ የሽንት መሽኛ ቧንባ ችግር፣ የጥርስና የአፍ ህመም፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ እና ጫት ተጠቃሚ አጥቢ እናቶች የጡት መድረቅ አካላዊ ችግሮችን ሲያስከትል፤የስሜት መረበሽ፤ተደጋጋሚ ድብርት፤የሱስ ጥገኛ መሆንና ለከፍተኛ የአእምሮ ህመም መጋለጥን እነደሚያስከትል፤ የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር አመታዊ ኮንፍረንስ (2006) አትቷል።

ከመጤ ባህሎች ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ደባል ባህርያት (ለምሳሌ- እንደ መጠጥ፤አደንዛዥ እጾችና የመሳሰሉት) ምክንያት የሚደርሱ ችግሮች በርካታ ናቸዉ። ሞተረኛና መኪና አሽከርካሪ ወጣቶች ለሞት ይዳረጋሉ፤የወሲብ ባህሪያቸው ይጨምል፣የሥራ ብቃታቸዉ ይቀንሳል፣ሌሎች ሕገወጥና ደባል ሱሶችን ለመልመድ ይገፋፋሉ ሲሉ (Brandon, 1999 እና Grove, 2002)ገልፀዋል::

## መ. በትምህርት ዘርፍ የሚታዩ አሉታዊ ተፅዕኖዎች

መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶች የትምርት አቀባበል ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚያደርሱ Brandon (2002) ገልጿል። በተለይ በ10,000 የአሜሪካን የመለስተኛ

ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ባካሔደው ጥናት አደንዛዥ እጽ ከሚጠቀሙት ይልቅ የማይጠቀሙት የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፤በሒሳብ ስሌት፣ በምንባብ እና በጽሑፍ ውጤታቸው አደንዛዥ እጽ የማይጠቀሙት ከሚጠቀሙት በላይ ውጤታቸው በመቶኛ 53፣ 24 እና 53 በቅደም ተከተል ማስመዘገባቸውን ይጠቅሳል፡፡ በዚሁ ጥናት ላይ በተለይ በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ በተካሔደው ጥናት አደንዛዥ እጽ የማይጠቀሙ እና በሕገወጥነት/በወጣት ጥፋተኝነት መዝገብ ውስጥ የሌለ ተማሪዎች የተሻለ የትምህርት ውጤት እንዳላቸው (እንደቀደመው) ገልጿል፡፡

በሌላ በኩል በ14,000 ተማሪዎች ላይ በተካሔደ ጥናት 21.6% የሚሆኑት ጠጥተው ወደ ትምህርት ቤት በመግባታቸው በትምህርታቸው የደገሙ ሲሆን፤ 29.5% የሚሆኑት ደግሞ በመጠጥ ምክንያት ከትምህርት ቤት የሚቀሩ ሆነው ተገኝተዋል The Higher Education Center for Alcohol and other Drug Abuse and Violence Prevention (2010) ፡፡

## ሠ. በፀጥታ ዙሪያ የሚከሰቱ ተፅዕኖዎች

የአልኮል መጠጥ ወይም የሱስ አስያዥ ዕፆችን በመጠቀም ወንጀልን መፈጸም ከተጠያቂነት የሚያድንበት ዕድል የሰፋ አይደለም፡፡ብዙውን ጊዜ የነዚህ ነገሮች ተጠቃሚዎች የአልኮል መጠጥ ወይም ሱስ አስያዥ ዕፆችን ከተጠቀሙ በኋላ በከፊል አልያም ከዚያ በላይ አስተሳሳባቸው ሊዛባ ይችላል፡፡ በዚህም የተነሳ ከቀላል እስከ አደገኛ ወንጀሎች እንደሚፈጽሙ ጥናቶች ያሳያሉ (Tom, 1996)::

በአዲስ አበባና በሌሎች ሠላሳ ከተሞች በሱስ አስያዥ ዕፆች እና ተፅዕኗቸው ዙሪያ በተደረገ ጥናት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሱሰኝነት እንደተጠቁ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ብዙዎቹ ሱስ አስያዥ ዕፆችንና የአልኮል መጠጦችን ለመጠቀማቸው ምክንያት ሲያስቀምጡ ከጭንቀት፣ ስራ ከማጣትና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ከሚያደርሱባቸው ጫና ለመላቀቅ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከተጠቀሙ በኋላ ግን በተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች ተሳታፊ ሆነው እንደተገኙ ጥናቱ ገልፏል (S.Gebre, 1996)፡፡

### 2.6.2. ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ

በትምባሆ ኢንዱስትሪ ንግድ ሥራዎች በጣም ትርፋማ ከሆኑት ሀገሮች አንዷ የሆነችው አሜሪካ ፤ በሲጋራ ማጨስ ሰበብ በሞት በምታጣው አምራች ሀይል የተነሣ በሚያጋጥማት የምርታማነት ማሽቆልቆል ምክንያት በየዓመቱ ከ$196 ቢሊዮን (ከአንድ መቶ ዘጠና

ሥድስት ቢሊዮን ዶላር) በላይ እንደምታወጣ በ WWW.Concern.Org Questions About Smoking Tobaco and Health ላይ ተጠቅሷል፡፡

ከዚህም ሌላ እ.ኤ.አ. ከ2000-2004 ባለው ጊዜ ውስጥ ከትምባሆ ማጨስ ጋር ግንኙነት ላለው ሕመም ለሕክምና በየዓመቱ በአማካይ ከ$100 ቢሊዮን (ከአንድ መቶ ቢሊዮን ዶላር) በላይ ማጣቷን፤ይህም ዘርዘር ተደርጎ ሲታይ ለእያንዳንዱ አጫሽ የወጣወው የሕክምና ወጪ በዓመት በአማካይ $2247 (ሁለት ሺ ሁለት መቶ አርባ ሰባት የአሜሪካ ዶላር) መሆኑ ተገልጿል፡፡

በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት ከሲጋራ ማጨስ ጋር በተያያዘ ሀገሪቱ በሞተባት አምራች ኃይል የተነሣ በዓመት በአማካይ ከ$97 ቢሊዮን (ከዘጠና ሰባት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር) ያላነሰ ገቢ ማጣቷ (እንደቀደመው) ተጠቅሷል፡፡

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ የኢትዮጵያ መድኃኒት ፋብሪካ በ2002 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት ላይ ግማሽ ሺሻ ለማጨስ ብር 30 (ሠላሳ ብር)፤ሙሉ ሺሻ ለማጨስ ደግሞ ብር 60 (ሥድሳ ብር) ይጠይቃል፡፡ይህም እንደሚጨስበት ቤትና በተጨማሪ እንደሚወሰደው ሱስ አስያዥ የዕፅ ዓይነት ይለያያል፡፡ እነደ ጫትና ሌላም ሱስ አስያዥ ዕፅ ከሺሻው በተጨማሪ ከተወሰደ ደግሞ፤ክፍያው እሰከ ብር 100 (አንድ መቶና ከዚያ በላይ) ይደርሳል ሲል በወቅቱ በነበረው የገበያ ሁኔታ ገልጿል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሌላ ሱስ አስያዥ ዕፅ ሳይጨመር ሺሻን ብቻ በወር አራት ቀን የሚያጨስ ተጠቃሚ በወር በአማካይ ከብር 120 እሰከ 240 (ከብር አንድ መቶ ሃያ እሰከ ሁለት መቶ አርባ)፤አዘውትሮ የሚጠቀም ደግሞ ከብር 600እሰከ ብር 1000 (ከስድስት መቶ እሰከ አንድ ሺ ብር) በትንሹ ያወጣል፡፡ ይህም በቤተሰቡ ኑሮ ላይ የኢኮኖሚ መናጋት ያስከትላል፡፡ በማጨስ የሚባክነው ጊዜም እንዲሁ የገቢ መቀነስን የሚያስከትል መሆኑን የአዲሰ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጥናት (2003 ዓ.ም) ያስገነዝባል፡፡

### 2.6.3. ስነ-ልቡናዊ ተፅዕኖዎች

የዓለም አቀፋዊነት መሰረታዊ የስነ-ልቡናዊ ተፅዕኖ የሚባለው የግለሰቦችን ማንነት የሚለውጠው ክስተት ሲሆን፤ በዚህ ውስጥ ግለሰቦች በአካባቢያቸው ባለው ማህበራዊ

እሴትና መስተጋብር መሰረትነት ስለራሳቸው የሚሰጡትን ግምትና ቦታን ይገልፃል (Jeffrey, 2002)። Jeffrey በዓለምአቀፋዊነት ምክንያት የሚከሰቱ የስነ-ልቡናዊ ተፅዕኖዎችና የማንነት መጣረሶችን አስመልክታ ስትገልጽ፤ ከምዕራባውያኑ ባህል ውጭ ያሉ ግለሰቦች በዓለምአቀፋዊነት ምክንያት ካላቸውና ከለመዱት ባህል ውጭ የሆነ የተቀላቀለ ባህልን ለመቀበል በሚገደዱበት ወቅት ስለራሳቸውና ስለባህላቸው ያላቸው ግምትና ቦታ ያነሰ ሲሆንባቸው የሚከሰት ክስተት ነው ብላለች(2002)።

የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኞች በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ይሳናቸዋል፤ብቸኝነት ያስደስታቸዋል። እንዲሁም የሚያስደስቱና የሚወዷቸው ነገሮች አንድአንዴ ይረብሿቸዋል፤ ያስፈሯቸዋል። በተጨማሪም ሱሰኝነት ግለሰብን ብቻ ሳይሆን ቀስ በቀስ የቤተሰብንና የወዳጅ ዘመድ የሰላምና የተረጋጋ ህይወት ጠንቅ ይሆናል፤ እንዲሁም በቤተሰብ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳድራል በማለት The Ethiopian Public Health Association Annual Conference Report (2006) ገልጸታል።

## 3. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ምዕራፍ ጥናቱን ለማድረግ ጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴዎችን ይዟል። ጥናቱ የገላጭ (Descriptive) ጥናትና ምርምር ዘዴን በመጠቀም አይነታዊና መጠናዊ የአጠናን ሥልትን የተከተለ ነው። በመሆኑም የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን እንዲያካትት ተደርጓል። መጠናዊ የጥናቱ መረጃ ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ (2002 ዓ.ም) በተገኘው መረጃና የተመረጡ ወረዳዎችን ጠቅላላ የነዋሪ ቁጥር መሰረት ያደረገ ነው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህዝብ ብዛት 2,739,551 ሲሆን የወንዶች ቁጥር 1,305,387፤ የሴቶቹ ደግሞ 1,434,164 መሆኑን መረጃው ያሳያል። ከነዚህ ውስጥ 517,284 ወንዶችና 644,704 ሴቶች በድምሩ 1,161,988 ወጣቶች መሆናቸው ሲጠቀስ፤ 329,331 ደግሞ ከ30-50 ዕድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ሴቶች ናቸው።

የአይነታዊ ጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብም ሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል። እነሱም የቃለ መጠይቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት እና የተሳትፎ ምልከታዎች ናቸው። በመሆኑም በእነዚህን መጠናዊና አይነታዊ የናሙና አወሳሰድ ስልቶች፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችና የተገኙት መረጃዎች የተተነተኑበት መንገድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 3.1. የመጠናዊ መረጃ የናሙና ምጣኔ

### 3.1.1. የናሙና ምጠና ስሌት

$$n = \frac{Z^2_{\alpha/2}\ p(1-P)}{d^2}$$

P = በዚህ ርእስ ዙሪያ ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ የተጠና ጥናታዊ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይህም በመሆኑ ሃምሳ ፐርሰንት (50%) የሚሆኑ ዕድሚያቸው ከ15-29 የሆኑ ወጣቶችና 30 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሴቶች በመጠ ባህሎችና በልማዳዊ ድርጊቶች ምክንያት ተፅእኖ ይደርስባቸዋል ተብሎ ግምት ተወስዷል፡፡

d = ወጣቶችና ሴቶች በመጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች እየደረሱባቸው ያለውን ተጽእኖ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ያላቸውን ፍቃደኝነት፣ በናሙና ምጠና እና ስብሰባ ወቅት ሊፈጠሩ ይችላሉ ተብለው የተገመቱ የተለያዩ ችግሮች ምክንያት 50% ሊሆን ይችላል ተብሎ ተገምቷል

$\alpha$ = 0.05 የይሁንታ እርከን

n = የሚወሰደውን የናሙና መጠን

Z = ከስታንዳርድ ሠንጠረዥ ላይ የሚገኝ ውጤት ሆኖ በ0.05 የይሁንታ እርከን የስህተት ክፍተት ይኖራል ተብሎ በማሠብ የተወሰደ ነው፡፡

በተጨማሪም 15% የሚሆነውን በጥናቱ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ለማይመለሱና ለሚጠፉ መጠይቆች በመያዝ ሦስት ደረጃ የናሙና ምጣኔ ስልት (three stage sampling technique) ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በዚህ መሰረት 1,324 የናሙና ተሳታፊዎች መውሰድ የሚቻል ቢሆንም ህብረተሰቡ ለጥናት መረጃ ከመስጠት አንፃር ያለውን ግንዛቤና ንቃተ

ህሊና ከግምት በማስገባትና የመረጃዎቹን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ለማረጋጋጥ እንዲያስችል የናሙና መጠኑ 3000 እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## 3.2. የመጠናዊ መረጃ ናሙና አመራረጥ ስልት

በሁሉም ክ/ከተሞች ስር ያሉትን የወረዳዎች ቁጥር ባገናዘበ መልኩ ከእያንዳንዱ ክ/ከተማ 30% የሚሆኑትን ወረዳዎች በዓላማ ተኮር የናሙና ምጠና ዘዴን (purposive sampling) በመጠቀም ተወስዷል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡ የወረዳዎች ብዛትና ስብጥራዊ ናሙና አወሳሰድ**

| ተ/ቁ | ክ/ከተማ | የወረዳዎች ብዛትና ስብጥራዊ ናሙና አወሳሰድ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወረዳ | | ምላሽ እንዲሰጡ በእቅድ የተያዙተሳታፎዎች ብዛት | | | ምላሽ የሰጡ ተሳታፊዎች ብዛት | | |
| | | ብዛት | ናሙና | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | አዲስ ከተማ | 10 | 3 | 247 | 53 | 300 | 100 | 130 | 230 |
| 2 | አቃቂ ቃሊቲ | 11 | 3 | 178 | 72 | 250 | 102 | 128 | 230 |
| 3 | አራዳ | 10 | 3 | 239 | 47 | 286 | 101 | 114 | 215 |
| 4 | ቦሌ | 14 | 4 | 168 | 48 | 216 | 77 | 100 | 177 |
| 5 | ጉለሌ | 10 | 3 | 381 | 75 | 456 | 83 | 137 | 220 |
| 6 | ቂርቆስ | 11 | 3 | 242 | 49 | 291 | 83 | 156 | 239 |
| 7 | ኮ/ቀራኒዩ | 15 | 4 | 239 | 74 | 313 | 143 | 160 | 303 |
| 8 | ልደታ | 10 | 3 | 171 | 34 | 205 | 93 | 81 | 174 |
| 9 | ን/ስልክ | 12 | 3 | 244 | 82 | 326 | 178 | 152 | 326 |
| 10 | የካ | 13 | 4 | 286 | 71 | 357 | 158 | 183 | 341 |
| ድምር | | 116 | 33 | 2481 | 519 | 3000 | 1118 | 1341 | 2455 |
| ክ/ከተማቸውን ያልገለፁ ተሳታፊዎች ብዛት | | | | | | | | | 73 |
| ጠቅላላ ድምር | | | | | | | | | 2,529 |

በዚህም መሰረት በከተማው ካሉት 116 ወረዳዎች ወስጥ ዕድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴን (Random Sampling Technique) በመጠቀም 33 ወረዳዎች በእጣ ተመርጠዋል፡፡ ከየወረዳው በተገኘው የቤቶችና የህዝብ ቁጥር መሰረት ስልታዊ የአጋጣሚ ናሙና ዘዴ

(Systematic random sampling method) በመጠቀም 3000 ተሳታፊዎች የተመረጡ ሲሆን፤ ለእያንዳንዱ ቤት እኩል እድል በመስጠት ቤቶቹ እንዲመረጡ ተደርጓል። በተጨማሪም ለጥናቱ የሚፈለጉትን ተሳታፊዎች ታሳቢ በማድረግ በተመረጡት ቤቶች ውስጥ እድሜያቸው ከ15-29 ዓመት የሆኑ ወጣት ሴቶችና ወንዶች እንዲሁም ከ29 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶች የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

## የአይነታዊ መረጃ አሰባሰብ ስልት

የጥናቱን መረጃ ግኝት ተዓማኒና የተሟላ ለማድረግ አላማ ተኮር አይነታዊ መረጃ አሰባሰብ ስልቶች ተተግብረዋል። በዚህም መሰረት ሰባት የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች (ከሴት አደረጃጀት አመራሮችና ከቢሮ ሴቶች፣ ከተማሪዎች፣ ከጫት ቃሚዎች፣ በወሲብ ሥራ ከሚተዳደሩ ሴቶች፣ ከቤት እመቤቶች፣ በማረሚያ ቤት ከሚገኙ ወጣት ታራሚዎች እና ከትምህርት ቤት ውጪ ካሉ ወጣቶች) ጋር ተደርገዋል።

በተመሳሳይ መልኩ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፤ ማለትም ከሃይማኖት አባቶች (የኦርቶዶክስ፣ ሙስሊም፣ የወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ህብረትና ካቶሊክ)፣ ከህክምና ባለሙያዎች፤ ከርዕሳነ መምህራን፤ ከጫት አስቀሚዎች፤ ከግብረሶዶማዊያን፣ ከፍትህ አካላት (የአዲስ አበባ ፍትህ ቢሮና ፖሊስ ኮሚሽን ተወካዮች) እና ከዕድር ተወካዮች ጋር በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ቃለ መጠይቅ ተደርጓል።

በተጨማሪም በአሳታፊ የአካል ምልከታ የቀን ጭፈራ ቤቶች፣ የማታ ጭፈራ ቤቶች፣ እርቃን ጭፈራ ቤቶች፣ የዕፅ መጠቀሚያ ቤቶች፣የግብረ-ሶዶማዊያን ማዘወተሪያ ቦታዎች፣የመኪና ላይ ወሲብ መፈፀሚያና ጫት መቃሚያ ቦታዎችን በሚገባ በመቃኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል።

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት የተዘጋጁ የጽሑፍ መጠይቆች፣ ለምልከታ የሚያግዙ የመከታተያ ቅፆች(check list)፣ ለትኩረት ቡድን የሚረዱ የመወያያ ጥያቄዎች ፣ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ባለሙያዎች ቃለ መጠይቆች መረጃዎችን ለማሰባሰብ በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል። የጽሁፍ መጠይቁ በአጠቃላይ በአምስት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን፤ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መመለስ የሚያስችሉ 66 (ስድሳ ስድስት) ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል።

በአጠቃላይ የተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች በመጠቀም ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

## የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

መረጃ ለማሰባሰብ ከአሥሩም ክ/ከተሞች በናሙና ከተመረጡት ወረዳዎች በሥነ-ምግባራቸዉና በመረጃ ስበሰባ ስራ ልምድ ያላቸው 128 (አንድ መቶ ሃያ ስምንት) ረዳት መረጃ ሰብሳቢዎችና 12(አስራ ሁለት) አስተባባሪ ወጣቶች ተመልምለው ስለጥናቱ አስፈላጊነት፣ ስለመጠይቅ አሰረጫጨት፣ አሞላል እና የተሞሉ መጠይቆች አሰባሰብ ስልት ላይ የአንድ ቀን ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የመረጃ ማሰባሰቢያዎቹን ጥራት ለመመዘንና አስተማማኝነታቸውን ለማረጋገጥም ናሙና መጠይቆች ተወስደው ለረዳት መረጃ ሰብሳቢነት በተመረጡ ወጣቶች ላይ የሙከራ መጠይቅ የማስሞላት ሥራ ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት ግብረ መልስ ከተሰበሰበ በኃላ መጠይቆቹ ተስተካክለው ለሁሉም በናሙናው ለተወከሉ ወረዳዎች እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡

የመረጃ አሰባሰብ ሥራው የተካሄደው ከመስከረም 9-14/2004 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህም ወቅት በየወረዳው ከተሰማሩት አስተባባሪዎች በተጨማሪ የጥናት ቡድኑ ራሱን በቡድን በማደራጀት መረጃው በሚሰበሰብበት ቦታ እየተገኘ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመረጃ ስብሰባውን የተሳካ አድርጎታል፡፡

የአይነታዊ መረጃ አስባሰብን በተመለከተ ከላይ ከተዘረዘሩት የመረጃ ምንጮች (የሃይማኖት አባቶች፣ አመራሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች...) ቀጠሮ በመያዝና በግምባር ተገናኝቶ ጠለቅ ያለ ውይይት በማካሄድ በጽሁፍና በመቅረጸ ድምጽ ቀዳማይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በተጨማሪም በቀንና በሌሊት ተከታታይ ተሳትፎአዊ ምልከታዎች ተደርገዋል፡፡ ይህንንም ለማሳካት አጥኚ ቡድኑ የተመረጡ የቀንና የሌሊት ጭፈራ ቤቶችን በዳሰሳ እንዲለዩ ካደረገ በኃላ ራሱን በሁለት ቡድን በማደራጀት ምልከታ አድርጓል፡፡

### 3.4. የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን

በዚህ ጥናት ሁለት ዓይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የመጀመሪያው በጽሑፍ መጠይቅ ከወጣቶችና ሴቶች የተሰበሰበ መጠናዊ መረጃ ሲሆን ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዓይነታዊ ስልት ሲሆን ለዚህም የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ የቃለ መጠይቅና የአካል ምልከታዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

መጠናዊ መረጃዎችን ወደ ማደራጀት ከመገባቱ በፊት የማጥራት ሥራዎች ከተሰሩ በኃላ ወደ "ኤስ.ፒ.ኤስ.ኤስ" (SPSS) "ሶፍት ዌር" እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ወደ ኮምፒውተር የገቡ መረጃዎችም፤ በሠንጠረዥ፣ በአሀዝ፣ በመቶኛና በ"ግራፍ" ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡

ዓይነታዊ መረጃዎችም በመቅረጸ ድምጾች የተሰባሰቡ በመሆናቸው፤ ከድምጽ ወደ ጽሁፍ ከተገለበጡ በኋላ ለትንተና ወደ ኮምፒውተር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

## 3.5. የጥናቱ ህጋዊነት

የጥናቱን መረጃዎች (መጠናዊና ዓይነታዊ) ህጋዊ በሆነ መልኩ ለማሰባሰብ ይረዳ ዘንድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ እና ከንቲባ ጽ/ቤት ህጋዊ ደብዳቤዎች ተዘጋጅተው ለክ/ከተሞችና ለጥናቱ በናሙና ለተመረጡት ወረዳዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለተተኳሪ ቡድን ውይይትና ለቃለመጠይቅ የተሰማሩ ባለሙያዎችም፤ ህጋዊ ደብዳቤ ይዘው ለሚመለከታቸው ግለሰቦችና ተቋማት በማድረስ መረጃዎቹን ሰብስበዋል፡፡

ከዚህም ሌላ መጠይቁን በፈቃደኝነት የሞሉ መረጃ ሰጭዎችን ምስጢር ለመጠበቅ ሲባል፤ ስማቸውን በመጠይቆቹ ላይ እንዳይጽፉ ተደርጓል፡፡እንዲሁም በአንዳንድ የቡድን ውይይቶችና ቃለመጠይቅ የተሳተፉ (በወሲብ ሥራ የሚተዳደሩ ሴቶች፣ በጫት ሱስ የተያዙ ወጣቶች እና ግብረ ሰዶማዊያን) መረጃ ከመሰባሰቡ በፊት ከግለሰቦቹ ጋር በተደረገው ውይይት መሠረት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ ስማቸው ሳይጠቀስ መረጃውን ሰጥተዋል፡፡

# 4. የጥናቱ መረጃ ግኝት

ይህ ጥናት "መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች፤ በተለይም በሴቶችና ወጣቶች ላይ እያስከተሉት ያለው ተፅዕኖ" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ማሳካት ይቻል ዘንድ መጠናዊና ዓይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡በዚህም መሰረት ይህ ምዕራፍ በፅሁፍ መጠይቅ፣በቃለመጠይቅ፣ በአትኩሮት ቡድን ውይይት እና በተሳትፎአዊ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች በቅደም ትንተና በቅደም ተከተል ይቀርቡበታል፡፡

## 4.1. የመጠናዊ መረጃ ግኝት

በዚህ የመጠናዊ መረጃ ግኝት እንዲካተቱ የተደረጉት መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ለመጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡ ምክንያቶችና የሚያስከትሏቸው ተፅዕኖዎች ናቸው፡፡

### 4.1.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ

የጥናቱ ተሳታፊዎች በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ አስሩም ክፍለ ከተሞች በተለያዩ መንገዶች የተመረጡ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት 3000 መጠይቅ የተሰራጨ ቢሆንም፤ ተሞልተው ከመጡት ውስጥ 471 የሚሆኑት መጠይቆች ያልተሟሉ በመሆናቸው በመረጃነት አልተካተቱም፡፡ በመሆኑም በመጠናዊ ትንተናው ምሉዕ ከሆኑት 2529 መጠይቆች የተገኙት መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 2. የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ**

| ተ.ቁ | | | ቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ፆታ | ሴት | 1,373 | 54.30 |
| | | ወንድ | 1,156 | 45.70 |
| | | ጠቅላላ | 2,529 | 100.00 |
| 2 | ዕድሜ | 15-19 | 809 | 32.00 |
| | | 20-24 | 922 | 36.50 |
| | | 25-29 | 476 | 18.80 |
| | | ከ29 ዓመት በላይ | 322 | 12.70 |
| | | ጠቅላላ | 2,529 | 100.00 |
| 3 | የትምህርት ደረጃ | ከ8ኛ ክፍል በታች | 363 | 14.40 |
| | | ከ9ኛ-12ኛ ክፍል | 1,001 | 39.60 |
| | | ሰርተፍኬትና ዲፕሎማ | 263 | 10.40 |
| | | ዲግሪ እና ከዛ በላይ | 437 | 17.30 |
| | | በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመማር ላይ ያሉ | 181 | 7.20 |
| | | ያልገለጹ | 284 | 11.20 |
| | | ጠቅላላ | 2,529 | 100.00 |
| 4 | የትዳር ሁኔታ | ያገባ/ች | 568 | 22.50 |
| | | ያላገባ/ች | 1,431 | 56.60 |
| | | የፈታ/ች | 87 | 3.40 |
| | | በሞት የተለየ/ች | 64 | 2.50 |
| | | ከፍቅረኛ ጋር አብሮ የሚኖር/የምትኖር | 319 | 12.60 |
| | | ያልገለጹ | 60 | 2.40 |
| | | ጠቅላላ | 2,529 | 100.00 |
| | | | | |
| 5 | የስራ ሁኔታ | የመንግስት ሰራተኛ | 171 | 6.80 |
| | | የግል ስራ | 246 | 9.60 |
| | | ተማሪ | 1545 | 61.10 |
| | | ስራ ፈላጊ | 525 | 20.80 |
| | | የቤት እመቤት | 42 | 1.70 |
| | | ያልገለጹ | __ | ___ |
| | | ጠቅላላ | 2,529 | 100.00 |

በሠንጠረዥ 2 እንደተመለከተው፣ መረጃውን በመስጠት ከተሳተፉት 2,529 መላሾች ውስጥ 1,373 (54.3%) የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ፣ የተቀሩት 1,156 (45.7%) ደግሞ ወንዶች ናቸው። በዚህ ጥናት ውስጥ ምላሽ የሰጡት ተሳታፊዎች ዕድሜ ከ15-29 ዓመት ያሉ ወጣቶችና ከ29 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶች ናቸው። በዚህም መሰረት 1156 (45.7%) ወጣት ወንዶች፣1051(41.6%) የሚሆኑት ወጣት ሴቶች ሲሆኑ፤ ከ29 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶች ደግሞ 322 (12.7%) የሚሆነውን ድርሻ ይይዛሉ።።

በሌላ በኩል ከጥናቱ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፤ 1001 (39.6%) የሚሆኑት ተሳታፊዎች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ 181 (7.2%) የሆኑት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እየተማሩ ያሉ፣ እንዲሁም ሰርተፍኬትና ዲፕሎማ ያላቸው 263 (10.4%) ፣

ዲግሪና ከዛ በላይ ያላቸው 437 (17.3%) ሲሆኑ፤ ከስምንተኛ ክፍል በታች ያሉ ደግሞ 363 (14.4%) መሆናቸውን መረጃው ያሳያል፡፡ ይህን ጥያቄ ያልመለሱት ተሳታፊዎች ደግሞ 284(11.2%) የሚሆኑት ናቸው፡፡ በመሆኑም የትምህርት ደረጃ ስብጥሩ ለሚፈለገው ዝርዝር መረጃ ከተለያየ የአስተሳሰብ ጥግ ለመቃኘት በእጅጉ የረዳ ሆኗል፡፡

በክተማዋ ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚስተዋለው በየደረጃው ትምህርት በማቋረጥ ለተለያዩ አላስፈላጊ ድርጊቶች የሚጋለጡ ወጣቶች ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህም የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ የስነ-ምግባር፣ ቤተሰባዊና ሌሎች ችግሮች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህንን አስመልክቶ የተሰበሰበው መጠናዊ መረጃ እንደሚያመለክተው በመጠይቁ ከተሳተፉት ውስጥ 875(34.7%) የሚሆኑት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ 462ቱ (52.8%) ሴቶች ፣ 413(47.2%) ያህሉ ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ ይህም የሚያሳየው ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ከሚገደዱት ወጣቶች ውስጥ የሴቶቹ ቁጥር ከፍ ያለ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም 41.3% የሆኑት ለማቋረጣቸው ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ችግር መሆኑን ሲጠቅሱ፣ 15.1% የሆኑት ደግሞ በተለያዩ ሱሶች ምክንያት ትምህርት እንዳቋረጡ ገልፀዋል፡፡ የተቀሩት 43.6% መላሾች የማቋረጣቸው ምክንያት የስነ-ምግባር ችግር፣ ከቤተሰብ ጋር ያለመስማማትና መሰል ጉዳዮች መሆናቸውን ከመረጃው ለማየት ይቻላል፡፡

ከምላሹ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፣ የትዳር ሁኔታን አስመልክቶ 568 (22.5%)ቱ መላሾች ትዳር የመሰረቱ፣ 1431 (56.6%) የሆኑት ትዳር ያልመሰረቱ እና 319(12.6%)ኙ ደግሞ በቃል ኪዳን ደረጃ እንዳሉ ጠቅሰዋል። የተቀሩት 151(5.9%) የትዳር አጋሮቻቸውን በሞት ያጡና በፍቺ የተለዩ ሲሆን፤ 60(2.4%)ቱ ደግሞ መልስ ያልሰጡ ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ፤ ካላገቡት ውስጥ ከፍ ያለውን ቁጥር የያዙት (52%) ወንዶች ሲሆኑ 48% የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የትውልድ ስፍራቸውን በተመለከተ ተሳታፊዎች ተጠይቀው ሲመልሱ 63.4% የሚሆኑት የትውልድ ቦታቸው አዲስ አበባ መሆኑን ሲጠቅሱ፤ የተቀሩት 36.6% ደግሞ የትውልድ ቦታቸው ከአዲስ አበባ ውጪ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ከአዲስ አበባ ውጪ ከተወለዱት ውስጥ 67.6% የሚሆኑት አዲስ አበባ መኖር ከጀመሩ ከስድስት ዓመት በላይ የሆናቸው ሲሆን፤ 15.7 የሚሆኑት ደግሞ ከአራት እስከ ስድስት አመት እንደሆናቸው ገልጸዋል። ከዚህም በተጨማሪ 16.8 % የሚሆኑት አዲስ አበባ መኖር ከጀመሩ ሦስት አመት ያልሞላቸው መሆኑንም የተገኘው መረጃ ያስረዳል።

በተጨማሪም የተሳታፊዎችን የሥራ መስክ አስመልክቶ ለተጠየቀው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ መሰረት 1545 (61.1%) የሚሆኑት ገና በትምህርት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ 20.8%ቱ ደግሞ ስራ የሌላቸው መሆናቸውን ገልፀዋል።

## ለመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡ ምክንያቶችና ተፅዕኖዎች

### ሀ. የመዝናኛ፣ የመገናኛና የመረጃ መረቦች

የመዝናኛ፣ የመገናኛና የመረጃ መረቦች፤ ወጣቶችና ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ባህርያትና ድርጊቶች እንዲያመሩ ምክንያት ስለመሆናቸው እና ስለሚያስከትሉት ተፅዕኖ የቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3. የመዝናኛ፣ የመገናኛና የመረጃ መረቦች አጠቃቀምና ተፅዕኖ**

| ተ.ቁ | | | ቁጥር | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አብዛኛውን ግዜ እንደ መዝናኛ ወይም ግዜ ማሳለፊያ የሚጠቀሙበት | ፊልም በማየት | 1461 | 57.8 |
| | | በንባብ | 578 | 22.9 |
| | | በሞፊራ ቤቶች | 102 | 4.0 |
| | | የአልኮል መጠጦች በመጠጣት | 82 | 3.2 |
| | | ኢንተርኔት በመጠቀም | 164 | 6.5 |
| | | አነቃቂ እፆችን በመጠቀም | 104 | 4.1 |
| | | ያልገለጹ | 38 | 1.5 |
| | | ጠቅላላ | 2529 | 100.0 |
| 2 | አብዛኛውን ግዜ የመጠቀም እድል ያሎት የመረጃ ማግኛ ዘዴ | የአገር ውስጥ ቴሌቭዥን | 1065 | 42.1 |
| | | የውጭ ቴሌቭዥን/ ዲሽ/ | 476 | 18.8 |
| | | መጽሄት | 151 | 6.0 |
| | | ጋዜጣ | 102 | 4.0 |
| | | ኢንተርኔት | 288 | 11.4 |
| | | ሬድዮ | 423 | 16.7 |
| | | ያልገለጹ | 24 | .9 |
| | | ጠቅላላ | 2529 | 100.0 |
| 3 | የማህበረሰብ ድረ-ገጽ/ፌስ ቡክ፣ትዊተር.../ ተጠቃሚ ኖት? | አዎ | 1144 | 45.2 |
| | | አይደለሁም | 1381 | 54.6 |
| | | ያልገለጹ | 4 | 0.2 |
| | | ጠቅላላ | 2529 | 100.0 |
| 4 | በድረ-ገጽ ከተዋወቁት ሰው የፍቅር ወይም ወሲብ ጥያቄ ቀርቦሎት/ወሲብ ነክ ምስል ደርሶት ያውቃል? | ያውቃል | 534 | 21.1 |
| | | አያውቅም | 606 | 24.0 |
| | | የማይጠቀሙ | 1382 | 54.6 |
| | | ያልገለጹ | 7 | 0.3 |
| | | ጠቅላላ | 534 | 21.1 |

የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች አብዛኛውን ግዜ በምን ዓይነት መልኩ መዝናናት እንደሚመርጡ ተጠይቀው ሲመልሱ፤ አብዛኛዎቹ 1461(57.8%) ፊልም በማየት እንደሚዝናኑና 578 (22.9%) የሚሆኑት ደግሞ ንባብን እንደመዝናኛ እንደሚመርጡት የተገኘው መረጃ ያሳያል። ከዚህም ሌላ 164(6.5%) የሆኑት መላሾች ኢንተርኔት በመጠቀም፣ 104

(4.1%)ቱ የተለያዩ እያችን በመጠቀም እና 102 (4%)ቱ ደግሞ በሞፌራ ቤቶች እንደሚዝናኑ ጠቅሰዋል። ይህም የሚያሳየው አብዛኛው ተሳታፊ በፊልም የሚተላለፍ መልዕክቶችን የማግኘት ዕድሉ የሰፋ መሆኑን ነው። የፅሑፍ መጠይቅ ተሳታፊዎቹ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስና የህትመት መገናኛ ብዙሀን ከሚተላለፉ ፕሮግራሞች መካከል የትኞቹን በቅርበትና በቀላሉ የማግኘትና የመጠቀም እድል እንዳላቸው ተጠይቀው ነበር። ለዚህም በሰጡት ምላሽ 1065(42.1%) የሆኑት በሀገር ውስጥ ቴሌቪዥን የሚተላለፉትን ፕሮግራሞች በቀላሉ የማግኘት እድል እንዳላቸው ሲገልፁ፣ 476(18.8%) የሚሆኑት ደግሞ በሳተላይት የሚተላለፍ የውጭ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን እንደሚከታተሉ ጠቅሰዋል። 288(11.4%)ቱ ደግሞ ከኢንተርኔት የሚገኙ መረጃዎችን፣ 423(16.7%) በሬዲዮ የሚተላለፉትን እና የተቀሩት 253(10%) የሆኑትን ደግሞ በቀላሉም ሆነ በቅርበት የሚያገኙትና የሚዝናኑት በመፅሔትና በጋዜጦች እንደሆነ ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ በእጅጉ የተስፋፋው የኢንተርኔት አገልግሎት ዘርፍ ብዙ ተጠቃሚዎች እንዳሉ ይታወቃል። በሌላ በኩል ደግሞ በእድሜ፣ ፆታ፣ የትምህርት ወይም የንቃተ ህሊና ደረጃ፤ እንዲሁም ሌሎች ግለሰባዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ባላገናዘበ መልኩ የሚለቀቁ መረጃዎች አሉታዊ ተፅዕኖአቸው በተለይም በወጣቶችና ሴቶች ላይ ጎላ ብሎ እንደሚታይ ይገመታል። ከዚህ ጋር በተያያዘም የግል መረጃን ለመለዋወጥና በድረ-ገፅ በቀላሉ ለመገናኘት የሚያግዝ የማህበረሰብ ድረ-ገፆች ("ፌስቡክ"፣"ቲውተር" ወዘተ) ተጠቃሾች ናቸው። በዚህም አማካይነት የድምጽ፣ የምስልና የፅሁፍ መልእክቶችን በቀጥታ ለመለዋወጥ ያስችላሉ።

ከማህበረሰብ ድረ-ገፅ ጋር በተያያዘ መላሾች መሰል ድረ-ገፆችን ይጠቀሙ እንደሆነ ተጠይቀዋል። ከመረጃው መረዳት እንደተቻለው 1144 (45.2%) የሚሆኑት የነዚህ ድረ-ገፆች ተጠቃሚ መሆናቸውን መረጃው ያሳያል። ከነዚህ ተጠቃሚዎች ውስጥም 39.5% የሚሆኑት ከ15-29 ዓመት የእድሜ ክልል የሚገኙ ወጣት ሴቶች ሲሆኑ፣ 49.9%ቱ ደግሞ ወጣት ወንዶች ናቸው። በሌላ በኩል ከ30 ዓመት በላይ ያሉ ሴት የድረ-ገፅ ተጠቃሚዎች 10.6% መሆናቸው ተመልክቷል። እነዚህ ተሳታፊዎች በድረ-ገፅ ጓደኝነት የፈጠሩት ከነማን ጋር መሆኑንም ተጠይቀው ነበር። በምላሹም 34.6% የሚሆኑት ሴቶች ጓደኝነት የመሰረቱን በተለያዩ አጋጣሚ ከሚያውቋቸውና በድረ-ገጽ የጓደኝነት ጥያቄ ካቀረቡላቸው፣ ነገር ግን በአካል ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር ነው። በተመሳሳይ ጓደኝነት የመሰረቱት ወንዶች ደግሞ 35.9% የሆኑት ናቸው። የሌሎችን ግላዊ መረጃና ምስል በመመልከትና

ከላይ በተጠቀሱት የተለያዩ መንገዶች ጓደኝነት የመሰረቱት ከሁለቱም ፆታ 18.1% የሚሆኑት ናቸው።።

በነዚህ ድረ-ገጾች የሚደረግ የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ፣ በተለይ የፍቅር ጥያቄ የቀረበላቸውና የወሲብ ምስል ከሌሎች የደረሳቸውን ለማወቅ የቀረበ ጥያቄ ነበር።። የማህበረሰብ ድረ-ገጽ ከሚጠቀሙትም ውስጥ 534 (46.8%) የሚሆኑት በፌስ ቡክ የፍቅር ጥያቄ እንደቀረበላቸው፣ አልያም ወሲብ ነክ ምስልና መልዕክት እንደተቀበለ መረጃው ያሳያል።። ከነዚህም ውስጥ መልእክቱ የደረሳቸው ሴቶች 53.6% የሚሆኑት ናቸው።።

በተጨማሪም የመጠይቁ ተሳታፊዎች አብዛኛውን ጊዜ ምን ዓይነት ፊልም መመልከት እንደሚመርጡም ተጠይቀው ነበር።። በዚህም መሰረት ከአጠቃላዩ የጥናቱ ተሳታፊዎች 44.9% ፍቅር ነክ ፊልሞችን መመልከት እንደሚያዘወት ሲገልጹ፣ በተመሳሳይ ከተሳታፊዎቹ 42.5%ቱ አስቂኝ ይዘት ያላቸውን ፊልሞች የሚመለከቱ ናቸው።። ከላይ የተጠቀሱት ተሳታፊዎች ሌሎችንም የፊልም ዓይነቶች እንደሚመለከቱ የገለጹ ሲሆን ከዚህም ጋር በተያያዘ የሚመለከቷቸውን ፊልሞች ማን እንደሚመርጥላቸው ተጠይቀው 81.8% የሚሆኑት ራሳቸው እንደሚመርጡ ጠቅሰዋል።።

**ግራፍ 1. የወሲብ ፊልም የተመለከቱ ተሳታፊዎች በመቶኛ**




የተለያዩ ፊልሞችን ከመመልከት ጋር በተያያዘ የመጠይቁ ተሳታፊዎች የወሲብ ፊልም አይተው ያውቁ እንደሆነ ተጠይቀው ነበር።። ከዚህም የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ (60.9%) የሆኑት መሰል ፊልሞችን የተመለከቱ መሆናቸውን ነው።።

ከነዚህም ውስጥ 55% የሆኑት ወንዶች ሲሆኑ የተቀሩት 45% ሴቶች ናቸው። በተያያዘም የወሲብ ፊልም ከተመለከቱት ውስጥ 90.6% የሚሆኑት ከ15 እስከ 29 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ታዳጊ ወጣቶች ናቸው። በሌላ በኩል የወሲብ ፊልምን የተመለከቱት አብዛኞቹ (40.8%) የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሲሆኑ፤ በመቀጠል በብዛት ተመልክተናል ብለው የመለሱት ሰርተፍኬትና ዲፕሎም ያላቸው ተሳታፊዎች ናቸው። ይሁን እንጂ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በመማር ላይ የሚገኙና የወሲብ ፊልም የተመለከቱት ቁጥር (10.9%) ቀላል ግምት የሚሰጠው አደለም።

ከዚህም ጋር በተያያዘ የወሲብ ፊልሞችን ተመልክተናል ካሉት ተሳታፊዎች ውስጥ 58.3% የሚሆኑት ያላገቡ ሲሆኑ፤ በመቀጠል ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት (35.4%) በትዳር ውስጥና በቃል ኪዳን ደረጃ ያሉት ናቸው።

በሌላ በኩል የወሲብ ፊልምን የመመልከት ልምድ ካላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች ውስጥ፣ (55.7%) ያህሉ ፊልሙን ያዩት በአጋጣሚ መሆኑን ሲያመለክቱ፤ በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጡት (33.1%) አልፎ አልፎ የሚመለከቱ መሆናቸውን መረጃው ያሳያል። ይሁን እንጂ ሁልግዜ የመመልከት ልምድ አለን ብለው የመለሱት 11.3% የሚሆኑት ናቸው።

**ሠንጠረዥ 4. የወሲብ ፊልም የተመለከቱ ተሳታፊዎች ፊልሙን ያገኙበት መንገድ**

| ተ.ቁ | | | አዎ | | አይደለም | | የማይመለከታቸው | | ጠቅላላ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| 1 | የወሲብ ፊልም የተመለከቱ ተሳታፊዎች ፊልሙን ያገኙበት ሁኔታ | በኪራይ | 521 | 20.6 | 1019 | 40.3 | 989 | 39.1 | 2529 | 100 |
| | | በውሰት | 350 | 13.8 | 1191 | 47.1 | 988 | 39.1 | 2529 | 100 |
| | | ቪድዮ ቤት በመሄድ | 314 | 12.4 | 1227 | 48.5 | 988 | 39.1 | 2529 | 100 |

የወሲብ ፊልምን የተመለከቱ የመጠይቁ ተሳታፊዎች እነዚህን ፊልሞች የት እንደሚያገኙዋቸውም ተጠይቀው ነበር፡፡ በዚህም መሰረት (28%) በሞባይል በማላላክ ፣(20.6%) በኪራይ የሚያገኙ ሲሆን፣ ሌላው (17.8%) ደግሞ ከኢንተርኔት መሆኑን ከላይ በሠንጠረዥ 4 ተመልክቷል ፡፡

ከማንበብ ልማድ ጋር በተያያዘ የጥናቱ ተሳታፊዎች ምን ዓይነት የህትመት ውጤት እንደሚያዘወትሩ ተጠይቀው ነበር፡፡ በመልሳቸውም አብዛኞቹ (65.1%) የፍቅርና የወሲብ ነክ ጉዳዮችን የማንበብ ልምድ እንዳላቸው ጠቅሰዋል፡፡

| ተ.ቁ | | | ቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአልኮል መጠጦችን ተጠቅመው ያውቃሉ? | አውቃለሁ | 1535 | 60.7 |
| | | አላውቅም | 994 | 39.3 |
| | | **ጠቅላላ** | **2529** | **100.0** |
| 2 | የአልኮል መጠጦችን የሚጠቀሙ ከሆነ ምን አይነት? | በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ | 318 | 12.6 |
| | | በፋብሪካ የሚዘጋጁ | 623 | 24.6 |
| | | ሁለቱንም | 555 | 21.9 |
| | | የማይመለከታቸው | 994 | 39.3 |
| | | ያልገለጹ | 39 | 1.5 |
| | | **ጠቅላላ** | **2529** | **100.0** |
| 3 | የአልኮል መጠጦችን በምን ያህል ጊዜ ይጠቀማቸዋል | በየቀኑ | 145 | 5.7 |
| | | በእረፍት ቀናት | 378 | 14.9 |
| | | በአመት በዓላት | 463 | 18.3 |
| | | በአጋጣሚ | 506 | 20.0 |
| | | የማይመለከታቸው | 994 | 39.3 |
| | | ያልገለጹ | 43 | 1.7 |
| | | **ጠቅላላ** | **2529** | **100.0** |
| 4 | የአልኮል መጠጦችን የሚጠቀሙባቸው ቦታዎች | በመኖሪያ ቤት | 645 | 25.5 |
| | | መጠጥ ቤት በመሄድ | 542 | 21.4 |
| | | ገለል ያሉ ቦታዎች በመምረጥ | 122 | 4.8 |
| | | የማይመለከታቸው | 994 | 39.3 |
| | | ያልገለጹ | 226 | 8.9 |
| | | **ጠቅላላ** | **2529** | **100.0** |

ለመጠይቁ ተሳታፊዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች አንዱ የሚያደንቋቸው ሰዎች ከየት እንደሆኑ ነበር። በመልሳቸውም 46.8%ቱ የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ ታዋቂ ሰዎችን እንደሚያደንቁ ሲገልፁ፣ 30.6% የሆኑት ግን ከሀገር ውስጥ ብቻ እንደሚያደንቁ ጠቅሰዋል። ከዚህም ጋር በተያያዘ 14.8% የሚሆኑት መላሾች ከሚያደንቋቸው ሰዎች ትኩረት የሚሰጡት የአለባበስ፣ አጋጌጥና የመዝናኛ ምርጫቸውን/ "እስታይልላቸውን" እንደሆነ ገልፀዋል።

### ለ. የሱስ አስያዥ ዕፆችና የአልኮል መጠጦች

የሱስ አስያዥ ዕፅና አልኮል መጠቀም ግለሰባዊ ባህሪ ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ ሊኖር ይችል እንደሆነ ተሳታፊዎች ተጠይቀው ነበር። ይህንንም አስመልክቶ የተሰጠው የተሳታፊዎች ምላሽ ቀጥሎ ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ 5. የተለያዩ አልኮል መጠጦች አጠቃቀም**

| ተ.ቁ | | | እጠቀማለሁ | | አልጠቀምም | | የማይመለከታቸው | | ጠቅላላ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| 1 | ተሳታፊዎች ተጠቅመው የሚያውቁት የሱስ አስያዥ ዕፆች ዓይነት | ሲጋራ | 251 | 9.9 | 466 | 18.4 | 1812 | 71.6 | 2529 | 100.0 |
| | | ጫት | 528 | 20.9 | 189 | 7.5 | 1812 | 71.6 | 2529 | 100.0 |
| | | ሺሻ | 337 | 13.3 | 380 | 15.0 | 1812 | 71.6 | 2529 | 100.0 |
| | | ሀሺሽ | 180 | 7.1 | 537 | 21.2 | 1812 | 71.6 | 2529 | 100.0 |
| | | ሄሮይን/ኮኬይን | 51 | 2.0 | 666 | 26.3 | 1812 | 71.6 | 2529 | 100.0 |
| 2 | አብዛኛውን ጊዜ ሱስ አስያዥ ዕፆችን የት ይጠቀማሉ? | ከሱቅ በመግዛት ቤት ውስጥ | 258 | 10.2 | 457 | 18.1 | 1814 | 71.7 | 2529 | 100.0 |
| | | ለዚህ በግልፅ በተዘጋጁ ቦታዎች በመሄድ | 179 | 7.1 | 536 | 21.2 | 1814 | 71.7 | 2529 | 100.0 |
| | | ከጓደኞቼ ጋር ቦታ በመምረጥ | 338 | 13.4 | 377 | 14.9 | 1814 | 71.7 | 2529 | 100.0 |
| | | በድብቅ በተዘጋጁ ቦታዎች በመሄድ | 240 | 9.5 | 475 | 18.8 | 1814 | 71.7 | 2529 | 100.0 |

ከሠንጠረዥ 5 ማየት እንደሚቻለው፣ ለዚህ ምላሽ ከሰጡት ውስጥ 1535 (60.7%) የሚሆኑት የአልኮል መጠጦችን ተጠቅመው እንደሚያውቁ ሲጠቅሱ፤ ከነዚህም ውስጥ 52.3% የሆኑት ወንዶች ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ 24.6% የሆኑት የፋብሪካ ውጤት የሆኑ የአልኮል መጠጦችን እንደሚጠቀሙ ጠቅሰዋል። ከነዚህም ውስጥ 25.3% የሆኑትን ታዳጊ ወጣቶች (15-19 ዓመት) ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ አልኮል መጠጥን ከሚወስዱት 52.3% የሆኑት ወንዶች እንደሆኑ ተመልክቷል። በተጨማሪም አልኮል

ተጠቃሚ ነን ካሉት ውስጥ በምን ያህል ግዜ የመጠቀም ልምድ እንዳላቸው ተጠይቀው ነበር፡፡ በመልሱም 523(20.6%) የሚሆኑት በየቀኑና በዕረፍት ቀናት እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል። የአልኮል መጠቀሚያ ቦታቸውን በተመለከተም ተጠይቀው ሲመልሱ 645 (25.5%) የሚሆኑት በመኖሪያ ቤታቸው፤ 542 (21.4%)ቱ ደግሞ መጠጥ በሚሸጥባቸው ቤቶች በመሄድ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡

ሱስ አስያዥ ዕፅን በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ፣ በት/ቤት ቆይታቸው አልያም ከት/ቤት ውጪ ባሉ አጋጣሚዎች ግንዛቤ አግኝተው ያውቁ እንደሆነ ተጠይቀው፤ 81.6% ግንዛቤው እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ አብዛኞቹ (52.4%) ግንዛቤውን ያገኙት ከተለያዩ የሚዲያ ውጤቶች ሲሆን፣ 35.7% የሆኑት ደግሞ በስረዓተ-ትምህርቱ ውስጥ ተካቶ በመሰጠቱ መሆኑን መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 29.2%ቱ ብቻ በተለያዩ ክበቦች በመሳተፍ ግንዛቤውን እንዳገኙ ጠቅሰዋል፡፡

**ግራፍ 2. ሱስ አስያዥ ዕፆችን ተጠቅመው የሚያውቁ ተሳታፊዎች በመቶኛ**




የጥናቱ ተሳታፊዎች ማንኛውንም ሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቅመው ያውቁ እንደሆነ ተጠይቀው 717 (28.4%) የሚሆኑት አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 56.8% የሚሆኑት ወንዶች ሲሆኑ የተቀሩት ሴቶች ናቸው፡፡ ዕፅ ተጠቅመናል ያሉትን በእድሜያቸው ስንመለከት፣ 86.8% ወጣቶች ሲሆኑ፤ እድሜያቸው 15-19 ያሉት ታዳጊ ወጣቶች ድርሻ 22.5% ነው፡፡ በሌላ በኩል በምላሹ ከተሳተፉትና እድሜያቸው ከ 30 ዓመት በላይ ከሆኑት ሴቶች ውስጥ 30.5% የሆኑት የአነቃቂ እፅ ተጠቃሚ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 6. የተለያዩ ሱስ አስያዥ ዕፆች አጠቃቀም በመቶኛ**

በጥናቱ ከተሳተፉት የሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቃሚዎች 528 (20.9%)ቱ የጫት፣ 337 (13.3%) የሺሻ ፣251 (9.9%) የሲጋራ ፣ የሀሺሽ 180 (7.1%) ተጠቃሚዎች ሆነው ሲገኙ፣ የሄሮይን/ኮኬይን ተጠቃሚዎች ደግሞ 51(2%) እንደሆኑ ከሰንጠረዥ 5 መረዳት ይቻላል ።

በሌላ በኩልም የሱስ ዕፅ ተጠቃሚ ቤተሰብ ወይም ጓደኛ እንዳላቸው ተጠይቀው ሲመልሱ፣ 41.1% የሚሆኑት አወንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህም ጋር በተያያዘ የአነቃቂ ዕፅ ተጠቃሚ ቤተሰብ ወይም ጓደኛ አለን ካሉት ውስጥ 50.1% የሚሆኑት ራሳቸው ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የተለያዩ ሱስ አስያዥ ዕፆችን ከሚጠቀሙት ውስጥ 80.6% የሚሆኑት ከጓደኞቻቸው ጋር ለዚህ ተግባር አመቺ በሆኑና ድብቅ ቦታዎች እንደሆነ ገልፀዋል። ከአጠቃላይ ተጠቃሚዎች ውስጥ 53.6% የሆኑት ተማሪዎችና ስራ አጥ መሆናቸውንም የተገኘው መረጃ ያሳያል። በሌላ በኩል የዕፅ ተጠቃሚዎቹ ለዕፅ የሚያውሉት ገንዘብ ምንጭ ከየት እንደሆነ ተጠይቀው 28.3% የሆኑት ከቤተሰብ እንደሚያገኙት ሲናገሩ፣ የተቀሩት ከስራ ከሚገኝ ገቢ፣ ከጓደኛና ከሌሎች የተለያዩ ምንጮች እንደሆነ ገልጸዋል። በተጨማሪም ተሳታፊዎቹ በአካባቢያቸው ስላለው የዕፅ አዘዋዋሪዎችና ሻጮች ሁኔታ ሲገልጹ 56.7% የሚሆኑት እንቅስቃሴው ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰዋል። በሌላ በኩል የዕፅ ተጠቃሚ ነን ካሉት ውስጥ 84.3%ቱ ወደ እምነት ተቋማት የመሄድ ልምድ እንዳላቸው ገልፀዋል።

### ሐ. ፆታዊ ግንኙነት

የመጠይቁ ተሳታፊዎች በፆታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ ጥያቄዎችን ተጠይቀው ሲመልሱ፤ ከጠቅላላው ተሳታፊዎች ውስጥ 1513 (59.8%) የሚሆኑት ወሲብ እንደፈፀሙ ገልፀዋል። ወሲብ ፈፅመናል ካሉት ውስጥ 53.6%ቱ ሴቶች ሲሆኑ የተቀሩት ወንዶች ናቸው። ከዚህ ውስጥ እድሜያቸው ከ15-19 ዓመት የሆኑት ታዳጊ ወጣቶች ድርሻ 18.5% ይያዛል።

**ግራፍ 3. ተሳታፊዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ የፈጸሙበት የዕድሜ ክልል በመቶኛ**




በሌላ በኩል ተሳታፊዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ የፈጸሙበትን ዕድሜ ተጠይቀው ነበር። በምላሹም 93 (3.7%) የሆኑት ከ15 ዓመት በታች እንደነበር ሲገልጹ፤ 674 (26.9%) ተሳታፊዎች ደግሞ የመጀመሪያ ወሲብ የፈፀሙት ከ15-18 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ መሆኑን ተናግረዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ የፈፀሙት ከማን ጋር እንደሆነ ተጠይቀው፤ አብዛኞቹ (52%) የፍቅር ጓደኞቻችን ካሏቸው ጋር መሆኑን ሲጠቅሱ፣ በአጋጣሚ ከተዋወቁት ሰው ድንገተኛ ወሲብ የፈፀሙት ደግሞ 19.9%(295) ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር 5%(74)ቱ ፣ እንዲሁም ተገደው የተደፈሩት 2.2%(32) መሆናቸውን መረጃው ያሳያል።

ከየታዊ ግንኙነት ጋር በተያያዘ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ያላቸው 30.2% እንደሆኑ መረጃው ያሳያል። ከነዚህም 53.4% የሆኑት ወንዶች ሲሆኑ፤ የተቀሩት ደግሞ ሴቶች ናቸው። ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ያላቸው ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡ አብዛኞቹ (40.1%) ልምድ ለማካበት እንደሆነ ሲገልጹ፤ 27.5%ቱ ደግሞ ከጓደኞቻቸው በማየትና እንደ ትክክለኛ ነገር በመቁጠር እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በሌላ በኩል ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ስለሚደረግ ወሲባዊ ግንኙነት ግንዛቤው እንዳላቸው የገለፁት ተሳታፊዎች 86%ቱ ሲሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ 51%ቱ ግንዛቤውን ያገኙት ከተለያዩ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ መረብ መሆኑን አስቀምጠዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ 14.2 %ቱ ስለጉዳዩ ያወቁት ግብረ ሰዶማዊ የሆኑ ሰዎችን ስለሚያውቁ መሆኑን ጠቅሰዋል።

**ግራፍ 4. ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የወሲብ ግንኙነት አድርገው የሚያውቁ ተሳታፊዎች በቁጥር**




ከላይ በ"ግራፍ" 4 እንደተገለጸው፤ 182 (7.2%) ተሳታፊዎች ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የወሲብ ግንኙነት አድርገው እንደሚያውቁ ጠቅሰዋል። ለዚህም ምክንያት ሲያስቀምጡ፤ 65 ተሳታፊዎች (38.2%) ለመሞከር ፣ 49ኙ (28.8%) ተገዶ በመደፈር፣ 29ኙ (17%) በጓደኛ ግፊትና የተቀሩት 27 ተሳታፊዎች (15.9%) ደግሞ በአልኮልና ዕፅ ተገፋፍተው እንደፈፀሙት ገልፀዋል። ከግብረ ሰዶማዊነት ጋር በተያያዘ ተሳታፊዎቹ ያላቸውን አስተያየት እንዲገልፁ ተጠይቀው ከመለሱት፤ 80.1%ቱ ይህን ተግባር የሚቃወሙት ከባህልና እምነት አንፃር ተቀባይነት ስለሌለው እንደሆነ ገልጸዋል። ይሁን እንጂ ጥቂት የማይባሉ 182 (7.3 %) የሚሆኑት እንደሚደግፉትና ለዚህም ምክንያታቸው መብትና የዘመናዊነት መገለጫ በመሆኑ እንደሆነ አስቀምጠዋል።

ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ወሲብ ፈጸምን ካሉት ውስጥ 104 (57.1%) የሚሆኑት ወንዶች ሲሆኑ የተቀሩት 78(42.9%)ቱ ሴቶች ናቸው። ከዚህ ውስጥ 66 (36.3%)ቱ ዕድሜያቸው ከ15-19 ዓመት የሆናቸው ታዳጊዎች፣ 53 (29.1%)ቱ ከ20-24 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ፣ 44 (24.2%) ዕድሜያቸው ከ25-29 ሲሆን፤ 19 (10.4%) የሚሆኑት ደግሞ ከ30 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶች መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያሳያል።

### መ. ለሱስ አስያዥ ዕፆችና ለአልኮል መጠጦች የሚያጋልጡ ቦታዎች

**ግራፍ 5. በወጣቶች እና በሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የመዝናኛ ቦታዎች**




ለወጣቶችና ሴቶች የስነ-ምግባር ጉድለትና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች የሚጠቀሱ በርካታ ምክንያቶች አለ፡፡ ይህንንም በተመለከተ የጥናቱ ተሳታፊዎች ወጣቶችን ለአላስፈላጊ ነገሮች የሚዳርጉ ካሏቸው ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የጫትና ሺሻ ቤቶች (37.7%) እና የምሽት ጭፈራ ቤቶች (36.4%) በዋናነት ተጠቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም የቀን ጭፈራ ቤቶችን እንደ ዋነኛ ችግር የጠቀሱት ደግሞ 8.9% የሚሆኑ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ነገሮች የሚያመሩ ተብለው ከተጠቀሱት ዋነኛው የምሽት ጭፈራ ቤት (44.8%) ሲሆን፤ በመቀጠል ጫትና ሺሻ ቤቶችን (25.1%) ተፅእኖ አሳዳሪ ናቸው ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡በሌላ በኩል 13.5% የሚሆኑት መረጃ ሰጪዎች የቀን ጭፈራ ቤትን በምክንያትነት አስቀምጠዋል፡፡

**ግራፍ 6. ለአላስፈላጊ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ተጋላጭ የሆኑ የህብተረተሰብ ክፍሎች**




ለተለያዩ አላስፈላጊ ድርጊቶች ይበልጥ ተጋላጭና ተጎጂ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል የቱ እንደሆነ ተጠይቀው ሲመልሱ፤ 28.4%ቱ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ 25.9%ቱ ተማሪዎች፣ 24.9%ቱ የወሲብ ስራ ተዳዳሪዎች እና 10.6%ቱ ወጣት ሴቶች መሆናቸው በተሳታፊዎቹ ተገልጿል።

በሌላ በኩል የዕፅና የአልኮል ተጠቃሚዎች በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉት ችግር ምን እንደሆነ ከተጠየቁት መላሾች፤ 59.4%ቱ የዕፅና የአልኮል ተጠቃሚዎች በወንጀል ድርጊት ውስጥ እንደሚያሳተፉ ሲገልፁ፣ 57.8%ቱ የስራ መጥላት ባህሪ እንደሚታይባቸው ተናግረዋል።

**ግራፍ 7. ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና አላስፈላጊ ባህሪያት የሚያጋልጡ ማህበራዊ ምክንያቶች**




**ከላይ በግራፍ 7 እንደተመለከተው፤ ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና አላስፈላጊ ባህሪያት የሚያጋልጡ ማህበራዊ ምክንያቶችን ተጠይቀው፤ 52.5%ቱ የቤተሰብ መፍረስ፣ 47.1%ቱ ስራ ማጣት፣ እንዲሁም 46.3%ቱ የቤተሰብ የፅፅና የአልኮል ተጠቃሚ መሆንን በምክንያትነት አንስተዋል።።**

**ግራፍ 8. ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና አላስፈላጊ ባህሪያት የሚያጋልጡ አካባቢያዊ ሁኔታ፣ የመገናኛ ብዙሃንና የአቻ ጓደኛ ግፊት በመቶኛ**




አካባቢ፣ መገናኛ ብዙሃንና የአቻ ጓደኛ ተፅዕኖዎች ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና አላስፈላጊ ባህርያት ያጋልጡ እንደሆነ፤ ተሳታፊዎች ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ በግራፍ 8 ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት 63.7%ቱ መላሾች በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያጋልጡ የጠቀሱት፤ የጭፈራ ፣ የጫት፣ የሺሻና የመጠጥ ቤቶችን መስፋፋት ሲሆን፣ 52.3%ቱ የጓደኛ ተፅዕኖ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም 42.1%ቱ የትምህርት ቤትና የመኖሪያ አካባቢ ለሱስ በሚያጋልጡ ነገሮች መከበብ፣ 39%ቱ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ መረቦች መስፋፋትን በምክንያትነት ሲጠቅሱ፤ የተቀሩት የተለያዩ ምክንያቶችን ሰጥተዋል፡፡

በትርፍ ጊዜ ከመዝናናት ጋር በተያያዘ ሴቶች ብዙውን ጊዜ በምን ሁኔታ እንደሚያሳልፉ ተሳታፊዎቹ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ 78.2%ቱ በቤት ውስጥ ስራ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም 72.5%ቱ ፊልም በማየት፣ 58.2%ቱ በጭፈራ ቤቶች በመዝናናትና 41.9%ቱ እፅ በመውሰድ ጊዜያቸውን ሊያሳልፉ እንደሚችሉ ጠቅሰዋል፡፡

**ግራፍ 9. ሴቶችን ለመጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡ ሁኔታዎች**




ሴቶችና ወጣቶችን ወደ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲያመሩ የሚያደርጉ ምክንያቶች በርካታ መሆናቸውን በግራፍ 9 የተጠቀሰው መረጃ ያሳያል። ተሳታፊዎቹ በሴቶች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ካሉዋቸው ምክንያቶች መካከል፣ 65.3%ቱ የውጭ ባህልን መከተልን እንደ ስልጣኔ መቁጠር፣ 56.5%ቱ የራስን ባህል ጠንቅቆ አለማወቅ፣ 54.3%ቱ የራስን ባህል መናቅ፣ 38.8%ቱ የገቢ ምንጭ ፍለጋ፣ 37.7%ቱ የመገናኛ ብዙሃን፣ የመረጃ መረቦችና "ፊልሞች" ተፅዕኖን በዋናነት አንስተዋል።

**ግራፍ 10. ወጣቶችን ለመጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡ ሁኔታዎች**




| | የራስን ባህል ጠንቅቆ አለማወቅ | የራስን ባህል መናቅ | የውጭ ባህል መከተልን እንደ ስልጣኔ በመቁጠር | በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የውጭ ዜጎች በሚያሳድሩት ተፅዕኖ | የመገኛኛ ብዙሃን፣ኢንተር ኔትና የፊልሞች ተፅዕኖ | የመዝናኛ ቦታዎች አማራጭ አለመኖር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አጅግ በጣም | 59.9 | 55.6 | 61.7 | 24.2 | 40 | 44.4 |
| በጣም | 22.9 | 30.1 | 26.3 | 30.2 | 30.5 | 26 |
| በትንሹ | 13.5 | 9.5 | 8 | 31.4 | 20 | 19.8 |
| አላውቅም | 3.7 | 4.7 | 4 | 14.3 | 9.5 | 9.8 |

በግራፍ 10 እንደተመለከተው፤ ወጣቶች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩት ምክንያቶች ውስጥ 61.7%ቱ የውጭ ባህልን መከተልን እንደ ስልጣኔ በመቁጠር፣ 59.9%ቱ የራስን ባህል ጠንቅቆ አለማወቅ፣ 55.6%ቱ የራስን ባህል መናቅ፣ 44.4%ቱ የመዝናኛ ቦታዎች አማራጭ አለመኖር፣ 40%ቱ የመገናኛ ብዙሃን፣ የመረጃ መረቦችና "ፊልሞች" ተፅዕኖን በዋናነት አንስተዋል፡፡

በመጨረሻም የጥናቱ ተሳታፊዎች፤ የአዲስ አበባ ሴቶችና ወጣቶች በመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የተነሳ ለስነምግባር ችግርና ለአላስፈላጊ ባህሪያት ተጋልጠዋል ብለው ያስቡ እንደሆነ ተጠይቀዋል፡፡ለዚህም በሰጡት ምላሽ ሴቶች ለነዚህ ችግሮች ተጋልጠዋል ብለው የሚያምኑት 82% ተሳታፊዎች ሲሆኑ፣ ወጣቶች ለተመሳሳይ ችግር ተጋልጠዋል ያሉት ደግሞ 83.7% የሚሆኑት ናቸው፡፡

**ሠንጠረዥ 7. ሱስ አስያዥ ዕፆችና የአልኮል መጠጦች በተጠቃሚዎች ላይ የሚያደርሱት የስነልቡናና ማህበራዊ ተፅዕኖ**

| ተ.ቁ | | | ቁጥር | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የዕፅና የመጠጥ ተጠቃሚዎች የሚደርስባቸው የስነ-ልቦናዊ ችግሮች | ተስፋ መቁረጥ | 1122 | 44.4 |
| | | ራስን ማጥፋት | 220 | 8.7 |
| | | ትምህርት መጥላት/ማቋረጥ | 438 | 17.3 |
| | | ስንፍናና ስራ መጥላት | 211 | 8.3 |
| | | ግብረ ሰዶማዊነት(ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ወሲብ መፈጸም) | 102 | 4.0 |
| | | ድብርትና ጭንቀት | 231 | 9.1 |
| | | የበታችነት ስሜት | 167 | 6.6 |
| | | የማይመለከታቸው | 38 | 1.5 |
| | | ጠቅላላ | 2529 | 100.0 |
| 2 | የዕፅና የመጠጥ ተጠቃሚዎች የሚደርስባቸው የማህበራዊ ችግሮች | የቤተሰብ መፍረስ | 787 | 31.1 |
| | | የጤና ችግር | 735 | 29.1 |
| | | ከስራ መፈናቀል (ስራ ማጣት) | 288 | 11.4 |
| | | ስደት | 110 | 4.3 |
| | | ወደኃዳና መውጣት | 191 | 7.6 |
| | | ሴተኛ አዳሪነት | 128 | 5.1 |
| | | የጥገኝነት ባህል መጨመር | 263 | 10.4 |
| | | የማይመለከታቸው | 27 | 1.1 |
| | | ጠቅላላ | 2529 | 100.0 |

ከዕፅና አልኮል ተጠቃሚነት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ የተለያዩ ስነ-ልቦናዊ ተፅዕኖዎች ማለትም፤ ተስፋ መቁረጥ፣ ራስን ማጥፋት፣ ትምህርት ማቋረጥና የመሳሰሉት መሆናቸው በሠንጠረዥ 7 ተመልክቷል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ተስፋ መቁረጥ 44.4%፣ ትምህርትን ማቋረጥ ወይም መጥላት 17.3% ሲሆን፤ 8.3%ቱ ራስን ወደ ማጥፋት እንደሚያመሩ በተሳታፊዎች ተጠቅሷል፡፡

ከማህበራዊ ችግሮች ጋር በተያያዘም በነዚህ ሰዎች ላይ የቤተሰብ መፍረስ ሊያጋጥም እንደሚችል የጠቀሱት 31.1% የሚሆኑ መላሾች ሲሆኑ፣ የጤና ችግር እንደሚገጥማቸው የገለፁት ደግሞ 29.1% ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ይህ ባህሪያቸው ለስራ መፈናቀል/ማጣት እንደሚዳርጋቸው 11.4%ቱ ሲገልጹ፤ 10.4%ቱ ደግሞ የጥገኝነት ባህሪ እንደሚስተዋልባቸው ገልጸዋል፡፡

የዕፅና መጠጥ ተጠቃሚዎች በህብረተሰቡ የሚደርስባቸው ተፅእኖ ምን እንደሆነ ተሳታፊዎቹ ተጠይቀው ሲመልሱ፣ 55.5%ቱ ከህብረተሰቡ መገለል፣ ከቤተሰብ መጣላት፣ በወንጀል መጠርጠርና የበታች ተደርጎ መቆጠር እንደሚደርስባቸው ጠቅሰዋል።

## 4.2. ተዛምዶአዊ ትንተና

የመጠናዊ መረጃው ግኝት እንደሚያሳየው፣ በወጣቶችና ሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊች ማሳያነት በርካታ ጉዳዮች ተነስተዋል። እነዚህ ድርጊቶችም ከተለያዩ የተሳታፊዎች ግላዊ ሁኔታና አነዱ ከሌላኛው ጋር ያላቸው ተዛምዶ (Correlation and Cross Tabulation) ደግሞ እንደሚከተለው ተተንትኗል።

### 4.2.1. የተሳታፊዎች ግላዊ ሁኔታ( ፆታ፣እድሜና የትምህርት ደረጃ) ከመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ያላቸው ተዛምዶ/Cross Tabulation

የወሲብ ፊልሞች በውጪ ሀገራት እየተመረቱ፣ በወበተለያዩ መንገዶች ወደ ኢትዮጵያ እየገቡና እየተሰራጩ እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ። በጥናቱ ከተሳተፉትና የወሲብ ፊልምን ከተመለከቱት ውስጥ 847(55%) ወንዶች ሲሆኑ፣693 (45%) ደግሞ ሴቶች ናቸው። ከዚህም ጋር በተያያዘ የወሲብ ፊልምን ከተመለከቱት አብዛኞቹ 629(40.8%) ከ20-24 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ሲሆኑ፣ ከ29 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶች ቁጥርም ከፍተኛ ነው።

የአልኮል መጠጦች ተጠቃሚነት ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ያለውን ተዛምዶ ስንመለከት፣ አልኮል ከሚጠቀሙት ውስጥ 803(52.3%) ወንዶች ሲሆኑ፣ የተቀሩት 732(47.7%) ደግሞ ሴቶች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ 580(37.8%) የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ20-24 ዓመት ሲሆን፣ 389(25.3%) ከ15-19 የእድሜ ክልል፣ 353(23%) ከ25-29 የእድሜ ክልል፣ እንዲሁም 213(13.9%) የሆኑት ደግሞ ከ29 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶች ናቸው። በዚህም መሰረት በርካታ የአልኮል ተጠቃሚ ሆነው የተገኙት ወንዶች ሲሆኑ፣ ከፍተኛ የአልኮል ተጣቃሚ ቁጥር ያለው የእድሜ ክልል ደግሞ ከ20-24-ዓመት ያለው ነው። የአልኮል ተጠቃሚነትን ከስራ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር አልኮል እንጠቀማለን ካሉት ውስጥ 506(33.1%) የሚሆኑት ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በግል ስራ እንተዳደራለን ያሉ መላሾች 448(29.3%)ቱም የአልኮል ተጠቃሚዎች መሆናቸው ታውቋል። በተጨማሪም 189(12.3%)ቱ የመንግስት ሠራተኞች ሆነው ተገኝተዋል። ከሁሉም ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት በተለያየ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ናቸው።

በሌላ በኩል ወሲብ ከፈፀሙት የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል 811(53.6%) ሴቶች ሲሆኑ፣ 702(46.4%) ወንዶች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ 532(35.2%) ከ 20-24 ዓመት የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሲሆኑ፣ 407(26.9%)ቱ ከ 25-29 ዕድሜ ክልል፣ 249(19.4%) ደግሞ ከ29 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶች ሲሆኑ፤ የተቀሩት 280(18.5%) ያህሉ ደግሞ ከ15-19 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች ናቸው።

ከወሲባዊ ግንኙነት ጋር በተያያዘ፣ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ያላቸው ወንዶች 406 (53.4%) ሲሆን፣ ሴቶቹ 355(46.6%) ናቸው። ይህ ተግባር ከእድሜ ጋር ያለውን ተዛማጅነት ስንመለከት፣ 267(35.1%) የሆኑት ከ20-24 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ሲሆኑ፣ 206(27.1%)ቱ ከ25-29፣ 72(22.6%)ቱ ከ15-19 ያሉ ሲሆኑ፤ ከ29 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶች ደግሞ 116 (15.2%) ናቸው። ተዛምዶአዊ ትንተናው እንደሚያሳየው በአብዛኛው ወሲብ የፈፀሙና ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ያላቸው ከ 20-24 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች ሲሆኑ፤ ከ29 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶችም፤ በዚህ የእድሜ ክልል ምላሽ ከሰጡት ቁጥር አንፃር እጅግ ከፍተኛ ነው።

በተጨማሪም ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ወሲብ ከፈፀሙት ውስጥ፣ 104(57.1%) የሆኑት ወንዶች ሲሆኑ፣ 78(42.9%) ደግሞ ሴቶች ናቸው። ከነዚህም 66(36.3%) የሚሆኑት ከ 15-19 ዓመት ያሉ ሲሆኑ፣53(29.1%) ከ 20-24 ዓመት ያሉ፣44(24.2%) ከ25-29 ዓመት የእድሜ ክልል ያሉ ሲሆኑ፤ 19(10.4%) የሆኑት ደግሞ ከ29 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶች ናቸው። ተዛምዶአዊ ግኝት የሚያሳየው ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የሚደረግ ወሲብ በከፍተኛ ሁኔታ የተመዘገበው ከ15-19 ዓመት ባሉ ታዳጊዎች ሲሆን፤ ከ29 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶች በዚህ ተግባር ውስጥ ተሳታፊ መሆናቸውንም መረጃው ያሳያል።

በዓለም አቀፍ የመረጃ መረቦችና ከሚሰራጩት መልእክቶች ጋር በተያያዘ፣ መጤ ባህሎች የመስፋፋት አቅማቸው ከፍ ያለ መሆኑን መረጃው ያሳያል። በዚህም መሰረት የማህበረሰብ ድረ-ገፅ (ፌስ ቡክ፣ቲውተር) ከተጠቀሙት ውስጥ 573(50.1%) ሴቶች ሲሆኑ፣ የተቀሩት 571(49.9%) ደግሞ ወንዶች ናቸው። ከነዚህም  ውስጥ 466(40.7%)ቱ እድሜያቸው ከ20-24 ዓመት ሲሆን፣ 353(30.9%) ከ15-19 የእድሜ ክልል፣ 208(17.8%) ደግሞ ከ25-29 ዓመት የእድሜ ክልል፤ እንዲሁም 121(10.6) ከ29 ዓመት በላይ ያሉት ሴቶች ናቸው። ይህ ተዛምዶ እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ የድረ-ገፅ ተጠቃሚዎች ሴቶች ሲሆኑ፣ ከእድሜ

ክልል ጋር ያለውን ተዛማጅነት ስንመለከት ደግሞ ከ20-24 ዓመት ያሉት ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ።።

የሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቃሚነት ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ያለውን ተዛማጅነት ለማየት በተደረገ ሂደት 407(56.8%) የሆኑት ወንዶች ሲሆኑ፤ የቀሩት 310(43.2%) ደግሞ ሴቶች ናቸው።። ከነዚህም ውስጥ 252(35.1%) የሆኑት ከ20-24 ዓመት ያሉ፣ እንዲሁም 209(29.1%)ቱ ከ25-29 የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው።። በተጨማሪም ከሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቃሚነት ጋር በተያያዘ 161(22.5%) ከ15-19 እንዲሁም 95(13.2%) ከ29 አመት በላይ ያሉት ሴቶች ናቸው።። የሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቃሚነት ከስራ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር እንጠቀማለን ካሉት ውስጥ 234(36.4%)ቱ በግል ስራ እንተዳደራለን ያሉ መላሾች መሆናቸው ታውቋል።። በተጨማሪም ሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቃሚ ከሆኑት ውስጥ 189(36%)ቱ ስራ አጦች እና 81(11.3%)ቱ የመንግስት ሠራተኞች ሆነው ተገኝተዋል።። የዕፅ ተጠቃሚ ተማሪዎች ቁጥርም 194(19.4%) ነው።። ከሁሉም ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት በግል ስራ የሚተዳደሩና ስራ አጥ የሆኑ ሰዎች ናቸው።።

በተመሳሳይ ሱስ አስያዥ ዕፅ ከተጠቀሙት ውስጥ፣ 623(87%) የወሲብ ፊልም የተመለከቱ ሲሆን፤ 1163(75.8%) የሚሆኑት የአልኮል ተጠቃሚዎችም በተመሳሳይ የወሲብ ፊልም ተመልክተዋል።። በሌላ በኩል የየሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቃሚ ሆነው ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የወሲብ ግንኙነት ያላቸው 130(18.2%) ሲሆኑ፤ አልኮል ተጠቃሚ ሆነው ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ወሲብ የፈፀሙት ደግሞ 154(10%) ናቸው።።

በሌላ በኩል ተማሪ ሆነው አልኮል መጠጦችን የሚወስዱት 506(50.5%) ሲሆኑ፣ ስራ ከሌላቸው ውስጥ ደግሞ 340(64.8%) የሚሆኑት ናቸው።። በተመሳሳይም ከተማሪዎች ውስጥ የተለያዩ አነቃቂ ዕፆች ተጠቃሚ የሆኑት 380(38%) ሲሆኑ፤ ስራ ከሌላቸው ውስጥ ደግሞ 322(61.3%) የሆኑት የተለያዩ አነቃቂ ዕፆች ተጠቃሚ ናቸው።።

በአጠቃላይ ከተዛምዶአዊ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው፤ ለተለያዩ ያልተገቡ ድርጊቶች (አነቃቂ ዕፅ ፣አልኮል መጠጥ፣ የወሲብ ፊል መመልት፣ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ መያዝ....) በይበልጥ ተጋላጭ የሆነው ከ20-24 አመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች ሲሆኑ፤ በፆታ ደረጃ ያላቸው ልዩነት ብዙም የጎላ አይደለም።።

ከ29 ዓመት በላይ እድሜ ኖሯቸው በመጠይቁ የተሳተፉ ሴቶች ቁጥር አነስተኛ ቢሆንም ከተመሳሳይ ያታ ጋር ወሲብ በማድረግ፣ እፅና አልኮል በመጠቀም፣እና ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ በመያዝ ድርጊት ውስጥ ግን በከፍተኛ ሁኔታ ተሳትፈዋል፡

| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የወሲብ ፊልም የተመለከቱ(1) | Pearson Correlation | - | .379** | .336** | .299** | .141** | .234** |
| | Sig. (2-tailed) | - | .000 | .000 | .000 | .000 | .000 |
| | N | - | 2528 | 2528 | 2517 | 2523 | 2524 |
| የአልኮል መጠጦችን የሚጠቀሙ(2) | Pearson Correlation | - | - | .402** | .435** | .136** | .169** |
| | Sig. (2-tailed) | - | - | .000 | .000 | .000 | .000 |
| | N | - | - | 2529 | 2518 | 2524 | 2525 |
| አነቃቂ እጾችን የሚጠቀሙ(3) | Pearson Correlation | - | - | - | .428** | .267** | .175** |
| | Sig. (2-tailed) | - | - | - | .000 | .000 | .000 |
| | N | - | - | - | 2518 | 2524 | 2525 |
| ከአንድ በላይ የወሲብ ¹ደኛ ያላቸው(4) | Pearson Correlation | - | - | - | - | .181** | .099** |
| | Sig. (2-tailed) | - | - | - | - | .000 | .000 |
| | N | - | - | - | - | 2514 | 2514 |
| ከተመሳሳይ ጸታ ጋር ወሲብ የፈጸሙ(5) | Pearson Correlation | - | - | - | - | - | .076** |
| | Sig. (2-tailed) | - | - | - | - | - | .000 |
| | N | - | - | - | - | - | 2520 |

### 4.2.2. መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ያላቸው ተዛምዶ/Correlation

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የማህበረሰብ ድረ ገጽ የሚጠቀሙ(6) | Pearson Correlation | - | - | - | - | - | - |
| | Sig. (2-tailed) | - | - | - | - | - | - |
| | N | - | - | - | - | - | - |

**ሠንጠረዥ 8.** መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች አንዱ ከሌላኛው ጋር ያላቸው ተዛምዶ/Correlation

*** የጎላ ተዛምዶ መኖሩን ያመለክታል*

ከላይ በሠንጠረዥ 8 እንደተመለከተው፣ የወሲብ ፊልሞችን መመልከት አልኮል ከመጠቀም (r=0.38)፣ አነቃቂ እጾችን ከመጠቀም (r=0.34)፣ በአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ከመያዝ (r=0.30)፣ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የወሲብ ግንኙነት ከመፈፀም (r=0.14)፣ እና ድረ ገጾችን ከመጠቀም (0r=0.23) ጋር የጎላ የሚባል አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው። ይህም ማለት የወሲብ ፊልም የሚመለከቱ ወጣቶችና ሴቶች የአልኮል መጠጦችንና አነቃቂ እፆችን ይጠቀማሉ። በተመሳሳይ መልኩ የወሲብ ፊልም የሚመለከቱ ወጣቶችና ሴቶች ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደና እንዳላቸውና የተመሳሳይ ፆታ ወሲብ እንደሚፈፅሙ መረጃው ያሳያል። በተያያዘም የወሲብ ፊልም የሚመለከቱ ሴቶችና ወጣቶች የተለያዩ የማህበረሰብ ድረ ገፆችን (ማለትም ፌስ ቡክ ቲውተር) የሚያዘወትሩ መሆናቸውን ያሳያል።

በተያያዘ መልኩ የአልኮል ተጠቃሚዎች፣ የተለያዩ አነቃቂ እፆችን ከመጠቀም (r= 0.40)፣ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ከመያዝ (r=0.44)፣ የተመሳሳይ ፆታ ወሲብ ከመፈፀም (0r=0.14) እና የማህበረሰብ ድረ ገፆችን ከመጠቀም ጋር ጠንካራ አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው።

በመሆኑም የተለያዩ የአልኮል መጠጦችን የሚጠቀሙ ወጣቶችና ሴቶች አነቃቂ እፆችን የመጠቀም፣ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ የመያዝና የተመሳሳይ ፆታ ወሲብ የመፈፀም እድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የተለያዩ አነቃቂ እፆችን መጠቀም፣ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ከመያዝ (r=0.43)፣ የተመሳሳይ ፆታ ወሲብ ከመፈፀም (r=0.28) እና የተለያዩ ድህረ ገጾችን ከመመልከት( r=0.076) ጋር የጎላ የሚባል አዎንታዊ ተዛምዶ/ግንኙነት አላቸው። ይህ ማለት አነቃቂ እፆችን የሚጠቀሙ ወጣቶችና ሴቶች፣ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ የመያዛቸውና የተመሳሳይ ፆታ ወሲብ የመፈፀማቸው እድል ከፍተኛ መሆኑን

ያመለክታል። በአጠቃላይ የወሲብ ፊልሞችን መመልከት አልኮል መጠጦችን መጠቀም፣ አነቃቂ እፆችን መጠቀም፣ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ መያዝ፣ የተመሳሳይ ፆታ ወሲብ መፈፀም እና የተለያዩ የማህበረሰብ ድረ ገፆች መመልከት በተወሰነ መልኩ የመጠን ልዩነት ቢኖርም አንዱ ከሌላው ጋር የጎላ የሚባል አዎንታዊ ግንኙነት እንዳላቸው ከተዛምዶአዊ ውጤቱ መረዳት ይቻላል።

## 4.3. የዓይነታዊ መረጃ ግኝት

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ዓይነታዊ መረጃ በሦስት መንገዶች ማለትም በቃለ መጠይቅ፣የተተኳሪ ቡድን ውይይትና ተሳትፎአዊ ምልከታ ተሰብስቧል። በነዚህ ዘዴዎች አማካኝነት የመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶችን ምንነት፣ ወጣቶችና ሴቶችን ለእነዚህ አላስፈላጊ ባህሎችና ድርጊቶች ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደረጓቸውን ምክንያቶች፣ እነዚህ እነዚህ ያልተገቡ ባህሎችና ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ ያስከተሉትን አሉታዊ ተፅዕኖና ችግሮቹን ለማስወገድ መደረግ ስለሚገባቸው የማስተካከያ ስራዎች ነገሮች የተሳታፊዎችን አመለካከትና አስተያየት ለመሰብሰብ ተሞክሯል።

መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ስምንት የቡድን ውይይቶች ከሴት አደረጃጀት አመራሮችና ከቢሮ ሠራተኛ ሴቶች ፣ ከቤት እመቤቶች፣ በወሲብ ሥራ ከሚተዳደሩ ሴቶች፣ ከሁለት ት/ቤት ተማሪዎች፣ ከት/ቤት ውጭ ካሉ ወጣቶች፣ በማረሚያ ቤት ካሉ ወጣት የህግ ታራሚዎችና ጫት በመቃም ሱስ ከተጠመዱ ወጣቶች ጋር ተደርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ ስምንት የቃለ-መጠይቆች ጫት በመሸጥና በማስቃም ስራ ከተሰማሩ ፣ በግብረ-ሰዶም ችግር ውስጥ ካሉ ፣ ከአእምሮና የስነ ልቦና ህክምና ባለሙያዎች፣ ከዕድር አመራሮች፣ ከፍትህ አካላት፣ ከፖሊስ፣ ከተለያዩ የእምነት ተቋማት መሪዎችና ከትምህርት ቤት ርዕሳነ-መምህራን ጋር ተደርገዋል። ከነዚህ የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች፣ ቃለ-መጠይቆችና ከተሳትፎአዊ ምልከታ የተገኘው መረጃ በየርዕሱ እንደሚከተለው ተተንትኗል።

### 4.3.1. በሴቶችና ወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች

የመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ምንነትን አስመልክቶ አንድ ወጥ ብያኔ መስጠት አዳጋች ቢሆንም የተለያዩ አካላት በውይይቱ ወቅት የነሱ መገለጫና ማሳያ ናቸው ያሉዋቸውን አስተያቶች ሰንዝረዋል። በዚህም መሰረት ያልተገቡ መጤ ባህሎችና ድርጊቶች የሚባሉት ሱስ አስያዥ ዕፆችን (የሺሻ ፣ሀሺሽ፤ ጫት፣ መጠጥ እና የመሳሰሉትን)

መጠቀም ፣ በቀን፣ በሌሊትና በራቁት ጭፈራ ቤቶች መዝናናት፣ ግብረ-ሰዶማዊነት፣ ለየት ያሉ ተግባራት በሚፈጸሙባቸው መታሻ/ማሳጅ ቤቶች መጠቀም፣ የግለኝነት አስተሳሰብ፤ ያልተገቡ የአለባበስ ሁኔታዎች እና የመሳሰሉት ናቸው በማለት ጠቅሰዋል፡፡ እነዚህንም ቀጥሎ እንመለከታለን

### ሀ. ሱስ አስያዥ ዕፆችን (ጫት፣ ሲጋራ፣ ሀሺሽ፣ ሺሻ፣ ሄሮይን) እና የአልኮል መጠጦችን መጠቀም

ይህ ችግር ከሁሉም በላይ የሆነ እና ለሌሎች ችግሮች ሁሉ መስፋፋት በመንስኤነት ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ በሁሉም ተሳታፊዎች ተጠቅሷል፡፡ በየትኛውም የዕድሜ ክልልና የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የተለያዩ ሱስ አስያዥ ዕፆችን እንደሚጠቀሙ መረጃ ሰጪዎቹ ያስረዳሉ፡፡ ይህንንም አስመልክቶ አንድ የፖሊስ ባልደረባ ሲገልጹ፡-

> *... እድሜያቸው ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ታዳጊ ወጣቶች በጫት ቤቶችና ሺሻ ቤቶች ይጠቀማሉ፤... በትምህርት ቤት ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በተጨባጭ አደንዛዥ እፅ በኪሳቸው ይዘው አጋጥመውናል...፤...ቁጥጥር ካልተደረገ በስተቀር ሺሻ ማጨስና ጫት መቃምን ልማዳዊ ባህል አድርገውታል...* ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ጫት በማስቃም ስራ የሚተዳደሩ ሌላ ተሳታፊ ደግሞ፤ ለተለያዩ ሱሶች ተጋላጭ የሆኑት ሰዎች ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ መሆናቸውን በሚከተለው መልኩ ገልጸውታል፤

> *...ከታክሲ ወያላ ጀምሮ እስከ ቢሮ ሰራተኞች ድረስ፣ ወታደርም ፖሊስም ይመጣሉ፡፡... እድሜያቸውንም ስንመለከት ከ16ና 17 ዓመት ጀምሮ ያሉ የተለያዩ ሰዎች ይመጣሉ፣ ይቅማሉ፡፡..ሁሉም ጫት፣ ይጠቀማሉ፤ተደብቀው ማድረግ የሚፈልጉት ነገር ስለሆነ ሁሉም ዓይነት ሰው ይመጣል፡፡በተለይ የቢሮ ሰራተኞች ባለቻቸው የምሳ ሰዓት ቅመው ለመሄድ ይመጣሉ፡፡ ሲመረቅኑ ግን "ባክህ ተወው" ብለው እዚሁ የሚቀሩበት ሁኔታም አለ፡፡*

በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተካፈሉ የቤት እመቤቶች፣ የቢሮ ሠራተኛ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች እንደገለጹት ሱስ የሚያስይዙ ነገሮችን የሚጠቀሙት ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ በትዳር ውስጥ ያሉ የቤት እመቤቶችና የቢሮ ሠራተኛ ሴቶችም ጭምር ናቸው ብለዋል፡፡ ችግሩ በተለይ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ባሉ ሴት ወጣቶች ላይ ጎልቶ እንደሚታይ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ለአንደኛው ሱስ ተጋላጭ መሆን ለሌላኛው መንገድ እንደሚከፍትና ተያያዥነትም እንዳላቸው በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህንን አስመልክቶ በሱሰኝነት ችግር ውስጥ ካሉ ወጣቶች ጋር በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ የሆነ አንድ ወጣት፤ "...ጫት ከሌሎች አነቃቂ ነገሮች ጋር ተያይዞ ይመጣል፡፡ መጀመሪያ ጫት ይቃማል፤ በመቀጠል ሲጋራ ወይም ሺሻ ወይም ሀሺሽ ከዚያ የአልኮል መጠጥ መጠቀም ይቀጥላል" በማለት ገልጿል፡፡

በተጨማሪም ያነጋገርናቸው በአማኑኤል የአእምሮ ህክምና ሆስፒታል አንድ የስነ-አእምሮ ሐኪም በሰጡት አስተያየት፤

> *...ወደ ሆስፒታላችን ከሚመጡት ቁጥር አንድ ከአልኮል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሁለተኛው የጫትም የሺሻም ችግሮች ይከተላል፡፡ የሄሮይንና የማሪዋና ችግሮችም አሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የማሪዋና ወይንም ካናቢስ ተጠቃሚዎች ቁጥር ከበፊቱ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ማሪዋና በፊት የሚጠቀሙት በመካከለኛው የዕድሜ ክልል ማለትም ከ25 እና 30 ዕድሜ በላይ ያሉት ሲሆን አሁን ግን በ10 እና በመጀመሪያዎቹ 20 የዕድሜ ክልል ባሉትም ይታያል...* ብለዋል፡፡

### ለ. በቀንና በሌሊት ጭፈራ ቤቶች መጠቀም

የቃለመጠይቅና የቡድን ውይይቱ ተሳታፊዎች እንደገለጹት፤ በአሁን ሰዓት ከተለመደው የማህበረሰባችን ወግና የአኗኗር ዘይቤ ወጣ ያሉ፣ የግለሰባዊ ስብዕናና ክብርን የሚፈታተኑ፣ የኢትጵያዊነት እሴቶችን የሚያወርዱና የሚያጠፉ የቀንና የሌሊት ጭፈራ ቤቶች፤ እንዲሁም የእርቃን ጭፈራ ቤቶች በከተማው ውስጥ ተስፋፍተዋል ብለዋል፡፡ ተሳታፊዎቹ አክለውም በዚህ የተነሳ ከልጅ እስከ አዋቂ ወደነዚህ ቤቶች በቡድን እየሆኑ በመሄድ መጠጣት፣ ማጨስና መጨፈር የተለመደ ተግባር ሆኗል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ከተለያዩ ሰዎች ጋር ወሲብ መፈጸም ያለ ሲሆን፤ ይህ ነገር እንደ ዘመናዊነት በመቆጠሩ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ እየተስፋፋ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡ ይህንንም የጥናት ቡድኑ አባላት ባካሄዱት የመስክ ምልከታ ተጨባጭ አድርገዋል፡፡

የጥናት ቡድኑ አባላት በመስክ ምልከታ ወቅት ካስተዋሏቸው ሁኔታዎች መካከል በከተማው ውስጥ ባሉ ከተለመደው ወጣ ያለ ክዋኔ የሚከወንባቸው የቀንና የሌሊት እንዲሁም የእርቃን ጭፈራ ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች በየፊናቸው የሚያከናውኗቸውን ነገሮች ታዝበዋል፡፡

በአብዛኛዎቹ የቀን ሞዶፈራ ቤቶች አካባቢ በርከት ያሉ የቤትና የንግድ መለያ ያላቸው መኪኖች ቆመው ተስተውለዋል። በመኪናዎቹ ውስጥም በጎልማሳና ከዚያ በላይ በሆነ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወንዶች፤ በአስራዎቹ የዕድሜ ክልል ካሉ ታዳጊ ሴት ተማሪዎች ጋር ጫት ሲቅሙ ለመመልከት ተችሏል።

ወደ ቤቶቹ ውስጥ ሲገባም ዕድሜያቸው ከ12-18 ዓመት የሚገመቱ ወጣት ወንዶች ለብቻ፤ ሴቶቹም እንዲሁ በቡድን በቡድን ሆነው ወደ ሞዶፈራው ክፍል ከመግባታቸው በፊት ከ5-10 ደቂቃ ቆይታ የሚያደርጉባቸው ሚስጢራዊ ክፍሎች ሲኖሩ፤ ከነዚህ ክፍሎች በመውጣትም በቀጥታ ወደ ሞዶፈራው ቦታ ሲገቡ ታይተዋል። አብዛኞቹ ሴቶች ወይንና ድራፍት የሚጠጡ ሲሆን፤ ወንዶቹም በቡድን በመሆን ድራፍትና ቢራ ይጠቀማሉ። ከቆይታ በኋላም ወጣቶቹ የተደበላላቁ የአልኮል መጠጦችን ሲጠቀሙ ታይቷል። የተወሰኑት ደግሞ ወደ ውስጥ ገብተው ከወጡ በኋላ ምንም መጠጥ ሳይዙ ለረጅም ጊዜ ሲጨፍሩ፤ ወንዶቹም ሆነ ሴቶቹ ሲጋራና ሲጋራ መሰል ግን የተለየ ሽታ ያለው ነገር በመቀባበል ሲያጨሱ ተስተውለዋል። የሞዶፈራ ቤቶቹ በሮች ስለሚዘጉም በሲጋራና በሌሎች ሞሶች የሚፈጠረው ሽታ የጤንነት ሁኔታን የሚፈታተን ነበረ።

ከአለባበሳቸውና ከሌሎች ሁኔታዎች አንፃር ሲታይ አብዛኞቹ ወጣቶች ጥሩ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የመጡ ይመስላሉ።ለሞዶፈራውም የሚከፈቱት የእንግሊዘኛ ዘፈኖች ሲሆኑ፤ አብዛኞቹም ወሲብ ቀስቃሽ ናቸው። በነዚህ ሙዚቃዎች በመታጀብም ጥንድ ጥንድ ሆነው ወጣ ያለና የአካል ንክኪ ያለው ዳንስ ሲደንሱ ታይተዋል። በመጨረሻም በነዚህ ቤቶች ውስጥ ተማሪዎቹ/ወጣቶቹ የአልኮል መጠጦችና የተለያዩ ዕፆችን ሲጠቀሙና ሲጨፍሩ አምሽተው ጥንድ ጥንድ በመሆን ወሲብ ለመፈጸም በአካባቢው በሚገኙ ፔኒሲዮኖችና ሆቴሎች የሚገቡበት ሁኔታም እንዳለ ተስተውሏል።

የሌሊት ሞዶፈራ ቤቶችን በተመለከትንበት ወቅት እነዚህ ቤቶች በተለምዶ የመጠጥና የመዝናኛ አገልግሎት እንደሚሰጡ የሚታወቅ ቢሆንም፤ ያልተፈቀደላቸውን የሺሻ ማስጨስ ሥራም ሲሰሩ ታዝበናል። በነዚህ ቤቶች በየጠረጴዛው የሺሻ ማጨሻ ዕቃዎች ተቀምጠው ተስተናጋጆች ሲጠቀሙባቸው ለማየት ተችሏል። በቤቶቹ ውስጥ በተለያዩ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙና ሁለቱንም ፆታዎች ያማከሉ ተስተናጋጆች ሲኖሩ፤

አብዛኛው ተስተናጋጅም በአነቃቂ ዕፆችና መጠጦች የተነሳ ወጣ ያሉ ወሲባዊ ባህሪያትን ሲያሳዩ ተስተውለዋል፡፡

በሌሊት ሜዶፈራ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ የመድረክ ተወዛዋገሮችም በአብዛኛው ለውዝዋዜ የሚጠቀሙባቸው አልባሳት ባህልን ያልጠበቁና ወሲብ ቀስቃሽ ናቸው፡፡ በነዚህ ቤቶች በቡድን በመግባት የሚስተናገዱትም የከተማይቱ ሰዎችና የሌሎች አፍሪካ ሀገራት ዜጎች በብዛት የሚስተዋሉ ሲሆን፤ ለተወዛዋገሮች በመድረክ ላይ ብር እንደ ቁጪማ ሲጎዘጎዝና በካርቶን ሲጠራቀም ለመታዘብ ተችሏል፡፡ ሴት አስተናጋጆችም በተለይ ከሌላ አፍሪካ ሀገራት ለመጡ ሰዎች ልዩ ትኩረትና ክብካቤ ሲያደርጉ፤ እንዲሁም አካላዊ ንክኪን ሲፈቅዱ ተስተውለዋል፡፡

የእርቃን ዳንስ ቤቶች ውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታን በተመለከተ ከውጪ ለሚመለከታቸው ከአንዱ በስተቀር ብዙዎቹ እንደ ማናቸውም የምሽት ክበባት ናቸው፡፡ የተለየ ጥበቃ፣ ተገልጋይ የመምረጥም ሆነ ደንበኞችን በጥርጣሬ የመመልከት ሁኔታ የለም፤ እንደ ማናቸውም ህጋዊ ስራዎች ሁሉ ተገልጋይ ይገባል፡፡ ለየት ያለው አንድ ቤት ግን ከፍተኛ ጥበቃና የጥርጣሬ ፍተሻ ይካሄድበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከሴቶች በስተቀር ተስተናጋጆችን ተቀብሎ ከጥንቃቄ ጋር ማስተናገዱ አልቀረም፡፡ ከነዚህ ቤቶች መካከል ጥቂቶቹ የመግቢያ ክፍያ ያላቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የመግቢያ ክፍያ ባይኖራውም ለመስተንግዶ የሚጠየቀው ዋጋ ከተለመደው ከፍ ያለ ነው፡፡

በተጨማሪም ሁሉንም የእርቃን ሜዶፈራ ቤቶች ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው፤ ለየት ያለ የመደነሻ መድረክ መኖሩ ነው፡፡ መድረኮቹ የአልሙንየም ቋሚ ብረቶች ሁለትና ሶስት ቦታ ተተክለውባቸዋል፡፡ የመደነሻ መድረኩን ይዞ ግድግዳዎቹ ሙሉ መስታወት ናቸው፡፡ የመጠጥ አገልግሎት የሚሰጡ መደርደሪዎች፣ ለተስተናጋጅ የተደረደሩ የሶፋ መቀመጫዎች በሁሉም ቤቶች አሉ፡፡ በተወሰኑት ቤቶችም ውስጥ ልዩ ክፍሎች እንዳሉ ለመታዘብ ተችሏል፡፡

በሁሉም ቤቶች አብዛኛዎቹ ተስተናጋጆች የውጪ ሀገር ዜጎችና የገቢ መጠናቸው ከፍ ያለ እንደሆነ የሚገመቱ የከተማችን ነዋሪዎች ናቸው፡፡ በቤቶቹ አካባቢም የተለያዩ ታርጋዎችን የለጠፉ መኪናዎች ቆመው ተስተውለዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የተወሰኑ የዲፕሎማትና

የእርዳታ ድርጅት ታርጋን የለጠፉ ሲሆን፤ አብዛኛዎቹ ግን የግል፣ የመንግስትና የንግድ ታርጋ ያላቸው አውቶሞቢሎች ናቸው።።የዕድሜ ስብጥሩ ብዙም የተለያየ አይደለም።። የወጣቶች ቁጥር አነስ ያለ ሲሆን ብዙዎቹ በመካከለኛ የዕድሜ ክልል የሚገመቱና ለደናሽ ወጣት ሴቶች ጠቀም ያለ የገንዘብ ሽልማቶችን ለመስጠት ብዙም የማያመነቱ መሆናቸው ተስተውሏል።።

በነዚህ ቤቶች ውስጥ ከጠባቂዎችና ከእርቃን ደናሾች ጋር በተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት በቦታው መጥተው የሚገለገሉም ሆነ በየቤታቸው በግል በማስጠራት ግልጋሎት የሚያገኙት ደንበኞች፤ ታዋቂ ግለሰቦች፣የተለያዩ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞችና ኃላፊዎች፣ እንዲሁም በንግድ ሥራ የተሰማሩ ግለሰቦችና የውጭ ዲፕሎማቶች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።።

በነዚህ ቤቶች ውስጥ ያሉ ለጋ ወጣት ሴት የእርቃን ደናሾች ሙሉ በሙሉ ጡታቸውንና ሀፍረተ-ስጋቸውን በአግባቡ የማይሸፍኑ እራፊ የጡት ማስያዣና የውስጥ ሱሪ በመጠቀም ፍፁም ወሲብ ቀስቃሽ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ ለመታዘብ ተችሏል።። በየመድረኩ እንደተመለከትነው በሁለትና በሶስት ዘፈኖች እረፍት ሴቶቹ ወደ መድረክ በመምጣት ከ15-20 ደቂቃ እንቅስቃሴ ካደረጉ በኋላ በእያንዳንዱ ተስተናጋጅ ጭን ላይ በመቀመጥ የወሲብ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ።። ይህን ማድረግ የማይሹ ተስተናጋጆችን ጎንተል አርገው የሚያልፉ ሲሆን፤ በቤቶቹ ውስጥ ያሉ ሌሎች ደናሾችም በየሙዚቃ እረፍቱ በተለያዩ ተስተናጋጆች ጭን ላይ በመቀመጥ ወሲባዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ተስተውለዋል።።

በምልከታው ወቅት በታዩት ቤቶቹ ያሉ ደናሾች ወጣቶችና መልካም የሰውነት አቋም ያላቸው መልከ መልካም ሴቶች ሲሆኑ፤ ከተለያዩ የእርቃን ደናሾች በተገኘው መረጃ ወርሃዊ ክፍያቸውም ከሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ውጪ ከ3,000 እስከ 14,000 ብር እንደሚደርስ ገልጸዋል።። እነዚህን የእርቃን ደናሾች የሚያሰለጥኑ የዳንስ አሰልጣኞችን ሁኔታ በተመለከተ ከደናሾቹ ጋር በተደረገው ኢ-መደበኛ ውይይት ለመረዳት እንደተቻለው፤ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት፣ ከአውሮፓና ከአሜሪካ መሰል ልምድ ይዘው የመጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።። እነዚህ አሰልጣኞች ለዚህ ስራ የሚሆኑ ሴቶችን፤ የኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅ ያለና መልካም የሰውነት አቋም ያላቸውን የሁለተኛ ደረጃ፣ የኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን፣ ትምህርታቸውን መቀጠል ያልቻሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን እና ከሞዴሊንግ ማሰልጠኛ ተቋማትና ከተለያዩ የምሽት መጠጥ

ቤቶች አስተናጋጆችን፣ በተለያዩ ጠቋሚዎችና መልማዮችን በመጠቀም እንደሚመለምሉ ተገልጿል።

በተጨማሪም መረጃ ሰጪዎቹ ከእነዚህ ቦታዎች የተመለመሉ ወጣት ሴቶችን ከስልጠና በኋላ፣ በተለያዩ የምሽት እርቃን ቤቶች የመድረክ ላይ ዳንስ ለማካሄድ፣ በሀገር ውስጥ ላሉ ደንበኞች በየቤቱና በተፈለገበት ቦታ በመሄድ ለተወሰነ ቀናት ግልጋሎት ለመስጠትና ወደ ተለያዩ የአፍሪካና አረብ ሀገራት መሰል ተግባራትን ለመፈጸም እንደሚላኩ ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በኢ-መደበኛ ውይይት መረጃውን ከሰጡን ወጣት የእርቃን ጨፋሪዎች መረዳት እንደተቻለው፣ ከክፍያው ከፍተኛነት የተነሳ ብዙ ወጣት ተማሪዎች ይህን ዕድል ለማግኘት በመፈለግ፣ እነሱን እንደሚጠይቋቸውና ወደዚህ ተግባር በስፋት የመግባት ፍላጎት ጥያቄዎችን እንደሚያስተናግዱ ተናግረዋል።

## ሐ. የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነት/ግብረሰዶማዊነት

የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነት/ግብረሰዶማዊነት/ን በተመለከተ፣ የጥናቱ ተሳታፊዎች ተፈጥሮአዊ ከሆነ የተራክቦ ተግባር የተለየና ያፈነገጠ፣ ተግባሩም ከእምነት፣ከባህል፣ከሥነ ምግባርም ሆነ ሞራል አንጻር ብዙ ድጋፍ እንደሌለው አስረድተዋል። የጉዳዩን አሳሳቢነት ሲገልጹም፣ በአሁኑ ጊዜ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ሴቶችን በከፍተኛ ደረጃ እየተጠናወተ መሆኑን ተናግረዋል። ግብረሰዶማዊነት አስከፊና መጨ ልማድ ሲሆን ድርጊቱም እየተስፋፋ በማህበረሰቡ ላይ የስነ-ልቡናና የማህበራዊ ቀውስ እያስከተለ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ከነዚህ ውስጥ በተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ጥቃት የደረሰበት አንድ የቃለመጠይቅ መረጃ ሰጪ በራሱ ላይ የደረሰውን ችግር ሲያስረዳ፤

> *...ለመጀመሪያ ጊዜ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ወሲብ የፈፀምኩት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሁኜ ዕድሜዬ ከ15 እስከ 16 ሲሆን ነዉ። ...ከትምህርት ቤት ወጥቼ ታክሲ ስጠብቅ አንድ በእድሜው ትልቅ ሰዉ ወደ እኔ በመምጣት ስለትምህርት ያዋራኝ ጀመረ።... ሲጋራ ሲያጨስ ነበር፣ ... እኔ ምን እንዳስነካኝ አላዉቅም ብቻ አስከትለኝ የማላዉቀዉ ራቅ ያለ ጫካ በመዉሰድ ግብረሰዶም ፈጸመብኝ:: ከዚያም ወደ ቤቴ መጣሁ ለመናገር አልደፈረኩም:: በዚህ የተነሳ ብዙ የአዕምሮ ጉዳት ደርሶብኛል፣ትምህርቴንም ለአንድ አመት አቋርጫለሁ...*ብሏል።

በተጨማሪም መረጃ ሰጪው አሁን በከተማው ውስጥ ስላለው ሁኔታ ሲያስረዳ፤ ከዚህ በፊት ወንድ ወንድን የሚያስብበት ሁኔታ አንዳልነበረ ገልጿል። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ለሴት ከመደንገጥ ይልቅ ወንድ ሲያዩ መደንገጥ እየተለመደ የመጣ ክስተት እንደሆነ ጠቅሶ፤ የዚህ ዓይነቱ ነገር መስፋፋቱንም ሲገልጽ፡-

> *....አሁን ቆመህ ራሱ ሊያናግሩህ የሚፈልጉ አሉ፤ ሰትሄድም ተከትለው መጥቶ ሊለክፍህ ይችላል:: ሰዓት ሰንት ነጪ ብለው በመጠየቅ ይጠጋል:: የሚጠየቁት በብዛት ትንንሾች ናቸዉ:: የሚጠይቁትም ዕድሜአቸዉ በአዋቂ ዉሰጥ ይጠቃለላል:: አንድ ቦታ ላይ ከአምስት እስከ ስድስት ሆነዉ ቆመዉ እንደ ወሲብ ንግድ ሰራ ተዳዳሪ አይነት ሰራ የሚሰሩም አሉ...ብሏል።*

በወሲብ ስራ ከሚተዳደሩ ሴቶች ጋር በተደረገ የቡድን ውይይት ወቅት አንድ ተሳታፊ በተመሳሳይ ያታ የወሲብ ግንኙነት ላይ አስተያየት ሲሰጡ፤ ወንዶቹም ሴቶቹም የእነሱን ተመሳሳይ ሲያጡ በባዕድ አካል/"አርቴፊሻል" ነገር ተጠቅመን ስሜታቸውን ለማርካት ይወስዱናል ሲሉ ቅድሚያውን የወሰዱት ተናጋሪ፤ "...በጣም የማይረሳኝ እንደ ወንድ የለበሰች ሴት አናግራኝ ወደ ቤቷ ከወሰደችኝ በኋላ ልብሷን ስታወላልቅ ሴት ነች፤ በላስቲክ ነገር የተሰራ የወንድ ብልት አውጥታ በዚህ ወሲብ ፈጽሚብኝ አለችኝ..." በማለት ሲገልጹ ሁለተኛዋ ደግሞ፤ "....አንድ ግዜ አንድ ወንድ መጥቶ ይዞኝ ሄዶ። ወደ ቤቱ ከገባን በኋላ የፕላስቲክ የወንድ ብልት አውጥቶ በዚህ በፊንጢጣዬ በኩል ወሲብ ፈጽሚብኝ አለኝ..." በማለት ገጠመኛቸውን አካፍለዋል።

ከተማሪዎች ጋር ባደረግነው የቡድን ውይይት ወቅት ከተሳታፊዎቹ አንዱ፤ ግብረሰዶማዊነት በአሁን ሰዓት ህፃናቱንም ሆነ ትልቁን እየበከለ ያለ አላስፈላጊ ልማድ እንደሆነ ሲገልጹ፡- "....ግብረሶዶማዊነት በሁሉም ቦታ እንዳለ ይታወቃል፤..በዚህ ችግር በአንደኛ ደረጃ ከ8ኛና ከዚያ በታች ያሉ ሕፃናትም ከወጣቱ በላይ ተጠቂ ናቸው።" ሲል ሌሎችም የውይይቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ሀሳቡን ተጋርተው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በማረሚያ ቤት ካሉ ታራሚዎች ጋር በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት፤ ተሳታፊዎቹ በማረሚያ ቤት ውስጥ የተመሳሳይ ያታ የወሲብ ግንኙነት እንደማይፈቀድ ተናግረዋል። ይሁን እንጂ፣ ሴቶች እርስ በርሳቸው ሲሳሳሙና ባዕድ አካል በመጠቀም ወሲብ ሲፈጽሙ መገኘታቸውን ገልጸው፤ ወንዶቹም በዚሁ ጉዳይ ተፈርዶባቸው ከገቡ በኋላ በማረሚያው ውስጥም ከሚመስላቸው ጋር ወይም በሌሎች ላይ እንደሚፈጽሙ ተናግረዋል።

### መ. ለየት ያሉ ተግባራት በሚፈጸሙባቸው መታሻ/ማሳጅ ቤቶች መጠቀም

በጥናቱ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው በአሁን ጊዜ ለየት ያሉ ያልተገቡ ተግባራት የሚፈጸሙባቸው መታሻ/ማሳጅ ቤቶችን መጠቀም እየተለመደ የመጣ አዲስ ልምድ ነው፡፡ በምልከታ ወቅት ለጥናቱ ርዕስ የመረጃ ምንጭነት ከተተኮረባቸው ቦታዎች መካከል የመታሻ/"ማሳጅ" ቤቶች አንዱ ናቸው፡፡ መታሻ ቤቶቹ የሚገኙባቸውን አካባቢዎች ለመለየት በተደረገው ቅኝት ለማወቅ እንደተቻለው ብዙዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ ትልልቅ የመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ሲሆኑ፤ ሌሎች ደግሞ በትልልቅ የንግድ ህንፃዎች ላይ የተከፈቱ ናቸው፡፡ በመታሻ ቤቶቹ በተደረገው ምልከታ ወቅት በተረገው ኢ-መደበኛ ውይይት እነዚህ ቤቶች እንደ ማንኛውም ሥራ ፈቃድ ያላቸውና አንዳንዶቹም ሃያ አራት ሰዓት የሚሰሩ የንግድ ቤቶች መሆናቸው ታውቋል፡፡ ወደነዚህ ቤቶች አገልግሎት ለማግኘት ከሚሄዱት ተገልጋዮች በአብዛኛው ዕድሜያቸው ከፍ ያሉ ናቸው፡፡ በማሳጅ ቤቶቹ ለመስተንግዶ የተለያዩ የአገልግሎት አማራጮች የሚቀርቡ ሲሆን፤ ከነዚህም አንዱ ልዩ ተጨማሪ (Extra) የሚባለው ዓይነት ነው፡፡ ለዚህም አገልግሎት ተገልጋዩ መደበኛውን ሂሳብ ከፍሎ ከገባ በኋላ ይህን ግልጋሎት ከምትሰጥ ሴት ወይም ወንድ ጋር በመደራደር በተጨማሪ ክፍያ ወሲብና ወሲብ ነክ ድርጊቶች የሚፈጸሙበት አሰራር መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

### ሠ. የግለኝነት አስተሳሰብ

ይህንን ሀሳብ በቃለ መጠይቁ ወቅት የገለጹልን የአንድ እምነት ተቋም ተወካይ ሲሆኑ፤ ይህ የግለኝነት አስተሳሰብ ቀድሞ የነበረውን የሀገራችንን የማህበራዊ መስተጋብር እሴት የሚያጠፋ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ ተሳታፊው የዚህ አስተሳሰብ መዳበርም በሰዎች ህሊና ውስጥ የሚፈጥራቸው ነገሮችን በሚከተለው መልኩ አስቀምጠውታል፡

> *...ማህበረሰብ የራሱ እሴትና አስተሳሰብ አለው፡፡ ነገር ግን ግላዊ አስተሳሰብ በነዚህ የጋራ እሴቶችና አስተሳሰቦች ለመመራት አለመፈለግን፤ በመንፈሳዊው ካየነው ደግሞ በልዕለ-ተፈጥሮአዊ የሞራል እሴቶች ለመገዛት ፈቃደኛ አለመሆንን ያመጣል፡፡ ...ውጤቱም ማህበረሰቡ የሚያምንበት ነገር ቢሆንም እኔ ትክክል ነው ያልኩት ነገር ሁሉ ልክ ነው ብሎ ማሰብን፤ የቁሳዊ አስተሳሰብን ማዳበርና ጤነኛ ያልሆነ ተዝናኖት መፈለግን ያስከትላል፤ በመጨረሻም ለሱሰኝነት፣ ሙሰኝነትና ለመሳሰሉት ችግሮች ይዳርጋል፡፡...*

### ረ. ያልተገቡ የአለባበስ ሁኔታዎች

ይህ ሀሳብ በሁሉም የቡድን ውይይትና የቃለ-መጠይቅ ተሳታፊዎች የተነሳ ሲሆን በተለይ የእምነት ተቋማት ተወካዮች ችግሩን አጉልተው ገልጸውታል፡፡ ችግሩን ሲያብራሩትም ሀገርኛ ያልሆኑ የአለባበስ ስልቶች መጤ ባህሎች ናቸው በማለት አጽንኦት ሰጥተውታል፡፡ እነኚህ የተለያዩ የእምነት ተቋማት ተወካዮች በአሁን ጊዜ የምንከተለው የአለባበስ ሥርዓት ሀገራዊ እሴቶቻችንን ያልጠበቀ እየሆነ ነው ሲሉም ገልጸውታል፡፡ እንደ ምሳሌም ሱሪን ከወገብ በታች ወረድ አድርጎ ያለ ቀበቶ መልበስና የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ አለባበስን ጠቅሰዋል፡፡ የዚህን ጉዳይ አሳሳቢነት አንድ የእምነት ተቋም ተወካይ ሲገልጹ፤

> *...አላስፈላጊ አለባበስ ስንል አለባበስ ክብርን ያልጠበቀ፣ ገበናን ያልሸፈነ መሆን የለበትም፡፡ ይህ ዝሙትን ያባብሳል፣ የተቃራኒ ጾታን አትኩሮት ይስባል፣ ለጾታዊ ፍላጎት ይገፋፋል፣...ሀገራችን በአሁኑ ወቅት በዚህ ጉዳይ እየተቸገረች ነው፡፡ የሚድኑም ሆነ የማይድኑ ተላላፊ በሽታዎች ይበዛሉ፣ የሚመጡትም በነዚህ ሳቢያ ነው....*

በማለት የአላስፈላጊ አለባበሶች ያላቸውን ተጽዕኖ አብራርተዋል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የዕድሮች ህብረት፣ የቤት እመቤቶች፣ የቢሮ ሰራተኛ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች አለባበስን አስመልክተው በሰጡት ሀሳብ የኢትዮጵያዊነት አለባበስና አጋጌጥን ባህላዊ እሴት ያልጠበቁ፤ ከፊል አካልን እርቃን ስጋ እየሆኑ የመሄድ ችግሮች እንዳሉ ገልጸዋል፡፡

### 4.3.2. ወጣቶችና ሴቶችን ለመጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጧቸው ምክንያቶች

ወጣቶችና ሴቶችን ለመጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጧቸው ምክንያቶች በጣም በርካታ መሆናቸውንም ተሳታፊዎቹ ገልጸዋል፡፡ እነዚህም፡ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ፣ስነልቡናዊ፣ ዓለምአቀፋዊነትና የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ መረቦች መስፋፋት፣ የቤተሰብና የጓደኛ ተፅዕኖ፣ በት/ቤቶችና መኖሪያ አካባቢዎች ላይ የመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ማስፋፊያ ቦታዎች መከፈት፣ የት/ቤቶችና የቤተሰብ የጋራ ቁጥጥር መላላትና የፖሊሲና የህግ ክፍተትና ተፈፃሚነት መላላት የሚሉትን በዋነኛነት አንስተዋል፡፡

### ሀ. ማህበራዊ ምክንያቶች

ለወጣቶችና ሴቶች ወደ አላስፈላጊ ነገሮች ውስጥ መግባት ምክንያት ናቸው ተብለው በጥናቱ ተሳታፊዎች ከተነሱት አንዱ፤ ማህበራዊ ምክንያት ነው፡፡ በዚህም ወቅት ከተጠቀሱት ችግሮች መካከል የሴቶችና የወጣቶች አለመማር፣ የቤተሰብና የልጆች ማህበራዊ መስተጋብር አለመመጣጠን፣ የቤተሰብና ጓደኛ ተፅዕኖና የት/ቤቶችና የቤተሰብ የጋራ ቁጥጥር መላላት ተነስቷል፡፡

#### የሴቶችና የወጣቶች አለመማር

ከትምህርት ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር በተመለከተ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደተናገሩት ሴቶችና ወጣቶች ከትምህርት ማጣት የተነሳ የሚነዳና የሚጠቅማቸውን ነገር ለመለየት የማገናዘብ ችግር ስለሚኖርባቸው ለአላስፈላጊ ነገሮች ይጋለጣሉ ብለዋል፡፡ ይህ ካለመማር በተነሳ የሚንጸባረቀው ችግር የህብረተሰቡ በተለይም የሴቶችና የወጣቶች የአስተሳሰብ አለመጎልበትን ያስከትላል በማለት ገልጸዋል፡፡ ይህም ወደ አላአስፈላጊ ድርጊቶች ለመግባት እንደሚገፋፋና በመጨረሻም ማህበራዊ ቀውስን እንደሚያስከትል በአጽንኦት ተናግረዋል፡፡

#### የቤተሰብና የልጆች ማህበራዊ መስተጋብር አለመመጣጠን

የቤተሰብና የልጆች ማህበራዊ መስተጋብርን በተመለከተ የቤተሰብ ቁጥጥር መጥበቅም ሆነ መላላት ለወጣቶችና ሴቶች ወደ አላፈላጊ ነገሮች መግባት አስተዋጽየ እንደሚያደርግ የጥናቱ ተሳታፊዎች አመላክተዋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ ከተማሪዎች ጋር በተደረገ የቡድን ውይይት አንድ ተሳታፊ እንደተናገረው፤ የቤተሰብ ቁጥጥር ሲበዛም ሆነ ሲያንስ ክፍተት እንደሚፈጥር በአንክሮ ገልጿል፡፡ ለዚህም አብነት ሲያቀርብ፤ አንድ ተማሪ በቤተሰብ ቁጥጥር መጥበቅ ምክንያት ትምህርቱን አቋርጦ ጫት ቤት ይውል እንደነበረ አስረድቷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሌላው ተሳታፊ የጠበቀ የቤተሰብ ቁጥጥርና ግልጽ ውይይት አለመኖር ወጣቶችና ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ተግባራት እንዲገቡ እንደሚያደርጋቸው በሚከተለው መልኩ አስቀምጦታል፡-

> *...ልጆች በተለይም ሴቶች በአብዛኛው በቤተሰብ ታስረው የኖሩ ናቸው፡፡ ከቤት በሚወጡበት ጊዜ "የተለቀቀ ውሻ" ይሆናሉ፡፡ለችግሩም ተጋላጭ የሚሆኑት እነሱ ናቸው፡፡...በአንድ ቤተሰብ ጣሪያ ሥር ሆነው የማይተዋወቁ ሰዎችም አሉ...*

ይህንን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ በጫት ሱስ የተጠመደ አንድ ተወያይ ሲገልጽ ደግሞ፤

*...የቤተሰብ የልጅ አያያዝ ክህሎት ችግር ለዚህ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ነበዝ የ9ኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ፡፡ ማጥናት ባለብኝ ሰዓት አነባለሁ ፡፡ ነገር ግን አባቴ ከስራ ወደ ቤት ሲገባ የግድ ደብተር እያነበብኩ እንድጠብቀው ስለሚፈልግ ወደ መስኪድ የሄድኩ በማስመሰል እኔ የምሄደው በአካባቢያችን ወደ አለ ጫት መቃሚያ ቤት ነበር፡፡...*

በማለት የቤተሰብ የቁጥጥር ሁኔታ ከልጆች ጋር ግልጽ ውይይት ካለማድረግ ጋር ተዳምሮ በልጆች ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተፅዕኖ አስረድቷል፡፡

በሌላ መልኩ በቤተሰብ ውስጥ የሚደረግ አድልዎ ለወጣቶች ከመስመር መውጣት አንዱ ምክንያት እንደሆነ በሌላ የቡድን ውይይት ውስጥ የተካፈለ ተማሪ ጠቅሷል፡፡ በዚህም አባባሉ አንድ አንድ ቤተሰቦች ለነበዝ ልጆቻቸው አድልዎ ስለሚያደርጉ፤ በትምህርት አቀባበላቸው ድክመትና ችግር ያለባቸው ልጆች በዚህ የተነሳ ስሜታቸው ተጎድቶ ወደ አልባሌ ድርጊቶች እንደሚገፋፉ አስረድቷል፡፡

ከትምህርት ቤት ውጭ ካሉ ወጣቶች ጋር በተደረገ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፤ አንዲት ተሳታፊ ደግሞ፤ ለወጣቶችም ሆነ ለሴቶች ባህሪ መበላሸት ምክንያቱ የቤተሰብ ልጆቹን በአግባቡ አለመንከባከብና ግልጽ ውይይት አለማድረግ መሆኑን ገልጻለች፡፡ በዚህ ምክንያትም በራሷ ላይ የደረሰውን ስታስረዳ፡-

*....እኔ ወደ ጎዳና ተዳዳሪነት የወጣሁበት ምክንያት ከቤተሰብ እንክብካቤና ውይይት በማጣት ነዉ:: ... ሴቶች ጎዳና ተዳዳሪ ሰንሆን ሌሎች ወንዶች እንዳይጫወቱብን ስለሚያግዝ አንድ ወንድ መያዝ ግዴታ ነዉ፡፡ ...እንደ ጫት፣ ሲጋራ፣ ሀሺሽና ጠጅ ያሉ ሱሶችን መልመድ የግድ ይላል::...ቤተሰብ ዉስጥ ግልጽ ዉይይት ቢኖር ወደ ሱስ የመሄድ ነገር አይኖርም...* በማለት አስቀምጣዋለች፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የቤተሰብ እንክብካቤ መብዛትና ቁጥጥር መላላት በራሱ ለዚህ ችግር አስተዋጽየ እንዳለው ሌላ የወጣቶች የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

*....ልጅን ቤተሰብ ቢጋራ ካልተቆጣጠረዉ ለችግር ይጋለጣል:: ለምሳሌ እኔ እናቴ ስትቆጣጠረኝ አባቴ ሊቆጣጠረኝ አልቻለም ነበር፡፡ እንዲያውም ጠጥቼ ስመጣ አቅፎ ያስተኛኝ ነበር:: ...አባቴ ስለማይቆጣጠረኝ አረቄ ቤት እሄዳለሁ:: ሁለቱም ሊቆጣጠሩኝ ስላልቻሉ ወደ ጎዳና ወጣሁ ከዚያም ወደሱስ ልገባ ቻልኩ! ትልቅ ደረጃም ሳልደርስ ቀረሁ!* በማለት በራሱ ላይ የደረሰውን ችግር በማሳያነት አንስቷል፡፡

በአጠቃላይ ከወጣቶች ጋር በተደረገ ውይይት በቤተሰብ መካከል ግልጽ ውይይት አለመኖሩና የልጆችን ጥፋት ለመሸፈን መሞከር ልጆችን ወደአላስፈላጊ ነገሮች ሊገፋፉ እደሚችል አስምረውበታል፡፡

## የቤተሰብና የጓደኛ ተፅዕኖ

ለወጣቶችና ሴቶች በአላስፈላጊ ልምድ መወሰድ ምክንያት የቤተሰብ፣ የህብረተሰብና የጓደኛ አስተሳሰብና ድርጊት  ትልቅ አስተዋጽያ እንዳለው የጥናቱ ተሳታፊዎች በአጽንያት ገልጸዋል፡፡

የቢሮና በአመራር ላይ ያሉ ሴቶች በተሳተፉበት የተተኳሪ የቡድን ውይይት አንድ ተሳታፊ እንደገለጹት፤ ህብረተሰቡና ቤተሰብ ልጆች ሀገር ውስጥ ሰርተው ከሚለወጡ ይልቅ ወደ ሌሎች ሀገሮች ተሰደው መሄዳቸውን እንደ ክብር የመመልከት አስተሳሰብ እንዳላቸው ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ልጆቹ ሳይወዱ ይሰደዳሉ፤ በተሰደዱበትም ሁሉ ለአላስፈላጊ ነገሮች ተጋልጠው ይመጣሉ፤ እዛ ያዩትንም ነገር ይዘው በመምጣት ዛሬ በከተማችን የርቃን ሮፊራ ቤቶች፣ ሀሺሽ እና ሺሻ የሚጨሱባቸውን ቤቶች ከፍተዋል፡፡ በነዚህ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩትም ሆነ የሚጠቀሙት አብዛኛዎቹ ከስደት የተመለሱ ዜጎች ናቸው በማለት አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም የቤተሰብ ለተለያዩ ሱሶች ተገዥ መሆን ለወጣቶችና ለሴቶች ወደዚያ ነገር ማዘንበል የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለውም አክለው ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ከተማሪዎች ጋር በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ደግሞ፤ ለወጣቶችና ሴቶች ወደ አላስፈላጊ ነገር መግባት አንዱና ዋነኛው ምክንያት የጓደኛ ግፊት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ብዙዎቹ ወጣቶች በራስ የመተማመን ችግር ስላለባቸው በጓደኛ ግፊት ወደ ችግሩ ይገባሉ፡፡ አንድ የውይይቱ ተሳታፊ ይህንኑ አስመልክቶ ሲገልጽ፡

> *…አንዲት ጓደኛ ደባል ሱስ ካላት ለጓደኛዋ ታዳርሳለች፣እሷንም ትለውጣለች፡፡አንዳንድ ወጣቶች ደግሞ በሌሎች ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ ማጨስን፣መጠጣትን ይለማመዳሉ፡፡የራስ አስተሳሰብና የጓደኛ ተፅዕኖ ለችግሩ ተጋላጭ ያደርጋል …*በማለት አስረድቷል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በሱስ ከተያዙ ወጣቶች ጋር በተደረገ የቡድን ውይይት ላይ አንድ ወጣት በራሱ ላይ የደረሰውን ሲገልጽ፤

*...የእግር ኳስ ተጫዋች /በረኛ/ ነበርኩ፡፡ የምንጫወትበት ሜዳ ላይ እንዳንጫወት ተከለከልን፡፡ የሰፈር ልጆች የሚያደርጉትን ነገር አያለሁ፤ ለነሱ እላላካለሁ፡፡ ከዚያም ይችን ነገር እያት ይሉኛል ፡ ከዚያ "ቴስት" አደረኳት፡፡ ከዚያ ኳሱን ተውኩትና ጫት ወደ መቃም ገባሁ፡፡አንድ ሁለት ሰል እያለ እያለ ሙሉ በሙሉ ወደ ሱስ ገባሁ...*ሲል ገልጿል፡፡

በሌላ በኩል በማረሚያ ቤት ከሚገኙ የህግ ታራሚዎች ጋር በተደረገ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ላይ ተሳታፊ የነበረው ወጣት፤ ጫትና ሀሺሽ ይጠቀም እንደነበረና የጀመረውም በትምህርት ቤት ጓደኞቹ ግፊት ሲሆን፤ ይህንንም ለመጠቀም ያነሳሳው የስልጣኔና የዘመናዊነት ምልክት አድርጎ በመውሰዱ እንደሆነ ተናግሯል፡፡በዚህም ሳቢያ ደመወዙ ስለማይበቃው የሚሰራበትን የመኪና ዕቃ ሸጦ እስከ መጠቀም እንዳደረሰውም ገልጿል፡፡

ከትምህርት ቤት ውጭ የሚገኙ ወጣቶችም በውይይታቸው እንዳነሱት፤ ወጣቶችና ሴቶች አንዱ ሌላውን ተከትሎ የመሄድ ነገር ስላለ ለችግር በቀላሉ እንደሚጋለጡ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ዘመናዊ ነን ባይ ወላጆች ልጆቻቸው ባሉበት ስለሚቅሙ፣ ስለሚያጨሱና የወሲብ ፊልሞችንም ስለሚመለከ እና ልጅ እንደፈለገ ገንዘብ ማግኘት አለበት የሚል አስተሳሰብ ስላላቸው፤ ልጆቹም ከወላጆቻው ያዩትን ነገር በሚያገኙት ገንዘብ ለመሞከር ይነሳሳሉ በማለት ገልጸዋል፡፡

**የት/ቤቶችና የቤተሰብ የጋራ ቁጥጥር መላላት**

ወጣቶችና ሴቶችን ለአላስፈላጊ ልማዶች ያጋልጣሉ ተብለው በጥናቱ ተሳታፊዎች ከተነሱት ምክንያቶች አንዱ የትምህርት ቤቶችና የቤተሰብ የተናበበ ቁጥጥር መላላት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተሳተፉ የእምነት ተቋማት ተወካዮች፣ አመራር ሴቶች፣ ተማሪዎችና ወጣቶች እንደገለጹት ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ትምህርት ቤት መሄዳቸውን እንጂ፤ የት እንደሚውሉና ያሉበትን የትምህርትና የባህሪ ሁኔታ ቀርቦ ከትምህርት ቤቶች ጋር በመናበብ የሚሰሩት ሥራ የለም፡፡ በመሆኑም ልጆቹ የፈለጉበት ውለው ትምህርት ቤት የዋሉ በመምሰል በሰዓቱ ወደቤታቸው የሚመለሱበት ሁኔታ እንዳለ አስረድተዋል፡፡ ይህ ተቀናጅቶ የመስራትና የቁጥጥር መላላት የሚፈጥረው ክፍተት ተማሪዎቹ ለአላስፈላጊ ነገሮች እንዲጋለጡ ምክንያት ይሆናቸዋል በማለት አክለው ተናግረዋል፡፡

የትምህርት ቤቶችና የቤተሰብ የጋራ ቁጥጥር አለመኖር ችግሩን እንደሚያባብስ በተተኳሪ ቡድን ውይይት ከተካፈሉ ተማሪዎች አንዱ ሲያስረዳ፡

*..ወላጆች ልጆቻቸው ለምን ተግባር እንደሚፈልጉት ሳይመረምሩ አላስፈላጊ ገንዘብ ይሰጣሉ::...የአምስተኛና የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ሞባይል ይዘው መገኘታቸዉም የዚሁ ችግር መገለጫ ነው:: በሞባይሉ ላይ የሚጫነውንም ነገር ምንድን ነው ብሎ ወላጅ አይከታተልም:: በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ገንዘብና ሞባይል ይዘው እንዳይመጡ ከወላጆች ጋር የሚያደርጉት ምክክር ስለሌለ ተማሪዎቹ በትምህርት ሰዓት አላስፈላጊ መልዕክቶችን በመላላክና ከትምህርት ቤት በመውጣትም ወደተለያየዩ ቦታዎች እንዲሄዱና ላልተፈለጉ ድርጊቶች እንዲጋለጡ ይዳርጋቸዋል...* ብሏል፡፡

በተጨማሪም ከህግ አካላት ጋር በተደረገው ውይይት፤ ተማሪዎች በተጨባጭ አደንዛዥ ዕፅ ይዘው ወደ ትምህርት ቤት እንደሚገቡ ገልጸው፤ በዚህም ሳቢያ ትምህርታቸውን በማቋረጥ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲገቡ ተገደዋል፡፡ ይህም የትምህርት ቤቶችና የወላጆች የተቀናጀ ቁጥጥርና ክትትል አለመኖርን ያሳያል ብለዋል፡፡

### ለ. ስነ-ልቡናዊ ምክንያቶች

ከስነ-ልቡናዊ ሁኔታዎች ጋር የሚታየውን ችግር በተመለከተ የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲገልፁ፤ ወጣቶችና ሴቶችን ለአላፊላጊ ላልተገቡ ባህሪያት እንዲጋለጡ የሚያደርጓቸውን በርካታ ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ያለ ትምህርትና ስራ መቀመጥ፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ኋላቀር መስሎ ላለመታየት፤ዘመናዊነትን ለማሳየትና አዲስ ነገሮችን ለመሞከር መሻት እንደሆኑ በትኩረት ተጠቅሰዋል፡፡

በቡድን ውይይት ከተሳተፉ ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉ ወጣቶች መካከል አንድ ተሳታፊ፤ ወጣቶች ወደ ተለያዩ ነገሮች ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጓቸውን ምክንያቶች ሲያስረዳ፤

*...ወጣቱን ወደዚህ ነገሮች ውስጥ እንዲገባ የሚያደርገዉ አንዱ የዕድሜው ሁኔታ ነዉ:: በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ገደልም ቢሆን ሁሉን ነገር የማየትና የመቅመስ ፍላጎት አለው:: ሁለተኛ ዝመና ይመስለዋል:: ሌላው ተስፋ በማጣት ቁጭ በሚባልበት ጊዜ ወደነዚህ ነገሮች ይገፋፋል ብዬ አስባለሁ...* በማለት ገልጿል፡፡

ከተማሪዎች ጋር በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ደግሞ፤ ተማሪዎች ወደ ቀን ጭፈራ ቤቶች የሚሄዱት "ፍራ" ወይም ያልሰለጠነ ላለመባል እንደሆነም አንድ ተሳታፊ ገልጿል፡፡ በነዚህ ቦታዎች ላይ መጠጣትና የተለያዩ ዕፆችን ማጨስ የተለመደ ከመሆኑም በላይ ሴትና ወንድ ተማሪዎች የሚያገናኙ እንዳሉ ጠቅሷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ በተላላፊ

በሽታዎች የሚጠቁ ሲሆን፤ በተለይ ሴት ተማሪዎች ደግሞ ለእርግዝናና መሰል ተያያዥ ችግሮች ይጋለጣሉ ሲል አስረድቷል፡፡

በቃለ መጠይቅ ወቅት ካነጋገርናቸው የእምነት ተቋማት ተወካዮች አንዷ እንደገለጹት፤ ወጣቶችም ሆኑ ሴቶች ከሌላው ህብረተሰብ ይልቅ ለውጥና አዲስ ነገርን ፈላጊ፣ ከሁሉ በልጠ መታየትን፣ መወደድና መፈለግን የሚሹ በመሆናቸው፤ ይጥቀማቸውም ይጉዳቸው መጨ ለሆኑ ነገሮች በቀላሉ ይጋለጣሉ ብለዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከተማሪ ተሳታፊዎች ጋር በተደረገው ውይይት የትምህርት ቤት አስተዳደር፣ ህብረተሰቡና ቤተሰብ በተማሪዎቹ ላይ በሚያዩዋቸው ባህሪና አለባበስ ብቻ ተመርኩዞ ባላደረጉት ነገር በሚጠረጥሯቸውና እምነት በሚያጡባቸው ጊዜ በስነ-ልቦናቸው ላይ የሚደርሰውን ጫና ለመቋቋም ሲሉ ወደአልፈለጉት ነገር ለመግባት እንደሚገፋፉ ገልጸዋል፡፡

### ሐ. ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች

የጥናቱ ተሳታፊዎች ወጣቶችና ሴቶች ለአላስፈላጊ ባህሎችና ድርጊቶች እንዲጋለጡ ምክንያት ናቸው ካሏቸው መካከል፣ ስራ ፈትነት፣ ራስን በኢኮኖሚ የመደገፍ አቅም ማጣት፣ የኢኮኖሚ ጥገኝነትና የቤተሰብ ሀብት መብዛትና ማነስ እንደሆኑም አስቀምጠዋል፡፡ ተሳታፊዎቹ እንደገለጹት፣ በአብዛኛው ወጣቶች ለአላስፈላጊ ነገሮች እንዲጋለጡ የሚያደርጋቸው አንድም ስራ ማጣት፣ አልያም ስራ በመናቅ በየመንገዱ ስራ ፈትተው መዋላቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩልም ሴቶች በአብዛኛው የባሎቻቸውን እጅ ጠብቀው የሚኖሩ ወይም አነስተኛ ስራ ያላቸው በመሆኑም ላልተገቡ ድርጊቶች እንደሚጋለጡ ጠቅሰዋል፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ከትምህርት ቤት ውጭ ካሉ ወጣቶች ጋር በተደገረ የቡድን ውይይት አንድ ተሳታፊ በሰጠው አስተያየት፡

> *...ወጣቶች በራሳቸዉ ትኩሰነት ያላቸዉ በመሆናቸዉና ስራም በመፍታታቸው...ጊዜአቸዉን መንገድ ዳር በመቀመጥ የሚያሳልፉ ይሆናሉ፡፡...ምናልባትም የሚፈልጉትን የስራ ዘርፍ ባለማግኘታቸዉና ስራ በማጣታቸው ሱስ ዉስጥ ይገባሉ"* ሲል፤ በተመሳሳይ መልኩ ሌላኛው ተሳታፊ ደግሞ *"...ስራ አጦች*

*መደበሪያ በሚል በተለያዩ ቦታዎች የመሄድ ሁኔታ አለ:: ስለዚህ ጫትና ሺሻ በመዉሰድ አላስፈላጊ የወንጀል ፊልሞችን በማየት ጊዜ የሚያሳልፉ ወጣቶች ብዙ ናቸዉ...* በማለት አክሏል፡፡

የቢሮ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች በተሳተፉበት የቡድን ውይይት ላይ ሴቶች ወደ አላስፈላጊ ነገሮች የሚገቡበትን ምክንያት አንድ ተሳታፊ ሲገልጹ፤ "...የሴቶቻችንን ሁኔታ ስንመለከት አብዛኞቹ የባሎቻቸውን እጅ ጠብቀው የሚኖሩ ወይም ምንም የገቢ ምንጭ የሌላቸው ናቸው፡፡ ይህ የኢኮኖሚ ጥገኝነትና ችግር ደግሞ ወደ ማህበራዊ ጠንቆች ያሸጋግራቸዋል.." ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የቤት እመቤት ሴቶችን ባሳተፈው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ላይ አንዲት ተወያይ ያስቀመጡትን ሀሳብ ስንመለከት፡-

*...የቢሮ ሴቶችም ቢሆኑ ለአልባሳት፣ ለጌጣጌጥ፣ ለሌላም ሌላም ወጪ መሸፈኛ ሲሉ ወደዚህ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ባለትዳሮችም ቢሆኑ የጋራ ገንዘባቸው ከኑሮ ስለማይተርፍ የግል ወጪዎቻቸውን ለመሸፈን ሲሉ መዘሞት አለ፡፡ ይህ የኢኮኖሚ ጥገኝነት የፈጠረው ነው...* በማለት ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የሚያስከትሉትን ችግር ገልጸዋል፡፡

በወሲብ ስራ ከሚተዳደሩ ሴቶች ጋር በተደረገ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎቹ እንዳስረዱት ለዚህ ስራ የመዳረጋቸው ዋና ምክንያት የኢኮኖሚ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡በኢኮኖሚ ችግሩ የተነሳ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው፤ በሰው ቤት ሰራተኝነት ተቀጥረው ሲሰሩ በአሰሪዎቻው በሚደርስባቸው ወሲባዊ፣ ስነልቦናዊና አካላዊ ጥቃት ምክንያት ወደ ጎዳና በመውጣታቸው ላልተገቡ ድርጊቶች መጋለጣቸውንም አስረድተዋል፡፡

በቃለ መጠይቅ መረጃ የሰጡን የአንድ እምነት ተቋም ተወካይ የኢኮኖሚ አቅም ማነስ ወጣቶችና ሴቶችን ወደአላስፈላጊ ነገሮች ለመጋለጣቸው ያለውን አስተዋጽየ ሲገልጹ፡ "...ወጣቶችና ሴቶች በኢኮኖሚ አቅማቸው በብዛት ዝቅተኛ ናቸው፡፡ ስለዚህ ከውጭ የመጣ ማናቸውም ነገር፤ ዋጋው ቀለል ብሎ በነሱ አቅም ማድረግ የሚችሉት ከሆነ ጠቃሚነትና ጎጂነቱን ሳይመርጡ ይጠቀሙበታል፡" ብለዋል፡፡

ከላይ ከተነሱት ሀሳቦች በተቃራኒው የጥናቱ ተሳታፊዎች የቤተሰብ ሀብት መብዛትም ለወጣቶችና ለሴቶች ለአላስፈላጊ ነገሮች መጋለጥ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው አንስተዋል፡፡ በቃለመጠይቅ ወቅት ያነጋገርናቸው አንድ የአእምሮና የስነልቡና ሐኪም እንደገለጹት ጥሩ

ገቢ ያላቸውና ከውጭ ሀገር ገንዘብ የሚላክላቸው ወጣቶችና ሴቶች ለተለያዩ ሱሶችና ችግሮች በመጋለጥ ደረጃ ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ ብለዋል፡፡

## መ. ዓለምአቀፋዊነት፣ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ መረቦች

ዓለም አንድ በሆነችበት በዚህ ዘመን፤ በጎም ሆነ አሉታዊ ነገር የሚያመጡ አስተሳሰቦች ሰርገው የሚገቡበት ሁኔታ ቅርብ ነው፡፡ በመሆኑም ሴቶችና ወጣቶች በነዚህ አስተሳሰቦች በመጠመድ ወደ አላስፈላጊ መጤ ነገሮች ሊሳቡ እንደሚችሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር በተደረገ የቡድን ውይይት ወቅት አንድ የውይይቱ ተሳታፊ ተማሪ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ መረቦች መስፋፋትና በሀገራችን ሬድዮ ፕሮግራም በቀጥታ የሚተላለፉ ውይይቶች በተማሪዎች ላይ ያለውን ተፅዕኖ ሲገልጽ፡-

> *...አንዳንዶቹ ተማሪዎች ደግሞ በሞባይልና በኢንተርኔት የወሲብ ፊልም በመላላክ ይመለከታሉ ፡፡ ከዚህ የሚያገኟቸው መልዕክቶች ወደ ችግሩ እንዲገቡ ይገፋፏቸዋል...፡፡ በተጨማሪም በአንድ አንድ የሬድዮ ፕሮግራሞች የቀጥታ ውይይት ላይ ወጣቶች በግልጽ ያላቸውን ስሜት ይገልጻሉ፡፡ የውይይቱ መልካምነት ግልጽነትን የሚያነለብት ቢሆንም፤ ሌላውን ሰው ግን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ የሚመራ ነው፡፡* በማለት አስቀምጠታል፡፡

በተጨማሪም ተሳታፊዎቹ በተለያዩ መንገዶች የሚሰራጩት ያልተገቡ ፊልሞች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ በነሱ አገላለጽ፤ ምንም እንኳን ፊልሞቹን እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ያሉ ልጆች እንዳይመለከቷቸው ማሳሰቢያ የሚሰጥ ቢሆንም፣ መተላለፊያ መንገዶቹ ለሁሉም ሰው ክፍት በመሆናቸው ህጻናትና ወጣቶች ይመለከቷቸዋል፡፡ በፊልሞቹ ባዩአቸው ነገሮች ሳቢያ ህፃናትና ወጣቶቹ፤ ለሱስ ተገዢ፣ ወሲብና ወንጀል ፈጻሚ እንደሚሆኑም አስረድተዋል፡፡

ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉ ወጣቶችም በውይይታቸው ይህንኑ ሀሳብ አጠናክረውታል፡፡ አክለውም ሲያስረዱ በሞባይልና በኢንተርኔት የሚመጡ መረጃዎችን እና በራሪ ወረቀቶችን ወጣቱ ስለሚከታተላቸው አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያስከትሉበት ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ለቁጥጥር በማያመች ሁኔታ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መበራከታቸውንም አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል የእምነት ተቋማት ተሳታፊዎች እንደገለጹት ደግሞ ወጣቶችና ሴቶች ለውጥ ፈላጊ በመሆናቸው ምክንያት ለመረጃ በጣም ቅርብ ናቸው፤ ( በመሆኑም በዜናዎች፣ ፊልሞች፣ ኢንተርኔትና የማህበረሰብ ድረ-ገፆች የተለያዩ መረጃዎችን ያገኛሉ፡፡ በነዚህ መንገዶች የሚያገኙት መረጃ ምን ዓይነት ነው፣ አርአያዎቻቸውስ እነማን ናቸው የሚሉትን ነገሮች ሰናነሳ ደግሞ ፤ በአብዛኛው አሉታዊ ወደ ሆኑ ነገሮች እንዲገቡ የሚገፋፉቸው ናቸው ብለዋል፡፡

ከቢሮ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች ጋር  በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ላይ ተሳታፊዎቹ እንደገለጹት፤ ፈረንጅ የሰራው ነገር ሁሉ ትክክል ነው የሚል እሳቤ በወጣቶችና ሴቶች ዘንድ አለ፡፡ በመሆኑም በዲሽ ከሚተላለፉ ፕሮግራሞችና ፊልሞች፣ ከኢንተርኔት፣ በማህበረሰብ ድረ-ገፆች አማካኝነት ከሚያገኟቸው ሰዎችና በህገወጥ መልኩ ከሚሰራጩት የወሲብ ፊልሞች የሚያዩትን ነገር ሁሉ ለመተግበር በመሞከር ለችግሩ እንደሚጋለጡ አስረድተዋል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ በወሲብ ስራ የሚተዳደሩ ሴቶችም በተመሳሳይ መልኩ ገልጸውታል፡፡ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ የመገናኛ ብዙሀን የሚቀርቡ የውይይት ሀሳቦችን በተመለከተ  ከቢሮ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች ጋራ የተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት አንድ ተሳታፊ፤

> *...በሬድዮ ፕሮግራም የሚቀርቡና በወሲብ ዙሪያ የቀጥታ ውይይት ሰርጭቶች፣ ከአስተማሪነታቸው ይልቅ ወጣቶችና ህፃናትን ወሲብ ምንድን ነው? እንዴት ነው የሚፈጸመው? ብለው እንዲመራመሩና ለመተግበር ወደሚሰችሏቸው ቦታዎች እንዲሄዱ የሚገፋፉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ያንን ያዳመጡትን ለመተግበር ከቤት ወይም ከጎረቤት ጀምረው ወደ ሴተኛ አዳሪዎች እስከመሄድ እያደረሳቸው ነው፡፡... የሚቀርቡት ፕሮግራሞች አስተማሪነታቸው ምን ያህል ነው? ማንንስ ነው የሚያንጹት? በማለት የሚዲያን ተፅዕኖ አስረድተዋል፡፡*

በተጨማሪም ለጥናቱ ሲባል በተፈጠረች ስራ አጥ የሆነች የምናብ ሴት ስም በመስከረም 26 2004 ዓ.ም. በተከፈተ "የፌስ ቡክ አካውንት"፤ እስከ ህዳር 2 2004 ዓ.ም ድረስ 804 ግለሰቦች በጓደኝነት የተመዘገቡ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 762ቱ ወንዶችና 42ቱ ሴቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ በጓደኝነት ከተመዘገቡ ግለሰቦች የምናቧ ሴት የቀረቡላት 106 በአካል እንገናኝ ጥያቄዎች የተስተናገዱ ሲሆን ስልክ ቁጥራቸውን የገለጹላት ሰዎች ቁጥር ደግሞ 60 ያህል ነው፡፡

የምናቧ ሴት ከፊስ ቡክ ጓደኞቿ ከደረሷት መልዕክቶች አብዛኞቹ ያታዋን መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ የእናግኝሽ ጥያቄዎች፣ ስራ አስቀጥርሻለሁ ወይም እቀጥርሻለሁ የሚሉና ውበቷን የሚያደንቁ መልዕክቶች ናቸው።።

## ሠ. የአላስፈላጊ ድርጊቶች መፈጸሚያ ቦታዎች መስፋፋት

የአላፈላጊ ድርጊቶች መፈጸሚያ ቦታዎች በመኖሪያና የትምህርት ቤት አካባቢዎች መስፋፋት፤ ለወጣቶችና ሴቶች የባህሪ መበላሸት ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልጸዋል።። እንደ ተሳታፊዎቹ አባባል በመኖሪያና በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚስፋፉ የጫት መሸጫና መቃሚያ፣ የሺሻና ሀሺሽ ማጨሻ፣ የፊልም፣ የጭፈራና የመጠጥ ቤቶች ህብረተሰቡን በተለይም ወጣቶችና ሴቶችን በቀላሉ ወደነዚህ ነገሮች እንዲሳቡ ያደርጓቸዋል ብለዋል።።

ከቢሮ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች ጋር በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ ከሆኑት አንዷ፤ በአዲስ አበባ ጎጂ የምንላቸው የተለያዩ አላስፈላጊ ልምዶችን የሚያስፋፉ ቦታዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ እነዚህ ቦታዎች የሚስፋፉበትን ሁኔታም ሲያብራሩ፡ "...በተለይ የጫትና ሺሻ ቤቶች ሆን ብለው የሚከፈቱትና የሚስፋፉት ት/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ነው።። ይህ በመሆኑም በተማሪዎች ላይ በተለይ በሴት ተማሪዎች ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው..." ብለዋል።።

በጫት ንግድና ማስቃም ስራ ከሚተዳደሩ ነጋዴዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ የነዚህ ቦታዎች መስፋፋት በህብረተሰቡ ላይ የሚያሳድረውን  አሉታዊ ተፅዕኖ አስመልክተው አንዱ ተሳታፊ ሲገልጹ፡

> *...የእንደዚህ ዓይነት ቤቶች መስፋፋት በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ አለው።። ሰዉ ጊዜውን የሚያሳልፍበት ስራ ወይም መዝናኛ ቦታ ስለሌለው አማራጭ ሲፈልግ በአካባቢው እኛ አለንለት፣ ለመደበር ብሎ ይመጣል፣ በዚያው አንድ ሁለት ሲል ለምዶ ይቀራል።።... እኛም ይህችን ክፍተት ተገንዝበንና ተንተርሰን ነው ይህን ቤት የከፈትነው...*ብለዋል።።

ከትምህርት ቤት አመራሮች ጋር በተረገ የቃለመጠይቅ፤ አንድ ተሳታፊ በትምህርት ቤቶች ዙሪያ ስለሚከፈቱ አዋኪ ነገሮች ሲገልጹ፤

*...በትምህርት ቤቶች አካባቢ ለትምህርት አዋኪ የሆኑና ተማሪዎችን ለአልባሌ ሱሶች የሚያጋልጡ ነገሮች አሉ፡፡ እዚህ አጠገባችን ቪዲዮ ቤት አለ፣ በውስጡ ፑልና ከረንቡላ አለ፣ በክረምት ይዘጋል፣ ትምህርት ቤት ሲከፈት አብሮ ይከፈታል፣ እዚህ ተማሪዎች ይገባሉ፡፡ አንድአንዴ በትምህርት ሰዓትም ወደነዚህ ቤቶች ስለሚገቡ መምህራን በሚከታተሉበት ጊዜ ህብረተሰቡ ሽፋን ይሆናቸዋል፡፡እንዲያውም እንደ ጠላት ያዩናል.. ብለዋል፡፡*

በተመሳሳይ መልኩ የሌላ ትምህርት ቤት አመራርም በአካባቢያቸው ስላለው ሁኔታ ሲገልጹ፤ በትምህርት ቤታቸው አካባቢ በሚገኙ ትንንሽ ሱቆች ውስጥ በድብቅ የሚደረጉ ነገሮችን ማወቅ ባይቻሉም የተለያዩ ሱስ አምጪ ነገሮች እንደሚኖሩ ግን ግምታቸውን አስቀምጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢው በመቆም ህፃናት ሴት ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ሲወጡ ጠብቀው በመደለል ለሌሎች የሚያቀርቡ ወጣቶችም እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡

በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎችና የእምነት ተቋማት ተወካዮች የተለያዩ አላስፈላጊ ድርጊቶች የሚፈጸሙባቸው ቦታዎች መስፋፋት በአጠቃላይ ነዋሪው ላይ የሚፈጥሩት ጫና እንዳለ ሆኖ፤ በተለይ አዲስ ነገር ለመሞከር ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶችና ሴቶችን ይበልጥ ተጎጂ እንደሚያደርጋቸው አጽንዖት ሰጥተው ገልጸዋል፡፡ ከተማሪዎች ጋር በተደረገ ውይይት ተሳታፊ የሆነው ተማሪ የችግሩን አሳሳቢነት ሲገልጽ፡

*...በአካባቢያችን የሲጋራ፣የጫትና ሺሻ መሸጫና መጠቀሚያ ቤቶች አሉ፡፡በሰውር ሴቶችና ወንዶች የሚገናኙባቸው ቦታዎችም አሉ፡፡ሰውር ቦታዎቹ ለሱስ አጋላጭ መሆናቸው በጣም ግልጽ ነው፡፡ እነኝህ ቦታዎች ሴቶችና ወንዶችን በማታለል ስበው የሚያስገቡ ሲሆን ከተገባ በኋላ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡በነዚህ አካባቢዎች ግብረሶዶማዊነት ይካሄዳል፣ ቦታዎቹ የሚዘጋጁት በኮንፖንሳቶ ተከፋፍለው ሲሆን፣ ግማሹ ለጫት መቃሚያ ከሆነ ሌላው የወሲብ መፈጸሚያ ነው... ብሏል፡፡*

በቃለመጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ የሆኑ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተመሳሳይ መልኩ እንደገለጹት፤ ተማሪዎች አርፍደው በር በሚዘጋባቸው ሰዓት፣ ከመምህራኖቻቸው ጋር ሲጋጩም ሆነ ማሚላት የሚገባቸውን ሳያሟሉ ሲቀር በአብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ከግቢ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ በዚህን ጊዜ ወደ ቤት ላለመሄድና በትምህርት ቤት በር ላይ ላለመቆም ሲሉ በአካባቢያቸው በሚገኙ ማንኛውም ዓይነት አዋኪ ቤቶች ሳይመርጡ ይገባሉ፤ በገቡበት ቤት የሚደረገውን ነገር እየለመዱት ስለሚሄዱ በዛው ቀልጠው ይቀራሉ፤ ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በትምህርት ቤቶች አካባቢ መኪና በመያዝ አዘውትረው አዘውትረው የሚቆሙ ሀብታሞችና የውጭ ሀገር ሰዎች በተለይም አረቦች እንዳሉ ተሳታፊዎቹ ጠቁመው፤ የሚያረፍዱና ከመምህራኖቻቸው ጋር የሚጋጩ ሴት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ግቢ ሲወጡ ስለሚያገኟቸው ለአላስፈላጊ ነገሮች እንደሚጋለጡ አስረድተዋል፡፡ ይህንንም አንድ ተሳታፊ ተማሪ ሲያብራራ፡

> *...በትምህርት ቤቶች አካባቢ በእድሜ የገፉ ባለሀብቶችና አረቦች ላንድ ክሩዘር አቁመው አራትና አምስት ሴት ተማሪዎችን ጭነው ይሄዳሉ፡፡ከዚያም ይጠጣሉ፤ያላስፈላጊ ችግር ውስጥ ይገባሉ፡፡በዚህ ችግር ሁለት ተማሪዎች አርግዘው ከትምህርታቸው እንደተደናቀፉ አውቃለሁ፡፡ይህም "ህይወትን መቅጨት ነው"...* በማለት አስቀምጠታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የዕድሮች ህብረት ተወካይ፤ በትምህርት ቤቶችና በመኖሪያ አካባቢ የተስፋፉ የጫት መቃሚያና ፊልም ቤቶችን አማራጭ መዝናኛ በማድረግ፤ ተማሪዎች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የታክሲ ላይ ሰራተኞችና ሌሎችም የህበረተሰብ ክፍሎች በአስጊ ደረጃ በዚህ ተዕዕኖ ውስጥ ገብተዋል በማለት አሳሳቢነቱን ገልጸዋል፡፡

በቃለመጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይት የተሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደገለጹትና በጥናት ቡድኑ አባላት ምልከታም ለማረጋገጥ እንደተቻለው፤ ያልተገቡ ድርጊቶች የሚፈጸሙባቸው ቦታዎች በከተማው ውስጥ በርካታ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ በተለይ ችግሩ ጎልቶ ከሚታይባው አካባቢዎችም ለአብነት ያህል፤ ፒያሳ አራዳ አካባቢ፣ዳትሰን ሰፈር፣ሳሪስ፣ ቦሌ ፍሬንድ ሺፕ፣ቲኬ ህንፃና ሚሊንየም አዳራሽ ጀርባ፣ ካዛንቺስ፣ 22 ማዞሪያ አካባቢ፣ አውቶቡስ ተራ፣ ቺቺኒያ፣ቦሌ ሚካኤል፣ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ እና የመሳሰሉት ህፃናት ተማሪዎችን፣ ወጣቶችንና ሴቶችን ላልተገቡ ድርጊቶች የሚያጋልጡ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሌላው በምልከታ ወቅት የቡድኑን አባላትን ትኩረት የሳበው አሳሳቢ ጉዳይ፤ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎችና በሌሎች የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በመኪና ውስጥ በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን በመሆን ጫት መቃም፣ ወሲብ መፈጸምና ሌሎች ያልተገቡ ድርጊቶች ሲከናወኑ መታየታቸው ነበር፡፡

በመስክ ምልከታው ወቅት ለመታዘብ እንደተቻለው፤ በተለያዩ የከተማዋ ቦታዎች ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የጫት ማስቃሚያና የሺሻ ማስጨሻ ቤቶች በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም በስፖርት ማዘውተሪያ

ስፍራዎች አካባቢ መስፋፋታቸው ታይቷል። በተጨማሪም እነዚህ አላፊላጊ የሱስ አስያዥ ዕፅ መጠቀሚያ ቤቶች በርካታ ነዋሪ ወጣቶች፣ ሴቶችና ህፃናት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች የተስፋፉ ሲሆን፤ ከቤቶቹ የሚወጣው የዕፆች ሽታ፣ ድምፅና ተረፈ ምርት በነዋሪዎቹ ላይ የሚፈጥረው ጫና እና ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ለመታዘብ ተችሏል።

እነዚህ ቤቶች ለመኖሪያ ቤትነትና ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች ማስኬጃነት የተመዘገቡ ሲሆን ብዙዎቹ ቤቶች ዙሪያቸውን ፍራሽና ምንጣፍ የተነጠፈባቸው፣ የሺሻ ማጨሺያ እቃዎች ዝግጁ ሆነው የተቀመጡባቸውና ልዩ ልዩ ክፍሎች ተዘጋጅተው ለተስተናጋጆች የሚቀርቡባቸው ናቸው። እነዚህ ቤቶች የማስቃምና የማስጨስ አገልግሎት ስለመስጠታቸው ከውጭ የሚያመላክት ነገር የሌላቸው ሲሆን፤ በትውውቅና በጥቆማ የሚኬድባቸው ቦታዎች ናቸው። በዚህ ተግባር የተሰማሩ ሆቴሎች፣ የእንግዳ ማረፊያዎች ካፍቴሪያዎች፣ ትላልቅ የመኖሪያ ቤቶችና የጫት መሸጥ ፈቃድ ያላቸው የጫት ሱቆች ናቸው። ወደነዚህ ቤቶች የሚመጡ ደንበኞች ሁሉ የእድሜና ፆታ ልዩነት ሳይኖር፤ በአንድነትና እንደየፍላጎታቸው በልዩ ልዩ ክፍሎች እንደሚስተናገዱ ለማየት ተችሏል።

በነዚህ የጫት መቃሚያና ሺሻ ማስጨሻ ቤቶች የሚስተናገዱት በተለያየ የእድሜ ክልልና የስራ ሁኔታ ላይ ያሉ ወንዶችና ሴቶች ሲሆኑ፤ በተለይ በትምህርት ተቋማት አካባቢ በሚገኙ ቤቶች የሚስተናገዱት አብዛኞቹ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሚገመቱ ወጣቶች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ከፊሎቹ የት/ቤት ዩኒፎርም ለብሰው ሲታዩ፤ ከዚህ በተቃራኒ የሚገኙ፤ እድሜያቸው ከመካከለኛ ክልል ያለፉ ጎልማሶች ትናንሽ ሴት ተማሪዎችን ይዘው አብረው ሲቅሙና ሲያጨሱ ታይተዋል። በተጨማሪም በነዚህ የመቃሚያ ቤቶች የነበሩ ተገልጋዮች በተለያዩ ርዕስ ጉዳይ ላይ ሲወያዩ፣ የወንጀል ወሬዎችን ሲተርኩና የመ/ቤት ምስጢሮችን ሲያወሩ እንዲሁም የንግድ ስራዎችን ሲሰሩ ተስተውለዋል።

በመስክ ምልከታ ወቅት ከተደረጉ ኢ-መደበኛ ውይይቶች በተገኘው መረጃ መሰረት፤ አብዛኞቹ የማስቃሚያ ቤቶች ውስጥ በአስተናጋጅነት የሚሰሩት ወጣት ሴቶች ሲሆኑ፤ አንዳንዶቹ ቤቶች ደግሞ ለልዩ አገልግሎት ያዘጋጇቸው ክፍሎችና ሴቶች እንዳሏቸው ታውቋል።እነዚህ ቤቶች እንደየተስተናጋጆቹ ምርጫ ልዩ የመቃሚያ ክፍሎች፣ አብረው የሚያቃቅሙና ሌሎች የወሲብ ስራዎችን የሚሰሩ ሴቶችን በልዩ ክፍያ ለተገልጋዮቻቸው እንደሚያቀርቡ ለመረዳት ተችሏል።

## ረ. የፖሊሲና የህግ ክፍተትና ተፈፃሚነት መላላት

ያልተገቡ መጤ ባህሎችንና ልማዶችን ለማስቀረትና ለመከላከል፤ በሀገራችን የተዘጋጁ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች ክፍተት እንዳለባቸው እና ተፈጻሚነቱም ላይ መላላት እንደሚስተዋል የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡ ይህም ለአላስፈላጊ ነገሮች መከናወኛ ቦታዎች መበራከት ትልቅ አስተዋጽየ አድርጓል፤ በውጤቱም ህብረተሰቡን በተለይም ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና የወንጀል ድርጊቶች እንደሚገፋፋቸው አስረድተዋል፡፡

በቃለ-መጠይቅ ተሳታፊ የነበሩ የፍትህ ቢሮና የፖሊስ ተወካዮች በሰጡት መረጃ፤ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰበትና፤ የተባበሩት መንግስታት ያወጣውን የአደገኛ ዕፅ ክልከላን የተመለከተ ህግ ተቀብላ በወንጀል ህግ በአንቀጽ 525 ማካተቷን አስረድተዋል፡፡ በድንጋጌው መሰረት፤ ማንኛውንም መርዛማ የናርኮቲክ ወይም የሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶችን ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው፤ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ በማከፋፈል፣ በማዘዋወር፣ በማብቀል ወይም በመፈብረክ ስራ ላይ የተሳተፈ ማንኛውም ሰው፤ ህግ በመተላለፍ ወንጀል እንደሚጠየቅና በእስራትና በገንዘብ እንደሚቀጣም ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ከተሳታፊዎቹ አንዱ በሀገራችን ያለውን የህግ ክፍተት ሲያስረዱ፡

> *...በዓለም አቀፍ ስምምነት የተዘረዘሩትን በሙሉ የሀገራችን ወንጀል ህግ አካቷቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በኛ ሀገር ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ያለና ብዙ ዜጎችን በተለይ ወጣቶችን ላልተገቡ ባህሪያት ብሎም ለወንጀል እየዳረገ ያለው ሺሻና ጫት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወንጀል ህጋችን ውስጥ ግልፅ ክልከላ ያልተደረገበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ መረዳት እንደሚቻለው፣ እንደ ካናዳና አሜሪካ ያሉ ሀገሮች በሀገራቸው ጫትም የተከለከለ እንዲሆን ህግ አውጥተዋል...፡፡*

በማለት የህግ ክፍተቱ የመስፋፋት ሂደቱን እንዳፋጠነውና በዚህም የተነሳ ወጣቶችና ሴቶችን ለሱስ ተጋላጭነት እንዳደረጋቸው አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም ከጫትና ሺሻ ጋር በተያያዘ በሀገራችን ያለው ህግ እርስ በርሱ እንደሚጣረስ ከቤት እመቤቶች፣ የቢሮ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡ ከተሳታፊዎቹ አንዲ በተጨባጭ ያለውን ነገር ሲያስቀምጡ፡

> *...መንግስት በአንድ በኩል ለቪዲዮ ቤቶች ፍቃድ ይሰጣል በሌላ በኩል ደግሞ ጎጂነቱ ይወራል፤ ይሄ ተጣጥሞ መሄድ የማይችል ነገር ነው፡፡ በተጨማሪም ...ሺሻ ቤቶች ተስፋፍተው የሚገኙበት ሁኔታ አለ፡፡ እነዚህ ሺሻ ቤቶችን በተመለከተ መንግስት በየወቅቱ የማጥፋት ዘመቻ ያካሂዳል፤ ሺሻውንና ማጨሻውን እየሰበሰበ ያቃጥላል፤ ነገር ግን ይህን ስራ የሚከለክልና የሚቀጣ ህግ ስለሌለ ዕቃውን መልሰው በመግዛት ስራውን ይጀምራሉ፡፡ ሌላው ጫት*

*ነው፤ ጫት ለሀገራችን ኢኮኖሚ ትልቅ ድርሻ አለው ብለን ብንወስድም ችግሩ ግን ከአቅም በላይ እየሆነ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሀፃናትና ወጣቶች እየተበላሹ ያሉበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡.... "የፈለግኩትን ሰራ መስራትም ሆነ መጠቀም መብቴ ነው" በሚል እነዚህን አላስፈላጊ ዕፆች ማስፋፋትም ሆነ መጠቀም ሀብረተሰቡን ከማይወጣው ችግር ውስጥ እየከተተ ስለሆነ "ለመብትም ገደብ ሊበጅለት ይገባል"....* በማለት ተናግረዋል፡፡

የአንድ እምነት ተቋም ተወካይ በአሜሪካን ሀገር ቆይታቸው ያዩትን በምሳሌነት አንስተው ሲያስረዱ፤ "ዲሞክራሲ በስፋት በሚነገርባትና የሰብዓዊ መብት ይጠበቅባታል በምትባለው ሀገር እንኳን አላስፈላጊ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ የሚከለክል ህግ አለ" ብለዋል፡፡ በመሆኑም በሀገራችንም አላስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ስርጭትም ሆነ አጠቃቀም የሚሰጠው መብት፤ የህግ አግባብ ያለው ገደብ ሊቀመጥለት እንደሚገባ ገልጸው፤ ከዚህ ቀደም ይህ ባለመሆኑ አላስፈላጊ ነገሮች እንዲስፋፉና ህብረተሰቡንም እንዲበክሉ መንገድ እየከፈተ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም ከጫት አስቃሚዎች ጋር በተደረገ ውይይት የአረብ ሀገራትን ምሳሌ በመውሰድ አንድ ተሳታፊ ሲያስረዳ፤ አልኮል መጠቀም በአረብ ሀገራት ክልክል ስለሆነ አቅርቦቱ ሆነ ተጠቃሚነቱ እንደሌለ ገልጿል፡፡ በሀገራችን ግን የህግ ማዕቀፎች አለመኖርና የተፈጻሚነታቸውም መላላት ለአላስፈላጊ ነገሮች መስፋፋት ያለውን አስተዋጽዖ አጽንዖት ሰጥቶ ተናግሯል፡፡

ከቡድን ውይይትና ቃለመጠይቁ የተገኙ መረጃዎች፤ ለአላስፈላጊ ነገሮች መስፋፋት ምክንያት የሚሆነው አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ ባገኙበት የሥራ ዘርፍ ስለመሰማራታቸው የሚከታተልና ከመስመር ከወጡም የሚቀጣ የህግ አግባብ አለመቀመጡን ወይም ተፈጻሚ አለመሆኑን አሳይተዋል፡፡ በመሆኑም በሆቴልና አልጋ ኪራይ፣ በግሮሰሪ፣ በጫት መሸጥና በመሳሰሉት ስም ከስር የሀሺሽ፣ የሺሻ፣ የወሲብ ንግድና ሌሎች አላስፈላጊ ነገሮች እንደሚካሄዱ ገልጸው፤ ይህ ሁኔታም በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ተወካዮች፤ ለሆቴሎች፣ ለሬስቶራንቶች፣ ለእንግዳ ማረፊያ ቤቶች፣ ለኪነጥበብ ውጤቶችና ለሌሎች የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ህጋዊ የሙያ ፈቃድ የመስጠት ኃላፊነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ በዚሁም መሰረት የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ዘርግተው ለአገልግሎቱ

የሚያስፈልጉ ነገሮች መሟላታቸውንና በተፈቀደላቸው መልኩ እየሰሩ መሆኑን ለመቆጣጠር የሚያስችል የህግ አግባብ ቢኖርም ፈቃድ የወሰዱት የንግድ ተቋማት በአግባቡ ስለመስራታቸው በግልም ሆነ፤ በቅንጅት ተከታትሎ እርምጃ የመውሰድም ሆነ የማስወሰድ የአፈጻጸም ክፍተት እንዳለ ተናግረዋል፡፡

### 4.3.3. መጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያደርሱት ተፅዕኖዎች

የጥናቱ ተሳታፊዎች መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን እንደሚያስከትሉ በሚከተለው መልኩ አስረድተዋል፡፡

**ሀ. ማህበራዊ**

ወጣቶችና ሴቶች ለአላስፈላጊ ሱስ አስያዥ ዕፆችና ደባል ባህሪያት መጋለጣቸው በማህበራዊ ህይወታቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ አንድ የስነ-አእምሮና የስነ ልቡና ሐኪም ገልጸዋል፡፡ አክለውም ለተለያዩ ዕፆች ሱስ የተጋለጡ ሰዎች በስካር መንፈስ ውስጥ ሲሆኑ ለድብድብ፣ ለመኪና እና ሌሎች አደጋዎች ሊጋለጡ እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡ በመቀጠልም ባለሙያው በተለይ ጫት በሰው ላይ የሚያሳድረውን የጤና እክል ሲያስረዱ፤ ለጥርስ ህመም፣ የአፍ "ኢንፌክሽን"፣ የአፍ ካንሰርና የአንጀት ካንሰር ለመሳሰሉት የጤና ችግሮች እንደሚዳርግ ገልጸዋል፡፡ የዕፅ አወሳሰዱ መንገድም ለበሽታ አጋላጭ እንደሆነ ሲያብራሩ፤ አንዳንድ ዕፆች የሚወሰዱበት መንገድ በመርፌ በመሆኑ ፤በችኮላ ወይም ግንዘብ በሚያጥር ጊዜ በሚኖር የጋራ መጠቀም ለኤች.አይ.ቪ.ና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች እንደሚያጋልጥ አስገንዝበዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በጥናቱ የተሳተፉ የቢሮ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች እንደገለጹት፤ አንድአንድ ሴቶች የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለመደገፍ ሲሉ ወደ ወሲብ ስራ በመግባታቸው ምክንያት ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ለፊስቱላ በሽታ የሚጋለጡበት አጋጣሚ ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በተለያዩ ዕፆች ሱሰኝነት ምክንያት ወጣቶች ላይ የሚደርሰውን የጤና ችግር አስመልክቶ በማረሚያ ቤት የሚገኝ አንድ የህግ ታራሚ ወጣት ሲገልጽ፡

*....አንድ ጓደኛዬ ሀሺሽ ከቤት ውስጥ አሰቀምጦ ተገኝቶ እናቱ አሳስራው ነበረ፡፡ ሀሺሽ ሲያጣ ያስታውካል፣ ራሱን የመጥላት፣ተስፋ የመቁረጥ፣ ከእብደት የማያንስ ድርጊት ይፈፅማል፡፡... በዚህ ምክንያት አሁን ታሞ በአማኑኤል ሆስፒታል ይገኛል...*

በማለት የችግሩን አሳሳቢነት አስገንዝቧል፡፡በሌላ በኩል ወጣቶች ለአላስፈላጊ ነገሮች መጋለጣቸው በትምህርታቸው ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ የቢሮ ሴቶችና የሴት አደረጃጀት አመራሮች ሲገልጹ፡

*...በኢንተርኔትና በፊልም አማካኝነት የሚያዩዋቸውን ነገሮች ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግም ይሞክራሉ፤ እንዲሁም በሲዲ ተዘጋጅተው የሚከፋፈሉ ህገወጥ ወሲብ ቀስቃሽ ፊልሞችን በመመልከት ወደዚያው ተግባር ሲገቡ ይታያል፡፡ በዚህም ምክንያት የትምህርት ውጤታቸው መቀነስ፣ ብሎም ትምህርት እስከ ማቆም ይደርሳሉ፡፡ ከቤተሰብ ጋር ባለመስማማት ምክንያትም ከቁጥጥር ውጪ ሆነው ከቤት ለመውጣትና ለሌሎች ተያያዥ ችግሮች ይጋለጣሉ፡፡... በአጠቃላይ ይህ ችግር ትውልድ እስከመግደልና ተተኪ እስከ ማሳጣት የሚደርስ ተጽዕኖ አለው...* ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ሴቶችና ወጣቶች ባልተገቡ በመጠ ባህሎችና አላስፈላጊ ድርጊቶች መጠመዳቸው፤ ማህበራዊ ቀውስን ለሚያስከትሉ እንደ ስርቆት፣ ድብደባ፣ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የኃይል ጥቃቶችና ሌሎችም ወንጀሎች መበራከት ትልቅ አስተዋጽየ እንዳለው በጥናቱ የተሳተፉ የህብረተሰብ አካላት ጠቁመዋል፡፡ በተለይ ከፖሊስ አካላት ጋር በተደረገ ውይይት በሱሰኝነትና ከዚሁ ጋር በተያያዘ ችግር ምክንያት ከሌሎች ሀገራት ተባረው የተመለሱ ወጣቶች የፈጸሙትን ወንጀል ሲያስቀምጡ፤

*....ወንጀል ፈፃሚዎቹ ከአሜሪካ "ዲፖርት" ሆነው የመጡ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ፣ ዜግነታቸው አሜሪካዊ ነው፡፡ ...እነዚህ ወጣቶች የሀሺሽ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ሀሺሽ ተጠቅመው ሁለት ፖሊሶችን በአሠቃቂ ሁኔታ ሰውነታቸውን በስለት በመውጋታቸው፤ አንደኛው ሟንቅላቱ ተፈላልጦ ህይወቱ ሲያልፍ ሌላኛው ደግሞ አራት ቦታ ላይ ተወግቶ ህይወቱ ተርፏል፡፡...ወንጀል ፈፃሚዎቹን ተከታትለን ቤታቸውን ሰንፈትሽ ኩርቱ ፌስታል ሙሉ አደንዛዥ እፅ አግኝተናል...፡፡* በማለት የሱስ አስያዥ ዕፆች ተጠቃሚነት ምክንያት የሚደርሰውን ማህበራዊ ቀውስ አስረድተዋል፡፡

**ለ. ኢኮኖሚያዊ**

ሴቶችና ወጣቶች በአልባሌ መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ውስጥ መዘፈቃቸው ለኢኮኖሚ ቀውስ እንደሚዳርጋቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ በወሲብ ንግድ ከሚተዳደሩ ሴቶች ጋር በተደረገ ውይይት አንዲት ተሳታፊ በሱሱ ምክንያት የሚደርስባትን የኢኮኖሚ ጫና ስትገልጽ፤

*...እኔ የጀበና ሰዓት ጫት ግማሽ የ30 ብር እቅማለሁ፣ሲጋራ የ5ብር አጨሳለሁ፡፡ ከዚያ ከምሳ ሰዓት በኋላ መደበኛ የሚባል አለ፣ ጫት ግማሽ የ30 ብር ሲጋራ የ7ብር ያስፈልገኛል፡፡ በአጠቃላይ ወደ ሰባ ሁለት ብር አካባቢ ያስፈልገኛል፡፡ በተጨማሪ ማታ ደግሞ አለ አንድ 70 ብር ያስፈልጋል፡፡...*
**በማለት አስረድታለች፡፡**

**በተጨማሪም የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገለጹትና በመስክ ምልከታው ለመታዘብ እንደተሞከረው በቀን ውስጥ ለመጠጥ፣ ለሲጋራ፣ ለሺሻ፣ ለሀሺሽ፣ ለእርቃን ደናሾችና ተወዛዋዦች ስጦታና ሽልማት እንዲሁም ለአዳር ለተስማማች ሴት ክፍያ የሚወጡ ወጪዎች በጣም ከፍተኛ መሆናቸው ታይቷል፡፡ ተሳታፊዎቹ እንደገለጹት ይህ ልኩ የማይታወቅ ከፍተኛ ገንዘብ ከግለሰብና ቤተሰብ አልፎ የሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጫና እንደሚፈጥር አስገንዝበዋል፡፡**

**የጥናቱ ተሳታፊዎች በግለሰቦች ላይ በአላስፈላጊ ሱሶች መጠመድ ምክንያት ከሚደርሰው የኢኮኖሚ ጫና በዘለለ፣ በሱሱ ምክንያት ዜጎች ከስራ ቦታ አቋርጠው ወጥተው በመሄድ፣ ያለ ስራ በመቀመጥ፣ በጤና እክልና በወንጀል በመሳተፍ በሚመጣ እስር የተነሳ ከምርታማነት ውጭ ይሆናሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በማምረት ሂደት ውስጥ የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና እውቀት ስለሚሸረሸር በሀገር ኢኮኖሚና ልማት ላይ የሚፈጥረው ጫና በድህነት አረንቋ ውስጥ እንድንዳክር ምክንያት ሊሆን እንደሚችልም አስረድተዋል፡፡**

**ሐ. ስነ-ልቦናዊ**

**በወጣቶችና ሴቶች ላይ በአላስፈላጊ ድርጊቶች ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን የስነ-ልቡና ችግር በተመለከተ አንድ በተመሳሳይ ዕታ የወሲብ ጥቃት የደረሰበት ተሳታፊ፣ ለተስፋ መቁረጥና ራስን ዝቅ አድጎ ለማየት እንደሚዳርጓቸው ከራሱ ተሞክሮ ተነስቶ ሲገልጽ**

*...በድርጊቱ የቀጠልኩበት ምክንያት በቃ ተበላሽቻለሁ በሚል ተስፋ በመቁረጥ ነው:: ራሴን ዋጋ እንደሌለዉ ሰው አድርጌም አይ ነበር::...ይህ ነገር የአእምሮ ጠባሳ ጥሎብኝ አልፎአል::... ሰው ማየት ያስጠላኛል::... ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር እንዳያውቁብኝ አድርጌ እጫወታለሁ.... ብሏል፡፡*

**በተጨማሪም በማረሚያ ቤት በተደረገው ውይይት ወቅት አንዲት ተሳታፊ አላስፈላጊ ነገሮችን መጠቀም ለሱስ እንደሚዳርግና ካልተገኙም ለብስጭት፣ ገለልተኛ ለመሆንና ከሰው ጋር ላለመስማማት የሚዳርጉ መሆናቸውን ገልጻለች፡፡ በተጨማሪም ተማሪም ሆነ**

ሰራተኛ ለምንም ነገር ትርጉም እንዲያጣና ግድየለሽ በማድረግ ጉዳት ላይ እንደሚጥልም አስረድታለች፡፡

ጫት በመቃም ሱስ የተጠመደ ወጣት ደግሞ የሱሱን ስነልቦናዊ ጫና ሲገልጽ፡

> *...በዚህ ሰዓት ደስተኛ አይደለሁም፣ አሁን ከሰምንት ሰዓት የበለጠ ይመስለኛል፡፡ ለሰይጣን ልጅን የማረጃ ሰዓት የሚባልበት ጊዜ ነው፡፡...አሁን ቁጭ ቅላቴም፣ "ነርቬም" ወደ ዚያ ወደ ጫቱ ላይ ነው፡፡ ቀልቤ ሁሉ ጫት ላይ ነው፣ ምግብ እራሱ የዛን ያህል አያሰኝኝም፡፡ ከሱስ መውጣት እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን እስካሁን አልቻልኩም ....* በማለት አስቀምጦታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ሌላው ወጣትም፡

> *....እኔ የጫትና የሲጋራ ሱስ ብቻ ነው ያለብኝ፡፡መጠጥ አልጠቀምም፡፡የሴት አመለካከት የለኝም፡፡በሌሎች ጓደኞቼ ግን ይህን ተግባር አያለሁ፡፡ ሁለት ጓደኞች አሉኝ ካልጠጡ የማይሆንላቸው፡፡ ስትመረቅን የማይቻለው የሚቻል ይመስልሀል፣ ወንዝ ዘለህ የምትሻገር ይመስልሃል፡፡ የማይታሰበውን እንድታስብ ስለሚያደርግህ የዚያን ጊዜ ሰለ መጠጥ እንድታስብ ያደርግሃል፡፡..*

በማለት የሰውን ልጅ ጤናማ አስተሳሰብ በማዛባትና ባልተጨበጠ ነገር ውስጥ በማስገባት የሚያሳድረውን የስነልቡና ችግር ገልጿል፡፡

**መ. የፀጥታ ተፅዕኖ**

በመጤ ባሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በመጠመድ ምክንያት ወጣቶችና ሴቶች በአካባቢያቸው ሊያደርሱት ስለሚችሉት የፀጥታ ተፅዕኖ በተመለከተ የጽሑፍ መጠይቅ ተሳታፊ ከሆኑት መካከል 48.8%ቱ በቡድን ድብድብ ይሳተፋሉ በማለት አስቀምጠዋል፡፡ 35.4%ቱ ተሳታፊዎች ደግሞ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በአስገድዶ መድፈር ድርጊቶች ተሳታፊ እንደሚሆኑ ሲጠቅሱ 58.2%ቱ በስርቆት ሊሳተፉ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 54.2%ቱ ተሳታፊዎች በመጤ ባህልና አላስፈላጊ ልማዳዊ ድርጊቶች የተነሳ ወጣቶችና ሴቶች አካባቢን በማወክ ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የአልኮል መጠጦችንና የሱስ አስያዥ ዕፆችን ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ዘርፈ ብዙ የፀጥታ ችግሮች እንደሚከሰቱ አንስተዋል፡፡ የሱስ ተጠቂ ከሆኑ ወጣቶች ጋር በተደረገ ውይይት አንድ ተሳታፊ ሲያስረዳ፡-

*... ለጫትና ሲጋራ አራራ የሚሆን ገንዘብ ከየትም ፈልገን ማሟላት አለብን፡፡ አንዳንዴ ግን ለዚህ የሚሆን ሳንቲም ይጠፋል፡፡ ታዲያ ይህን ጊዜ አንዳንዶቻችን ለሱሳችን ስንል ሌሎች ነገሮችን ለማድረግ እንገደዳለን፡፡ ለዚህም የተለያዩ ወንጀሎችን የሚፈጽሙ ልጆች አሉ፡፡ በቃ ሱሰኛ መሆን እኮ ምንም እንዳትፈራ ያደርግሃል፡፡ትልቅ ወንጀልም ቢሆን...* ብሏል፡፡

በተመሳሳይ ከፖሊስና ከፍትህ አካላት ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ብዙ ግለሰቦች ከሱሰኝነትና ሱስን ለማስታገስ ከሚደረግ ጥረት ጋር በተያያዘ ለተለያዩ ወንጀሎች እንደሚዳረጉና በዚህም ምክንያት ጉዳያቸው በህግ የታየና እየታየ ያለ አለ፡፡

በቀንና በሌሊት ጭፈራ ቤቶች፣ እንዲሁም በጫት መቃሚያ ቤቶች በተደረገ ምልከታ የተለያዩ የፀጥታ ችግሮች ሲከሰቱ ለማስተዋል ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፣ ጠጥተው የሰከሩ ወጣቶች ሲደባደቡና አካባቢ ሲያውኩ ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም በጫት ቤት ውስጥ የነበሩ ተስተናጋጆች የተለያዩ የወንጀል ወሬዎችን ሲያወሩ ተደምጠዋል፡፡

በአጠቃላይ በሱስ አስያዥ ዕፅ ገፋፊነት ለወንጀልና ለአካባቢ ፀጥታ መረበሽ ምክንያት፣ ለሱስ ማሚያ ወንጀል መፈጸምና የመሳሰሉት ለአካባቢያዊ ብሎም ለከተማዋ ፀጥታ መደፍረስና አለመረጋጋት ምክንያት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.3.4. አላስፈላጊ መጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖና ችግር ለማስወገድ ከተሳታፊዎች የቀረቡ የመፍትሔ ሀሳቦች

ይህን ጥናት ለማካሄድ በተጠቅምንባቸው የመጠናዊና ዓይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መረጃ ሰጪ የነበሩት የከተማዋ ነዋሪዎች፣ የጉዳዩን ምንነት፣ የመስፋፊያ መንገዶችና ምክንያቶች፣ ያሳደሩትን ተጽዕኖና አሁን ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታ ባመላከቱበት አንደበታቸውና የጽሑፍ መልዕክታቸው መደረግ አለበት ያሉትን የመፍትሔ አስተያየት አስቀምጠዋል፡፡

በዚህም መሰረት በጽሑፍ መጠይቁ አስተያየቶቻቸውን ከሰጡት የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል 1077 ያህሉ መንግስት ችግሩን ለመፍታት ፖሊሲ፣ ህግ፣ ደንብና መመሪያ በማውጣትም ሆነ የወጡት ተፈጻሚነት እንዲኖራቸውና ጠንከር ያለ ተጠባቂ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበዋል፡፡ ከመረጃ ሰጪዎቹ 210 የሚሆኑት ደግሞ፣ ህብረተሰቡ ባህሉን

አውቆ በማክበርና አርአያ በመሆን ለሌሎች ማስተዋወቅ እንደሚገባው አስገንዝበዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 585 የሚሆኑ መረጃ ሰጪዎች መንግስት፣ህብረተሰቡና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በጋራም ሆነ በተናጠል በችግሩ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት፣ ችግሩ እንዲስፋፋ ምክንያት የሚሆኑ አጋጣሚዎችንና ቦታዎችን በመከታተል፣ቁጥጥር የማድረግና በግልጽ የመቃወም ኃላፊነት መውሰድ እንዳለባቸውም አስቀምጠዋል፡፡አክለውም እነኝሁ አካላት በቅንጅት የስልጠና፣ የማስተማሪያና ተገቢነት ያላቸው የመዝናኛ ማዕከላትን በማመቻቸት እና በችግሩ ውስጥ ለገቡትም አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ በማድረግ ወደ ምርታማነት የመመለስ ስራ መስራት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

የመገናኛ ብዙሃን የፕሮግራም ስርጭትም ሆነ፤ የባህል ተቋማት የኪነጥበባዊ ስራ ውጤቶች ይዘትና የአቀራረብ ዘዴ፤ በኢትዮጵያዊ ባህልና ወግ ቅኝት ውስጥ ማለፉን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ያሉት ደግሞ፤ 35 መረጃ ሰጪዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሲገልጹ፤ በጎ የሆኑ መጤ ባህሎችን ከራስ ባህል ጋር አስማምቶ ስለመጓዝ የመገናኛ ብዙሃንና የባህል ተቋማት ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት የማስተማር ስራ መስራት እንዳለባቸውም አሳስበዋል፡፡ እንዲሁም የእምነት ተቋማት ተከታዮቻቸውን በጎ ስነምግባርን የማስተማር ኃላፊነት በመውሰድ እንዲሰሩና፤ ምዕመናኑም በየእምነት ተቋማቸው በሚወጡ መመሪያዎች በመመራት ለመንፈሳዊ እሴቶች ትርጉም በመስጠት መተግበር እንደሚገባቸው 36 አስተያየት ሰጪዎች አስገንዝበዋል፡፡

ወጣቱና በችግር ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና የገለጹት 26 አስተያየት ሰጪዎች ደግሞ፤ ወጣቶች በወጣት ማዕከላትና በት/ቤት ውስጥ በሚቋቋሙ የተለያዩ ክበቦች ውስጥ ተሳታፊ በመሆን በችግሪ ዙሪያ የአቻ ለአቻ ውይይት በማድረግ የመፍትሔው አካል መሆን ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በነዚህ ማዕከላትና ክበባት አማካኝነት በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችም ገና ችግር ውስጥ ላልገቡት በኔ ይብቃ የማስተማሪያ ውይይቶች በተጠናከረ መልኩ ቢያካሂዱ መልካም እንደሆነ አስገንዝበዋል፡፡

በመጨረሻም ለዚህ ችግር ትልቅ አስተዋጽየ ያለው ቤተሰብ ከልጆቹ ጋር ግልጽ ውይይት የማድረግና የልጆቹን የቤት ውስጥና የትምህርት ቤት ውሎ መከታተል እንደሚገባው 101

አስተያየት ሰጪዎች ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ቤተሰብ ልጆቹን ምክርና ተግሳጽ በመስጠት ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዙ ማድረግ እንደሚኖርበት አመላክተዋል፡፡

በዓይነታዊ የመረጃ ማስባሰብ ስልት ማለትም በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃ የሰጡት ተሳታፊዎች ደግሞ፤ በሴቶችና ወጣቶች ላይ በእጅጉ እየተስተዋለ ያለውን በመጤ ባህል መጠመድን፣ በአጉል ልማድ መወሰድንና ለተለያዩ የስነ-ምግባር ችግሮች መጋለጥን ለመግታት ያስችላል ያሉትን የተለያዩ የመፍትሔ ሀሳቦች ሰንዝረዋል፡፡ የተሰነዘሩት የማስተካከያ ሀሳቦቹ እንዲተገበሩም መንግስት፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የእምነት ተቋማትና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ይወጡ ዘንድ ጠቁመዋል፡፡

አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ወጣቶችና ሴቶችን ይበልጥ ለጥፋት ይዳርጋሉ ብለው ከጠቀሷቸው ውስጥ፤ የጫትና ሺሻ ቤቶች ትውልድ የሚያበላሹ ቦታዎች በመሆናቸው በህግ መከልከል እንዳለባቸው አስቀምጠዋል፡፡ በተጨማሪም የቀን ጭፈራ ቤቶች ወጣት ተማሪዎችን ለስነ-ምግባር መበላሸት እና ለሌሎች ተወራራሽ ችግሮች እየዳረጉ ስለሆነ የማያዳግም እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች አክለውም፤ የተለያዩ የእምነት ተቋማት ወጣቱ በስነ-ምግባር የታነፀ፣ ባህሉን አክባሪና በጎ ስራ ወዳድ እንዲሆን ማስተማር እንደሚገባቸው አጥብቀው አስገንዝበዋል፡፡ በሌላ በኩል ሀገሩን አፍቃሪ፣ ለሀላፊነት የበቃ፣ መልካም እሴት ተረካቢ ዜጋ መፍጠር እንዲቻል የግብረ-ገብነት/ሞራል ትምህርት በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ተካቶ እንዲሰጥ መክረዋል፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት ያለገደብ የሚሰራጩ ያልተገቡ፣ ዕድሜን፣ የማህበረሰቡን ባህልና  የንቃተ ህሊና ደረጃ ያላገናዘቡ መረጃዎች ስርጭት ላይ ህጋዊ ቁጥጥር መደረግ እንዳበት ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ሀገራዊ ባህልና ትውፊትን ያልጠበቁ የውጪም ሆነ የሀገር ውስጥ ፊልሞች ላይ ጠበቅ ያለ ቁጥጥርና እርምጃ መወሰድ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ወጣቶችና ሴቶችን ለመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ከሚያጋልጧቸው ምክንያቶች አንዱ በቂ ስራ አለመኖርና የትምህርት ዕድል አለማግኘት ስለሆነ በበለጠ የስራ ፈጠራና የትምህርት እድል ሊመቻች እንደሚገባ በተሳታፊዎቹ ተጠቅሷል፡፡

ተቀናጅቶ ከመስራት ጋር በተያያዘም፤ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረትና በምትኩም ሀገር በቀል የባህል እውቀቶችን ለማስረፅ፤ መንግስት ከተለያዩ የኃይማኖት፣የትምህርት፣የማህበረሰብ ተቋማት እንዲሁም ከመገናኛ ብዙሃን ጋር በመሆን በእውቀት ላይ የተመሰረተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል ሲሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡ በተለይም የመገናኛ ብዙሃን ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በተዋቀረ አካል የሚቀርብ ተከታታይ ትምህርት ማስተላለፍ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

የህግ አስፈፃሚዎችን ኃላፊነት በተመለከተ ተሳታፊዎቹ በሰጡት ሀሳብ፤ የህግ ክልከላ የተቀመጠላቸው ነገር ግን ክልከላውን በመጣስ ተፈጸሙ ያሉ ህገወጥ ድርጊቶች ላይ በህጉ መሰረት ጠንካራና ተከታታይነት ያለው እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡ ህብረተሰቡም በየአጋጣሚው በጉዳዮቹ ላይ ጠንካራ አቋም ሊወስድ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በሌላ በኩል ለልጆች የቤተሰብ ድጋፍና ክትትል በተገቢው መልኩ መደረግ እንዳለበትና የልጆች ባህሪን በመቅረፁ በኩል ትልቁ ድርሻና ኃላፊነት የቤተሰብ መሆኑንም ተሳታፊዎቹ ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸው በስነ-ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ማስተማር፤ ሲያረፍዱ በር ከመዝጋት ይልቅ በግቢው ውስጥ የማቆያ ስልት በመቀየስ እንዲሰሩ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት በተቀናጀና ቀጣይነት ባለው ጥረት ወጣቶችና ሴቶችን እየገቡበት ካለው አስከፊ ችግር ሊታደጓቸው እንደሚገባ የጥናቱ ተሳታፊዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

## 5. የጥናቱ ግኝት ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ስር በመጠናዊና ዓይነታዊ የጥናት ስልቶች አማካይነት ከተሰበሰቡ መረጃዎች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ተተንትነዋል፡፡ የትንተናው አካሄድ የተከናወነው የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች በመመርኮዝ፤ የተገኙ መረጃዎችን ለጥናቱ ከተመረጡ ተዛማጅ ጽሑፎች ጋር በማዛመድ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የመጤ ባህሎችና ድርጊቶችን ምንነት፣ መንስዔዎቻቸውንና እያሳደሩት ያለው ተፅዕኖ በዝርዝር ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 5.1. በሴቶችና ወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉት መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች

በአዲስ አበባ ከተማ ሴቶችና ወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶችን ምንነት ለመለየት በተደረገው ጥናት መሰረት የተሰበሰቡት መረጃዎች ምንም እንኳን መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ለሚባሉት ወጥ የሆነ ብያኔ ለማግኘት አላስቻሉም፡፡ ይሁን እንጂ የነዚህ መገለጫና ማሳያ በመሆን ሱስ አስያዥ ዕጾች(ሺሻ፣ሀሺሽ፣ጫት፣መጠጥና የመሳሰሉትን) እና የአልኮል መጠጦችን መጠቀም፣የቀን፣ የምሽትና የእርቃን ጭፈራ ቤቶች መጠቀም፣ ግብረሶዶማዊት፣ለየት ያሉ ተግባራት በሚፈጸሙባቸው የመታሻ/የማሳጅ ቤቶች መጠቀም፣ የግለኝነት አስተሳሰብ፣ያልተገቡ የአለባበስ ሁኔታዎች እና የመሳሰሉት ተነስተዋል፡፡

### 5.1.1. አነቃቂ ዕፆችን መጠቀም

አነቃቂ ዕፆችን ማለትም ጫት፣ሺሻ፣ ሀሺሽ፣ አልኮል መጠጦችንና የመሳሉትን መጠቀም በአሁን ወቅት በከተማዋ ውስጥ ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቡናዊ ጫና እየፈጠረ ያለ ልማዳዊ ድርጊት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የጥናቱ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በጥናቱ ከተሳተፉት 2529 ያህል ሰዎች 1535(60.7%)ቱ የአልኮል መጠጦች፣717(28.4)ቱ ደግሞ የአነቃቂ ዕፅ ተጠቃሚዎች እንደሆኑ ያመላክታል፡፡ በቃለመጠይቅና በቡድን ውየይት የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙትም በከተማዋ ውስጥ ከተማሪ እስከ መንግስት ሰራተኛ፣ ከታክሲ ተራ አስከባሪ እስከ አስመጪና ላኪ ነጋዴ፣ ከፖሊስ እስከ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን የአነቃቂ ዕፆችና የአልኮል መጠጥ ተጠቃሚዎች እንደሆኑ ያሳያል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ዕድሜያቸው ከ15-29 ዓመት ያሉ ወጣቶችን ቢሆንም፤ የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው በዚህ ችግር በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቂ የሆኑት ዕድሜያቸው ከ12-14 ዓመት ያሉ ህፃናትና ከ15-29 ዓመት ያሉ ወጣቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከ29 ዓመት በላይ ያሉ ሴቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችም ተጠቂ ሲሆኑ ቁጥራቸው ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መምጣቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሥዩም (1996) የተከናወነው ጥናት እንደሚያሳየውም የከተማዋ ነዋሪ በተለይም ወጣቱ ክፍል የተለያዩ አነቃቂ ዕፆችንና አልኮል የመጠቀም ልምድን ከማዳበሩም በላይ ጊዜያዊ ደስታን ለማሳደግ በሚል አንዱን ከአንዱ እየቀላቀለ በመጠቀም ለከፋ ችግር እንደሚጋለጡ ይጠቅሳል፡፡

በዚህም ምክንያት በከተማዋ ወቅታዊና ዘለቄታዊ ዕድገትና ብልፅግና ላይ ትልቅ ነገር ማበርከት የሚገባቸው ወጣቶችና ህፃናት እንዲሁም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶች በማይገቡ ሱሶች በመጠመድ ከልማት እየራቁ ያሉበትን ሁኔታ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 5.1.2. የቀን፤ የሌሊት እና የራቁት ጭፈራ ቤቶች መጠቀም

ከዚህ ጋር በተያያዘ ወጣቶችና ሴቶች በተለያዩ የቀን፣ የሌሊትና የእርቃን ጭፈራ ቤቶች መዝናናትን እንደ ስልጣኔና የገቢ ምንጭ እየተመለከቱት ያሉት አዲስ ልምድ ነው፡፡ ዓይነታዊና መጠናዊ መረጃዎቹ እንደሚያሳዩትና በአካል በመገኘት ለማረጋገጥ እንደተቻለው በአስራዎቹ ውስጥ የሚገመቱ ህፃናት ተማሪዎች በቀን ጭፈራ ቤቶች በመገኘት ለመዝናናት በሚል እሳቤ ለመጠጥና ለተለያዩ ዕፆችም እየተጋለጡ ነው፡፡ በጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ 102ቱ ተሳታፊዎች ጭፈራ ቤቶችን እንደመዝናኛነት እንደሚጠቀሙባቸው ያሳያል፡፡ የምልከታው ውጤትም እንደሚያሳየውም ወጣቶች፣ ጎልማሳ ሴቶችና ወንዶች፤ እንዲሁም አዛውንቶች በቀን፣ በሌሊትና በእርቃን ጭፈራ ቤቶች በመዝናናትና በማዝናናት ሂደት ውስጥ የተጠመዱ ሲሆን በነዚህ ቤቶች ውስጥም የአልኮልና የዕፅ ፍጆታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ሠራተኞችና በኃላፊነት ላይ የሚገኙ ግለሰቦች፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ማህበራዊ ደረጃ የሚሰጣቸው ግለሰቦችና በኢኮኖሚው ዘርፍ ትልቅ አስተዋፅየ ሊያበረክቱ የሚችሉባለሙያዎችና የንግድ ሰዎች በዚህ መጤ ያልተገባ ልምድ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች በዚህ ያልተገባ ልማድ መጠመድ አርአያ ሊሆኑለት ለሚገባው ህብረተሰብ የሚያተላልፈው አፍራሽ መልዕክት ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በነዚህ ጭፈራ ቤቶች ውስጥ የሚዝናኑ ህፃናት፣ ወጣቶችና ሴቶች ለሱስ ተገዥ ከመሆናቸውም በላይ በሚተገበሩት ወሲብ ቀስቃሽ ዳንሶችና እንቅስቃሴዎች ምክንያትነትና፤ በሚጠቀሟቸው መጠጥና ዕፆች አደፋፋሪነት ለማይገባ የወሲብ ግንኙነት የተጋለጡ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ህፃናቱ፣ ወጣቶቹና ሴቶቹ ከትምህርታቸውና ከስራቸው ይልቅ ትኩረት የሚሰጡት ለነዚህ ተዝናኖቶችና ሱሶች ስለሚሆን በከተማይቱ ብሎም በሀገሪቱ እድገትና የልማት እንቅስቃሴ ላይ እየደረሰ ያለውንና ለወደፊቱም በባሰ ሁኔታ የሚደርሰውን የዝቅጠት አደጋ መገመት ቀላል ነው፡፡

### 5.1.3. የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነት/ግብሰዶማዊነት

ከመጤ ባህሎችና ልምዶች ጋር በተያያዘ በከተማዋ በመዛመት ላይ ካሉት ችግሮች ሌላኛው የግብሰዶማዊነት ችግር ነው፡፡ የጥናቱ መረጃዎች የሚያሳዩት የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነት ማንኛውም የከተማው ነዋሪ ከሚገምተውና ከሚያስበው እጅግ በበለጠ

መልኩ መስፋፋቱን ነው፡፡ ይህ ድርጊት ተፈጥሯዊ ከሆነው የፍትወት ስጋ የተራክቦ ተግባር የተለየና ያፈነገጠ፤ ከእምነት፤ከባህል፤ከሥነ-ምግባርም ሆነ ከሞራል አንጻር ድጋፍ እንደሌለው የተገኙት መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በዚሁ ህይወት ውስጥ ተገዶ የገባ ተሳታፊ እንደገለጸው እንደሞከረውና የእርሱን ጥቆማ መሰረት በማድረግ በአንድአንድ ቦታዎች ላይ በተደረገ ቅኝትለመረዳት እንደተቻለው ተመሳሳይ ፆታን ለወሲብ ማሰብ እየተለመደ ከመምጣቱም በላይ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር በመሄድ በወሲብ ስራ የሚተዳደሩ ሰዎች እየተበራከቱ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በጥናቱ ከተሳተፉ በወሲብ ንግድ ከሚተዳደሩ ሴቶች የተገኙ መረጃዎች የሚያሳዩትም ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ባዕድ አካልን በመጠቀም የወሲብ ግንኙነት ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት ነው፡፡ የድርጊቱን በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት የሚያሳዩት በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች፤ በተለይ ወጣቶች፤ሴቶችና የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ሕፃናት ተማሪዎች የችግሩ ተጠቂ መሆናቸውን ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማህበረሰቡ ላይ የሥነ-ልቡናና የማህበራዊ ቀውስ እያስከተለ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ ይህም ያልተለመደና ከተለመደው ፆታዊ ግንኙነት ወጣ ያለ ተግባር በሰዎቹ ላይ ከሚፈጥረው የስነልቡናዊና ማህበራዊ ጫና በተጨማሪ የከተማዋን ገጽታና የልማት እንቅስቃሴ የሚጎዳና የሚያበላሽ ድርጊት ቢሆንም በሚያስደነግጥ ፍጥነት እየተስፋፋ ያለ ጉዳይ ሆኗል፡፡

የዚህን እኩይ ተግባር መጥፎ ገጽታ/ተፅዕኖና መስፋፋት፤ ሞገስ(2008) በሰጠው አስተያየት ሲገልጽ፤ወጣቶች በተለያዩ ዕፆችና መጠጦች አነሳሽነት ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ከተለመደው ወጣ ባለ መልኩ የወሲብ ተግባር እንደሚፈጽሙና በተለይም ቆንጆና በትምህርታቸው ጎበዝ ሴት ተማሪዎች ለችግሩ ሰለባ እንደሆኑ አስረድቷል፡፡ይህንንም በዚህ ጥናት የተገኘውን ውጤት ይበልጥ ተጨባጭ ያደርገዋል፡፡

### 5.1.4. ለየት ያሉ ተግባራት የሚፈጸሙባቸው መታሻ ቤቶችን መጠቀም

በመጠናዊው የጥናት መረጃ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው 5.4% የሚሆኑት የማሳጅ ቤቶችን በመጠቀም ራሳቸውን ዘና ለማድረግ እንደሚሞክሩ ነው፡፡ በተጨማሪም በምልከታ የተገኘው ውጤትም፤ የ24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ መታሻ/ማሳጅ ቤቶች እየተስፋፉ መምጣታውን ሲሆን በቤቶቹ ውስጥም ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቁና ለየት ያሉ የመተሻሸትና ድብቅ የወሲብ ተግባራት እንደሚፈጸሙ አሳይቷል፡፡

በነዚህ የመታሻ/ማሳጅ ቤቶች የታየው ያልተገባ ድርጊት በጥናቱ ሂደት የተገኘ ተጨማሪ ግኝት ሲሆን፤ በቤቶቹ ውስጥ በሚሰጠው ስውር ግልጋሎት በመሳብም ከፍተኛ ቁጥር ያለው

ተገልጋይ ወደነዚህ ቤቶች እንደሚሄድ ለመረዳት ተችሏል። በመታሻ ቤቶቹ በመገኘት በተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት ተገልጋዮች የሰዓትና የቀን ቀጠሮ እየተያዘላቸው እንደሚስተናገዱ ለማወቅ ተችሏል።

ከላይ የተነሱት ሃሳቦች የሚያረጋግጡት በነዚህ ቤቶች መጠቀም እየተለመደ የመጣ ክስተት መሆኑን ነው። ይህም ግልጋሎት የሚሰጡትንም ሆነ ተገልጋይ ወጣቶችና ሴቶችን እንዲሁም አረጋውያንን ላልተገቡ የወሲብና ወሲብ ነክ ድርጊቶች የሚገፋፋ ነው።

### 5.1.5. የግለኝነት አስተሳሰብና ያልተገቡ የአለባበስ ሁኔታዎች

ከጥናቱ የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች የአዲስ አበባ ህብረተሰብ ቀድሞ ነበሩትን እሴቶች የሚያጠፉ፤ በስልጣኔና ዘመነኝነት ስም እየተንሰራፉ ያሉት የራስን ማንነት የማጣት ሁኔታዎችን የሚያንፀባርቁ ጉዳዮች ናቸው። እንደ መረጃዎቹ ገለጻ የሰው ልጅ አስተሳሰብ ለባህሪውና ለተግባሩ መሰረት ነው። ይህም በመሆኑ የአንድ ሰው አስተሳሰብ ማህበረሰቡ ካዳበረው የጋራ አስተሳሰብና እሴት ወጣ ሲል በባህሪውና በሚተገብራቸው ተግባራት ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ለዚህም ነው ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል የአንድ እምነት ተወካይ፤በኢትዮጵያ ያለው የሰዎች አስተሳሰብ በህብረት መኖርንና አንዱ ለሌላው ማሰብን የሚያበረታታ እሴት ያለው ሲሆን አሁን ግን እየሰለጠነ ያለው እኔን ብቻ ይድላኝ የሚል የግለኝነት አስተሳሰብ እንደሆነ ጠቅሰዋል።ይህ እኔን ብቻ ይመቸኝ የሚል አስተሳሰብ ሰዎችን ያልተገባ ሀብት ለመሰብሰብ በሚደረግ ሩጫ ለሙሰኝነት፣ ሌላውን ጨፍልቆ ራስን ለማውጣት፣ ከመጠን ላለፉ ተዝናኖቶችና ከትትክለኛው መስመር ወጣ ባለ መልኩ የመርካት ፍላጎቶችን እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል።በመሆኑም የግለኝነት አስተሳሰብ መዳበር ለሌሎች ችግሮች መነሻ ምክንያት እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል።

ከዚህ አስተሳሰብ መዳበር ጋር ተያያዥ የሆነው አንዱ ያልተገቡ አለባበሶች መስፋፋት ነው።ከጥናቱ የተገኙ መረጃዎች የሚያሳዩት ህብረተሰቡ ህገኛ ብሎ ከመደባቸው አለባበሶች ወጣ ባለ መልኩ የሚደረጉ እርቃንን እያሳዩና ሱሪ ዝቅ አድርጎ በመልበስ መሄድ የመሳሰሉ ድርጊቶች በአሁን ግዜ እየተስፋፉና እንደ ትክክለኛ አካሄድ እየታሰቡ ያለበትን ሁኔታ ነው። እነዚህ ያልተገቡ አለባበሶች ለያታዊ ፍላጎት በመገፋፋት/ዝሙት ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች በተለይም በጤና በኩል ለኤችአይቪና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች የራሱ የሆነ ትልቅ አአስተዋጽኦ አለው።

የግለኝነት አስተሳሰብና ያልተገቡ አለባበሶች መዳበርን በተመለከተ ከተነሳው ሀሳብ ጋር ተያያዥ በሆነ መልኩ Jeffrey(2002) በአሁን ወቅት ወጣቱ ከምዕራባውያን በተለያየ መንገድ በሚወርሳቸው አስተሳሰቦች፣ አመለካከቶችና አለባበሶች ምክንያት የራሱን ባህል፣ ወግ፣ እሴት፣ አስተሳሰብ፣ባህሪና አለባበስ እየተወ እንደሚገኝ ገልጻለች፡፡ ይህም የግለኝነት አሰስተሳሰብና ያልተገቡ የአለባበስ ሁኔታዎች በወጣቶችና ሴቶች የማንነት ጥያቄ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ያመለክታል፡፡

## 5.2. ሴቶችና ወጣቶችን ለመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጧቸው ምክንያቶች

### 5.2.1. ማህበራዊ ምክንያቶች

በጽሑፍ መጠይቁ የተሰበሰቡት ምላሾች በደረጃ የሚያሳዩት መረጃ ማህበራዊ ጉዳይ ከሆኑት ውስጥ 80.1% የሚሆነው የአቻ ጓደኛ ግፊት፣ 52.5% የቤተሰብ መፍረስና 46.3% የቤተሰብ የአነቃቂ ዕፅና አልኮል መጠጦች ተጠቃሚ መሆን ወጣቶችና ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ነገሮች እንዲገቡ እንደሚያደርጓቸው አመላክቷል፡፡

በሌላ በኩል በዓይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ ውጤቶች የሴቶችና ወጣቶች በመጤ ባህል መወሰድና አላስፈላጊ ድርጊቶች መጋለጥ ምክንያቶች፤ የሴቶችና ወጣቶች አለመማር፣ የቤተሰብ ግንኙነት መላላት፣ የቤተሰብ ክትትል ማነስና መብዛት፣ የቤተሰብ ዕፅና አልኮል ተጠቃሚ መሆን፣ የአቻ ጓደኛ ግፊትና የትምህርት ቤቶች ቁጥጥር መላላት መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡

በንድፈ ሀሳብ ክለሳው እንደተመለከተው፣ የBalders (2002) ፅንሰ ሀሳብ ልጆችና ወላጆች በጉዳዮቻቸው ዙሪያ በግልፅ መወያየት እንዳለባቸው፣ ወላጆች ለልጆቻቸው ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ መወጣት እንደሚገባቸው፣ እንዲሁም ልጆች መብትና ግዴታቸውን አውቀው ቤተሰቦቻቸውን፣ ማህበረሰቡን እንዲሁም መልካም እሴቶችን የማክበርና ሀገር ተረካቢነታቸውን በሚገባ የመቀበል ኃላፊነትን የሚገልጽ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በ2003 ባጠናው ጥናት የአቻ ጓደኛ ግፊት ሴቶችና ወጣቶችን ለተለያዩ አላስፈላጊ ድርጊቶች(ጫት፣ሲጋራ፣ አልኮል መጠጦች፣ሺሻ፣ሀሺሽና ያልተገባ የግብረ ስጋ ግንኙነት) እንደተጋለጡ ጠቅሷል፡፡ በ Hops ና ሌሎችም(1999) ጥናትም እንዲሁ ወጣቶች ከጓደኞቻቸው በማየትና በመገፋፋት ያልተገቡ ድርጊቶችን እንደሚፈፅሙ፣ በተለይ በዕፅ ተጠቃሚነት ላይ ጫናው የከፋ እንደሆነ ተገልጸዋል፡፡ የእነዚህ ጥናት ውጤቶች እሳቤም ከላይ የማህበራዊ ሁኔታዎችን አስመልክቶ የተነሳውን ትንታኔ የሚያጠናክር ነው፡፡

ይህም የሚያሳየው የአቻ ጓደኛ ግፊት፣ የቤተሰብ መፍረስና የቤተሰብ የአነቃቂ ዕፅና አልኮል መጠጦች ተጠቃሚ መሆን በልጆች ባህሪና ስነልቡና ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአቻ ጓደኛ ግፊት የሚያደርሰው ተፅዕኖ ከሌሎቹ የበለጠ ጫና እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨሪም የወጣቶችና ሴቶች አለመማር የነገሮችን ጠቃሚነትና ጎጂነት የማገናዘብ ክህሎት ስለሚያሳጣቸው ወደ አላስፈላጊ ነገሮች እንዲገቡ እንደሚያደርጋቸው ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል በቤተሰብ መካከል ግልፅ ውይይት አለመኖሩና ቤተሰቦች ለልጆቻቸው አስፈላጊውን እንክብካቤና ፍቅር አለመስጠታቸው፤ ልጆች ከቤተሰብ ቁጥጥር ውጭ መሆንና በጓደኞቻቸው በመመራት ለአላስፈላጊ ነገሮች መጋለጥ ምክንያት መሆኑንም ለመረዳት ያስችላል፡፡ ቤተሰብ ከሚገባው በላይ የሚቆጣጠራቸውም ሆነ፤ ነፃ የሚለቃቸው ልጆች ለችግሩ ተጋላጭ እንደሚሆኑና የቤተሰብ አርአያነትም ለልጆች ሁለንተናዊ ማንነት መሰረት እንደሚሆንም ነው፡፡ በአጠቃላይ ያልተረጋጋና አርአያነት የጎደለው የቤተሰብ ሁኔታና የአቻ ጓደኞቻቸው አሉታዊ ግፊት ወጣቶችና ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ነገሮች እንደሚገፋፉ መረዳት ይቻላል፡፡

### 5.2.2. ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች

የጥናቱ መጠናዊ የመረጃ ግኝት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ወጣቶችና ሴቶች ወደ አልተገቡ ድረጊቶች ከሚገፋፉ ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ ይኸውም 67.9%ቱ የገቢ ምንጭ ማነስ፣ 47.1%ቱ ስራ ማጣትና 67.9%ቱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ለማግኘት በመፈለግ ሴቶችና ወጣቶችን ወደአልተገቡ መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች እንደሚያጋልጡ ምክንያቶች መሆኑን አሳይቷል፡፡ በዓይነታዊ የመረጃ ስልቶች የተገኘው ውጤት ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ግኝቱም ሥራ ፈትነት፣ የገቢ ምንጭ ማነስ፣ የኢኮኖሚ ጥገኝነት እንዲሁም የቤተሰብ ሀብት መብዛትና ማነስ ሴቶችና ወጣቶችን ለአላስፈላጊ መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች መሆናቸውን አስገንዝቧል፡፡

ቀደም ሲል የሁለቱንም ዓይነት የጥናት ግኝቶች ማስተዋል እንደተቻለው ስራ ማጣት ወደ አላስፈላጊ ድርጊቶች የሚገፋፉ ትልቅ ምክንያት ቢሆንም በይበልጥ ለአላስፈላጊ ነገሮች የሚጋለጡት ትንሽም ቢሆን የራሳቸው ገቢ ያላቸው መሆናቸውንም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የቤተሰብ ድህነትና በተቃራኒው በኢኮኖሚ አቅም ማደግ ለልጆች ወደ አላስፈላጊ ድርጊቶች መግባት ምክንያት መሆናቸውንም ያስረዳሉ፡፡

የClacherty (2003) ስራ አጥነትና ቤት አልባ መሆን እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅማቸው ከፍተኛ ከሆኑ ወላጆች መገኘት ለዚህ ችግር የነላ አስተዋፅየ እንዲኖራቸው ያደርጋል ያለው ፅንሰ ሀሳብም የሁለቱን ጥናት ግኝቶች የሚያጠናክር ነው፡፡

የኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ቤተሰቦች የተገኙ ልጆች ራሳቸውን በደህና ቤተሰብ ውስጥ ከሚኖሩት ጋር በማነፃፀር የበታችነት ስሜት ስለሚሰማቸው ራሳቸውን ለማግለልና በሚሰማቸው የበታችነት ስሜት የተነሳ ትምህርት በማቋረጣቸው ምክንያት ከሚደርስባቸው ስነልቡናዊ ጫና ለመሸሽ ሲሉ ወደ አላስፈላጊና ደባል ልምዶች/ሱሶች ይገፋፋሉ ካሉት Kettakamp(1954) እና Kimmel(1985) ሀሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡

ከዚህ በመነሳት ከላይ የተጠቀሱት ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ቢስተካከሉ ወጣቶችም ሆኑ ሴቶች ካልተገቡ ድርጊቶች ተቆጥበው የልማት አጋር ሊሆኑ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡

### 5.2.3. ስነ-ልቦናዊ ምክንያቶች

በጽሑፍ መጠይቁ በተሰበሰበው መረጃዎች መሰረት ሌላው ሴቶችና ወጣቶችን ወደ መጤ ባህሎችና ድርጊቶች የሚገፉ ሌላው ምክንያት ስነልቡናዊ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህም ስር በተመሳሳይ ያታ በመደፈርና ለዚህ ተግባር ተገፋፍቶ መግባት(3.1%)ና የራስን ባህል መናቅ(83.1%) ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዓይነታዊ የጥናቱ መረጃ እንደተገኘውም ያለ ትምህርትና ስራ መቀመጥ፣ ተስፋ መቁረጥ፣ በሰዎች ዘንድ ዘመናዊ መስሎ ለመገኘት መፈለግ፣ የራስን ባህል መናቅና አዳዲስ ነገሮችን ለመሞከር ያሉ ጉጉቶችና መነሳሳቶች ሴቶችና ወጣቶችን ወደ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲገቡ የሚያደርጉ ስነ- ልቦናዊ ምክንያቶች መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከመረጃዎቹ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ወጣቶችና ሴቶች በ Kenway & Bullen (2008) የተገለጸውን የእራስን ባህል ካለማወቅና አዳዲስ ነገሮችን በመሞከር ዘመናዊ መስሎ ለመታየት ከመፈለግ ጋር የተያያዘውን ፅንሰ ሀሳብ የሚጋራ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Illana(2008) በዝቅተኛ የትምህርት ዕድል፣ ያለ ትምህርት እና ሥራ በመቀመጥ ምክንያት በሚደርሰው ተስፋ መቁረጥና የሥነ-ልቦና ጫና የተነሳ ወጣቶች ወደ አልባሌ ተግባር ይገፋፋሉ ብለው ካስቀመጡት ፅንሰ ሀሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡

በመሆኑም በተመሳሳይ ያታ መደፈርና ወዚህ ድርጊት ተገፋፍቶ መግባትና፣ የራስን ባህል መናቅ፣ ያለ ትምህርትና ስራ መቀመጥ፣ ተስፋ መቁረጥ፣ በሰዎች ዘንድ ዘመናዊ መስሎ ለመገኘት መፈለግ፣ አዳዲስ ነገሮችን ለመሞከር ያሉ ጉጉቶችና መነሳሳቶች ሴቶችና ወጣቶችን ወደ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲገቡ የሚያደርጉ ስነ- ልቦናዊ ምክንያቶች እንደሆኑ ያስገነዝባል፡፡ከዚህ ውጪ በተለይ በተመሳሳይ ያታዎች መካከል የሚፈጸም የወሲብ ጥቃት ምክንያት ወጣቶችና ሴቶች በሚደርስባቸው የሥነ ልቡና ጫና ወደ አላስፈላጊ ድርጊቶች እንደሚገፋፉ ለመረዳት ተችሏል፡፡

### 5.2.4. ዓለማቀፋዊነት፣የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ መረቦች/ኢንተርኔት

መጠናዊ መረጃዎቹ እንደሚሳዩት 45.2%ቱ የማህበረሰብ ድረ-ገጽ /ፌስ ቡክና ቲውተር ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልፀው ከነዚህ ውስጥ 21.1%ቱ የወሲብ ነክ ምስል ፣ፅሁፍ ወይም የፍቅር ጥያቄ ቀርቦላቸዋል በተያያዘም የወሲብ ፊልሙን 28%ቱ በሞባይል በመላላክ እንዲሁም 17.8%ቱ ከኢንተርኔት እንደተመለከቱት መረጃው ያሳያል፡፡ይህ ሁኔታም ወጣቶችና ሴቶችን ላልተገቡ ባህሪያት መገፋፋት ምክንያት እንደሚሆን ያስረዳል፡፡

የጥናቱ ዓይነታዊ ግኝቶች እንዳሳዩት፤ በተለያዩ መንገዶች የሚሰራጩት የወሲብ፣የወንጀልና መሰል ፊልሞች፣ በሞባይልና በመረጃ መረብ /ኢንተርኔት የሚሰራጩ አላስፈላጊ የምስልና የፅሁፍ መልእክቶች፣ በሳተላይት ቴሌቪዥን የሚሰራጩ ወጣ ያሉ ፕሮግራሞችና መልእክቶች ወጣቶችና ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ድርጊቶች እንደሚመሩ አሳይተዋል፡፡ በሌላ በኩል ከውጪ የሚመጡ የሌላ ሀገር ዜጎችና ውጪ ቆይተው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን ይዘውት የሚመጡት አላስፈላጊ ልምድና ተግባር እንዲሁም የውጭ ባህልን እንደ ዘመናዊነት መቁጠር፤ ከአለማቀፋዊነት፣ የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ መረቦች ጋር በተያያዘ የሚነሱ፤ ወጣቶችና ሴቶችን ለአላስፈላጊ ባህሪ የሚዳርጉ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በተመሳሳይም በአንድ ወር ከአንድ ሳምንት ውስጥ በምናብ የተፈጠች ሴት በ"ፌስ ቡክ" ከደረሷት መልዕክቶች መረዳት የሚቻለው ቴክኖሎጂ በቀላሉ የተለያዩ አላስፈላጊ መልዕክቶችን ለመለዋወጥ የሚያስችል መንገድ በማመቻቸቱ ወጣቶችና ሴቶች ለማይገቡ ድርቶች ሊገፋፉ እንደሚችሉ ነው፡፡

የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎችም አለማቀፋዊነት፣ የመገናኛ ብዙሀንና የመረጃ መረቦች/ኢንተርኔት በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያስከትሉት ተፅእኖን አስቀምጠዋል፡፡

ዓለማቀፋዊነት የሀገሮችን ድንበር ክፍት እንዲሆን ባለው አስተዋፅያ ወጣቶች በነፃነት እንዲንቀሳቀሱና ከውጭ የሚመጡ ቁሶችንና ልምዶችን እንዲቀበሉ ምክንያት እንደሆናቸው llanna (2008) ገልጻዋለች:: በተያያዘም በመገናኛ ብዙሀን የሚተላለፉ የሙዚቃ ፊልሞች፣የታዋቂ ሰዎች ስብዕና፣ የአለባበስ ሁኔታ ፣የአኗኗር ዘይቤና የመሳሰሉት ሴቶችን በተለይ ወጣቶችን ወደ ግድያ ድብደባና አስገድዶ መድፈር የመሳሰሉ አላስፈላጊ ድርጊቶች እንዲገቡ ምክንያት መሆናቸውን underwood (2000) እና Glen(2003) አስገንዝበዋል፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው ከአለማቀፋዊነትና የመረጃ መረብ /ኢንተርኔት መስፋፋት፤ ሴቶችና ወጣቶች ወደ አላስፈላጊ ድርጊቶች እንዲገቡ ያለው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ መሆኑን ነው፡፡

### 5.2.5. የአላስፈላጊ ድርጊቶች መፈፀሚያ ቦታዎች መስፋፋት

ከመጠናዊ መረጃው ግኝት፤ 31.4% የጫትና ሺሻ ቤቶች፣ 50.3% የምሽት፣የቀንና የራቁት ፂፈራ ቤቶች፣ 5.9% የፊልም ማሳያ /ቪዲዮ ቤቶች እንዲሁም 5.4% የማሳጅ ቤቶች፤ ለሴቶችንና ወጣቶች ወደ አልባሌ ድርጊቶች መግባት ምክንያት መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የዓይነታዊ መረጃዎችም የጫትና ሺሻ ቤቶች፣ የምሽት፣የቀንና የራቁት ፂፈራ ቤቶች፣ የፊልም ማከራያና ማሳያ/ቪዲዮ ቤቶች፣ለየት ያለ ተግባር የሚፈፀምባቸው "ማሳጅ" ቤቶች፣ የተመሳሳይ ፆታ ግብረሰዶማዊያን መገናኛና ማዘውተሪያ ቦታዎች እንዲሁም የመኪና ላይ ወሲብና ጫት መቃሚያ ቦታዎች መስፋፋት ሴቶችና ወጣቶች ወደ አላስፈላጊ ድርጊቶች እንዲገቡ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡

በዚህም የተነሳ ቁጥራቸው እጅግ ከፍ ያሉ ወጣቶችና ተማሪዎች በተለያዩ ሱሶች እየተጠመዱና ላልተገባ ወሲብ እየተዳረጉ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የሚያሳየው የእነዚህ ቦታዎች መስፋፋት በማህበረሰቡ ላይ እያስከተሉት ያለው ተፅእኖ እጅግ ከፍ ያለ መሆኑን ነው፡፡

### ሀ. የሱስ አስያዥ ዕፆች መጠቀሚያ ቤቶች (የጫት፣ ሺሻ፣ ሀሺሽ፣ አልኮልና ሌሎች) መስፋፋት

ከላይ እንደሚታየው የጫትና ሺሻ ቤቶች መስፋፋት ለወጣቶችና ሴቶች ወደ አላስፈላጊ ነገሮች መግባት አንዱ ምክንያት መሆኑን የገለፁት 31.4% የሚሆኑት የመጠናዊ መረጃ ሰጪዎች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ይህንን ሀሳብ በተጋሩት የዓይነታዊ መረጃ ሰጪዎችም፤ የጫትና ሺሻ ቤቶች በመስፋፋታቸው እጅግ በርካታ ታዳጊዎች በተለያዩ አነቃቂ እፆች መጠመዳቸውና ይህም ለአጠቃላይ ማህበረሰባዊ ቀውስ መዳረግ ምክንያት መሆኑ ተገልጿል፡፡

ይህን ሀሳብ የሚጋሩት ሥዩም (1996) በጥናታቸው አነቃቂ ዕፆችን በመጠቀምና በማዘዋወር የወጣቶች ቁጥር ከፍ ያለ መሆኑን ሲገልፁ፤ ኃይሉ (2002)ም የጫት፣ሀሺሽ፣ አልኮልና የትምባሆ ሱስ በከፍተኛ ሁኔታ በወጣቱ ዘንድ ሀይማኖትና ባህል ሳይገድበው በመስፋፋት ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል፡፡ በሌላ በኩል በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በ2002 እና በ2003 የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ጫትና የአልኮል መጠጦች በወጣቶችና ሴቶች ከመለመዳቸውም ባሻገር በትምህርት ተቋማትም ሳይቀር እየተስፋፋ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም በጥናቱ ላይ ከተገኙት ውጤቶች ጋር ቁርኝት ያለውና የግኝቶቹም እውነተኛነት ተጨባጭ የሚያደርግ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት ለመረዳት የሚቻለው፤ በከተማዋ ውስጥ የሱስ አስያዥ ዕፆች መጠቀሚያ ቤቶች እየተስፋፉ መምጣት ወጣቶችና ሴቶችን ወደ አልተገቡ ባህሪያት እንዲገቡ እየገፋፏቸው መሆኑን ነው፡፡

### ለ. የምሽት፣የቀንና የራቁት ጭፈራ ቤቶች መበራከት

ወጣቶችና ሴቶች ትርፍ ጊዜያቸውን በምሽት፣የቀንና የእርቃን ጭፈራ ቤቶች እንደሚያሳልፉ 50.3% ያህሉ የመጠናዊ መረጃ ሰጪዎች የሰጡት ምላሽ ያሳያል፡፡ የዓይነታዊ መረጃው እንደሚያሳየውም በአሁን ሰዓት የቀን፣ የሌሊትና የእርቃን ጭፈራ ቤቶች በከተማው ውስጥ እየተስፋፉ መምጣታቸው ወጣቶችና ሴቶች በነዚህ ቦታዎች በመገኘት ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውንና ማንነታቸውን እያጡ መሆኑን አመላክቷል፡፡ በተጨማሪም ከልጅ እስከ አዋቂ ወደነዚህ ቤቶች በቡድን በቡድን እየሆኑ በመሄድ መጠጣት፣ ማጨስና መጨፈርን የተለመደ ተግባራቸው ማድረጋቸውን መረጃዎቹ ይጠቁማሉ፡፡

ይህ በግልጽ እንደሚያሳየው ወጣቶችና ሴቶች በርካታ ስራዎች ሊሰሩባቸው የሚችሉበትን ወርቃማ ጊዜ በነዚህ አልባሌ ቦታዎች በማሳለፍ እንደሚያባክኑና ለሌሎች ሱሶችም ተጋላጭ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው።

### ሐ. የወሲብና ሌሎች ያልተገቡ ፊልሞች የሚገኙባቸው ቤቶች መስፋፋት

የወሲብና ሌሎች ያልተገቡ ፊልሞች የሚገኙባቸው ቤቶች መስፋፋት፤ ወጣቶችና ሴቶች በቅርብና በቀላሉ ስለሚያገኙዋቸው እና ሁኔታውም ስለሚጋብዛቸው፤ አዘውትሮ የማየት ልምድ እንዲያዳብሩ አድርጓቸዋል። ይህንንም 5.9% የሚሆኑት የመጠናዊ መረጃ ሰጪዎች ምላሽ ሲያሳይ፤ የዓይነታዊ መረጃው ውጤትም በፊልም ማሳያ /ቪዲዮ ቤቶችና በተለያዩ መንገዶች የሚሰራጩት ያልተገቡ ፊልሞች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መምጣቱን አመላክቷል። እነዚህን ፊልሞች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ያሉ ልጆች እንዳይመለከቷቸው ማሳሰቢያ የሚሰጥ ቢሆንም፤ መተላለፊያ መንገዶቹ ለሁሉም ሰው ክፍት በመሆናቸው፤ ህጻናትና ወጣቶች ይመለከቷቸዋል። ህፃናትና ወጣቶቹ ባዩአቸው ነገሮች ሳቢያም፤ ለሱስ ተገዢ፣ ወሲብና ወንጀል ፈጻሚ እንደሚሆኑ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

በሌላ በኩል Glen (2003) በጥናቱ፤ በአሜሪካን ሀገር ከ1994 ጀምሮ በወጣቶች የተፈጸሙ የግድያ፣ድብደባና፣አስገድዶ መድፈር ወንጀሎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱንና ለወንጀሎቹም መስፋፋት ምክንያቱ፤ በዘፈን ክሊፖችና ፊልሞች የሚተላለፉ መልዕክቶች ባሳደሩት ተፅዕኖ ሳቢያ መሆኑን አንስቷል። ይህም ሀሳብ በዚህ ጥናት ከተገኘው ውጤት ጋር ተዛማጅነቱ የጎላ ነው።

በመሆኑም ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው የወሲብና ሌሎች ያልተገቡ ፊልሞች የሚገኙባቸው ቤቶች መስፋፋት ህፃናትን፣ ወጣቶችንና ሴቶችን ለአልባሌ ድርጊቶች ይበልጥ ተጋላጭና ተገዢ እንደሚያደርጋቸው ነው።

### መ. ለየት ያሉ ተግባራት የሚፈጸምባቸው የመታሻ /ማሳጅ ቤቶች መበራከት

በከተማዋ ውስጥ ባሉ ማሳጅ ቤቶች የሚሰጠው የመታሸት አገልግሎት ከተዝናኖትም ሆነ ከጤና አንጻር ያለው ጠቀሜታ አሌ የሚባል አይደለም። ይሁን እንጂ በተለየ ሁኔታ ለምርጫ የሚቀርቡት ያልተገቡ ድርጊቶች አገልግሎት ግን፤ ተገልጋዩንም ሆነ ህብረተሰቡን ወደ አላስፈላጊና ከባህልና ስነምግባር ውጭ ለሆነ ባህሪ እየዳረጉት ይገኛሉ።

ከዚህም ለመገንዘብ የሚቻለው የነዚህ አገልግሎት መስጫ ቤቶች በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች እየተስፋፉ መምጣት፤ በውስጡ የሚፈጸሙትም አልባሌ ተግባራት ቁጥጥር ካልተደረገባቸው በስተቀር ወጣቶችና ሴቶችን ላልተገባ የወሲብና ወሲብ ነክ ድርጊቶች ተጋላጭ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋፅየ ማድረጉን ነው፡፡

### ሠ. በመኪና ውስጥ የሚፈጸሙ ጫት የመቃምና የወሲብ ድርጊቶች መስፋፋት

በጥናቱ የተገኘው ሌላው የአልባሌ ድርጊቶችን መስፋፋት የሚያሳየው አዲስ ግኝት በመኪና ውስጥ የሚፈጸሙ ጫት የመቃምና የወሲብ ድርጊቶች መስፋፋት ሲሆን፤ ይህም በምልከታ ወቅት የቡድኑ አባላትን ትኩረት የሳበ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በቦሌ በሚገኙ ትልልቅ ህንፃዎች፣ ባሮችና ሬስቶራንቶች ስር፣ በመንገዶች ግራና ቀኝ፤ እንዲሁም የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን በማጨናነቅ በመኪና ውስጥ በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን በመሆን ጫት መቃም፣ ወሲብ መፈጸምና ሌሎች ያልተገቡ ድርጊቶች ሲከናወኑ ታይተዋል፡፡ በዚህ ድርጊት ተሳታፊ የነበሩት በአብዛኛው ህፃናት ወጣቶች ቢሆኑም፤ በዕድሜ የገፉ ሴቶችና ወንዶችም ተዋናይ ነበሩ፡፡

ከዚህ ጥናት  ግኝት ለማወቅ እንደተቻለው፤ ምንም እንኳን ህገወጥ ወሲብ በተለያዩ ቦታዎች እንደሚፈጸም ቢታወቅም በተለይ በመኪናዎች ውስጥ የሚደረገው ድርጊት ለቁጥጥር የማይመችና በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ ያለ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የዚህ አላስፈላጊ ድርጊት መስፋፋት ይበልጥ ተጠቂ የሚያደርገው ከትምህርት ቤት የሚወጡ ህፃናትና ወጣት ተማሪዎችን ነው፡፡ ይህ በመኪናዎች ውስጥ የሚፈጸም አላስፈላጊ ድርጊት ወጣቶች፣ ሴቶችና ህብረተሰቡን ለአልባሌ ባህርያት የሚጋለጥ ድርሻው ከፍተኛ እንደሆነ የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ያልተገቡ የአላስፈላጊ ድርጊቶች ማስፋፊያ ቦታዎች መበራከት በወጣቶችና ሴቶች ላይ እንዲሁም በህብረተሰቡ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው ቀውስ ከፍተኛ መሆኑንም ከመረጃዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህ ድርጊት አሁን ባለበት ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ ሀገር ተረካቢ የሆነውን ትውልድ በእጅጉ የሚጎዳና ከፍተኛ ሀገራዊ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም፡፡

### 5.2.6. የፖሊሲ፣የህግ ክፍተትና ተፈፃሚነት መላላት፣

የጥናቱ መረጃ፤ አላስፈላጊ ድርጊቶችንና የድርጊቶቹ መስፋፊያ ቦታዎች የሚከለክልና የሚገታ ህግ በበቂ አለመኖሩንና በወንጀል ህጉ የተደነገጉትንም ቢሆን፤ በአግባቡ ማስፈጸም

ላይ ክፍተት እንዳለ ያሳያል፡፡ በዚህም የተነሳ በከተማዋ ውስጥ የጫትና ሺሻ ቤቶች፣የቀን፣የምሽትና የራቁት ጭፈራ ቤቶች እና ለየት ያሉ ተግባራት የሚከናወኑባቸው ማሳጅ ቤቶች እየተበራከቱ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

በተለይ ጫትና ሺሻ በዓለም አቀፍ የአደገኛ ዕፆች ዝርዝር ውስጥ አለመካተትና በሀገራችንም የወንጀል ህግ አለመካተት የነዚህ አነቃቂ ዕፆች ተጠቃሚዎችና መጠቀሚያ ቦታዎች መበራከት አስተዋፅዖ እያደረገ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

በሌላ በኩል የአልኮል መጠጦችን እድሚያቸው 18 ዓመት ላልሆኑ ታዳጊ ወጣቶች መሸጥ በህግ የተከለከለ ቢሆንም፤ ከአፈፃፀም መላላት የተነሳ ግን ተግባር ላይ ሲውል አይታይም ፡፡ይህ በመሆኑም ታዳጊ ወጣቶች እንዲጠፉ፣ሱሰኝነት እንዲስፋፋና ወንጀለኝነትና ህገ-ወጥነት በእጅጉ እንዲበራከት ምክንያት እንደሆነ የተገኘው መረጃ አመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተነሱት በህግ መላላትና ክፍተት ምክንያት እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች፣ለአልባሌ ላልተገቡ ድርጊቶች መበራከትና ወጣቶችና ሴቶችም በችግሩ ውስጥ እንዲዘፈቁ ምቹ መደላድል ፈጥሯል፡፡

## 5.3. መጫ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያሳድሯቸው ተፅዕኖዎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር መጫ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያሳድሩት ፣ ማህበራዊና ስነልቡናዊና ኢኮኖሚያዊተፅዕኖዎች ተተንትነዋል፡፡

### 5.3.1. ማህበራዊ ተፅዕኖዎች

የጥናቱ መጠናዊ ግኝት እንዳሳየው፤ ዜጎች የዕፅና አልኮል መጠጥ ተጠቃሚ በመሆናቸው በራሳቸው ከሚደርስባቸው ማህበራዊ ችግሮች፤ 31.1%፣29.1% እና 11.4% የሚሆኑት ተሳታፊዎች የቤተሰብ መፍረስ ፣ የጤና ችግር እና ከስራ መፈናቀል በተከታታይ፤ እንደሚደርስባቸው ከሰጡት ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 27.4% በሚሆኑ ተሳታፊዎች፤ ስደት፣ ወደ ጎዳና መውጣት፣ ሴተኛ አዳሪነትና የጥገኝነት ባህል መዳበር እንደሚያጋጥማቸው ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፤ በአላስፈላጊ ሱሶች ተጠቂ የሆኑ ዜጎች በማህበረሰቡ፤ የመገለል፣ የመጠላት፣ በወንጀል መጠርጠርና የበታች ተደርጎ የመቆጠር ችግር እንደሚደርስባቸው 55.5% በሚሆኑ ተሳታፊዎች ተገልጿል፡፡

የዓይነታዊ መረጃ ግኝትም የሚያመላክተው የዕፅና የአልኮል ተጠቃሚነት በርካታ ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን እንደሚያስከትል ነው፡፡ የዕፅና የአልኮል ተጠቃሚዎች ከማህበረሰቡ የመገለል፣ በወንጀል ለመጠርጠር፣ ለፀብ አጫሪነት፣ ለመኪናና ሌሎች አደጋዎች እንዲሁም ለቤተሰብ መፍረስና አለመስማማት ችግር እንደሚዳረጉ ተነስቷል፡፡ በሌላ በኩል ከዕፅና አልኮል አጠቃቀም መንገድ ጋር በተያያዘ፤ ተጠቃሚዎቹ በጋራ በሚጠቀሙባቸው ቁሶች ምክንያት ለኤችአይቪ/ኤድስና ሌሎች መሰል ተላላፊ በሽታዎች እንደሚጋለጡ እና በዕፅ ተጠቃሚነት የተነሳ ግለሰቦች ለጥርስ ህመም፣ለአፍ ኢንፌክሽን፣ ለአፍና አንጀት ካንሰር እንደሚዳረጉ ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም ለትምህርት ማቋረጥ፣ ለውጤት መቀነስ፣ እንዲሁም ለጎዳና ህይወት መዳረግ እና የመሳሰሉት ችግሮች እንደሚዳረጉ መረጃው ያሳያል፡፡

ከሱሰኝነት በተለየ በሌሎች መጤ ልማዳዊ ድርጊቶች ማለትም በግብረሰዶም፣ በግለኝነት አስተሳሰብ፣ ባልተገባ የአለባበስ ሁኔታና በመኪና ውስጥ በሚፈጸሙ የወሲብ ድርጊቶች ውስጥ የሚሳተፉ ህፃናት፣ወጣቶችና ሴቶች ባህልና ወግን በሚጣረሱ ድርጊቶች በመሰማራታቸው፤ በህብረተሰቡ ጥላቻና መገለል ይደርስባቸዋል፡፡

የዕፅ ተጠቃሚ ተማሪዎች ውጤት ዝቅተኛ መሆኑን እና ሱስ አስያዥ ዕፆችም በመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ Bradon(2002) ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም Bradon(1999) እና Grove(2002) የዕፅ ተጠቃሚዎች ለተለያዩ አደጋዎች፣ ለሞት፣ ለልቅ ወሲብ ተጋላጭ በመሆናቸው ብቃት ማነስና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ውስጥ እንደሚገቡ ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም የሱስ ተገዥ የሆኑ ሰዎች፤ ተደባዳቢ፣ አጉራዘለል፣ አስገድዶ ደፋሪ፣ህገወጥ ወሲብ ፈጻሚና አዋኪዎች እንደሚሆኑ ደግሞ Education center for alchol and other abuse and violence prevention(2010) ገልጿል፡፡ ከዚህም ሌላ The Ethiopian Public Health Association…(2002) በዚህ ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች ማህበራዊ ተሳትፎ እንደሌላቸውና ራሳቸውን እንደሚያገለሉ፣ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ሰላምና መረጋጋት ጠንቅ እንደሚሆኑ አሳይቷል፡፡

ከላይ ለመመልከት እንደተቻለው በመጤ ባህሎችና ያልተገቡ ልማዳዊ ድርጊቶች ተጠቂ መሆን፤ ለጤና ችግር፣ለራስም ሆነ ለቤተሰብ መረጋጋትና ሰላም ማጣት፣ እንዲሁም የማህበረሰቡን ማህበራዊ ተቀባይነት፣ ጥበቃና ክብካቤ ያሳጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተሰማሩበት መስክ ውጤታማ ሆኖ ለመስራት አለመቻልና ስራም ሆነ ትምህርት ለመጥላትና ማቋረጥ፣ በመጨረሻም ለተስፋ መቁረጥ እና ራስን ለማጥፋት ይዳርጋል፡፡ በዚህም ሳቢያ የቤተሰብ መፈናቀልና መበተን ይደርሳል፡፡ ይህ ሁኔታም በቤተሰብ፣

በማህበረሰብ ሆነ በሀገር ደረጃ ሁለንተናው የተሟላና መልካም ስብዕና ያለው ዜጋ ግንባታ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

### 5.3.2. ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች

በመጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የተጠመዱ ሴቶችና ወጣቶች የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች እንደሚደርሱባቸው በጥናቱ የተገኙ መጠናዊ መረጃዎች ያሳያለ፡፡ በዚሁ መሠረት 60.7%ቱ የአልኮል መጠጦችን፤ 28.4% ደግሞ የተለያዩ አነቃቂ እፆችን እንደሚጠቀሙ ከመረጃው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይም ከዓይነታዊ ግኝቶች ለመረዳት እንደተቻለው ሴቶችና ወጣቶች በምሽትና በቀን ጭፈራ ቤቶች ለመዝናናት ከፍ ያለ የገንዘብ ወጪ እንደሚያወጡ የተገኙት መረጃዎች ያሳያለ፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ በነዚህ ሱሶች የተጠመዱ ሴቶችና ወጣቶች ለዚህ ሱሳቸው ማስታገሻ የሚሆን ገንዘብ ካጡ ወደ ወንጀል፤ ስርቆትና ወሲብ ወደ መፈጸም እንደሚያመሩ ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም በሱስ መጠመድ ምክንያት ስራ አቋርጦ መሄድ፣ ስራ መፍታትና የመሳሰሉት ቀጥተኛ ኢኮኖሚያዊ ጫና ለሚስከትሉ ችግሮች እንደሚዳርጉ ታውቋል፡፡

በሌላ በኩል በሱስ ውስጥ የሚገኙ ሴቶችና ወጣቶች እነዚህን ሱስ አስያዥ ዕፆች ለመጠቀም፣ የአለባበስ ፋሽን ለመከተል፣ በቀን፣ በማታና በእራቁት ጭፈራ ቤቶች ለመዝናናት እና ለመሳሰሉት ድርጊቶች መፈጸሚያ ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ እንደሚጠይቅ መረጃው አሳይቷል፡፡ በዚህ መሰረት ከመረጃው ለመገንዘብ እንደሚቻለው፤ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኝ ሰው ለጫትና ሲጋራ ወጪ በአማካኝ በቀን ብር 130 /አንድ መቶ ሰላሳ ብር ያስፈልጋል/ ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአንድ የምሽትና የእርቃን ጭፈራ ቤት መስተንግዶ ለመግቢያ፣ ለአልኮል መጠጥ፣ለሺሻ፣ሲጋራ፣ ለሽልማት በቀን በትንሹ ለአንድ ሰው ከብር1500 - 2000 (ከአንድ ሺ አምስት መቶ እስከ ሁለት ሺ ብር) እንደሚያስፈልግ በምልከታ ወቅት ታይቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በምሽትና እራቁት ዳንስ ቤቶች ለሚደንሱ ሴቶች በወር ከብር 3000 — 14000 (ከሦስት ሺ እስከ አስራ አራት ሺ ብር) የሚደርስ ደሞዝ በነፍስ ወከፍ እንደሚከፈላቸው ታውቋል፡፡

የዕፅና አልኮል ሱሰኝነት የሚያስከትለውን የኢኮኖሚ ችግር የተለያዩ ጥናቶች ያሳያለ፡፡ የኢትዮጵያ ጤና አገልግሎት ማህበር ዓመታዊ ኮንፈረንስ ሪፖርት (2006) ከዕፅ መጠቀም ጋር በተያያዘ የሚመጡ አካላዊና አዕምሮአዊ የጤና ችግሮችን ለመታከም የሚወጣው ገንዘብ በግለሰቦችም ሆነ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ቀውስ እንደሚያስከትል

አመልክቷል። በተጨማሪም በተለያዩ ዕፅና አልኮል መጠጦች የተነሳ በበሽታና ሞት ከአምራችነት የሚቀነሱ ዜጎች በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የጎላ ተፅዕኖ እንደሚያሳርፉ "questions about smoking Tobacco and health" በሚል የወጣው ጥናታዊ ፅሁፍ ያሳያል። በተጨማሪም ለሺሻ፣ ጫትና ለመሳሰሉ አደንዛዥ ዕፆች የሚወጣውን የግንዘብ ወጪ ከፍተኛ መሆኑን አስመልክቶ የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጥናት (2003) አመላክቷል።

የዚህ ጥናት ግኝትም ሆነ ዓለምአቀፋዊ ጥናቶቹ የሚያሳዩት፤ ለተለያዩ ዕፆችና የአልኮል መጠጦች ተጋላጭ መሆን፤ በግለሰብ፣ በህብረተሰብም ሆነ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ነው። ይህም በሱስ ውስጥ ያሉ ዜጎች የሱስ ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚያወጡት ወጪ፣ ከሱሰኝነት ጋር በተያያዘ ለሚመጣ የጤና እክል ህክምና ወጪ፣ በህመም ምክንያት በሚከሰት የምርታማነት መቀነስና በዚህ የተነሳ በሚደርስ የዜጎች ሞት ከተማዋ ብሎም ሀገሪቱ አምራች ዜጎቿን ታጣለች። ይህ ሁኔታም በግለሰብ፣ በቤተሰብም ሆነ በሀገር ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ያሳድራል።

በተጨማሪም በምሽትና እራቁት ጭፈራ ቤቶች፤ በተገልጋዮች በአንድ ምሽት ለመዝናናትና ለሽልማት በሚል እየተጎዘጎዘ የሚጠፋው የግንዘብ መጠን፤ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የሀገር ሀብት ነው።በመሆኑም ይህ ለአንድ ምሽት የሚወጣው ገንዘብ ወደ ወርና ዓመት ቢተመን፤ ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ትልቅ ግብዓት በመሆን ትልልቅ የልማት ስራዎችን ማንቀሳቀስ የሚያስችል ነው። ከዚህም በላይ ለሴት ጨፋሪዎች የሚከፈለው አማላይ ወርሃዊ ደመወዝ፣ ፤ ለሌላ የልማት አገልግሎት ቢውል ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ፤ይህ ከፍተኛ የክፍያ መጠን ሌሎች ዜጎች በእውቀት ከመሰልጠንና በልማት ስራ ላይ ከመሰማራት ይልቅ፤ ወደነዚህ አልባሌ ስራዎች እንዲሳቡ ስለሚያደርግ፤ በሀገር ኢኮኖሚና የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያስፈልገውን የሰው እውቀትና ጉልበት ያሳጣል። ይህም ሀገሪቱ ልታገኝ የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያቀጭጭ መሆኑን ያሳያል።

### 5.3.3. ስነ-ልቡናዊ ተፅእኖ

በመጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች መጠመድ ምክንያት በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚደርሱትን የተለያዩ የስነ-ልቡና ችግሮች አስመልክቶ፤ 44.4% የሚሆኑት የመጠናዊ መረጃ ሰጪዎች ተስፋ መቁረጥ፣ 17.3%ቱ ድብርትና ጭንቀት፣ 9.1%ቱ ራስን ማጥፋት፣ እንዲሁም 8.7%ቱ ስንፍና፣ ስራ

መጥላት፣ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ወሲብ ለመፈፀም መነሳሳትና የመሳሰሉት ችግሮች እንደሚደርሱባቸው አመላክተዋል፡፡

ከዓይነታዊ መረጃው የተገኘው ግኝትም የሚያሳየው፤ ወጣቶችና ሴቶች በነዚህ ያልተገቡ ድርጊቶች ማለትም፤ የሱስ አምጪ ዕፆች ጫት፣ ሀሺሽ፣ የአልኮል መጠጥ ተጠቃሚነትና ግብሰዶማዊነት/የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ጥቃት ምክንያት ከፍተኛ የስነልቡና ችግር እንደሚደርስባቸው ነው፡፡ በዚህ ችግር ውስጥ የገቡት ወጣቶችና ሴቶች፤ በራስ መተማመንን ማጣት፣ ራስን ዝቅ አድርጎ ማየት፣ በአእምሮ ማዘዝ አለመቻል፣ ከንቱ ቅዠት ውስጥ መግባት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ትምህርት መጥላት ወይም ማቋረጥ፣ ድብርት፣ የበታችነት ስሜት፣ ግብረሰዶማዊ መሆንና ራስን ማጥፋት እንደሚደርስባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህንንም Center for Alcchol and other drugs abuse and violence prevention (2010) ሲያጠናክር ተማሪዎች የዕፅና የአልኮል ተጠቃሚ ሲሆኑ በትምህርታቸው እንደሚደግሙና እንደሚያቋርጡ ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም The Ethiopian Public Health Association Annual Conference (2002) ደግሞ ለብቸኝነት እንደሚዳረጉ በሚደርስባቸውም የስነ ልቡና ችግር የተነሳም የተረጋጋ ህይወትም ሆነ ሰላም እንደሌላቸውና ይኸውም በቤተሰብና አካባቢያቸውም እንደሚንጸባረቅ ገልፏል፡፡

እነዚህ ጥናቶች ያነሱት ንድፈ ሀሳብ፤ ከላይ የተገለጹትን በመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርቶች ሳቢያ ወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚደርሰውን የስነ ልቡና ችግር ከዓለም አቀፉ ሁኔታ ጋር ተጨባጭ የሚያደርግ ነው፡፡

ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው መጤ ባሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በከተማዋ የሚገኙ ወጣቶችና ሴቶችን ለአልባሌ ተግባራት እንደሚዳርጓቸውና በሂደቱም የስነ ልቡና ተፅዕኖ እንደሚያደርሱቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ስነ ልቡናው የተጎዳ ዜጋ ደግሞ ለራሱ፣ ለቤተሰቡም ሆነ ለህብረተሰቡ ከሚሰጠው አገልግሎት ይልቅ ሸክም ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡

በተጨማሪም በመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በመጠመድ ሳቢያ የከተማዋ ወጣቶችና ሴቶች ለአህምሮ መዛባት ይዳረጋሉ፡፡ የተለያየ ስምና ባህሪ ያለው የአእምሮ መዛባትም በሰው ልጅ ጤናማ የዕለት ከዕለት ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ችግር ውስጥ የገቡ ዜጎችም ለራሳቸው፣ ለቤተሰብም ሆነ ለሀገር ከሚሰጡት አገልግሎትና ጠቀሜታ ይልቅ ሸክም ይሆናሉ፡፡ይህ የአምራችነት ሀይልን

የሚሰልብ የስነልቡና ችግር ከፍተኛውን የማህበረሰብ ቁጥር በያዙ ወጣቶችና ሴቶች ላይ ሲደርስ ደግሞ በሀገር ምርትና ምርታማነት ላይ የሚያስከትለው ውድቀት ከፍተኛ ነው።

### 5.3.4. የፀጥታ ተፅዕኖ

በመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በመጠመድ ምክንያት ወጣቶችና ሴቶች በአካባቢያቸው ሊያደርሱት ስለሚችሉት የፀጥታ ተፅዕኖ በተመለከተ የጽሑፍ መጠይቅ ተሳታፊ ከሆኑት መካከል 35.4%፣ 58.2% እና 54.2%ቱ በቡድን ድብድብ፣ በአስገድዶ መድፈር ድርጊቶች፣ በስርቆትና አካባቢን በሚያውኩ ድርጊቶች ላይ ይሳተፋሉ በማለት በቅደም ተከተል አስቀምጠዋል።

በተጨማሪም በቃለመጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካፋይ ከነበሩ ተሳታፊዎችና በተሳትፎአዊ ምልከታ ወቅት በተገኘው መረጃ መሰረትም ጠጥተው የሰከሩ ወጣቶች እንደሚደባደቡና አካባቢን እንደሚያውኩ የታወቀ ሲሆን፤ በተጨማሪም በጫት ቤት ውስጥ የነበሩ ተስተናጋጆች የተለያዩ የወንጀል ወሬዎችን ሲያወሩ ተደምጠዋል።

ይህም ሀሳብ በTom (1996) እና በS.Gebre (1996) ጥናቶች፤ የአልኮል መጠጥ ወይም ሱስ አስያዥ ዕፆች ተጠቃሚዎች በከፊል አልያም ከዚያ በላይ አስተሳባቸው ሊዛባ ስለሚችል፤ በዚህም የተነሳ ከቀላል እስከ አደገኛ ወንጀሎች እንደሚፈጽሙ ከተጠቀሰው ሀሳብ ጋር የሚዛመድ ነው።

በዚህም መሰረት በተለያዩ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች መጠመድ በግለሰብም ሆነ በሀገር የፀጥታና መረጋጋት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳው ለማወቅ ይቻላል።

# 6. ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ

## 6.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ወጣቶች ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖዎች ወይም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቡናዊና የፀጥታ ቀውሶችን ማጥናትና ለችግሮቹ የመፍትሄ ሀሳብ ማመንጨት ነው።በዚህም መሠረት በመሠረታዊ ጥያቄዎቹ የመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ምንነት፣ ለመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡ ምክንያቶችና እነዚህ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያደርሷቸው ተፅዕኖዎች ተዳሰዋል።

ለጥናቱ የናሙና አመራረጥ መነሻ ሣይንሳዊ የስሌት ዘዴን በመጠቀም ከአስሩም ክፍለ ከተሞች 33 ወረዳዎች ዕድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመከተል፤ እንዲሁም 3000 የጽሑፍ መጠይቅ ተሳታፊዎች ስልታዊ የአጋጣሚ ናሙና ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል።

በተጨማሪም ለጥናቱ የሚፈለጉትን ተሳታፊዎች ታሳቢ በማድረግ በተመረጡት ቤቶች ውስጥ እድሜያቸው ከ15-29 ዓመት የሆኑ ወጣት ሴቶችና ወንዶች እንዲሁም ከ29 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶች የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

የመረጃውን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ የተለያዩ አላማ ተኮር የአይነታዊ መረጃ አሰባሰብ ስልቶች ማለትም የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ቃለ መጠየቅና ተሳትፎአዊ ምልከታ ተደርጓል።

በመጨረሻም መረጃዎቹ ተሰብስበው በየመልክ መልካቸው በመደራጀት፤ ወደ ኮምፕዩተር እንዲገቡ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት የመጠናዊና ዓይነታዊ ግኝቶቹ ተጣምረው ትንታኔው በገለጻ ዘዴ ቀርቧል። በትንታኔው ትኩረት ከተሰጠባቸው ግኝቶች/ውጤቶች ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

1. በሴቶችና ወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉት መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ሱስ አስያዥ ዕጾች(ሺሻ፤ሀሺሽ፤ጫት፤መጠጥና የመሳሰሉትን) እና የአልኮል መጠጦችን መጠቀም፤የቀን፣ የምሽትና የእርቃን ሜዳራ ቤቶች መጠቀም፣ ፣ግብረሶዶማዊት፣ ያልተገቡ ድርጊቶች በሚፈጸሙባቸው መታሻ/ማሳጅ ቤቶች መጠቀም፤የግለኝነት አስተሳሰብ፤ያልተገቡ የአለባበሰስ ሁኔታዎች መሆናቸው ታውቋል።

እነዚህ መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በከተማዋ ወጣቶችና ሴቶች በስፋት እየተፈጸሙና ለቀውስ እያጋለጧቸው መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በተለይም ከ20- 24 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወንድና ሴት ወጣቶች ለችግሩ የበለጠ ተጋላጭ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ዕድሚያቸው ከ29 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶች ለነዚህ ችግሮች ተጋላጭነታቸው የጎላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

2. ሴቶችና ወጣቶችን ለመጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጧቸው ምክንያቶች ፤ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቦናዊ ፤ ዓለማቀፋዊነት፣የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ መረቦች/ኢንተርኔት መስፋፋት፤የአላስፈላጊ ድርጊቶች መፈፀሚያ ቦታዎች መስፋፋት፤የፖሊሲና የህግ ክፍተትና ተፈፃሚነት መላላት መሆናቸውን የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡
3. መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ፤ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቡናዊ፤ እና የፀጥታ ተፅእኖዎች እንደሚያሳድሩ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡

## 6.2. የመፍትሔ ሀሳቦች

ይህ ጥናት መጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች፣በተለይም በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያስከትሏቸውን አሉታዊ ተፅዕኖዎች በመዳሰስ የመፍትሔ ሀሳቦችን ለማቅረብ ይረዳ ዘንድ የተካሄደ ነው፡፡ ስለሆነም በጥናቱ መሠረት የታዩትን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

- ሱስ አስያዥ እጾች በወጣቶችና ሴቶች ኢኮኖሚ፤ማህበራዊ ጉዳይ እና ሥነልቦና ላይ እያደረሱ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ስለዚህ ሀገር ተረካቢ ለሆነው ትውልድና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት ጫትና ሺሻን ከተከለከሉ አደገኛ እጾች ዝውውር ውስጥ በማካተት ማዘዋወር፣መሸጥና መጠቀም ህጋዊ ክልከላ የሚደረግበት መንገድ ቢመቻች፤
- አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ወጣቶችና ሴቶችን ለአላስፈላጊ ባህሪያትና ተግባራት እያጋለጡ ያሉት የጫትና ሺሻ መሸጫ ቤቶች፣ በመኖሪያና በትምህርት ተቋማት አካባቢ በስፋት እየተከፈቱ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ እነኝህ የጫትና ሺሻ መሸጫ ቤቶች ከመኖሪያና ከትምህርት ተቋማት አካባቢ ፍጹም ተለይተው በተወሰነላቸው

ገለልተኛ ቦታ ብቻ የሚሠሩበት መንገድ በሕግ/ደንብ ቢቀመጥና አሁን በሥራ ላይ ያሉትም ቢሆኑ፣ ከነዚህ አካባቢዎች በተቻለ ፍጥነት እንዲነሱ ቢደረግ፤

- ወጣቶችና ሴቶችን ለመጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች እያጋለጡ ያሉት የቀን፤ የማታና የእርቃን ጭፈራ ቤቶች እንዲሁም መጠጥ ቤቶች ላይ የዕድሜ ገደብ ቢጣልባቸውም ተፈጻሚነታቸው ላይ ክፍተት እንዳለባቸው ታውቋል፡፡ ስለሆነም አፈጻጸሙን አስመልክቶ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማረግ ቀጣይነት ያለው እርምጃ ቢወሰድ፤
- ከኢትዮጵያዊነት ባህልና ስነ-ምግባር ወጣ ያሉ ተግባራት በሚከናወንባቸው ቦታዎች ለሚገቡ የውጭ የቱሪዝም ዘርፍ ተገልጋዮችም ሆነ ግልጋሎት ሰጪዎች የውጪ ዜጎች ሆነው በተለየ የመስተናገጃ ቪዛ ብቻ ቢስተናገዱ፣
- ከተመሳሳይ ዖታ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ከእምነት፣ከባህልም ሆነ ከማህበራዊ ህይወት ጋር መልካም ተዛምዶና በህብረተሰቡም ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ነው፡፡ ድርጊቱ በዚህ ከቀጠለ ደግሞ መጪውን ትውልድ ለከፍተኛ ቀውስ የሚዳርግና የትውልድን ቀጣይነት የሚፈታተን ነው፡፡ በመሆኑም በችግሩ ዙሪያ የማህበረሰብ ንቅናቄ መድረክ ተፈጥሮ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርትና ውይይት ቢደረግ፤
- ከተመሳሳይ ዖታ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጽሙ ግለሰቦች የምክር አገልግሎት የሚያገኙበትና ከዚህ ቀውስ የሚወጡበት ሁኔታ ቢመቻችና ይህን ተግባር ከመፈፀም በማይቆጠቡት ላይ ግን፤ በተቀመጠው ህግ መሠረት እርምጃ ቢወሰድ፤
- ለመጠ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች መስፋፋት እንዲሁም ለባህል መበላሸት ምክንያት ከሆኑት አንዱና ዋናው በከተማዋ የሚገኙ ትላልቅ ፎቆችንና መዝናኛዎችን ተገን በማድረግ በመኪና ውስጥ የሚፈፀሙ ጫት የመቃም፤ የተለያዩ እፆችን የመጠቀም እና የወሲብ ድርጊቶችን መፈጸም መሆናቸውን የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡ ስለዚህ ድርጊቶቹ የአገርን ባህልና መልካም ገፅታ እንዲሁም የከተማዋን ስምና ዝና የሚያጎድፉና የመልካም ባህሪይ ተፃራሪ ስለሆኑ፤ ህብረተሰቡ እነዚህን አስነዋሪ ድርጊቶች ማውገዝ ይችል ዘንድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ቢሠራ እና በህግ አካላት በኩልም ህግና ደንብ ወጥቶላቸው ክትትል፣ ቁጥጥርና የማያዳግም የእርምት እርምጃ ቢወሰድ፤
- የቱሪስት አገልግሎት መስጫ፣ የባህል ኪነጥበብና የፈጠራ ውጤቶችን የሚያዘጋጁ፣የሚያከፋፍሉና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል የአሠራር ክፍተት መኖሩን የጥናቱ ግኝት አሳይቷል፡፡ስለዚህ የሥራና የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ

ክትትልና እርምጃ አወሳሰድ በሚያደርጉ በንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮና በባህልና ቱሪዝም ቢሮ መካከል ያለው የጋራና የግል ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ቢቀመጥ፣ እንዲሁም የሙያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት፣ የማስታወቂያ፣ የመዝናኛና ለሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በወሰዱት ፈቃድ እና በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ መሠረት ስለመስራታቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ቢደረግና ከዚህ አግባብ ውጪ የሆኑትንም የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ቢዘረጋ፤

- ከውጭ የሚገቡ ፊልሞችንና የህትመት ውጤቶችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እና በጎ የሆኑትን ከራስ ባህል ጋር አስማምቶ ለመጓዝ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ቢዘረጋ፤ እንዲሁም የህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ለተግባራዊነቱ ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት የማስተካከያ ሥራ ቢሠራ፤
- በህብረተሰቡ በተለይም በወጣቶችና ሴቶች ላይ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች እያደረሱት ያለውን ሁለንተናዊ ቀውስ ለመግታት፣ ከታዋቂ ግለሰቦች፣ ከምሁራን፣ ከንግዱ ህብረተሰብ፣ ከኃይማኖት ተቋማት፣ ከህግ አውጪዎች፣ ከሕግ አስፈፃሚዎች፣ ከትምህርት ተቋማት፤ከዕድሮች ጥምረት፣የሙያ እና ሲቪክ ማህበራት ከሚመለከታቸው የመንግሥት የአስተዳደር መዋቅሮች ወዘተ...የተውጣጡ አካላት ከመገናኛ ብዙሀን ጋር በመቀናጀት ለሁሉም ህብረተሰብ በሚዳረስ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን፤ሥልጠናዎችንና ትምህርት ለህብረተሰቡ በመስጠት፤ ተከታታይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ችግሩ እስከ መጨረሻው የሚቀረፍበትን ሥርዓት የሚዘረጋበትን መንገድ እንዲያመቻች ቢደረግ፤
- በዚህ ጥናት ግኝት አብዛኛው ወጣቶችና ሴቶችን ላላስፈላጊ ድርጊት ከሚገፋፏቸው ምክንያቶች አንዱ ያልተገቡ ወሲብ ነክ ድረ ገጾች ተጠቃሚነት መስፋፋት ነው። በመሆኑም የከተማው አስተዳደር ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመተባበር በተለያዩ የመረጃ መረቦች/ኢንተርኔት የሚያሠራጩ ያልተገቡ ወሲብ ነክ ድረ-ገጾች ላይ በቀጥታ እገዳ የሚደረግበትን መንገድ ቢያመቻች፤
- በትምህርት ቤቶች አካባቢ የውጭ ዜጎችና በእድሜ የገፉ ግለሰቦች ሴት ተማሪዎችን በገንዘብ በመደለል ወዳላስፈላጊ የወሲብ መፈጸሚያ ቦታዎች እንደሚወስዷቸው ታውቋል። ስለሆነም ወጣቶችና ሴቶችን በመደለል ለወሲብና ለመሰል አላስፈላጊ ተግባራት በሚዳርጉ ግሰቦች ላይ ጠንካራና ቀጣይነት ያለው የክትትል፣ የቁጥጥርና የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋ፤ እንዲሁም ህብረተሰቡ ችግሩን አይቶ ከመታዘብ ይልቅ ለሚመለከተው ክፍል የመጠቆምና የማጋለጥ ልምድ እንዲኖረው የሚያስችል

የግንዛቤና የውይይት መድረክ ቢዘጋጅ፤ በትምህርት ቤት አካባቢም የትምህርት ቤት አመራሮች፤መምህራን፤ ወላጅ-ተማሪ-መምህር ህብረት (ወተመህ)፣ የተማሪዎች መማክርትና ክበባት፤ ተማሪዎች ለችግሩ ተጋላጭ እንዳይሆኑ ጠንከር ያለ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ቢሰሩ፤

- ታዋቂ ግለሰቦች፤የመንግሥት ሠራተኞች፤ከፍተኛ ባለሙያዎችና አመራሮች፤የፖሊስ አካላትና ሌሎችም በችግሩ ውስጥ እንደሚገኙ ጥናቱ አመላክቷል፡፡በመሆኑም ካለባቸው ሀገረዊ፤ህዝባዊና ሙያዊ ኃላፊነትና ግዴታ፤እንዲሁም ለሌሎች አርዓያ ሆኖ ከመገኘት አንፃር ሀላፊነታቸውን በሚገባ ይወጡ ዘንድ በየተቋማቱ ግምገማዊ ሥልጠና በመስጠት ራሳቸውን እንዲያዩ ቢደረግና መስተካከል ባልቻሉት ላይ ግን ጠንከር ያለ የማስተካከያና የስነስርዓት እርምጃ ቢወሰድ፤
- የወጣቶችና ሴቶችን ፍላጎት ያማከለ አማራጭ የመዝናኛ ማዕከላት ቢስፋፉና ያሉትም ቢጠናከሩ፣ የወጣትና የሴት አደረጃጀቶችን ስለመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች አስከፊነት በማወያየት የመፍትሔው አካል እንዲሆኑ ቢደረግ፤ በተጨማሪም በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰቡ ክፍሎች ወደ ችግሩ ላልገቡት "በኔ ይብቃ!" የማስተማሪያ ውይይቶች እንዲካሂዱ ሁኔታዎች ቢመቻቹ፣
- ሴቶችና ወጣቶች በስራ ማጣት ምክኒያት ላልተፈለጉ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች እንደሚጋለጡ ጥናቱ አሳይቷል። ስለሆነም የቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር የትምህርት ዕድል አቅርቦትና የስራ ዕድል በመፍጠር ወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ ቢመቻች፤
- ሴቶችና ወጣቶች፤ ጤናማ የሆነና የኢትዮጵያዊነትን ባህልና ወግ የጠበቀ የአለባበስ፤የፀጉር አሠራርና በአጠቃላይ ያአኗኗር ዘይቤ ሥርዓት እንዲኖራቸው የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተዘጋጅተው እርስ በእርስ ውይይት የሚያካሂዱበት አግባብ ቢኖር፣
- የባህል ተቋማት ኪነ-ጥበባዊ የስራ ውጤቶች ይዘትና የአቀራረብ ዘዴ በኢትዮጵያ ባህልና ወግ ቅኝት ውስጥ ማለፉን የማረጋገጥ፣ የንባብ ቤቶች የሚስፋፉበትን አግባብ የማጠናከር፣ እንዲሁም ሀገራዊ ባህልና እሴቶችን የማይጣረሱ ልብሶችን በብዛት ማምረትና በስፋት መጠቀም ይቻል ዘንድ፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ከህብረተሰቡ ጋር በቅንጅት ቢሰሩ፣
- ትምህርት ቤቶች አርፍደው የሚመጡ ተማሪዎች ወደ ቅጥር ግቢ እንዳይገቡ ከመከላከል ይልቅ ሌሎች የአሰራር ስልቶችን የመቀየስ፣ሁለተኛ ደረጃና ከዚያ በታች

ያሉ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ የሞባይል ስልክ ይዘው እንዳይገቡ የማድረግና ሀገራዊ እሴቶችን ያልጠበቁ የተማሪዎች የሙዚቃ ድግስ 'ፌስቲቫሎችን' የሚከለክል የአሰራር መመሪያ ቢወጣ፣

- በትምህርት ቤቶች የአላስፈላጊ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ክበባት ቢቋቋሙና ተማሪዎቹ ለውጥ ሊያስገኝ የሚችል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ቢደረግ፣
- በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ተካትቶ እየተሰጠ ያለው የስነምግባርና የስነ ዜጋ ትምህርት፣ ተማሪዎች መብታቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁና እንዲያስከብሩ አስችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ሀገራቸውን የሚወዱ፣ ታሪክና እሴቶቻቸውን የሚጠብቁ፣ ግዴታቸውንም ጭምር ጠንቅቀው የሚያውቁ፤ እንዲሁም ያልተገቡ ድርጊቶችና መጤ ባህሎችን የሚጠየፉ ዜጎች ከማፍራት አንጻር ግን ክፍተት እንዳለ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ስለዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ጉድለቶች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የስነምግባር ትምህርቱ የተጠናከረ ይዘት ታክሎበት እንዲሰጥ ቢደረግ፣
- የቴሌቪዥንና የራዲዮ ፕሮግራሞች እድሜ፣የትምህርት ደረጃ፣ ንቃተ ህሊናንና መልካም ባህልን ባገናዘበና በተጠናከረ መልኩ እንዲተላለፉ ግልፅ መመሪያ ቢወጣ፤እንዲሁም በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የሚያገለግሉ ጋዜጠኞችን ስለ መልካም እሴትን ያገናዘበ ፕሮግራምና ዘገባ፣ በአነቃቂ እፅና የአልኮል መጠጦች ተጠቃሚነትና ተፅእኖ፣ እንዲሁም ወጣቶችና ሴቶችን ከጥቃትና ጉዳት ተጋላጭነት መጠበቅ ዙሪያ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ቢሰጥ፣
- የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ስርጭት ይዘት፣ ባህልና እሴትን የጠበቀ ስለመሆኑ፣ የቀጥታ ስርጭትና ቋሚ ፕሮግራሞችን የሚሰሩ ጋዜጠኞች ተገቢው ሙያዊ ልምድና ሥነ ምግባር እንዳላቸው እንዲሁም በፕሮግራም እንግድነት የሚጋበዙ ግለሰቦች ለወጣቶችና ሴቶች በስራቸው፣ በስብዕናቸውና በመልካም ባህሪያቸው የተመሰገኑና አርአያ ስለመሆናቸው ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ቢደረግ፣
- በልጆች አስተዳደግና በቤተሰብ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ጤናማ ግንኙነት፤ ወላጆች ለልጆቻቸው ስለሚሰጡት ገንዘብና የመገልገያ ቁሶች ተገቢነት፤ የቤተሰብ ክትትልና ቁጥጥር፣ ወላጆች ከትምህርት ቤቶች ጋር ስለሚኖራቸው የቅርብ ግንኙነት በተመለከተ፤ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ በሚመለከተው አካል በኩል ተጠናክሮ ቢሰጥ፤

- ባልተገቡ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የተጠመዱ ወጣቶችና ሴቶች ከችግሩ ተላቀው የተሻለ ህይወት መምራት ይችሉ ዘንድ የማገገሚያ ተቋም ቢኖር፤ በችግሩ ተዘፍቀው ወንጀል ውስጥ በመግባታቸው ከማረሚያ ቤት ገብተው የሚወጡ ዜጎችም ተመልሰው ወደ ወንጀሉ እንዳይገቡ ክትትል እየተደረገ የማስተማርና የማማከር አገልግሎት ቢያገኙ እና ታራሚዎቹ ከማረሚያ ቤት ይዘው በወጡት የሙያ ክህሎትና እውቀት ሊሠሩ የሚችሉበት መንገድ ቢመቻች፤
- የየእምነት ተቋማቱ ወጣቶችና ሴቶችን ስለ በጎ ሥነምግባር፤ስብዕና፣ ግብረገብነት፤ሀገራዊ ባህልና እሴቶች እንዲሁም መሰል ጉዳዮች የማስተማር ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት በየተቋማቱ ለመንፈሳዊ እሴቶች ትርጉም ያለው ከበሬታ እንዲሰጡ ሳይታክቱ በተጠናከረ መልኩ ቢያስተምሩ፤
- የጥናቱ ግኝት እንዳመለከተው በአብዛኛው ያልተገቡ መጤ ባህሎችና ድርጊቶች የሚፈጸሙት በግለሰቦች፣በመንግስትና በደርጅት ቤቶች ተከራይተው በሚኖሩ ሰዎች ነው፡፡ አከራዮች ስለ ድርጊቶቹ መፈጸም በቅድሚያ አውቀውም ሆነ ሳውቁ ሊሆን ቢችልም፣ ቤቱን ሲያከራዩ ግን ለማንና ለምን ተግባር እንደሚውል በቅድሚያ ቢያረጋግጡ፤ በቤቱ ውስጥ ምን እየተከናወነበት ስለመሆኑ ክትትል ቢያደርጉ፤ እንዲሁም መልካም ባህሪን የሚፃረሩና እሴትን የሚያጎድፉ ድርጊቶች ሲፈፀሙ ቢያውግዙ ቢከላከሉና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ለመፍትሔ እርምጃው ቢሰሩ፤

## ማጣቀሻ መጽሐፍት /References /

**የአማርኛ ዋቢ መጽሐፍት**

አዳነች አበራ (2001)፡፡ “የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መጻህፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ” አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነጹሁፍ ትምህርት ክፍል ለኤም-ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፡፡

አዳነች ካሣ(2002)፡፡ “የሀድያ ሴቶች በቡድን በሚከውኗቸው ተግባራት ላይ የተመሠረተ ቁሳዊ ባህል ጥናት”

አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢተረዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፡፡

ሥንቅነሽ አጣለ ፡፡ “ሙስና ስደትና ኤች አይ ቪ ኤድስ ከ1990-1996. በታተሙ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች” አዲስ አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ድህረ ምረቃ ት/ቤት፡፡

የኔዓለም አረደ (2000)፡፡ “የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት” (በኮኮሳና ገደብ ሰሳ ወረዳዎች)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡

የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስትር(1995)፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክሲያዊ ሪፑብሊክ የባህል ፖሊሲ፡

አዲስ አበባ. ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት ፡፡

የወጣቶች ባህል ሚኒስቴር “ትዉልድ” ሀብታሙ ወንድሙ ቅፅ 1 ቁጥር 1/ሐምሌ 1996. አዲስ አበባ፡አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ሽሻና የጤና ችግሮቹ፤ (2003) ፡፡ አዲስ አበባ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ “ሺሻና መዘዙ”፤ በፈሰሰወርቅ አሥራት፤ አዲስ አበባ ፤(2002)፡አዲስ አበባ፡

**References**

Alcohol and Drug Problems, Retrieved from http://www.peacehealth.org

Allison, Kenneth. 1992. "***Academic Stream and Tobacco, Alcohol, and Cannabis Use Among Ontario High School Students***." The International Journal of the Addictions 27(5): 561-570.

Andrews,Judy and Susan Duncan.( 1997). "***Examining the Reciprocal Relation between Academic motivation and substance use: Effects of family relationships, self-Esteem, and general deviance."*** Journal of Behavioral Medicine 20(6): 523-549.

Braggio, etal. (1993).***"Academic Achievement in Substance Abusing and Conduct Disordered Adolescents***." Journal of Clinical Psychology 49(2): 282-291.

Brandon & Hill. (2002). ***Substance use and Violence/ Delinquency have significant impacts on Academic Achievement among Middle and High School Students in Washington State***. Department of Social and Health Services. Retrieved from [www.irawma.com](http://www.irawma.com)

Brandon Richard N. and Abhay Thatte. 1999. "***Alcohol, Tobacco, and Substance Abuse and Washington Children.***" Prepared for Division of Alcohol and Substance Abuse.

Brook et al. (1989). ***"The consequences of marijuana use on intrapersonal and interpersonal Functioning in black and white adolescents***": Genetic, Social and General Psychology, Monographs 115(3): 349-369.

Bryk et al. (1998). ***Examining Productivity: Ten-Year Trends in the Chicago Public School.*** A report Sponsored by the Consortium on Chicago School Research.

Caldas, Stephen and Carl Banks ton III (1997). "Effect of School Population Socioeconomic Status on Individual Academic Achievement." *The Journal of* Educational Research 90(5): 269-277.

Balderu, N. (2002). ***Helping Children deal With Difficult Issues***: ***A Guide for Parents***. Soul City, the Institute for Health and Development Communication, South Africa.

Chalferty (2003): ***Learning Resource for Youth in the Grade 7 Life Orientation Program****: Why do Young People take Drugs*? Soul City; South Africa.

Crum et al.( 1998). ***"The Association of Educational Achievement and School Dropout With risk of alcoholism: A twenty-five year prospective study with inner City Children***." Journal of Studies on Alcohol 59(3): 318-326.

Dishion et al.( 1985). "***Adolescent Marijuana and Alcohol Use: The Role of Parents and Peer Revisted."*** American Journal of Drug Alcohol Abuse 11(1&2): 11-25.

Evan et al. 1992. "Academically Successful Drug Users: An Oxymoron?" *Journal of*

Drug Education 22(4): 353-365.

Dandues, Ala. (1965). ***The study of Folklore***. University of California at Berkeley. Prentice International Edition, Vol.19. USA Grolier Incorporate

Dorson, M. ed. (1972). ***Folklore and Folk life: An Introduction.*** Chicago, London, The University of Chicago Press.

Emerging Public Health problems in Ethiopia" (2006). ***Proceedings of the 17$^{th}$ annual conference of the Ethiopian public Health Association***.

Eyasu, M. (2005). ***An over view of the Pharmacology of khat***. Department of Pharmacology: faculty of Medicine; Addis Ababa University.

Encyclopaedia Americana. USA(1995). ***International Edition***, vol.19, USA: Grolier Incorporated,

Evan et al. (1992). "***Academically Successful Drug Users***: ***An Oxymoron***?" Journal of

Drug Education 22(4): 353-365.

Fekade,A.(2003).***Teaching Material Selected and Compiled****:* Reader for Elti 621'Departement of Ethiopia Literature and Folklore.

Galambos, et.al (1987). ***"Substance use in W. German Youth***: ***A longitudinal study of adolescents' use of alcohol and tobacco***." Journal of Adolescent Research 2(2): 161-174.

Galambos, Nancy and Rainer Silbereisen. 1987. "***Substance use in W. German Youth: A longitudinal study of adolescents' use of alcohol and tobacco."*** Journal of Adolescent Research 2(2): 161-174.

Gebereselassie.S. & Gebere.A.(1996) ***Rapid Assessment of Drug Abuse in Ethiopia***.

Golub et al. 2000. ***"Response Reliability and the Study of Adolescent Substance Use Progression***." Journal of Drug Issues 22: 103-118.

Grissmer et al. 1994. ***Student Achievement and the Changing American Family***. Santa Monica: RAND

Hailu T, Jeans B. khat.(2002). ***khat expansion in the Ethiopia highlands***: ***Effect on the farming system in Habro District***. Available at http://www.bioone.org./

Hawkins et al. 1992. "***Risk and Protective Factors for Alcohol and Other Drug Problems In Adolescence and Early Adulthood: Implications for Substance Use Prevention."*** Psychological Bulletin 112:64-105.

Hops et al. 1999. "***The Development of Alcohol and Other Substance use: A Gender Study of Family and Peer context***." Journal of Studies on Alcohol 13: 22-31.

Jessor et al. 1980. "***Psychosocial correlates of marijuana use and problem drinking in A national sample of adolescents."*** American Journal of Public Health 70: 604-613.

Impact of Peer Substance Use on Middle School Performance in Washington: **Summary**. Retrieved from hspcnews@u.washington.edu,

Jill Grove(2002). ***Protective Factors for Illicit Drug use*: *The Role of Schools in crime Prevention***. Retrieved from *http://www.who.int/hpr*

Lopez Garcia KS and Junior ML. (2008). ***Antisocial Behavior and Alcohol Consumption by School Adolescents.*** Rev. Latino-am Information. Retrieved from *www.eerp.usp.br/rlae*.

Lurie, Alison (1981). ***The Language of clothes***, Newyork.Random House Inc.

McNeal et al. 1999. "***Developmental Patterns Associated with the Onset of Drug Use: Changes in Postulated Mediators during Adolescence***." Journal of Drug Issues 29(2): 381-400.

Merrill et al. 1999. ***"Cigarettes, alcohol, marijuana, other risk behaviours, and American Youth.***" Drug and Alcohol Dependence 56: 205-212.

Miller, Patrick and Martin Plant. 1999. ***"Truancy and perceived school performance: an Alcohol and drug study of UK Teenagers***." Alcohol and Alcoholism 34(6): 886-893.

Ministry of Youth, Sports &Culture (2004). ***Federal Democratic Republic of Ethiopia National Youth Policy.*** Addis Ababa: Printed by Berhanena Selam Printing enterprise,

Moges (2008).***Sexual Orientation and Practises of Young People in Addis Ababa High Schools***:in EPHA Eds.Extract no.5,Addis Ababa, Ethiopia.

Paulson et al. 1990. ***"Substance abuse and associated psychosocial problems among Argentina adolescents: sex heterogeneity and familial transmission***." Drug and Alcohol Dependence 52: 221-230.

Rosenberg ,M. Michael and etal. (1987). ***An Introduction to sociology***. Second ed. Toronto: Methuen Publication.

Seyoum .G (1996). ***Drug and Substance Abus as an Emerjing Urban Problem in Ethiopia*: *In Proceedings of the National Work shop on Khat Habit and other Psychotropic Drugs in the***

***Spread of HIV/AIDS and their Impact on Health and Socio Economic Well-being***. Addis Ababa University; Addis Ababa.

Snyder et al. 1986. "***Determinants and consequences of associating with deviant peers During preadolescence and adolescence."*** Journal of Early Adolescence 6(1): 29-43.

Swadi, Harith. 1999. ***"Individual Risk Factors for Adolescent Substance Use."*** *Drug And Alcohol Dependence 55: 209-224.*

The Higher Education Center for Alcohol and other Drug Abuse and Violence Prevention (2010). ***College Academic Performance and Alcohol and other Drug use***. Retrieved from *http://www.higheredcenter.org*

Tewabech T., etal.(2010***). A study on the knowledge, Attitude and Practice of Reproductive health & HIV/AIDS Education among statements in Secondary Schools in Addis Ababa.*** Addis Ababa Education Bureau.

Tom Bisson (1996). ***Social Security Diability Low:Alchol or Drug Addiction***.

United Nations Office on Drugs and Crime (2002). UNITED NATIONS, New York. Retrieved from WWW. Concern. Org.Questions about Smoking Tobacco and Health.(Unpublished)

World Health Organization Regional Office for Eastern Mediterranean (2006). ***The Health Hazards: Smoking Shisha.*** Cairo, 2006.

Weeks, Greg. 1999. "***Hierarchical Model of Student Performance on Standardized Tests***." Working Paper for Joint Legislative Audit and Review Committee.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

**መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያስከትሏቸው ተፅዕኖዎች ላይ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ**

የዚህ ጥናት ዓላማ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በአዲስ አበባ ነዋሪ፤ በተለይም በወጣቱና በሴቶች ላይ እያሳደሩ ያሉትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች በማወቅ የችግሩ ሰለባዎች ከችግሩ ሊወጡ የሚችሉበትን መንገድ በመጠቆም የመፍትሔ አቅጣጫ ማመላከት ነው፡፡ መጠይቁን በመሙላት ተሳታፊ በመሆንዎ አሁን ላለውና የመጪው ትውልድን ማንነት ለማስተካከል በሚደረገው ጥረት የራስዎን አስተዋጽዖ እያደረጉ መሆንዎን በማመን በጥንቃቄ እንዲሞሉ በትህትና እንጠይቃለን፡፡

*ለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን!*

**ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ መረጃዎች**

**ከተራ ቁጥር 1-13 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች የተስማሙበትን ፊደል በመክበብ መልስ ይስጡ**

1. *ፆታ* ሀ. ሴት ለ. ወንድ
2. *ዕድሜ* ሀ. 15-19 ዓመት ለ. 20-24ዓመት ሐ. 25-29ዓመት መ. 30 ዓመት እና ከዚያ በላይ
3. የትምህርት ደረጃ ሀ. ያልተማረ/ች ለ. 1-8 ሐ. 9-12 መ. ሰርተፍኬት ሠ.ዲፕሎማ ረ. ዲግሪና ከዚያ በላይ ሰ. በመማር ላይ ያለ/ች
4. ጀምረው ያቋረጡት ትምህርት አለን? ሀ. አለ ለ. የለም

**(መልስዎ የለም ከሆነ ወደ ተ.ቁ 6 ይለፉ)**

5. ለ4ኛው ጥያቄ መልስዎ አለ የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሀ. በኢኮኖሚ ችግር ለ. ከሱሰኝነት ጋር በተያያዘ ችግር ሐ. በባህሪ ችግር መ. ከቤተሰብ ጋር ባለመስማማት ሠ.ሌላ

6. የትዳር ሁኔታ ሀ. ያገባ/ች ለ. ያላገባ/ች ሐ. የፈታ/ች መ. በሞት የተለየ/ች ሠ. ከፍቅር ጓደኛ ጋር የሚኖር/የምትኖር
7. በአሁኑ ጊዜ ከማን ጋር ይኖራሉ?

ሀ. ከወላጅ ጋር ለ. ከዘመድ/አሳዳጊ ጋር ሐ. ለብቻ መ. ከትዳር/ከፍቅር ጓደኛ ጋር

8. ሀይማኖት ሀ. ኦርቶዶክስ ለ. ሙስሊም ሐ. ካቶሊክ መ. ፕሮቴስታንት ሠ. ሌላ

9. ወደ እምነት ተቋማት የመሄድ ልምድ አልዎትን? ሀ. አዎ ለ. የለኝም (**መልስዎ የለኝም ከሆነ ወደ ተ.ቁ 11 ይለፉ**)

10. ለ9ኛው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ በምን ያህል ጊዜ ይሄዳሉ? ሀ. ሁልጊዜ ለ. አልፎ አልፎ ሐ. ሲመቸኝ

11. የትውልድ ቦታ ሀ. አዲስ አበባ ለ. ከአዲስ አበባ ውጪ (**መልስዎ አዲስ አበባ ከሆነ ወደ ተ.ቁ 13 ይለፉ**)

12. ለ11ኛው ጥያቄ መልስዎ "ለ" ከሆነ በአዲስ አበባ ውስጥ ለምን ያህል ዓመት ኖሩ?
ሀ. ከ1 ዓመት በታች ለ. ከ1-3 ዓመት ሐ. ከ4-6 ዓመት መ. ከ6 ዓመት በላይ

13. የስራ ሁኔታ ሀ. የመንግስት ሰራተኛ ለ. የግል ስራ ሐ. ተማ ሪ መ. ስራ ፈላጊ ሠ. የቤት እመቤት

## ክፍል ሁለት፡ የተለያዩ የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ተፅዕኖዎች ዙሪያ የቀረቡ ጥያቄዎች

**ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ፊደሉን በማክበብ ወይም ሰንጠረዥ ውስጥ ምልክት በማድረግ ይመልሱ**

14. አብዛኛውን ጊዜ እንደ መዝናኛ/ጊዜ ማሳለፊያ የሚጠቀሙትን በመምረጥ **ከ1-6 በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | የመዝናኛ ዓይነት | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | ፊልም በማየት | |
| 2 | የህትመት ውጤቶችን በማንበብ | |
| 3 | በጭፈራ ቤቶች በመዝናናት | |
| 4 | አልኮል በመጠጣት | |
| 5 | ኢንተርኔት በማየት | |
| 6 | አነቃቂ ዕፆችን በመጠቀም | |

15. ከሚከተሉት የመረጃ ማግኛ መንገዶች የበለጠ የመጠቀም ዕድል ያሎት በየትኛው እንደሆነ በመምረጥ **ከ1-6 በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | የመገናኛብዙሃን ዓይነት | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | የአገር ውስጥ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች | |
| 2 | በዲሽ የውጪ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች | |
| 3 | መፅሔት | |
| 4 | ጋዜጣ | |
| 5 | ኢንተርኔት | |
| 6 | ሬድዮ | |

16. የማህበረ ሰብ ድረ-ገፅ(ፌስ ቡክ፣ ትዊተር...) ተጠቃሚ ነዎት? ሀ. አዎ ለ. አይደለሁም **(አይደለሁም ካሉ ወደ ተ.ቁ 19 ይለፉ)**

17. ለ16 ኛው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ግንኙነትዎ ከነማን ጋር እንደሆነ ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. በተለያዩ አጋጣሚዎች ከማውቃቸው ሰዎች ጋር ለ. በድረ- ገፁ ጓደኝነት ጥያቄ ከሚያቀርቡልኝ ጋር

ሐ. የድረ- ገፁ ተጠቃሚዎችን ግለ-መረጃ በመመልከት ከመረጥኳቸው ጋር

18. በድረ- ገፅ ከተዋወቁት ሰው የፍቅር/ወሲብ ጥያቄ ቀርቦሎት ወይም ወሲብ ነክ ምስልና መልዕክት ደርስዎት ያውቃል?

ሀ. ያውቃል ለ. አያውቅም

19. በአብዛኛው የሚመለከቷቸው ፊልሞች ምን ዓይነት እንደሆኑ ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. በድርጊት የተሞላ/አክሽን ለ. የፍቅር ሐ. አስፈሪ/ሆረር

መ. የቤተሰብ ሠ. አስቂኝ

20. የሚያዩዋቸውን ፊልሞች የሚመርጥልዎት ማን ነው? ሀ. ቤተሰብ

ለ. ጓደኛ ሐ. ራሴ

21. የወሲብ ፊልም አይተው ያውቃሉ? ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም **(አላውቅም ካሉ ወደ ተ.ቁ 24 ይለፉ)**

22. ለ22ኛው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ በምን ያህል ጊዜ ያያሉ? ሀ. ሁል ጊዜ

ለ. አልፎ አልፎ ሐ. በአጋጣሚ

23. የወሲብ ፊልሞቹን የት እንደሚያገኟቸው ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. በኪራይ ለ. በውሰት ሐ. ቪዲዮ ቤት በመሄድ መ. በኢንተርኔት ሠ. ከጓደኞቹ ጋር በሞባይል በመላላክ

24. በብዛት የሚያነቧቸው ምን ዓይነት የህትመት ውጤቶችን እንደሆነ ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. ስለ ፍቅር የተጻፉ ለ. ስለ ወሲብ የተጻፉ ሐ. ስለ ፋሽን የተጻፉ መ. ስለ ፍልስፍና የተጻፉ ሠ. ስለ ስፖርት የተጻፉ

25. በጣም የሚያደንቁዋቸው ወይም አርአያ የሚያደርጉዋቸው ሰዎች ከየት ናቸው?

ሀ.ከሀገር ውስጥ ለ. ከሀገር ውጪ ሐ. ከሁለቱም መ. የማደንቀው የለኝም **(የለኝም ካሉ ወደ ተ.ቁ 27 ይለፉ)**

26. አርአያ ከሚያደርጓቸው ታዋቂ ሰዎች የሚያደንቁትና አርአያ የሚያደርጉት ምናቸውን እንደሆነ ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)** ሀ. የአለባበስ ዘይቤያቸውን/ስታይላቸውን ለ. የፀጉር አሰራር ዘይቤያቸውን/ስታይላቸውን ሐ. የአጫጫስ ዘይቤያቸውን/ስታይላቸውን መ. የሚጠቀሙትን መጠጥ ሠ. ስኬታቸውን

## ክፍል ሦስት፡ የተለያዩ አልኮሎችና

### ዕፆችን(ጫት፣ሀሺሽ...) አጠቃቀምና ተፅዕኖዎች ዙሪያ የቀረቡ ጥያቄዎች

### ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ፊደሉን በማክበብ ወይም ሰንጠረዥ ውስጥ ምልክት በማድረግ ይመልሱ

27. አልኮል ተጠቅመው ያውቃሉ? ሀ. አዎ ለ. አላውቅም **(አላውቅም ካሉ ወደ ተ.ቁ 31 ይለፉ)**

28. ለ27ኛው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ በአብዛኛው ምን ዓይነት መጠጦችን ነው የሚጠቀሙት?**(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ** ሀ. በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ(ጠላ፣ጠጅ፣አረቂ...) ለ. የፋብሪካ ምርቶች(ቢራ፣ ድራፍት፣ ነጭ አረቂ፣ውስኪ....) ሐ. ሁለቱንም

29. የሚወስዷቸውን አልኮሎች በምን ያህል ጊዜ ይጠቀማሉ? ሀ. በየቀኑ ለ. በዕረፍት ቀናት ሐ. በዓመት በዓላት ሠ. በአጋጣሚ

30. የሚወስዷቸውን አልኮሎች የት ይጠቀሟቸዋል? **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. በመኖሪያ ቤት ለ. መጠጥ ቤት በመሄድ ሐ. በግል በድብቅ የተዘጋጁ ቦታዎች በመሄድ መ. ከጓደኞቼ ጋር ቦታ በመምረጥ

31. በትምህርት ቤት/በስራ ቆይታዎ በአደንዛዥ ዕፅ ዙሪያ ግንዛቤ አግኝተው ያውቃሉ ወይ? ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም

32. ለ32ኛው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ትምህርት ያገኙት ከምን እንደሆነ ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. በት/ቤት በሥርዓተ-ትምህርቱ ተካቶ ስለሚሰጥ ለ. ከመገናኛ ብዙሃን ሐ. በክበባት/ማህበራት ስልጠና ስለሚሰጥ

መ. ከጓደኛ ወይም ከበቤተሰብ ጋር እርስ በእርስ በመነጋገር

33. ለመነቃቃት ወይም ለሌላ ጉዳይ አነቃቂ ዕፆችን ተጠቅመው ያውቃሉ? ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም **(አላውቅም ካሉ ወደ ተ.ቁ 38 ይለፉ)**

34. ለ34ኛው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ምን ዓይነት ዕፆችን እንደሚጠቀሙ ያመላክቱ **(ከአንድ በላይ የሚጠቀሙ ከሆነ በመክበብ ያሳዩ)**

ሀ. ሲጋራ ለ. ጫት ሐ. ሺሻ መ. ሀሺሽ ሠ. ሄሮይን፣ኮኬይንና የመሳሰሉትን

35. አነቃቂ ዕፆችን በአብዛኛው በየትኛው የአጠቃቀም ዓይነት እንደሚጠቀሙ ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. በማጨስ ለ. በእንክብል ሐ. በማኘክ መ. በመርፌ በመወጋት

36. እርስዎ አብዛኛውን ጊዜ አነቃቂ ዕፆችን የት እንደሚጠቀሙ ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. ከሱቅ በመግዛት ቤት ውስጥ ለ. ለዚህ በግልፅ በተዘጋጁ ቦታዎች በመሄድ

ሐ. ከጓደኞቼ ጋር ቦታ በመምረጥ

መ. በድብቅ በተዘጋጁ ቦታዎች በመሄድ

37. ለተለያዩ አነቃቂ ዕፆች ወይም ለአልኮል መጠጦች የሚሰፈልግዎትን ገንዘብ ከየት ያገኛሉ? **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ያክብቡ)**

ሀ. ከስራ ከሚገኝ ገቢ ለ. ከቤተሰብ ሐ. ከጓደኛ መ. ሌላ

## ክፍል አራት፡ የፆታ ግንኙነትን የተመለከቱ ጥያቄዎች

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ፊደሉን በማክበብ ወይም ሰንጠረዥ ውስጥ ምልክት በማድረግ ይመልሱ**

38. ወሲብ ፈጽመው ያውቃሉ? ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም **(መልስዎ አላውቅም ከሆነ ወደ 43ኛው ጥያቄ ይለፉ)**

39. ለ38ኛው ጥያቄ መልስዎ አውቃለሁ ከሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጸሙት በየትኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ ነው?

ሀ. ከ15 ዓመት በታች ለ. ከ15-18 ዓመት ሐ. ከ19-23 ዓመት መ. ከ24-29 ዓመት ሠ. ከ29 ዓመት በላይ

40. ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ የፈጸሙት ከማን ጋር ነው?

ሀ. ከፍቅረኛዬ ለ. ከትዳር ጓደኛዬ ሐ. በወሲብ ስራ ተዳዳሪ ጋር

መ. በማላውቀው ወይም በማውቀው ሰው ተገድጄ ሠ. ከማላውቀው ወይም ከማውቀው ሰው ጋር በአጋጣሚ

41. ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ኖርዎት ያውቃልን? ሀ. ያውቃል ለ. አያውቅም

42. ለ41ኛው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ለምን እንደሆነ **ከ1-6 በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | ምክንያት | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | የወሲብ ልምድ ለማካበት | |
| 2 | ጓደኞቼ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ ስላላቸው ችግር ያለው ስላልመሰለኝ | |
| 3 | ከቤተሰብ በማየት | |
| 4 | በፊልም ስለማይ | |
| 5 | እንደ ገቢ ምንጭ ለመጠቀም | |
| 6 | የስልጣኔ ምልክት ስለመሰለኝ | |

43. ስለ ግብረ ሰዶማዊነት(የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነት) ሰምተው ያውቃሉ? ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም

44. ለ44ኛው ጥያቄ መልስዎ አውቃለሁ ከሆነ በምን መንገድ አወቁት? **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. በመገናኛ ብዙሀን ለ. በፊልም ሐ. በህትመት ውጤቶች መ. ስለዚህ ጉዳይ ከሰሙ ጓደኞቼ ጋር በመነጋገር

ሠ. በዚህ ህይወት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ስለማውቅ

45. ስለ ግብረ ሰዶማዊነት(የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነት) ከሚከተሉት ውስጥ የሚስማሙበትን ሀሳብ ይምረጡ፡፡

ሀ. በሌሎች ሀገሮች መብት ስለሆነ በእኛ ሀገርም ቢኖር ምንም አይመስለኝም

ለ. በሌሎች ሀገሮች የሚደረግ ስለሆነ የስልጣኔ ምልክት መስሎ ይታየኛል ሐ. ከባህላችንና ሃይማኖታችን ጋር ስለማይሄድ አልደግፈውም መ. አስተያየት የለኝም

46. ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የወሲብ ግንኙነት አድርገው ያውቃሉ? ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም

**(አላውቅም ካሉ ወደ ተ.ቁ 48 ይለፉ)**

47. ለ46ኛው ጥያቄ መልስዎ አውቃለሁ ከሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረጉት ግንኙነት በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ሲወራ ሰምቼ ለመሞከር ለ. ተገድጄ(ተደፍሬ)

ሐ. በጓደኛ ግፊት መ. አልኮልና ዕፅ ተጠቅሜ በመገፋፋት

## ክፍል አምስት፡ ወጣቶችን/ ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ባህሪያት የሚመሩ ጉዳዮችንና የሚያስከትሉ ችግሮችን የተመለከቱ ጥያቄዎች

**ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ፊደሉን በማክበብ ወይም ሰንጠረዥ ውስጥ ምልክት በማድረግ ይመልሱ**

48. አነቃቂ ዕፅ ተጠቃሚ ቤተሰብ ወይም ጓደኛ አሎት? ሀ. አለኝ ለ. የለኝም

49. በአካባቢዎ የዕፅ አዘዋዋሪዎች/ሻጮች እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?

ሀ. በጣም ከፍተኛ ለ. ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ መ. ዝቅተኛ ሠ. ፈጽሞ የለም

50. በወጣቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የመዝናኛ ቦታዎችን በመለየት **ከ1-6 በደረጃ ያስቀምጡ፡፡**

| ተ.ቁ | የመዝናኛ ቦታ | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | የማታ ጭፈራ ቤቶች | |
| 2 | የቀን ጭፈራ ቤቶች | |
| 3 | የጫትና ሺሻ ቤቶች | |
| 4 | የመጠጥ ቤቶች | |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | የቪዲዮ ቤቶች | |
| 6 | ማሳጅ ቤቶች | |

51. በሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የመዝናኛ ቦታዎችን በመለየት **ከ1-6 በደረጃ ያስቀምጡ።**

| ተ.ቁ | የመዝናኛ ቦታ | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | የማታ ጭፈራ ቤቶች | |
| 2 | የቀን ጭፈራ ቤቶች | |
| 3 | የጫትና ሺሻ ቤቶች | |
| 4 | የመጠጥ ቤቶች | |
| 5 | የቪዲዮ ቤቶች | |
| 6 | ማሳጅ ቤቶች | |

52. በአካባቢዎ ለአላስፈላጊ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች(ያልተገባ አለባበስ፣ ዕፅ መጠቀም፣ ጥንቃቄ የጎደለው ወሲብ ...) በይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች የትኞቹ እንደሆኑ በመምረጥ **ከ1-7 በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | የህብረተሰብ ክፍሎች | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | የጎዳና ተዳዳሪዎች | |
| 2 | ተማሪዎች | |
| 3 | በወሲብ ስራ የሚተዳደሩ | |
| 4 | ወጣት ወንዶች | |
| 5 | ወጣት ሴቶች | |
| 6 | ጎልማሳ ሴቶች | |
| 7 | ጎልማሳ ወንዶች | |

53. በአካባቢዎ የዕፅና የመጠጥ ተጠቃሚዎች በህብረተሰቡ ላይ የሚያሳዩዋቸው አላስፈላጊ ባህሪያትን በመለየት ያስቀምጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)**

ሀ. መደባደብ  ለ. አስገድዶ መድፈር ሐ. በወንጀል መሳተፍመ. አካባቢ ማወክ

ሠ. ስራ መጥላት

54. በአካባቢዎ የዕፅና የመጠጥ ተጠቃሚዎች በተጨባጭ ይደርሱባቸዋል የሚሉትን **የስነ-ልቦናዊ** ችግሮችን በመለየት **ከ1-7 በደረጃ ያስቀምጡ**።

| ተ.ቁ | የችግር አይነት | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | ተስፋ መቁረጥ | |
| 2 | ራስን ማጥፋት | |
| 3 | ትምህርት መጥላት/ማቋረጥ | |
| 4 | ስንፍናና ስራ መጥላት | |
| 5 | ግብረ ሰዶማዊነት(ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ወሲብ መፈጸም) | |
| 6 | ድብርትና ጭንቀት | |
| 7 | የበታችነት ስሜት | |

55. በአካባቢዎ የዕፅና የመጠጥ ተጠቃሚዎች በተጨባጭ ይደርሱባቸዋል የሚሉትን **የማህበራዊ** ችግሮችን በመለየት **ከ1-7 በደረጃ ያስቀምጡ**።

| ተ.ቁ | የችግር አይነት | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | የቤተሰብ መፍረስ | |
| 2 | የጤና ችግር | |
| 3 | ከስራ መፈናቀል (ስራ ማጣት) | |
| 4 | ስደት | |
| 5 | ወደጎዳና መውጣት | |
| 6 | ሴተኛ አዳሪነት | |
| 7 | የጥገኝነት ባህል መጨመር | |

56. በአካባቢዎ የዕፅና የመጠጥ ተጠቃሚዎች በህብረተሰቡ የሚደርስባቸውን ተጽዕኖ ይምረጡ **(ከአንድ በላይ ምርጫ ካሎት ማክበብ ይችላሉ)** ሀ. ከህብረተሰብ መገለል ለ. ከቤተሰብ መጣላት ሐ. በወንጀል መጠርጠር መ. የበታች ተደርጎ መቆጠር

57. ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና አላስፈላጊ ባህሪያት የሚያጋልጡ ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን በመለየት **የራይት (✓) ምልክት በማድረግ በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | አይነት | እጅግ በጣም | በጣም | በትንሹ | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቤተሰብ ድህነት | | | | |
| 2 | የቤተሰብ በኢኮኖሚ ማደግ | | | | |
| 3 | የቤተሰብ ዕፅና አልኮል ተጠቃሚ መሆን | | | | |
| 4 | የቤተሰብ አለመግባባት | | | | |
| 5 | የቤተሰብ መፍረስ | | | | |
| 6 | በቤተሰብ ውስጥ ግልፅ ውይይት አለመኖር | | | | |
| 7 | የቤተሰብ ክትትል ማነስ | | | | |
| 8 | የቤተሰብ ቁጥጥር መብዛት | | | | |
| 9 | ስራ ማጣት | | | | |

58. ወጣቶችና ሴቶችን ለሱሰኝነትና አላስፈላጊ ባህሪያት የሚያጋልጡ አካባቢያዊ፣ የሚዲያና የአቻ ጓደኛ ተፅዕኖዎችን በመለየት **የራይት (✓) ምልክት በማድረግ በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | አይነት | እጅግ በጣም | በጣም | በትንሹ | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጓደኛ ተፅዕኖ | | | | |
| 2 | በሌሎች በመገደድ | | | | |
| 3 | የት/ቤትና የመኖሪያ አካባቢ ለሱስ በሚያጋልጡ ነገሮች መከበብ | | | | |
| 4 | የዕውቀትና የግንዛቤ ማነስ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የመዝናኛ ቦታ በበቂ አለመኖር | | | | |
| 6 | የመገናኛ ብዙሃን፣ የኢንተርኔት፣ የሞባይልና የፊልሞች መስፋፋት | | | | |
| 7 | የጭፈራ ቤቶች፣ የጫትና ሺሻ ቤቶችና የመጠጥ ቤቶች መስፋፋት | | | | |
| 8 | ከውጪ ሀገር በሚመጡ ሰዎች ተፅዕኖ | | | | |
| 9 | የስነ ምግባር ትምህርት በተጠናከረ መልኩ በት/ቤቶች አለመሰጠት | | | | |

59. በእርስዎ እይታ ሴቶች አብዛኛውን ትርፍ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በምን እንደሆነ **የራይት (✓) ምልክት በማድረግ በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | አይነት | እጅግ በጣም | በጣም | በትንሹ | በጭራሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፊልም በማየት | | | | |
| 2 | መፅሐፍ በማንበብ | | | | |
| 3 | በቤት ውስጥ ስራ | | | | |
| 4 | በስፖርት ሜዳ | | | | |
| 5 | በዙረት | | | | |
| 6 | ጭፈራ ቤት በመሄድ | | | | |
| 7 | ጫት በመቃም | | | | |
| 8 | መጠጥ በመጠጣት | | | | |
| 9 | የተለያዩ እፆችን በመጠቀም | | | | |

60. ሴቶችን ለመጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲጋለጡ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ? **የራይት (✓) ምልክት በማድረግ በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | አይነት | እጅግ በጣም | በጣም | በትንሹ | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የራስን ባህል ጠንቅቆ አለማወቅ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | የራስን ባህል መናቅ | | | | |
| 3 | የውጭ ባህል መከተልን እንደ ስልጣኔ በመቁጠር | | | | |
| 4 | በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የውጭ ዜጎች በሚያሳድሩት ተፅዕኖ | | | | |
| 5 | የመገኛኛ ብዙሃን፣ኢንተርኔትና የፊልሞች ተፅዕኖ | | | | |
| 6 | የገቢ ምንጭ ፍለጋ | | | | |
| 7 | ተስፋ መቁረጥ | | | | |
| 8 | የመዝናኛ ቦታዎች አማራጭ አለመኖር | | | | |

61. በእርስዎ እይታ ወጣቶች አብዛኛውን ትርፍ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በምን እንደሆነ **የራይት (✓) ምልክት በማድረግ በደረጃ ያስቀምጡ**

| ተ.ቁ | አይነት | እጅግ በጣም | በጣም | በትንሹ | በጭራሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፊልም በማየት | | | | |
| 2 | መፅሐፍ በማንበብ | | | | |
| 3 | በቤት ውስጥ ስራ | | | | |
| 4 | በስፖርት ሜዳ | | | | |
| 5 | ጭፈራ ቤት በመሄድ | | | | |
| 6 | ጫት በመቃም | | | | |
| 7 | አልኮል በመጠጣት | | | | |
| 8 | የተለያዩ እፆችን በመጠቀም | | | | |
| 9 | በጎዳና ላይ ያለ ስራ በመቀመጥ አላፊዎችን በመተናኮል | | | | |
| 10 | የውጪ ስፖርቶችን በዲኤስቲቪ በመከታተል | | | | |

62. ወጣቶችን ለመጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲጋለጡ ያደረጋቸው ምን እንደሆነ የራይት (✓) ምልክት በማድረግ በደረጃ ያስቀምጡ

| ተ.ቁ | አይነት | እጅግ በጣም | በጣም | በትንሹ | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የራስን ባህል ጠንቅቆ አለማወቅ | | | | |
| 2 | የራስን ባህል መናቅ | | | | |
| 3 | የውጭ ባህል መከተልን እንደ ስልጣኔ በመቁጠር | | | | |
| 4 | በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የውጭ ዜጎች በሚያሳድሩት ተፅዕኖ | | | | |
| 5 | የመገኛኛ ብዙሃን፣ኢንተርኔትና የፊልሞች ተፅዕኖ | | | | |
| 6 | የመዝናኛ ቦታዎች አማራጭ አለመኖር | | | | |

63. የአዲስ አበባ ሴቶች በመጤ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የተነሳ ለአላስፈላጊ የስነ-ምግባርና የማንነት ቀውስ ተጋልጠዋል ብለው ያስባሉ? ሀ. አስባለሁ
ለ. አላስብም

64. የአዲስ አበባ ወጣቶች በመጤ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የተነሳ ለአላስፈላጊ የስነ-ምግባርና የማንነት ቀውስ ተጋልጠዋል ብለው ያስባሉ? ሀ. አስባለሁ
ለ. አላስብም

65. የአዲስ አበባ ወጣቶችና ሴቶች በመጤ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የተነሳ ለአላስፈላጊ የስነ-ምግባርና የማንነት ቀውስ ተጋልጠዋል ብለው ካሰቡ መፍትሔው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ? _____

_____

_____

_____

_____

_____

_____::

66. የተለየ አስተየየት ወይም የሚጨምሩት ሀሳብ ካለዎት ይግለጹ _____

_____

_____

_____::

# *አባሪ ሁለት*

## ለተተኳሪ የቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

## ሀ) ከትምህርት ቤት ውጪ ላሉ ወጣቶች

1. በአካባቢያችሁ ያልተገቡ የምትሏቸውና  ወጣቱን ወደ መጤ ባህል የሚገፋፉ ባህሪያት ምንድን ናቸው?
2. ወደተዘረዘሩት ችግሮች እንዲገቡ የሚገፋፉዋቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
3. መጤ ባህሎች ብላችሁ የዘረዘራችኋቸውን ባህሪያት የሚያንፀባርቁና በነዚህ ተግባራት የተጠመዱ የትኞቹ ወጣቶች ናቸው?
4. ወደ አላስፈላጊ ባህሪያት የሚገፋፉ ቦታዎች ወይም ቤቶች በአካባቢያችሁ አሉ ካሉ የነዚህ ቦታዎች መኖር በወጣቱ ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ ምንድን ነው?
5. ቤተሰባዊ መስተጋብር በልጆች አዋዋልና ስብዕና የሚያመጣው ተፅእኖ ምንድን ነው?
6. በትምህርት አካባቢ የአቻ ጓደኛ ተፅዕኖ፣ የትምህርት ቤት አስተዳደራዊ ሁኔታ፣ የተማሪና መምህር ግንኙነት፣ በወጣቶች ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ምንድን ነው?

## ለ. በወሲብ ንግድ ለተሰማሩ  እና በመሰል ችግሮች ውስጥ ላሉ ሴቶች

1. በሴቶች ላይ በጎ ያልሆነ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ አላስፈላጊ ባህሎችና ጎጂ ድርጊቶች እነማን ናቸው?

2. ወደዚህ ተግባር እንዴት ልትገቢ ቻልሽ?

3. በዚህ ተግባር ለምህ ያህል ጊዜ ቆየሽ? በቆይታሽስ ያጋጠሙ ችግሮች ምንድን ናቸው? ይህንን ሂወት እንዴት ትገልጪዋለሽ?

   - አብዛኛውን ጊዜ ደንበኞችስ በየትኛው እድሜ ክልል የሚገኙና ምን ለየት ያለ ባህሪ አላቸው
   - በዚህ ህይወት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ቆየሽ
   - አንቺስ የየትኛው ሱስ ተጠቂ ነሽ
   - በዚህ ህይወት ውስጥ ያጋጠሙሽ ችግሮችና ችግሮችን ለመቅረፍ ያረግሽው ጥረትና የመፍሄ እርምጃዎች ምንድን ናቸው

4. የሱስ ማስፋፊያ ቦታዎች መበራከት ሴቶችን ወደ ሴተኛ አዳሪነትና መሰል አላስፈላጊ ህይወት ይገፋፋል ወይ?

5. የትምህርት ተቋማት ፣የቤተሰብና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ህይወት ለመግባት ምክንያት ናቸው ወይ

## ሐ. ለቤት እመቤትና ለቢሮ ሴቶች

1. በአካባቢያችሁ ያልተገቡ ይምትሏቸው ሴቶችን ወደ መጤ ባህል የሚገፋፉ ባህሪያት ምንድን ናቸው?
2. ሴቶች ወደ ተጠቀሱት ችግሮች እንዲገቡ የሚገፋፉዋቸው
3. ለተጠቀሱት ጉዳዮች የሚጋለጡ ሴቶች ምን አይነት ሁኔታ ላይ ያሉ ናቸው?
4. በአካባቢያችሁ ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ሱሶችና ባህሪ የሚገፋፉ ቦታዎች አሉ? ካሉ የነርሱ መኖር በሴቶች ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ ምንድን ነው?
5. የግሎባላይዜሽንና የኢ.ኮ.ቴ መስፋፋት በሴቶች ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ ምንድን ነው

   - ከውጪ የሚገቡ ፊልሞችን ያያሉ? ካዩ ምን አይነቶችን አዘውትረው ያያሉ?
   - በቴሌቪዥን ከሚተላለፉ ፕሮግራሞችና በዲሽ ከሚተላለፉት የበለጠ ጊዜ ሰጥተው የሚያዩት የትኛውን ነው?

- ፊልሞችን የሚያዩት መቼና ለምን ዓላማ ነው?

6. የህብረተሰብ የቤተሰብና የትምህርት ቤቶች ነባራዊ ሁኔታዎች በሴቶች ባህሪ ላይ የሚያስከትሏቸው ተፅዕኖዎች ምንድን ናቸው?

   - ህብረተሰቡ ሴቶችን ወደ አላስፈላጊ ባህሪ እንዲገቡ የሚገፋፉቸው በምን ሁኔታ ነው?
   - በአካባቢዎ በሴቶች ላይ የሚደረግ ያታዊ ጉንተላ እንዳለ ያውቃሉ?

## መ. በማረሚያ ቤት ላሉ ወጣት ታራሚዎች የቀረበ የቡድን ውይይት

1. ታራሚዎች ወደ ማረሚያ ቤት የገባችሁበትን ምክንያት ብትገልጹልን?

2. ወደ ማረሚያ ቤት ከመግባታችሁ በፊት በውጪ ያለው የዕፅና የአልኮል ተጠቃሚ ነበራችሁ? የሌሎቹስ ተጠቃሚነት ምን ይመስል ነበረ?

3. በአስገድዶ መድፈር፣ለዕፅ ዝውውር ወንጀልና መሰል ድርጊቶች መንስኤዎች ምንድን ናቸው?

4. በማረሚያ ቤት ከገባችሁና ከዚያም በፊት ስለ ግብረሰዶማዊነት ታውቁ ነበር?

## ሠ.ለጫት ቃሚዎች (ተጠቃሚዎች)

1. በአካባቢያችሁ ባብዛኛው ወጣቶች የሚጠቀሙባቸው (የተለመዱ) አደንዛዥ (አነቃቂ) ዕፆች ምን ምን ናቸው?
2. ለአደንዛዥ(አነቃቂ) ዕፆች በተለይም ጫትና ሺሻ መለመድ ምክንያት ይሆናሉ የምትሏዋቸው መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
3. ጫትና ሺሻ አዘውትረው የሚጠቀሙ ወጣቶችና ሴቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምንድን ናቸው?

4. በየቀኑ ጫት የሚቅሙ ወጣቶች /ሴቶች በአማካይ ምን ያህል ገንዘብ ሊያወጡ ይችላሉ ?የገንዘብ ምንጭ ከየት ነው?
5. ጫት ባልተቃመ ቀን ምን ዓይነት የባህሪ ለውጦች ይታያሉ? ይህንንስ ለማካካስ የሚወሰዱ? ርምጃዎች ምን ይመሥላሉ ?
6. ከጫት ምርቃና ጋር ተያይዘው የሚወሰዱ ዕፆች ምን ምን ናቸው ?ሲጋራ፣ ሀሺሽ ... አልኮል
7. ከአልኮል መጠጥ(ጨብሲ) በኋላ ወደ ወሲብ ስሜት መገፋፋት ይታያል? ከሆነስ በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ ያለው ጥንቃቄ አወሳሰድ ምን ይመስላል?
8. በጫትና ሺሻ ሱስ የተጠመዱ ወጣቶችና ሴቶች ከዚህ ችግር እንዲወጡ ለማድረግ የመፍትሄ ሀሳቦችዎምንድን ናቸው?

## ረ. ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለተተኳሪ ቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በወጣቶች ላይ የሚታዩ አላስፈላጊ ባህሪያት ምን ምን ናቸው?
2. ወጣቶችና ሴቶችን ወደ አልባሌ ባህሪያት የሚገፋፉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
3. የመጠ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተጠቂዎች እነማን ናቸው?
4. የመጠ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተፅእኖዎች ምን ምን ናቸው?
5. ቤተሰባዊ መስተጋብር ከመጠ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ጋር ግንኙነት አለው ? ካለው ግንኙነቱ ምን ይመስላል፡፡
6. በት/ቤት አካባቢ ያለው ሁኔታ ለመጠ ባህሎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መስፋፋት አስተዋፅኦ አለው?

# አባሪ ሦስት

# ለቃለ ምልልስ የቀረቡ ጥያቄዎች

## ሀ. ለጫት አስቃሚዎች ለቃለ ምልልስ  የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ይህንን ሥራ (ቢዝነስ) መቼ ጀመሩት ሥራው አዋጪ ነው?
2. ደንበኞችህ በምን የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው? በየትኛው የስራ መደብ ውስጥ ይገኛሉ? (ተማሪዎች፣ የመንግስት ሠራተኞች፣ ሥራ የሌላቸው፣ሴቶች ወዘተ....)
3. ጫት ከማስቃም ውጪ ሌላ ተመሳሳይ የምትሰሩት ሥራ ምንድን ነው?
4. ደንበኞቻችሁን የሚያስተናግዱላችሁ እነማን ናቸው? ምን አይነት መስተንግዶ ትጠቀማላችሁ( የአቃቃም ስልታችሁ ከተለመደው ወጣ ያለ ባህሪ አለው)?
5. በአብዛኛው ደንበኞቻችሁ በስንት ሰዓት ይገኛሉ? ለም ያህል ጊዜስ ይቅማሉ?
6. ደንበኞችህ/ሽ ጫት እየቃሙ ወይም ከቃሙ በኋላ የሚጠቀሟቸው አነቃቂ ነገሮች ምንድን ናቸው? እነኝህን ተጠቃሚ በመሆናቸው በደንበኞቻችሁ ላይ የደረሰ ችግር ምንድን ነው? እነኚህን ተጠቃሚ በመሆናቸው በደንበኞቻችሁ ላይ የደረሰ ችግር ምንድን ነው?
7. በዚህ አካባቢ ተመሳሳይ ሥራ የሚሰሩ ሙያተኞች ምን ያህል ይሆናሉ? የነዚህ ቦታዎች መስፋፋት የአካባቢውን ነዋሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይገፋፋል ብለው ያስባሉ?
8. አነቃቂ ነገሮችን የሚወስዱ ደንበኞቻችሁ ምን አይነት የባህሪ ለውጥ ያሳያሉ?

## ለ. ለኃይማኖት አባቶች ለቃለ ምልልስ  የቀረቡ ጥያቄዎች

1. መጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚባሉት ምንድን ናቸው?
2. ወጣቱ ትውልድና ሴቶ ወደነዚህ ተግባራት የሚገቡት ለምንድን ነው ይላሉ?
3. አሁን በአብዛኛው ወጣቶች ላይ የሚታዩትን አላስፈላጊ ድርጊቶች(ዝሙት፣ስካር፣ደባል ሰሶች...) ከኃይማኖች አንፃር እንዴት ይመለከቱታል?
4. በእርስዎ የእምነት ተቋም ይህንን ችግር ለመቅረፍ ምን እየተሰራ ነው? ወደፊትስ ምን ቢደረግ ይሻላል ይላሉ?

## ሐ. ለሕክምና ባለሙያዎች  ለቃለ ምልልስ  የቀረቡ ጥያቄዎች፣

1. ወጣቶችና ሴቶች ለመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ተጋላጭ መሆናቸው ባጤናቸው ላይ የሚያስከትልባቸው ችግር ምንድን ነው?(ጫት፣ሺሻ፣ አልኮል፣ወዘተ....)
2. ግብረ ሰዶማዊያን ወደዚህ ተግባር የሚገቡበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. የግብረሰዶማዊያን ልዩ ባህሪ ምንድን ነው?
4. ከሙያ አንፃር ምን ቢደረግ ይሻላል ይላሉ?(መፍትሔው ምን ይመስሎታል)

## መ. ለፍትሕ አካላት ለቃለ ምልልስ  የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ወንጀል ፈጽመው ወደ እናንተ ከሚመዩ ተጠርጣሪዎች መካከል ወንጀል ለመፈጸም ምክንያቶቻቸው ምንድን ነው ይላሉ?(በመጠጥ መገፋፋት፣ጫትና አነቃቂ ሱሶች፣ፊልም በማየት፣.....)
2. ይህን ችግር ለመከላከል የሚያስችል ግልጽ የሆነ የህግ አግባብ አለ?
3. ህብረተሰቡ በህጉ ላይ ምን ያህል ግንዛቤ አለው? በእናንተ በኩል ግንዛቤ ለመፍጠር ምን የተሰራ ስራ አለ?
4. የህግ ተፈፃሚነቱስ ምን ያህል ነው?
5. በእርስዎ አስተያየት ወደፊት ምን ቢደረግ ይሻላል ይላሉ?

## ሠ. ለት/ቤት ር/መምህራን ለቃለ ምልልስ  የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በት/ቤቶች አካባቢ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ይተገበራሉ ይባላል ምን ያህል እውነት ነው?
2. የደባል ሱሶች ተጠቂ የሆኑ ተማሪዎች ይኖራሉ? ካሉ እነኝህ ተማሪዎች ከሌሎች የሚለዩአቸው ባህሪያት ምንድን ናቸው?(በትምህርት አቀባበላቸው ከጓደኞቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ ከመምህራን፣ ከወላጅ ያላቸው ግንኙነት....)
3. ከት/ቤቶች አካባቢ ለትምህርት አዋኪ የሆኑና ተማሪዎችን ለደባል ሱሶች አጋላጭ የሆኑ ነገሮች አሉ?
4. ለዚህ ተገዢ የሆኑ ተማሪዎች የትምህርት ውጤታቸው ከሌሎቹ ሲነፃፀር ምን ይመስላል?
5. ይህን ችግር ለመከላከል በእናንተ በኩል ምን የተሠራ ሥራ አለ? ወደፊትስ ምን ቢደረግ ይሻላል?

## ረ. በተመሳሳይ ፆታዎች መካከል ወሲብ ለሚፈጽሙ(ለግብረሶዶማዊያን) ለቃለ ምልልስ  የቀረቡ ጥያቄዎች

1. አንተ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር ወሲብ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጸምከዉ መቼና እንዴት ነዉ?
2. የግብረሰዶማዊነት ተግባር የሚፈጽሙ የሚግባቡበት የቋንቋ ኮድ ምንድን ነዉ?
3. በቤተሰብህ ወይም በማህበረሰቡ የደረሰብህ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ምን ነበር?
4. አሁን የምንጠይቅህ ከራስህ ትንሽ ወጣ ያለ ነዉ:: ችግሩ በህብረተሰቡ ምን ያክል የተስፋፋ ይመስልሃል?
5. ስርጭቱ ቢስፋፋ ነዉ፣ ቢገታ የምትደግፈዉ?

## ሰ. ለአዲስ አበባ ዕድሮች ጥምረት አመራሮች ለቃለ ምልልስ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በአዲስ አበባ ሁላችንም የምናስተውላቸው መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?
2. ወጣቶችና ሴቶች ወደነዚህ ተግባራት የሚገቡት ለምንድን ነው ይላሉ?
3. አሁን በአብዛኛው ወጣቶች ላይ የሚታዩት አላስፈላጊ ድርጊቶች ከኢትዮጵያነት ባህላችን አንጻር?
4. በአዲስ አበባ እድሮች ሙታንን በመቅበር ከሚያደርጉት ጥረት ባለፈ አሁን ከሚታየው የልማት እንቅስቃሴ በተያያዘ እነዚህንና ሌሎች መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ በመከላከሉ ምን እየተሰራ ነው?ለወደፊቱ ምን ታስቧል?
5. መፍትሔው ምን ቢሆን ይሻላል ይላሉ?

## ረ. ለአዲስ አበባ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ለቃለ ምልልስ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. መጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚባሉት ምንድን ናቸው?
2. በንግድ ላይ ለተሰማሩ የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች የሙያ ፈቃድ አሰጣጣችሁ አንዴት ነው ? የድጋፍ፣ክትትልና ቁጥጥር ስልታችሁስ ምን ይመስላል?
3. በንግድ እንቅስቃሴ ላይ የተሠማሩ አገልግሎት ሰጪዎች ከፈቃድ ውጪ ሲሰሩ ቢገኙ የሚወሰደው እርምጃ ምንድን ነው?
4. ቢሮው ይህንን ችግር ለመቅረፍ ምን እየተሰራ ነው?
5. የእናንተ ቢሮ ከንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ እንዲሁም ከሌሎች መሥሪያ ቤቶች ጋር ያለው ትስስር ምን ይመስላል?
6. ለወደፊቱስ ምን ቢደረግ ይሻላል ይላሉ?

# አባሪ አራት

| ተ.ቁ | ከጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ የመፍትሔ ሀሳቦች | የ ድግግሞሽ ብዛ ት |
|---|---|---|
| 1 | በተለያዩ መንገዶች ለህብረተሰቡ(ወጣቱንም ያካተተ) ስለ ሀገር ባህል በማስተማር ባህላቸው እንዲንከባከቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ | 151 |
| 2 | በተለያዩ መንገዶች ለህብረተሰቡ በተለይም ለወጣቱ ለአላስፈላጊ መጤ ባህሎች፣ ሱሶችና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይጋለጡ ስለ ጉዳቱ በማስተማር ግንዛቤ ማስጨበጥና በጎውን ባህል ከመጥፎው በመለየት ከራስ ባህል ጋር ስለማጣጣምና የውጭ ባህልን መከተል ስልጣኔ እንዳልሆነ በማስተማር ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ | 280 |
| 3 | የራስን ባህል ማወቅ፣ ማክበርና ማስተዋወቅ፣ | 194 |
| 4 | ለወጣቱና ለሴቶች የሚስማሙ የመዝናኛ ቦታዎች፣ የንባብ ማዕከላት("ላይበራሪዎች")፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ በስፋት እንዲቋቋሙ ማድረግ፣ | 275 |
| 5 | በቤተሰብ ውስጥ ነጻ ውይይት እንዲኖርና ወላጆች ልጆቻቸውን በቅርብ እንዲከታተሉ፣ ምክር እንዲሰጡና በልጆቻቸው ላይ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዲኖራቸው ግንዛቤ መፍጠር፣ | 101 |
| 6 | የኢኮኖሚ ችግር ለመፍታት ለወጣቶች የትምርትና የስራ ዕድል መፍጠርና የፈጠራ ባለቤቶች እንዲሆኑ በማስተማር፤ በተለይ ለሴቶች ለየት ያለ ድጋፍ በማድረግ የትምርትና የስራ ዕድል ማመቻቸት፣ | 217 |
| 7 | በት/ቤት አካባቢም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች ያሉ የጫት፣ሺሻ፣መጠጥ፣የቀንና የማታ እንዲሁም የራቁት ጭፈራ፣የወሲብ ፊልም፣ፑልና የመሳሰሉ ቤቶችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመዘጋት እገዳና ቅጣት ቢጣልባቸው፤ ወደ ሌላ ገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ቢደረግ፣ | 212 |
| 8 | በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የጫት፣ሺሻ፣መጠጥ፣የቀንና የማታ እንዲሁም የራቁት ጭፈራ፣የወሲብ ፊልም፣ፑልና የመሳሰሉ ቤቶችን የዕድሜና የሰዓት ገደብ አንዲኖራቸው በማድረግና ማስፈጸሚያ የህግ ማዕቀፍ ቢዘጋጅና ቢጸድቅ፣ | 16 |
| 9 | ከውጭ የሚገቡ የወሲብ ፊልሞች፣ ሺሻና ሀሺሽ እንዲሁም የነዚህ መጠቀሚያ የሆኑ ቁሳቁሶች እንዳይገቡ እገዳ ቢደረግና | 66 |

| | | |
|---|---|---|
| | ህገወጥ ዝውውሩንም በመከታተል የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚያስችል የህግ አግባብ ተፈጻሚ እንዲሆን ቢደረግ፣ | |
| 10 | በተለያዩ የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች፣ ቲያትርና ፊልም ቤቶች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ቲያትሮች፣ ፊልሞች፣ ድራማዎች፣ ማስተዋወቂያዎችና የውይይት መድረኮች ከባህል፣ከስነምግባር፣ ከአለባበስ እና መሰል እሴቶቻችን አንጻር ቢጠኑና ጥንቃቄ ቢደረግባቸው፣ | 6 |
| 11 | የእምነት ተቋማት ህብረተሰቡን የማስተማር ኃላፊነትን በመውሰድ ቢሰሩ ምዕመኑም በየእምነት ተቋሙ በሚወጡ መመሪያዎች በመመራት ለመንፈሳዊ እሴቶች ትርጉም መስጠት ቢችሉ፣ | 36 |

| | | |
|---|---|---|
| 12 | በየትምህርት ቤቶች የግብረገብ፣ የስነ-ምግባርና የባህል ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት በስርዓተ ትምህርቱ ተካቶ ተጠናክሮ የሚሰጥበት ሁኔታ ቢመቻች፣ | 76 |
| 13 | ወጣቶችን በወጣት ማዕከላትና በት/ቤት ውስጥ በሚቋቋሙ የተለያዩ ክበቦች ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማበረታት በማዕከላትና በክበባቱ አማካኝነት ችግር ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ገና ላልገቡት በኔ ይብቃ የመቀጣጫ ውይይቶች (የተዕዕኖውን አስከፊነት ማሳያ መድረኮች) በተጠናከረ መልኩ ቢካሄዱ፣ | 26 |
| 14 | ለተለያዩ ሱሶችና አላስፈላጊ መጤ ባህሎች ለተጋለጡ ሰዎች፣ ለጎዳና ተዳዳሪዎና በወሲብ ስራ ለተሰማሩ ሰዎች ከችግሩ እንዲወጡ የሞራልና የስነ-ልቦና ምክርና እገዛ ተደርጎላቸው ወደ ስራ እንዲሰማሩ ቢደረግ፣ | 12 |
| 15 | በኢንተርኔት የሚሰራጩ የወሲብ ፊልሞችና ማስታወቂያዎች ላይ ቁጥጥርና እገዳ ቢደረግ፣ | 19 |
| 16 | የውጭ ሀገር ዜጎችና በውጭ ሀገር ሲኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሲመጡ ይዘዋቸው በሚገቡ ነገሮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ቢደረግ፤በሀገር ውስጥ የሚከፍቷቸውን የንግድ ድርጅቶች ህገ-ገብነት መከታተልና መቆጣጠር ቢቻል፤(በብዛት የግብረ ሰዶም፣ የራቁት ጭፈራ ቤቶች፣ የሺሻና ሀሺሽ ቤቶችን የሚከፍቱት ከውጪ የሚመጡ ግለሰቦች ስለሆኑ) | 2 |
| 17 | ስለበጎ አለባበስ ትምህርት ቢሰጥና ባህላዊ የሆነው ልብሳችንን በዘመናዊ መልኩ በማዘጋጀት ለጥቅም ማዋል ቢቻል | 20 |
| 18 | መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ከህብረተሰቡና ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ፣ ማህበረሰባዊና ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ጋር በችግሩ ዙሪያ ግልጽ ውይይት በማድረግና የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር ጠንከር ያለ እርምጃ በመውሰድ መፍትሔ ቢሰጠው፣ | 67 |

| | | |
|---|---|---|
| 19 | የተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነትን በተመለከተ ጠበቅ ያለ ቁጥጥር ቢደረግበት፤ በማረሚያ ቤቶች፣ በወታደር ካምፖችና በቡና ቤቶች ዙሪያ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠበቅ ያለ የማስተማር፣ ቁጥጥርና ክትትል ስራ ቢሰራ፤እርምት ቢደረግ፣ | 13 |
| 20 | የጫት ምርትን መቀነስ ከተቻለ ማጥፋት ወይም የጫት፣የአልኮል፣የሀሺሽና ሺሻን ዋጋ እጅግ ከፍ ማድረግ ቢቻል ወይም ቀረጣቸው በጣም ከፍ ቢደረግ፣ | 5 |
| 21 | የባህል ዘርፍ ተቋማትና ቢሮዎች የሀገር ባህልን የሚያስተዋውቁ የባህል ማዕከላትን ቢያስፋፉና ተከታታይ ኤግዚቢሽኖችን ቢያካሂዱ፣ | 4 |
| 22 | ከጥናቱ የሚገኘውን ውጤት ለህብረተሰቡ በማቅረብ በማወያየት ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ተግባራዊ ቢደረግ | 75 |
| 23 | መንግስት መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማጥፋት ህግና ፖሊሲ ቢያዘጋጅ | 22 |
| 24 | የመብት መከበርና መጠቀም ግዴታን ያገናዘበ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የማስተማር ስራ ቢሰራ፣ | 3 |
| 25 | በሀገሪቱ ባሉ ንግድ ቤቶች ውስጥ ሁሉ ባህላዊ እሴቶችን ለመዘከር የሚያስችሉ ነገሮች እንዲሟሉ ቢደረግ፣ | 2 |
| 26 | የመኖሪያ፣ የትምህርትና የስራ ቦታዎች ከአላስፈላጊ ነገሮች የጸዱና ምቹ እንዲሆኑ ቢደረግ፣ | 24 |
| 27 | የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች የሀገር ባህልና ወግን የሚያጠናክሩ፣ በጎና መጥፎ የሚባሉ ባህሎችን በመለየት፣ በጎ የሆኑ መጤ ባህሎችን ከራስ ባህል ጋር አስማምቶ ስለመጠቀም የሚያስተምሩ ፕሮግራሞችና ውይይቶችን ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ፣ ማህበረሰባዊና ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ቢያዘጋጁ | 29 |
| 28 | የሀገራችን ታዋቂ ሰዎች ለወጣቱ አርአያ በመሆናቸው ወጣቱን በሚያስተምር መልኩ በባህልና በተስተካከለ አስተሳሰብ ዙሪያ በቃልም በተግባርም ትምህርት ቢሰጡ | 16 |